

የሀይማኖት ፅሁፎች














ከታፈሰ ሙሉነህ

1997

የሃይማኖቶች ልዩነት

ከታፈሰ ሙሉነህ

አዲስ አበባ
1997

ይህ መጽሐፍ መታሰቢያነቱ ለፋናዬ አወከ ነው።

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

የሃይማኖቶች ልዩነት

ማውጫ

መግለጫ

ርዕስ	ገጽ
ጥንታዊ እምነቶች	3
ሂንዱይዝም	8
መግቢያ	
አራቱ የሰው ዘር መደቦች	9
የዓለም አፈጣጠር	11
አንዳንድ ዋና ዋና እምነቶች	13
ሀ- የሳምሳራ ዙሮሽ	
ለ- ዮጋ	14
የሃይማኖቱ መከፋፈል	15
አፅማደ ምስጢራት	16
የሃይማኖቱ ፅድጉት	17
ቡድሂዝም	20
የቡድሃ መንፈሳዊ አስተምሮት	
ጉተማ	21
የሃይማኖቱ ዓይነተኛ መለያዎች	24
የእምነቱ አተረጓጎም ልዩነት	26
መንፈሳዊ ጉባኤዎችና የሃይማኖቱ ተሃድሶ	27

ርዕስ	ገጽ
የሃይማኖቱ መስፋፋት	28
አይሁድነት	30
መሰረታዊ እምነት	
የአብርሃም ታሪክ	31
የሙሴ ታሪክ	32
የአይሁድነትታሪካዊ አመጣጥ	34
በዓላት	38
ሰንበት	40
ምኩራብ	41
ማጠቃለያ	42
የክርስትና ሃይማኖት	46
የናዝሬቱ ኢየሱስ	
የመጽሀፍ ቅዱስ ክፍሎች	50
የሃይማኖቱ መከፋፈል	52
ምስጢረ ስላሴ	53
ጸሎተ ሃይማኖት	
የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት በኢትዮጵያ	56
አጀማመር	
አፅማደ ሚስጢራት	60
በዓላት	63
የጾም ጊዜያት	
የፋሲካ ቀን አወሳሰን	69
ቤተ ክርስቲያን	71
ስርዓተ ቅዳሴ	72

ርዕስ	ገጽ
የካቶሊክ ሃይማኖት	77
የኦርቶዶክስና የካቶሊክ መለያየት ታሪክ	
የካቶሊክ ሃይማኖት በኢትዮጵያ	83
የቤተ ክርስቲያን ቅርጽና ሥነ ሥርዓት	85
አእማደ ምስጢራት	88
የፕሮቴስታንት ሃይማኖት	89
የካቶሊክና የፕሮቴስታንት እምነቶች መለያየት	
የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ይዘት	92
መካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን	93
የፕሮቴስታንት ሃይማኖት አከፋፈል	98
በኢትዮጵያ የሚገኙ አንዳንድ የፕሮቴስታንት ሃይማኖቶች (ሙሉ ወንጌል ቃለ ህይወት መሠረተ ክርስቶስ አድቬንቲስት የያህዌ ምስክሮች ሃዋርያዊ ቤተ ክርስቲያን)	101
የእስልምና ሃይማኖት	119
የእስልምና ሃይማኖት ይዘት	
ነቢዩ መሐመድ	122
የእስልምና መሰረታዊ ተግባሮች	123
ሌሎች ተግባራት	128
የሃይማኖቱ መከፋፈል	130
የሺያት እስልምና ተከታዮች	
መስጊድ	132
በዓላት	133
የጨረቃ ወር	

ርዕስ	ገጽ
እስልምና በኢትዮጵያ	135
የባሃይ ሃይማኖት	138
መግቢያ	
የሃይማኖቱ ይዘት	
የነቢያቱ አስተምሮት	141
ባብ	
ባሃኡላህ	143
አብዱልባሃ	145
ሾጊ ኢፌንዲ	146
የባሃይ ተግባራት	
በዓላት	148
የዘመን አቆጣጠር	
መደምደሚያ	150
አባሪ	160
ዋቢ መጻሕፍት	161

መግለጫ

የሃይማኖት ትምህርት አስፈላጊ ነው። ዛሬ በዓለም ዙሪያ ያሉት ክርስቲያኖች ዓይነት ከ260 በላይ ደርሷል። አድቬንቲስት፤ ሜቶዲስት፤ ቃለ ህይወት፤ ሜኖናይት ወዘተ. . . ብዙዎቹ እርስ በርሣቸው በጥልቀት አይተዋወቁም። ግን ሁሉም የየራሣቸውን ብቻ ለማሣወቅና ለማሣመን ጥረት ያደርጋሉ። ለምሣሌ፦ አንድ ካቶሊክ ለሀንዳዊ ቡዲስት ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሊያስረዳ ዝግጁ ነው። ሀንዱም ስለራሡ ሃይማኖት ሊያስተምር ይችላል። ግን አንዳቸው የሌላውን ለማጥናት በቂ ጥረት አያደርጉም። ለዚህም ምክንያት ይኖረዋል። በብዙዎቹ ቅዱስ መጽሐፍት ውስጥ ስለ ሃዋርያዊ ተልዕኮ ድንጋጌ አለ "ሂዱ አስተምሩ አሣምኑ" የሚል ዓይነትና የእግዚአብሔርን ቃል ለሁሉም ለማዳረስ በሚል መንፈስ የተቀመጠ ትዕዛዝ አለ። ስለዚህ ሁሉም ሃይማኖቱን ለማሠራጨት ሃላፊነትና ግዴታ አለበት። በሌላ በኩል ግን ከዚያ ውጭ እንዲሄድ የሚያበረታታ ጥቂት ነው። ከዚህ መጽሀፍ የአጎደለ ወይም የጨመረበት . . . . . የሚል አይነት ትዕዛዝ ይኖራል።

እርግጥ ብዙ የሃይማኖት ትምህርት ቤቶች ስለ ሌሎች ሃይማኖቶችም ያስተዋውቃሉ፤ ያስተምራሉ። ነገር ግን ይህ በገለልተኝነት አቀራረብ ሣይሆን የራሣቸውን ሃይማኖት እንደመሠረት ይዞ በመነሣት በመሆኑ ንጽጽሩ አድሏዊነት ያመጣል። ት/ቤቱ ከተቋቋመበት ዓላማና ከሚሰጠው ድጋፍ አኳያ ሲታይ ይህ መሆን ያለበት ነው።

ነገር ግን አንድ ዜጋ ሙሉ ግንዛቤ እንዲኖረው ከተፈለገ ትምህርቱ በመንግሥት ወይም በገለልተኛ አካል ሊሰጥ መቻል አለበት። የዚህ ዓላማ ደግሞ ተጨባጭ ሁኔታዎችን በማስረዳት ሰው የተሟላና ሚዛናዊ አመለካከት እንዲኖረው ለማስቻል ነው።ይህ ማንም ሰው በዜግነቱ አንጻር የራሱን ዕምነት ከሌሎች በማስበለጥ ስሜት ትምክህት እንዳያድርበትና የሌሎችንም ሃይማኖቶች የመረዳትና የማክበር ስሜት እንዲያድርበት ያግዛል።

ይህ ችግር በግለሰቦች ደረጃ ብቻ ሳይሆን በብሄራዊ ደረጃም ችግሮችን አስከትሏል። አንዳንዶችን ለማስታወስ ያህል የኢራን መንግሥት የእንግሊዝን ደራሲ ሳልማን ረሽዲን ለገደለ ሰው ሁለት ሚሊዮን ዶላር ለመሥጠት የወሰነው ውሣኔ ብዙ አወያይቷል። ምክንያቱም ደራሲው ሃይማኖቱን ስላንቋሸሸ ነው። በሱዳን ያለው እስላማዊ መንግሥት የሸሪያን ህግ ብሄራዊ ለማድረግ ይፈልጋል። ግን የደቡባዊ ክ/ሃገር ሕዝቦች ክርስቲያን በመሆናቸው ሊቀይሩ አይፈልጉም። ስለ ሆነም የከፋ ጦርነት ሲካሄድ አሥር ዓመታት አልፈዋል። የሕንድ መንግሥት ለሁለት የተከፈለው በሃይማኖት ልዩነት ነው። ዛሬ ፖኪስታን የሚባለው ተገንጣይ ክፍል ራሱን የቻለ ከመሆኑም በላይ ከሕንድ ጋር የከረረ ትግል እያካሄደ ነው። እሰከ ዛሬም ሶስት ጊዜ ጦርነት ገጥመዋል። ታድያ ህንድ ለራሷ

መከላከያ ነው በማለት ኑክሊየር ቦምብ ሰራች። ይህ በቢሊዮን ብር የሚቆጠር ወጪን ያስከትላል። እሷ መሣሪያውን የሞከረች ዕለት የፓኪስታኑ መሪ "ሣር በልተንም ቢሆን እንሠራለን" ሲል ቃል ገባ ተጨማሪ ወጪ መሆኑ ነው። ዛሬ ደግሞ ይህንን ቦምብ ተ ሸካሚ የሚሆኑ ሚሳይሎችን በመገንባት ሌላ ግዙፍ ወጪ እያወጡ ናቸው። የዚህ ሁሉ መሠረቱ የሃይማኖት ልዩነት ነው።

በቦሲኒያ (የቀድሞ ዩጉዝላቪያ) እና በቺቺኒያ (ከሩስያ ለመገንጠል) የፈሰሰው ደም እና የደረሰው ስቃይ ዋና መነሻው የሃይማኖት ልዩነት ነው። በታሪክ ወደ ኋላ መለስ ብለን ስናይ ደግሞ አያሌ የሚዘገንኑ ጦርነቶች ተደርገው እንደነበረ እንመለከታለን።

ይህ ሁሉ ዳግም እንዳይከሰት ስጋት አለኝ። ለዚህ መፍትሔው ሁሉም ሰው እንዲያውቅና እንዲያገናዝብ ማድረግ በዚህም ሚዛናዊ አመለካከት እንዲኖረው ዕድል መስጠት ነው። በበኩሌ ሙከራዬን እነሆ አቅርቤአለሁ።

ይህንን ጥናት ሳካሄድ ላቀረብኩላቸው ቃለ መጠይቆች ለተባበሩኝና ትምህርት ለሰጡኝ መንፈሳዊያን ሁሉ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በተለይ ቀሲስ ምህረት ዘውዴ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖትን በተመለከተ ለሰጡኝ ትምህርት እና ለአደረጉልኝ ድጋፍ ትልቅ ባለውለታዬ ናቸው።

እርግጥ በርዕሱ ስፋት የተነሣ ሃይማኖት ሁሉ በሚገባው መጠን በስፋትና በዝርዝር ሊቀርብ አልቻለም። ምናልባትም የቀረበውም ቢሆን በተገቢው ገላጭ ቃል አልተገለጸም። ከዚ ያም አልፎ ስህተትም ሊኖር ይችላል። ይህ ቢሆን ግን ጉዳዩ ከእኔ ግንዛቤ ዕጥረት እንጂ ሆን ተብሎ ሃይማኖቶችን ለማበላለጥ ወይም በማናቸውም ላይ አሉታዊ ገጽታ ለማንጸባረቅ ከቶ አይደለም።

ዋናው ዓላማዬ ሰዎች በእምነት ረገድ የበለጠ መግባባት ላይ እንዲደርሱ መድረክ ለመክፈት ነው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሰው ዘመን ሁሉ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር (እ.አ.አ) ነው።

ጥንታዊ እምነቶች

በ1995 ዓ.ም በአርኪዎሎጂ ጥናት መስክ ከተከሰቱት አዲስ ግኝቶች ዋንኛው በደቡብ አሜሪካ የአንዲስ ተራራ ላይ የተገኘው አጽም ነው። ይህም 500 ዓመታትን ያስቆጠረ የሴት ልጅ አጽም በበረዶ ውስጥ ተጋግሮ ሳይበላሽ የኖረና በወቅቱ ኢንካ በተባለው ጎሣ አባላት ለተራራው አምላክ በመስዋዕትነት የተሰጠች የአንዲት ታዳጊ ወጣት አካል ነው። የተራራው አምላክ በተቆጣ ጊዜ እሳተ ገሞራ እየፈነዳ የቀለጠ ድንጋይና አመድ በማፍሰስ የአካባቢውን ሰብል እንስሳና መኖሪያ ቤት ሳይቀር በቀለጠ የድንጋይ ናዳ እያቃጠለ አውሎንፋስ እያስነሣ በከባድ ዝናብ እየጠራረገ መብረቅ እየጣለና አየር እየመረዘ በሽታን በማምጣት ያስቸግር ስለነበር ከአምላኩ ጋር ለመታረቅ ሲሉ የአካባቢው ነዋሪዎች ያቀርቡት የነበረ መስዋዕት ነው።

ይህ ክስተት በደቡብ አሜሪካ ብቻ አልነበረም። የሜክሲኮ አስቴክ ጎሣ ሌላው የዘመኑ ታላቅ ስልጣኔ የነበረው ሕዝብ ሲሆን ለአማልክት የሰው መስዋዕት ማቅረብም ልምዱ ነበረ።

ወደ አውሮፓ መለስ ስልን የግሪክ አማልክት በሰፊው የታወቁ ነበሩ። ለምሳሌ የፍቅር (አፍሮዳይት) የጦርነት /አቴና/የባህር /ፖሲዮን/ አማልክት ነበሩ። አፖሎ በሚል የወል ስም የሚጠሩት የዩናይትድ ስቴትስ የጠፈር መንኮራኩሮች (ሰውን ወደ ጨረቃ ያደረሰችው ጭምር) የተሰየሙት የግሪክ የኪነት የሙዚቃና የሳይንስ አምላክ በነበረው አፖሎ ነበረ። ዚውስ የተባለው ደግሞ የአፖሎ አባት ሆኖ የአማልክቱ ሁሉ የበላይ እና ዋናው ጭሎ ነበረ። እነኝህ ሁሉ የሚመለክባቸውና ተገቢው መስዋዕት የሚደረግላቸው ነበሩ።

በአፍሪካ በእስያ እና በአውስትራሊያ አቦሪጂኖች ዘንድም ተመሣሣይ አምልኮ እንደነበረ የታወቀ ነው።

ይህ የማይጠበቅ አይደለም። ማንኛውም ሀብረተሰብ (ምንም ያህል ኋላ ቀር ቢሆን እንኳ) የራሱ እምነት (አምልኮ) የሌለው ከቶ የለም። እርግጥ የእምነቱ ሁኔታ ይለያያል፣ በወንዝ፣ በእሣት፣ በጸሐይ፣ በባሕር የሚያምኑ ነበሩ። ነገር ግን ስልጣኔ እያደገ ሲመጣና የባህር ሞገድ፣ የእሣት ሃይልና የወንዝ ባህርይ እየታወቁና በቁጥጥር ሥር እየዋሉ ሲመጡ አማልክት -አምላክነታቸው ቀርቶ ስልጣኑ ለማይታይ ለማይዳሰስ መንፈስ ይሰጣል። መናፍስትም ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸው እየቀነሰ ሃላፊነቱ ይማከልና አንድ አምላክ ብቻ የሁሉ በላይ ተደርጎ የተቀሩት ወደ መላዕክት ደረጃ ዝቅ ይላሉ ወይም ከዚያም ዝቅ ተደርገው በኋላም ይተዋሉ።

ግን ሥልጣኔ እያደገ ቢመጣም ከዝቅተኛው እርከን ብዙም ከፍ ያላሉ ህብረተሰቦች ስለሚገኙ በእምነትም እንዲሁ በተለያየ ደረጃ ላይ ያሉ ይኖሉ። ዛሬም በአባይ ወንዝ ዳርቻ ቡና እያፈሉ የሚለማመኑ ማየት የተለመደ ነው። ዛሬም ለግንቦት ጥቁር ቦሃ በግ ዛፍ ስር አርዶ ኡቃቢን መለማመን የተለመደ ነው። በየበዓሉ ለቦረንትቻ ግብር ማቅረብ እስከ ዛሬ ይከናወናል። ደብረዘይት ከተማ ሆራ ሃይቅ ዳርቻ ቡና እየተፈላ ኡቃቢን መለማመን ዛሬም በይፋ ይታያል።

እርግጥ መስዋዕት የማቅረቡ ሁኔታ ተሻሽሏል። በሀግ በመታገዝ ጭምር በብዙ አገሮች ሰውን መስዋዕት ማቅረብ እንዲቀር ተደርጓል። በአንዳንድ አገሮች ስርዓቱ ያለ መሆኑ አንዳንድ የውጭ ዘገባዎች



ለተራራው አምላክ የተሰጠ መስዋዕት አፅም (በቁፋሮ የተገኘ)

ይጠቁማሉ።* በተለይ የሰውን ስጋ ለመብልነት በሚጠቀሙ ህብረተሰቦች ዘንድ ይህ ሁኔታ ሰውን ለመስዋዕት የማቅረብ ልማድን እንደሚያበረታታ ግልጽ ነው። ዛሬ ለመስዋዕት የሚቀርበው በብዛት በግ እና ዶሮ ሲሆን ሌሎችም እንስሳት እንደየህብረተሰቡ ባህል ይቀርባሉ።

ይህ እንግዲህ ዓላማው መንፈስ የሕብረተሰቡን ወይም የቤተሰቡን ደህንነት እንዲጠብቅ ነው። በሽታን ለመከላከል ወይም ለመፈወስ የእህል ምርት እንዲበረክት ለማድረግ አደጋ እንዳይከሰትና አንዳንድ ምኞትም እንዲሳካ ለመለማመን ነው።

የአገራችንን ሁኔታ ስናይ ቡዳ የሚባል የተለመደ ነገር አለ። ቡዳ በዓይን በማየት ብቻ በሽታ ላይ ለመጣል ሃይል ያለው ሰው ነው። ታማሚው በሚገባ የባህል መድሃኒት ሲደረግለት ይለፈልፋል። ቡዳ የተባለውም ከእሱ ላይ በመናገር ሊለቀው ካሰፈለገ በቅድሚያ ምሱ እንዲሰጠው መብቱን ይጠይቀዋል።

ይህ በእኛ አገር ብቻ የተወሰነ አለመሆኑ በጣም ግልጽ መሆን አለበት፤ በሌላው ዓለምም የነበረና ዛሬም ጭምር ያለ ነው። የሚያስገርመው ግን በተለያዩ አህጉራት ያሉ ማህበረሰቦች በምንም ዓይነት ያልተገናኙ ሆነው ሳለ የእምነቶቻቻው ይዘት በጣም ተመሣሣይ ሆኖ መገኘቱ ነው። ለማስተያየት እንዲረዳ ያህል በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ያለው አሰራር በተመሣሣይ ደረጃ በህንድ አገር ካሉ ጎሣዎች ጋር እንዴት እንደሚመሣሠል እንመልከት።

እነዚህ የህንድ ጎሣዎች በአንድ እግዚአብሔር የሚያምኑ ናቸው። እርግጥ ዝርዝር ጠባይ አይወስኑለትም። ለምሣሌ- ቀይ፣ጥቁር፣ደግ፣ክፉ፣ አይሉትም። መንፈስ መሆኑን ብቻ ያሰምሩበታል። ይህ ብራህማ ይባላል።

ከዚያ ቀጥሎ ዓለምን የሚገዙ የሚያስተዳድሩ የሚቆጣጠሩ እና አንዳንድ ወሳኝ ስራዎችን የሚከታተሉ አምላኮች አሉ (ዲቫስ ይባላሉ)። ከእነዚህ የታወቁት ክሪሽና፣ራማ፣ሺቫ ናቸው።

ከእነዚህ በታች ደግሞ ሌሎች ትናንሽ አሉ። ኡቃቢ፣አቴቴ፣ አድባር፣ የመሣሠሉ የድሃ ግለሰቦችን ችግር የሚፈቱ ናቸው። በሰዎች ዕለት በዕለት ኑሮ ውስጥ እየገቡ ራስ ምታቱን የሚያዳምጡለትና ልመናውን የሚሰሙት በቅርብ የሚገኙለትና የሚጠብቁት እነዚህኞቹ ናቸው። ከተናደዱ ደግሞ ሊቀጡት ይችላሉ። በሽታ ሊያመጡ ወይም ሊገድሉት ስለሚችሉ በደንብ መያዝ አለባቸው። እነዚህ ግራማ ዲቪታ በመባል ይታወቃሉ።

---

*የሚሊየነሩ አሜሪካዊ የሮክፌለር ልጅ ለምርምርና ጥናት አማዞን ጫካ ሄዶ በተጠኝዎቹ ተበልቶ እንደቀረ ይታወሣል።

እንግዲህ አንድ መንደርተኛ ችግር ሲያጋጥመው በራሱ ሊፈታው ይሞክራል። ለችግሩ ገንዘብ፣ ለህመሙ መድሃኒት ለበደሉ ዳኝነት ይፈልጋል። ጉዳዩ ከእርሱ አቅም በላይ ከሆነ ወደ "አዋቂ" ዘንድ ይሄዳል። ይህ ባለ ኡቃቢ ወይም ትንቢት ተናጋሪ ወይም ጠንቋይ ሊሆን ይችላል። ባለኡቃቢ ከሆነ በስነ ስርዓቱ መሰረት መጠጥ ወይም ጫት ወይም ቡና ይዘጋጃል። ድቤ (ከበሮ) ይመታል። እንዲህ ተሰብስበው ሲለማመኑት ኡቃቢ ይወርዳል ይህም ማለት ባለኡቃቢው ሌላ መንፈስ እንደወረደበት ሆኖ በሌላ ድምጽ መናገር ይጀምራል። ራሱንም አያውቅም።

ከዚያ ችግረኛው ይጠራና ስለመጣበት ጉዳይ ይጠየቃል። በዚህ መካከል አጃቢዎች ኡቃቢውን በማክበር እልልታ ያሰማሉ፤ ወይም ይወዛወዛሉ፣ ይጨፍራሉ፣ ይጮሃሉ፣ይዘምራሉ፤ ትርዕይቱ ደማቅ ይሆናል።

ኡቃቢው ነገሩን ካዳመጠ በኋላ የችግሩን መንስዔ ይገልጻል። አድባሯ ስላልተገበረች ተቀይማለች፣ደም አልፈሰሰም፣በግ አልታረደም፣ ወይም የተረሳ ስነ ስርዓት አለ በማለት ይህን እንዲከናወን ያዛል። የችግሩ መንስዔ ሰውየውን ወይም የቤተሰብ አባሉን ቡዳ በልቶት ከሆነ ወይም ሰይጣን ተጸናውቶት ከሆነ ኡቃቢው ወዲያው እርምጃ ሊወስድ ይችላል። ሰይጣኑን የማስለቀቅ የራሱ ስነ ስርዓት አለው። "ልቀቀውና ሂድ" ተብሎ ይታዘዛል። ምሴን ስጡኝ ሲል ድርድር ይጀምራል። ካልተስማሙ ትግል ይጀመራል። ባለ ኡቃቢው ሕመምተኛውን ይገር ፈዋል። ሰይጣኑም በህመምተኛው አንደበት ይጮሃል፣ ግብግብ ይቀጥላል። በኋላም ሰይጣኑ ምሱን ተቀብሎ ይሄዳል። ወይም ይባረራል።

ይህ በህንድ መንደሮች የሚካሄድ የገጠር ሰዎች ኑሮ ነው። ከኢትዮጵያ የገጠር አኗኗር ጋር ያለው ተመሣሣይነት ግልጽ ነው።

አገራችን የክርስትናን እምነት ከተቀበለች ከአንድ ሺ ዓመታት በላይ አስቆጥራለች። እስልምናም እንዲሁ ረዥም ዕድሜ አለው። በዚህ የተነሣ በወንዝ በዛፍ እና በጣኦታት የማምለክ ልምድ በሕዝቦቻችን ዘንድ በእጅጉ ሊቀንስ በመቻሉ አገራችን ከሌሎች የአህጉሩ አባላት አንጻር ሰትታይ የባህል ዕድገት ያላት መሆኑ የማይካድ ነው ሆኖም ግን ከነዚህ ታላላቅ ሃይማኖቶች ጎን ለጎን የኡቃቢ፣ የቦረንትቻ፣ የቡዳ፣ እምነቶች እና የመሣሠሉት አብረው የሚሰራባቸው መሆኑ ይታወቃል። ይህ የራሱ በጎ ጎን ያለውን ያህል ክፉ ጎንም እንዳለው ግልጽ ነው። በአንድ በኩል ሰዎች የፖሊስ አገልግሎትና የመንግሥት የፍትህ ዳኝነት በሌለበት ቦታ በዳዮቻቸውን በመራገም ለኡቃቢዎቻቸው በመ ጸለይ እና በድግምት በመተማመን ለጊዜውም ቢሆን ንዴታ ቸውን የሚያበርዱበትና በትዕግስት ተቻችሎ መኖርን የሚተገ ብሩበት ጠቃሚ መንገድ ሆኖ ኖሯል። በሌላ በኩል ግን ብዙ ሰ ዎች በተለይም በጉልበት ለመቋቋም አቅም የሌላቸው ባልቴቶች ተሰቃይተዋል። ተሰውተዋል። ይህ በእኛ አገር ወይም በአህ

ጉራችን ብቻ የሚከሰት አልነበረም። ለምሳሌ ከአሜሪካ እና ከአውሮፓ አህጉራት የተዘገቡ የቀድሞ ክስተቶችን እናስታ ውሣለን።

ጊዜው 1688 ዓ.ም ነው። በዩናይትድ ስቴትስ የቦስቶን ከተማ ነዋሪ ሰው ሕጻኑን ቡዳ በላት ተባለ። ህጻኗ ህሊናዋን ስታ ትቀባዥር ጀመር። ለዚህ ምክንያቱ ሲፈለግ አንዲት በጎረቤት ያለች ልብስ አጣቢ መሆኗ ተደረሰበት። ስለዚህ ወዲያው ተይዛ ተሰቀለች። ይህም በዜና መልክ በይፋ ለሕዝብ ተገለጸ። ይህም ለሌሎች ትምህርት በመሆኑ ሰዎች ከችግሩ ለመከላከል ሲሉ በየአካባቢያቸው የሚጠረጥሩትን ቡዳ ሰዎች እየለቀሙ አስር ያህሉን ወዲያው ሰቀሏቸው።

እንዲሁም በእንግሊዝ አገር በ1590 ዓ.ም የተፈጸመውን በዝርዝር እንመልከት።

አንድ ባለጸጋ ሰው ልጆቹ በየጊዜው ይታመሙበታል። እነሱን ለመጠየቅና አንዳንድ አገልግሎት በማበረከት ቁራሽ ምግብ ለማግኘት የምትመላለስ ወ/ሮ ሳምዌል የምትባል ባልቴት ነበረች ። ታዲያ አንድ ጊዜ አንዷ ታማሚ ልጅ ወደ ሴትየዋ በማመልከት እየጮኸችና እያጓራች "እሷ በልታኝ ነው አስ ወጡልኝ" ትል ጀመር። ሴትየዋ ደንግጣ ወጣች። ባለቤቶቹም ለሴትይዋ አዝነው ልጅቷን ገስጸው ነገሩን ችላ አሉት። ግን ሌሎቹ ልጆችም ሲታመሙ ሁኔታው ተደጋገመ። ሴትየዋም ብት ክድም እያደረ ጥርጣሬው እየበረከተ መጣ። በኋላም እንድታምን ተጽዕኖ ተደረገባትና አቡኑ ፊት አቀረቧት። እንድታምን አደ ረጓት።

ከዚያ በኋላማ ፍርድ ቤት ሲያቀርቧት ምስክር እና ማስረጃ ማቅረብ አልገደደም። አንድ ምስክር "ቡዳ" ለመሆኗ ሲመሰክር እንዲህ አስመዝግቧል:- "አንድ ቀን ቡዳ አሮጊት ብዬ በሰው ፊት ሰደብኳት። ይህ በጣም አናደዳት። ታድያ አስር ቀን በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ምን የመሰለ ፈረሴ ሞተብኝ። ቀጥሎ ሳደልብ የኖርኩት አሣማ ሞተብኝ። በዚያው ወር ትልቅ ላሜ ሞተችብኝ። ከዚያ መተቱን ለማርከስ ብዬ የላሟን በድን አቃጠልኩት። ይገርማችኋል! ከዚያ በኋላ ከብቶቼ ተረፉልኝ።" ሌሎችም ምስክሮች ተገኙ። ፍርድ ቤቱም በማስረጃዋቹ መሠረት ወ/ሮ ሳምዌልን ጥፋተኛ ሆና አገኛት። የሞት ፍርድም ፈረደባት። በዚህ መሠረትም ተሰቀለች። እሷ ብቻም ሳትሆን ባሏ እና ልጃቸውም ተሰቀሉ።

በዚህ ሁኔታ በእንግሊዝ አገር ብቻ እስከ 30,000 ሰዎች በስቅላት እንደተቀጡ ይታመናል።

በሌሎች አውሮፓ አገሮችም የተከሰቱ ሌሎች በርካታ ድር ጊቶችን ለመጥቀስ ይቻላል። ይህ እንግዲህ በወቅቱ በአውሮፓ ሰፍኖ የነበረ እምነት ነው።

በአፍሪካ የነበረው እምነት ደግሞ ከዚህም የባሰ ነው። ዝርዝር ሁኔታዎችን ብናይ በአንዳንድ እምነቶች የተነሣ በሰዎች (በተለይም በባልቴቶችና በጨቅላ ህጻናት) ላይ የሚደርሰው ስቃይ የሚዘገንን ነው።

በአጠቃላይ አብዛኛው ሕዝብ በአንድ እግዚአብሔር መኖር የሚያምን ሆኖ ከዚያ በታች ግን በየደረጃው መናፍስት እንዳሉ ያምናል። የእነዚህ ተግባርም አብዛኛው ክፉ ሆኖ አንዳንዶቹ ግን ሰውን የሚረዱ ሆነው ይታያሉ። ኢትዮ ጵያን እንደ አንዲት የአፍሪካ አገር ምሣሌ ብንወስድ የእምነቱ ዓይነት በ4 ደረጃ ሊታይ ይችላል።

1ኛ- "ቡዳ" የበላውን የሚያድኑ፣ የርኩስ መናፍስትን የሚያስወግዱ ሰይጣን የሚጎትቱ ጠንቋዮች መተተኞች አሉ።

2ኛ- በ "ልክፍት" የተያዙ አሉ። ይህ ርኩስ መንፈስ ለጉዳት የሚዳርግ፣ በቀትር፣ በውድቅት፣ ሽታ ባለበት ቦታ እና በመሣ ሠሉት ሁኔታዎች የሚቀሰቀስ ነው። አብዛኛው የአእምሮ በሽታ በዚህ ይሣበባል።

3ኛ- ቃልቻዎች ባለኡቃቢዎች እና የመሣሠሉት በሰው ላይ አድረው ልክፍትን የሚፈውሱ ለሰዎች ምክር፣ መድሃኒት፣ መረጃና ማስጠንቀቂያ የሚሰጡ በአጠቃላይ በበጎ ጎናቸው የሚታዩ "ዳኞች" ናቸው።

4ኛ- ቦረንትቻ፣ አድባር የመሣሠሉት ከግለሰቡ ደረጃ በላይ መላውን ቤተሰብ ወይም ጎሣ ከክፉ ነገር 'የሚጠብቁ' ናቸው። እነዚህ በየዓመቱ (ወይም በየተወሰነ ወቅት) የዶሮ የበግ ወይም የበሬ ግብር ይገበርላቸዋል። ለዚህም ስነ ስርዓት ይኖረዋል።

በአጠቃላይ ከመናፍስት ጋር ተገናኝቶ እርዳታ ለመጠየቅ የሚያስፈልገው የአቀባበልና የአለማመን ስነ ስርዓት ከሞላ ጎደል ተመሣሣይ ነው፣ የቁጠማ እና የርጥብ ሳር ጉዝጓዝ ለምንጣፍ፤ ቅቤ፤ ቡና፤ ደም፤ ለመለማመኛ፤ ደወል፤ ቃጭል፤ ከበሮ፤ እጣን፤ ሽቶ፤ ለድምቀት እና ለሥነ ልቦና ዝግጅት ያገለግላሉ።

ይህ ዓይነት እምነት ጥንትም የነበረና አሁንም በብዙ ቦታዎች የሚታይ ነው። የክርስትና እምነት ወደ አውሮፓ ከደረሰ ሁለት ሺህ ዓመታት ገደማ ሆኖታል። በአፍሪካ እና በሌሎች አገሮችም ክርስትናና እስልምና ሃይማኖቶች ከገቡ ቆይቷል። ሆኖም በሃያሉ ፈጣሪ ማመን እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚያ በታች በመናፍስት ማመኑም አብሮ ቀጥሏል። ዛሬግን ታላላቅ ሃይማኖቶች በሳይንስ በመረዳት ሕዝብን እያስተማሩ ወደ ላቀ የአስተሳሰብ ደረጃ እያሸጋገሩት ነው።

ሂንዱይዝም

መግቢያ

"የተሰጠህን ተግባር በሚገባ አከናውን። ስለመጨረሻው አትጨነቅ፣ ይህ የእግዚአብሔር ፈንታ ነው፣ እሱ በጥበቡ ሁሉም እንደስርዓቱ እንዲከናወን እንዲሁ ፈቅዷልና። አንተ ድርሻህን አከናውን። ለጽድቅ ብሎ ስራ ፈትቶ መቀመጥ ፋይዳ የለውም። ይልቁንስ ለዓለም ደህንነት በማሰብ ያለማቋረጥ ድከምለት። ይህም እግዚአብሔር ለዓለም ያቀደውን ሥርዓት እውን ለማድረግ ስለሆነ ፈቃዱ እንዲፈጸም ስትል ስራ"

ይህ ከሂንዱ ቅዱስ መጽሀፍ በአንዱ ባጋቫድ ጊታ በተባለው የግጥም መጽሀፍ ውስጥ የተቀመጠ እና ክሪሽና በተባለው አምላክ አንደበት የተነገረ ነው።

መልዕክቱ ለአሁኑ ዘመንም ተቀባይነት ያለውና እንደ መሀ ትማ ጋንዲ የመሰሉ የህንድ መሪዎች የኑሮ መመሪያ ያደረጉት ቢሆንም በመሠረቱ ምክሩ የተለገሰው ለአንድ ጦረኛ (ወታደር) ነው። ወታደሩ በሰረገላው ላይ ሆኖ የታላቁን ጦርነት መጀመር እየተጠባበቀ ነው። ተፋላሚዎቹ መብታቸው ያልሆነውን ግዛት በግድ ለመውሰድ የተነሣሱ ቢሆንም ከነሱ መካከል የራሱ ዘመዶች የሆኑ ደጋግ ሰዎች፣ አስተማሪዎችና ባልንጀሮቹ ስላሉ በእነሱ ላይ ስቃይ ከማድረስ ይልቅ መተው ይሻላል ብሎ ይማከራል ግን "የተዋጊ ተግባር መዋጋት ነው እንጂ ሌላ ሰው ስራ ውስጥ ገብቶ መደናበር አይደለም" ለማለት ነው ከፍ ሲል የተጠቀሰው መልስ የተሰጠው።

በጥንቱ የሂንዱ እምነት መሠረት የሰው ዘር በአራት ምድብ ይከፈላል። ዝርዝር ተግባሩም እንደሚከተለው ነው።

አራቱ የሰው ዘር መደቦች

የሰው ዘር ብራህማ፣ ሻትሪያ፣ ቫዚያ እና ሱድራ በመባል ይከፈላል። የብራህማ መደብ የሆኑት ሰዎች ቀሣውስት፣ የተማሩ፣ የሚያስተምሩ፣ ምርጥ የእግዚአብሔር ፍጡሮች ናቸው። ዓለም የእነርሱ ናት፣ የተፈጠረችውም ለእነሱ ድሎት ነው። ሌሎች ሰዎች ከእነርሱ ተቸርዋቸው ወይም ተመጽውተው ሲመገቡ የብራህማ ወገን ግን ሊያጣ ሊቸገር የማይገባ መሆኑ እግዚአብሔር ያዘዘው የፈቀደው ነው።

ሻትሪያ ጦረኛ ወገን ነው። መሣፍንት፣ ነገስታት እና ቤተሰቦቻቸው የጨዋ ዘሮች ናቸው። ሰውን ማስተዳደር አገርን መግዛት፣ ጦርነትን ተዋግቶ በማሸነፍ ህግና ሥርዓትን ማስፈን የእነሱ መብትና ሃላፊነት ነው።

ቫዚያ የተባሉት ደግሞ ኑሮአቸውን በግብርና፣ በንግድ፣ በከብት ርቢ እና ጥበቃ በመሣሠሉት የሚመሩ "ተራ" ሰዎች ናቸው።

ሱድራ የተባሉት ግን አገልጋዮች ናቸው። እነዚህን የነካ ሰው ይረክሣል። በእነሱ ዕቃ መጠቀም፣ ከእነሱ ምግብ መጠጥ መቀበል እንኳ ያረክሳል። ስለዚህ አጸያፊ ናቸው። ከእነርሱ ጋር መቀመጥ መጓጓዝ፣ መመገብ፣ መነካካት፣ ክልክል ነው።

ይህ የብራህማ እምነት ዘመን በመባል ይታወቃል። ዘመኑ ከ1500 ዓመተ ዓለም እሰከ 500 ዓመተ ዓለም ነበረ። አነሣሱ በወራሪ ሀይሎች አማካኝነት ሲሆን እነዚህ በሰሜን በኩል ወደ ህንድ የመጡ ጦረኛ የኢራን ዝርያዎች በተሸነፈው ነባር የጥቁር ህንድ ዝርያ ላይ የጫኑት እምነት ነው። ተሸናፊው ዝርያ ቫዚያ መደብ ሆነ።

ይህ የመደብ ልዩነት በአማልክት ፈቃድ እና ውሣኔ የተደነገገ ነው ተብሎ ይታመናል። ስለሆነም የማኑ ህግጋት በሚል የሃይማኖት መጽሐፍ ውስጥ ይገኛል። ይህ መጽሐፍ ስለ እያንዳንዱ መደብ የስራ ድረሻ በዝርዝር ይተነትናል። ለምሣሌ የንጉስን ተግባር በተመለከተ እንደሚከተለው ያስቀምጣል።

"አህዛብ መሪ በማጣታቸው የተነሣ በፍርሃት ሲበታተኑ እግዚአብሔር ይህንን አይቶ ንጉስ ፈጠረላቸው። ንጉስ ደግሞ ተራ ሰው አይደለም። ከተለያዩ ባህርያትና አካላት ትንሽ ትንሽ ተቆርሶ በማዋሃድ የተገነባ አካል ያለው ነው። ይህም÷

1ኛ- ኢንድራ ከተባለው አምላክ አካል 2ኛ- ከንፋስ 3ኛ-ከጸሐይ 4ኛ-ከእሣት 5ኛ- ከጨረቃ እና ከመሣሉት እየተቆረሰ የተሰራ ነው። ስለሆነም ንጉስ ከሁሉም ፍጥረት በላይ ነው። የእርሱ ዋና ተግባርም የተለያዩ መደቦች ተግባራቸውን በሚገባ እንዲያከናውኑ ማረጋግጥ፣ ሕዝቡን ከጠላት መጠበቅ፣ በማንኛውም ጦርነት ወደ ኋላ ባለመሸሽ ተጋፍጠ መዋጋት፣ እና አሸንፎ መግዛት፣ ማስተዳደር የብራህማን መደብ ሃይማኖታዊ ትምህርት መከታተል፣ ማክበር እና ማስፈጸም ናቸው።

የብራህማን መደብ የስራ ድርሻ መንፈሳዊ ስርዓቶችን መማርና ማስተማር ነው። ስለሆነም ቅዳሴ የሚቀድስ፣ መስዋዕት የሚያቀርብ፣ በአጠቃላይ ከአማልክት የሚያገናኝ የሚያማልድ፣ የሚያስታርቅ እሱ ብቻ ነው።

ሌላው ሕዝብ በመንፈሳዋ ስራ ውስጥ ሚና የለውም። በተለይ ደግሞ የሱድራ መደብ የሚጸልይለት እና የሚሰማው አምላክ የለውም። ቤተጸሎትም የለውም። የእርሱ መኖር ሌሎችን ለማገልገል ብቻ ነው። ለእርሱ ጸሎት አስፈላጊው አይደለም። መንፈሣዊ ስርዓትም አያሻውም። በአንጻሩ የሱ ተግባር ሬሳ መሸከም፣ ጥንብ መግፈፍ፣ የመሣለውን ዝቅተኛ ሥራ ያጠቃልላል። እርግጥ ሱድራ አልኮል የመጠጣት መብት አለው፤ ሊሰክር፣ሊዝናና ይችላል።

ብርህማን ግን አልኮል አይፈቀድለትም። በጣም ንጹሕ መደብ ስለ ሆነ ንጽህናውን ለመጠበቅ ብዙ ጥንቃቄ ይወስዳል። በአጠቃላይ እያንዳንዱ መደብ የራሱን አባላት ንጽህና ይቆጣጠራል። ማህበራዊ ተጽዕኖም ያደርጋል። ምክንያቱም የአንዱ አባል መበከል የመደቡ መበከል ሆኖ ስለሚታይ ነው።

ለብክለት ምክንያት የሚሆኑት ነገሮች ከሌላው ሰው አካል የሚመነጩ (ሽንት፣ ላብ፣ ዐይነ ምድር፣ ምራቅ፣ የሴት የወር አበባ፣ የወንድ ፈሳሽ) ናቸው። ይህ የሌላውን መደብ አባል ከነካ ያረክሣል፣ ምግብ ላይ አርፎ ከተበላ እንዲሁ ያረክሣል። መውለድና መሞትም አካባቢውን ያረክሣል። ሬሣ የነካ፣ ሬሣ ያደረበት ቤት ውስጥ የገባ፣ ሁሉ ርኩስ ይሆናል።

ስለዚህ ምግብ መግዛት፣ ከሰው ጋር አብሮ መጓዝ፣ መነካካት ሁሉ በጥንቃቄ መሆን አለበት። እዚህ ላይ በጣም የሚቸገሩት በይበልጥ

ብራህማን ሲሆኑ ለሌሎች በተዋረድ እየቀለለ ሲመጣ ሱድራ ግን የመጨረሻው ሰለሆነ ግድ የለውም። ይህ ጥንታዊ የሕብረተሰብ አደረጃጀት ስርዓት ሁሉም ሰው የሥራ ድርሻውን አክብሮ በሰላም ለመኖር እንዲችል የተቀየሰ ነው።

የዓለም አፈጣጠር

መሬት የፍጥረት ማዕከል ሆና ሌላው ሁሉ በእርሷ ዙሪያ እንዳለ ተደርጎ የሚወሰደው አስተሳሰብ በሂንዱ እምነት ከቶ የለም።

በአጠቃላይም ፍጥረት ሰፊ እና ጊዜየለሽ ነው። ከመሬት በላይ ስድስት ሰማየ ሰማያት አሉ። መሬት ሰባተኛዋ ስትሆን ከእርሷም በታች እንዲሁ በርካታ ዓለማት አሉ።

የዓለም መፈጠርና መልሶ መጥፋት እንደ ጨረቃ መወለድና መጥፋት ዓይነት ዘለዓለም ሲደጋገም የሚኖር ነው። አንድ ዙሮሽ (ዓለም ተወልዶ እስከመጥፋት ድረስ) በብራህማን (አምላክ) አቆጣጠር አንድ ሙሉ ቀን ነው። ይህም በምድራዊያን አቆጣጠር 4,200 ሚሊዮን ዓመታት ነው። የብራህማን አንድ ዓመት 360 ቀናት (በራሱ አቆጣጠር) ነው። ቪሽኑ የተባለው አምላክ ዕድሜው 100 የብራህማን ዓመት ነው። ዕድሜው ሲያልቅ ከታላቁ እግዚአብሔር ጋር ይዋሃዳል። አሁን ቪሽኑ 51 ዓመቱ ነው። ይህ እኛ የተፈጠርንበት ዘመን መሆኑ ነው።

በአንድ ዓመት ውስጥ 1000 ወቅቶች አሉ። እያንዳንዱ ወቅት 4 ክፍሎች አሉት እኛ ያለንበት ዘመን 4ኛው ክፍል ነው። ይህ ክፍል የተጀመረው በ3102 ዓመተ ዓለም ነበረ። በአጠቃላይ 432,000 ዓመት ይኖረናል። እስካሁን 3102+1996 ዓመታት ስላለፉት ቀሪው የዓለማችን ዕድሜ 426,902 ዓመታት መሆኑ ነው። ከዚያ በኋላ ሌላ ዓለም ይቀየራል።

ምን ጊዜም ዓለም የሚፈጠረው ከቪሽኑ እምብርት ነው። ከዚያም ቪሽኑ አልፎ አልፎ የዓለምን ሁኔታ እያየ ሲያሳዝነው ወርዶ በሰው አምሣል ይፈጠርና ችግሩን ይፈታል። እሰከዛሬ ዘጠኝ ጊዜ ወርዷል። 7ኛው ውልድ ራማ የተባለ ጀግና ሲሆን 8ኛው ክሪሽና ነው። ክሪሽና በጣም ታዋቂና ተወዳጅ አምላክ ነው። በሀጻንነቱ በእግሩ ሲድህ ያለው ምስሉ በይበልጥ በእናቶች ይፈቀራል። በዚህ ወቅት ተአምር መስራቱም ይታመናል። ክሪሽና በወጣትነቱ ዘመን ካምሣ ከተባለ ክፉ አገረ ገዢ ዘመዱ ሸሽቶ ያመልጣል። ከዚያም ርቆ ሂዶ በእረኞች መካከል ያድጋል። በዚህ ወቅት ዋሽንት ይነፋል፣ ያፈቅራል፣ ይፈቀራል፣ (እንደማንኛውም ወጣት)። አማኞቹ ወቅቱንና ሁኔታውን በቅኔ በዜማ በስዕል ይገልጹታል። በይሁዳውያን እምነት መዝሙረ መዝሙር ሰለሞን በመንፈሳዊ መልክ እንደተወሰደ ዓይነት ክሪሽና ከፍቅረኛው ጋር ስለነበረው ሁኔታ በዚሁ መልክ ተወስዶለታል።



ጌታ ክሪሽና - የሂንዱይዝም አምላክ

ከዚያም አድጎ ሙሉ ሰው ሲሆን በታላቁ የማሃባራታ ጦርነት ተሳትፎ የህንድን ክፉ ነገሥታት አሸንፎና አጥፍቶ በ3102 ዓመተ ዓለም የተጀመረውን አዲስ ወቅት ለሰው ልጅ አመጣ።

ስለሆነም ክሪሽና እንደ አባት እንደ አፍቃሪ እና እንደ ወንድም ይከበራል፣ ይፈቀራል። ወደፊትም ይህ 4ኛው ወቅት ወደ መጨረሻው እየከፋ ሲመጣ ደስታና ፍቅር እየቀነሰ ክፋት እየባሰ ሲሄድ ቪሽኑ ተመልሶ በካልኪን ሥም ይመጣል። ክፉዎችንም ያጠፋና ወርቃማ ዘመንን ያነግሣል። (ይህ ከዞራስትራዝም እና ከሌሎች ሃይማኖቶች እምነት ጋር ተመሣሣይነት አለው።)

እንግዲህ በሂንዱይዝም እምነት መሰረት ክሪሽና፣ ራማ ሺቫ የተባሉ አምላኮች አሉ። እነዚህ ዓለምን የመፍጠር የማስተዳደርና የመቅጣት ሥልጣን አላቸው። ከእነሱ በላይ የሁሉ ጠቅላይ የሆነ እግዚአብሔር አለ። ይህ ግን ደግ፣ ክፉ፣ ቀይ፣ ጥቁር፣ የመሣሉት ባህርያት አይወሰኑለትም። መግለጫው መንፈስ መሆኑ ብቻ ነው።

ከአምላኮች በታች ደግሞ በሥልጣን ተዋረድ ሌሎች አሉ። እነዚህ ኡቃቢ፣ አቴቴ፣ አድባር፣ የመሣሉት ናቸው። እነዚህ የድሆችን ችግር የሚያደምጡለት የቤተሰብን ህልውና በተመለከተ የሚከታተሉና የሚጠብቁ ወይም በበሽታ የሚቀጡ ዕለት በዕለት በቅርብ ሆነው የየመንደሩን ሁኔታ የሚከታተሉ ናቸው።

እንደ ክሪሽና ያሉት ግን ትላልቅ ዓለም አቀፍ ተግባሮችን መቆጣጠር እንጂ በየጎጆው እየገቡ የእያንዳንዱን ራሥ ምታት የማዳመጥ ፍላጎት የላቸውም።

ስለዚህ አንድ መንደርተኛ ችግር ሲያጋጥመው በመጀመሪያ ራሱ ሊፈታው ይሞክራል። ካልቻለ ለህመሙ መድሃኒት ለችግሩ ገንዘብ ወይም የዘመድ ድጋፍ ይፈልጋል። ከዚህ ውጭ ከሆነበት (ለምሣሌ ልጅ መውለድ ካልቻለ) ችግሩን ለባለኡቃቢ ወይም ለጠንቋይ ያቀርባል። ይህም በስርዓት የሚከናወን ነው። (ገጽ 6 ይመልከቱ) እንግዲህ የዓለም አፈጣጠርና የስርዓቱ መዘርጋት በዚህ ሁኔታ ነው።

አንዳንድ ዋና ዋና እምነቶች

ሀ) የሳምሳራ ዙሮሽ

አንድ ሰው ሲሞት ነፍሱ ከስጋው ትለያለች። ግን ተለይታ ወዴት ትሄዳለች? መልሱ "ወደሌላ አካል ትገባለች" የሚለው ነው። ምን ዓይነት አካል ውስጥ እንደምትገባ የሚወሰነው ሰውየው በሕይወቱ ዘመን በሠራቸው ሥራዎች ዓይነት ነው።

ሰው ሁሉ የሳሣውን ህግ ማክበርና ሥርዓቱን መጠበቅ አለበት። ለምሣሌ አንድ የሱድራ ጎሳ ተወላጅ የሆነ ሰው ዕድሜውን ሙሉ ታዛዥና

አገልጋይ ሆኖ ተግባሩን በቅንነት ያከናወነ ከሆነ በሚቀጥለው ጊዜ ነፍሱ ሌላ ጎሣ ለማግኘት መብት ሰለምታገኝ ሚቹ ብራህማ ወይም ቫዚያ ሆኖ ሊወለድ ይችላል። በዚያን ጊዜ ደግሞ እሱ በተራው የሱድራ ተገልጋይ ለመሆን መብት ያገኛል ማለት ነው።

በዚሁ ዓይነት ሌሎች ጎሣዎችም ተግባራቸውን በተወሰነላቸው መንገድ በቅንነት ማከናውን አለባቸው። ካላከናወኑ ግን በሚቀጥለው ዘመናቸው ዝቅ ወደ አለ ጎሣ ሊወርዱ ይችላሉ። ወይም ከዚያም ባነሰ ሁኔታ እንስሳ (አይጥ፣ አህያ፣ ወዘተ. . .) ወይም ጭራሽ ግዑዝ ነገር ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ አንድ ብራህማን በትክክል ካልኖረ ሱድራ ሆኖ ወደ ዓለም ሊመለስ ይችላል፣ ወይም አህያ ሊሆን ይችላል ማለት ነው።

በአጠቃላይ ሰው ለሚሰራው ሥራ ሁሉ ዋጋውን ያገኛል። በተለይ ተንኮሉ ብዓላማ ላይ የተመሠረተ ከሆነ በምንም ዓይነት አይታለፍም። ሰው ደግ ከሰራ ይካሣል። ካጠፋም እንዲሁ ይቀጣል። ለሥራው ሁሉ ተገቢውን ዋጋ ያገኛል። ግን ይህ ሁሉ የሚሆነው በወቅቱ አይደለም። በሚቀጥለው ጊዜ ተመልሶ ሲወለድ ነው። ስለዚህ ተበዳይ ቂም በቀል መያዝ አያስፈልገውም።

በዚሁ መሠረት አንድ ሰው አሁን በኑሮው የሚደርስበት መከራ ባለፈው የሕይወቱ ዘመን በሰራቸው ሥራዎች የተነሣ ነው። ሰው ያለ ምክንያት ሱድራ ሆኖ አይወለድም። ያለምክንያት መከራ እና ስቃይ አይደርስበትም። ዋናው ነገር ግን ወደፊት ይህ እንዳይደገምበት መጠንቀቅ ብቻ ነው። ሰው ኑሮውን በትክክል መኖርና በቅንነት ማገልገል አለበት።

አንድ ሰው እንደ ጥፋቱ ደረጃ በተለያዩ እንስሳት መልክ እየተወለደ የሃጢያቱን ዋጋ ሁሉ ከፍሎ ከጨረሰ በኋላ እንደገና ሰው እንዲሆን ሌላ ዕድል ይሰጠዋል። አሁን ጥፋት ካላጠፋ ወይም ሃጢያት ካልሰራ ነፍሱ ወደ መንግሥተ ሰማያት ወጥታ ለዘለዓለም ከብራህማ ጋር በጸጋና በደስታ ትኖራለች።

ይህ እንግዲህ የሳምሳራን ዙሮሽ ሰብሮ መውጣት ማለት ነው። ይህም ነጻ መውጣት ሞክሻ ይባላል። ይህንን ድል ለማግኘት ሰው በዚህ ዓለም ላይ ሲኖር ዓለማዊ ነገሮችን እርግፍ አድርጎ ትቶ መንፈሳዊ ኑሮ መምራት አለበት። በሌላ አነጋገር ቤት፣ ንብረት ዘመድ፣ ገንዘብ፣ ሳይመኝ ሁሉን ንቆናትቶ መኖር አለበት ማለት ነው።

ለ/ <u>ዮጋ</u>

ይህ ከሂንዱ ሃይማኖት የአንዱ ክፍል ተከታዮች ፍልስፍና ሲሆን ዓላማውም መንፈስን ከዓለማዊ ፍላጎቶች በማላቀቅ ሞክሻ (ነጻነት) ማግኘት ነው። አስተምሮቱ የተለያየ የሰውነት እንቅስቃሴና ቁጥጥር በማድረግ መንፈስን ከአካላዊ ሸክም ነጻ አድርጎ ወይም አካልን ሙሉ በሙሉ

ተቆጣጥሮ ከስጋዊ ፍላጎቶች በላይ በመሆን ጸጋን ለመቀዳጀት መቻል ነው።

በቁጥጥር ሥር የሚውል የሰውነት እንቅስቃሴ የተለያየ ዓይነት ነው። ለምሣሌ 1ኛ) አየር መተንፈስን ለማቆም ወይም ለመቆጣጠር መሞከር 2ኛ) ወደ ሆድ የገባን እህል ጨጓራ እንዳይፈጨው ማገድ 3ኛ) ሃይልን (አቅምን) ሁሉ በአንድ ክፍለ አካል (ለምሣሌ ክንድ ወይም ጣት) ላይ አሰባስቦ ተራ ሰው ሊያከናውነው የማይችለውን የጉልበት ስራ መሥራት መሞከር (ለማሣሌ በጣት እንጨት መብሳት ወይም በክንድ ብረትን ማጠፍ)። እዚህ ላይ ዋናው ትኩረት ጎሊናን መቆጣጠር ላይ ነው። አንድ ሰው ትኩረቱን በሙሉ ጣቱ ላይ በማድረግ ሃይሉን ሁሉ ወደዚያ ሊያሰባስብ ይችላል። ስለዚህ እንጨት ሊበሳበት ይችላል። በዚሁ ዓይነት ጨጓራው ላይ በማተኮር እና ምግብን ሳይፈጭ እንዲያልፍ በማድረግ መርዛማ ምግብ እንኳ እንዳይገድለው ሊያደርግ ይችላል። እንዲሁም አየር መተንፈሱን በመቆጣጠር ሶስት ቀን ቢቀበር እንኳ ሳይሞት ተመልሶ ሊወጣ ይችላል። እንደገና ክብደቱን በመቀነስ ወይም በማስወገድ ሰውየው በአየር ላይ ተንሳፎ ወንዝ ሊሻገር ወይም ከተራራ ወደ ተራራ ሊሸጋገር ይችላል። ይህ ሁሉ እንግዲህ እምነት ነው። አንድ ሰው በተገቢው መንገድ ሰውነቱን እንደፈለገው ሊያዘው ከቻለና ጎሊናውን ሊቆጣጠረው ከበቃ ምድራዊ መከራንና ሥቃይን ሊያሸንፍ ይችላል። በአካሉ ላይ ቁጥጥር ሊያደርግ በመቻሉ ሥጋዊ ፍላጎቱን ሊገታ ይችላል። ስለዚህ ከዚህ ዓለም መከራና ፈተና በላይ ይሆናል ማለት ነው። ለሥጋው ተጥሮ ከመሆን ስለወጣ መንፈሣዊ ጸጋን ይጎናጸፋል።

የሃይማኖቱ መከፋፈል

የጎብረተሰቡ የሶሻልና የኢኮኖሚ አቋም እየተለወጠና እያደገ ሲመጣ የተለያዩ መደቦች መፈጠርን አስከተለ። በቀድሞው ጊዜ በአራት ጎሣዎች ብቻ ተከፋፍሎ ሊወሰን ይችል የነበረው አሁን በጣም እየበረከተ መጣ። ከዚሁ ጋር ታድያ የሕዝቡም ፍላጎትና እምነት የተለያየ አቅጣጫን ያዘ። ቅድሚያ ትኩረቱም እንደአካባቢው ሁኔታ የተለያየ ሆነ። በዚህ የተነሣ ሃይማኖቱ ተከፋፈለ። በፍልስፍና ዓይነቱ ተለያየ። ለምሣሌ ከፍ ብለን ያየነው የዮጋ አሰራር የአንድ ክፍል ፍልስፍና ነበረ። ሌሎች ደግሞ ሌላ ፍልስፍና መሰረቱ።

የብራህማ ሃይማኖት ድሆችን አግልሎ እንደነበረ ተወስቷል። አሁን በተደረገው መሻሻል ግን ለሁሉም የእግዚአብሔር አለኝታ እንዲኖረው ማድረግ አስፈላጊ ሆነ። ሰውንና እግዚአብሔርን ማቀራረብም አስፈላጊ ሆነ። ስለዚህ ሰውን ቀርቦ ከኑሮ መከራ የሚያድነው አዳኝ አምላክ (መሲህ) እንዲኖረው ተደረገ። በክርስቲያን እምነት መድሃኔ ዓለም እንደሚባለው ዓይነት በሂንዱይዝም እምነት ለምሣሌ ክሪሽና ከአማልክት በአንዱ

አምሣል የተፈጠረ ሆኗል። ክሪሽና ምድር ላይ ተፈጥሮ በጆግንነት የኖረ እዚሁ የሞተ በጣም ደግ ሰው ነበረ። አሁን ክሪሽና ሰውን ሁሉ ከመከራው ሊያወጣው የሚችል አዳኝ አምላክ ነው። ሌሎችም ደግሞ በየጎሣው በየብሄረሰቡ የሚታመንባቸው የተለያዩ አማልክት አሉ። ተግባራቸውም እንደ ህብረተሰቡ አኗኗር (ዘላንነት፣ ነጋዴ፣ ገበሬ፣ . . .) የተለያየ ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሆኖ የሂንዱይዝም ተከታዮች በጋራ የሚያምኑባቸውና የሚያከናውኗቸው ተግባሮች አሏቸው።

አፅማደ ምስጢራት (የሂንዱይዝም)

አማኞች ቅድስና እንዲያገኙ ከአደጋ እንዲጠበቁ ከብክለት (እርኩስነት) ነጻ እንዲሆኑየሚያከናውኗቸው ስነ ስርዓቶች አሉ። ሰው የሚረክሰው ከሌላው ሰው በሚመነጩ ነገሮች ነው። ከዚህ ለመከላከል የተለያዩ ዘዴዎች አሉ። ለምሣሌ ያህል አንድ የሻዝያ መደብ አባል የሆነ ሰው በስራው ነጋዴ ቢሆን አንድ የሱድራ አባል ሱቁ እንዲገባ አይፈቀድለትም። ዕቃ ለመግዛት የፈለገ ሰሱድራ አባል ውጭ ቆሞ የሚፈልገውን ዕቃ ይናገርና ገንዘቡን አስቀምጠ ርቆ ይቆማል። ነጋዴውም እቃውን አድርሶለት ገንዘቡን ወስዶ ሲመለስ ሱድራው ቀርቦ ዕቃውን ይወስዳል። ይህን የመሰሉ ልምዶች አሉ።

ከዚህ ባሻገር ዛሬም በሰፊው የሚሰራባቸው ማህበራዊ ስነ ስርዓቶች አሉ።

ሞት

የሂንዱ እምነት ተከታይ በሚሞትበት ጊዜ አስከሬኑ ይቃጠላል። እርግጥ ህጻን ወይም ጻድቅ ከሆነ ሊቀበር ይችላል። ሌሎቹ ይቃጠሉና አመዱ ወደ ወንዝ ይበተናል። በተለይ ጋንጀስ የተባለው ትልቅ ወንዝ (ጅረት) ቅዱስ ነው። እዚያ ውስጥ ገብቶ መታጠብም ሆነ ዳርቻው መሞት ከብክለት ያነጻል።

ሰው ሲሞት ነፍሱ በትክክል ካልተሸኘች እንደገና ሌላ ስጋ ለብሳ ለመወለድ ስለማይቻላት እዚያው አካባቢ እየተዘዋወረች ታስቸግራለች። እንደ ጣዕረ ሞት እየታየችም ቀሪውን ወገን ታሰቃያለች። ስለዚህ የአቀባበር ስነ ስርዓቱ በትክክል መፈጸም አለበት። ለምሣሌ አስከሬኑ እንጨት ተረብርቦበት እንዲቃጠል ሲዘጋጅ እሣቱን የሚለኩሰው ታላቅ ወንድ ልጅ መሆን አለበት። ስለዚህ ወንድ ልጅ መውለድ መቻል ትልቅ ግዴታ ነው። ስለዚህም ነው ሚስት ወንድ ልጅ ካልወለደች ባልየው ሌላ

ሚስት ለማግባት የሚገደደው።በወንድ ልጅ እና በሴት ልጅ አስተዳደግ ላይም ጉልህ አድልዎ የሚታይበት አንዱ ምክንያት ወንድ ልጅን የማሣደግ ማህበራዊ ግዴታ ስላለ ነው።

ልደትና ጋብቻ

ሕጻን ሲወለድ እትብቱን ለመቁረጥ ስነ ስርዓት አለው። መውለድ የመርከስ ሁኔታን ስለሚያስከትል በሰድስተኛው ቀን እናትና ልጅ ይባረካሉ፣ ቤቱም ከርኩሰት ይጸዳል። ለልጁም ሥም ይወጣለታል። በዓመቱ ራሱ ይላጫል ጆሮው ይበሳል።

ጋብቻን በተመለከተ የሁሉም አማኝ ግዴታ ነው። ለዘር መተላለፍ (በተለይም ለወንድ ልጅ መወለድ) ጋብቻ አስፈላጊ ነው። ዋናው የጋብቻ ስነ ስርዓት ቅዱስ እሳት የሚባለውን ሰባት ጊዜ መዞር (በዛሬ ዘመን ደግሞ ወደፊት ሰባት እርምጃ መውሰድ) ነው። ጋብቻ በሀጻናት መካከልም ይከናወናል። እዚህ ላይ ዋናው ችግር ከሀጻናቱ አንዳቸው በሚሞቱበት ጊዜ ሌላው ፈት ሆኖ መገኘት እና ለማያውቀው/ለማታውቀው "የትዳር ጓደኛ" ሲጸልዩ መኖር ነው።

የሃይማኖቱ ዕድገት

የሂንዱ ሃይማኖት ባለፉት ሶስት ሺ ዘመናት በነበረው ሁኔታ ትልቅ ማህበራዊ አገልግሎት ሰጥቷል። በመሠረቱ እምነቱ ሰላማዊ መንገድን የሚከተል ነው። አንድ ሰው ቢቸገር ቢሰቃይ ወይም ቢታመም ለዚህ ለችግሩ መንስዔውን ምክንያት ለማወቅ ግራ አይገባውም። ባለፈው ጊዜ በሰራው ሃጢያት ምክንያት ስለሆነ ወደፊት ደግሞ ሌላ ዕድል እንዳለው ስለሚያውቅም ተስፋ አይቆጥርም። ወደ ትጥቅ ትግልም አያስብም።

ዛሬ ግን በሥልጣኔ ዕድገት የተነሣ የሕዝብ ኤኮኖሚ አቋም እየተለወጠ መጥቷል። ደሃው ሀብታም ሆኗል። ለሀመምም መድ ሃኒት ተገኝቷል። ስለዚህ የእምነቱ መሠረት የሆነው የመደቦች ልዩነት እየተናጋ ነው። በዚህ የተነሣ የእምነቱ ይዘት መሻሻል እንዳለበት ታየ።

በተለይ የቡድሂዝም ሃይማኖት መጥቶ ሕዝቦችን ሁሉ በአንድ ዓይነት ሲያያቸውና ጸጋ እና መርገምት የሚመጡት በቀጥታ ሁሉም ሰው እንደየሥራው ነው ሲል የብራህማ መደቦች ስልጣ ናቸውና መከታቸው ሊቀርባቸው ስለሆነ ይዘቱን ማሻሻል ግዴታ ሆነባቸው። ስለሆነም ሂንዱይዝም ተሻሻለ ስለዚህ ዛሬ ድሆችን ከማግለል ይልቅ ሰው ሁሉ የእግዚአብሔር አለኝታ እንዲኖረው ሁሉም ቤተ ጸሎት እንዲኖረውና በእኩልነት ዳኝነት እንዲያገኝ እየተደረገ ነው።

ሂንዱይዝምን አጉልቶ የሚያሣየው ሌሎችም ልዩ ባህርያት አሉት። እምነቱ የህንዶች ለመሆኑ የቃሉ ስያሜ ራሱ ያስረዳል። ሂንዱ ማለት በኢራን ቋንቋ ህንድ ማለት ነው መደቦችም በአራት ስለተከፈሉ በሌላው

ዓለም ላሉት ሰዎች የሚገጥም አይደለም። በሌላ አነጋገር ከአራቱ መደቦች ውጭ የተወለደ ሰው ቦታ የለውም ማለት ነው።

ሂንዱይዝም ቀኖና የለውም። ከሰማይ የወረዱ ትዕዛዛት የሉትም። ቅዱስ መፅሀፍ እንደ እግዚአብሔር ቃል የሚወሰድ የለም ለቤተመቅደሶችም ሆነ ለቀሳውስት ቦታ የለውም። የእግ ዚአብሔር ሚናም በሕይወታቸው ውስጥ ጎልቶ አይታይም።

እርግጥ ክሪሽና ዛሬ እንደ አዳኝ (መድሃኔ ዓለም) እየተቆጠረ መጥቷል። ቀድሞ ምድር ላይ ተወልዶ በጀግንነት የኖረና የሞተ ሰው ዛሬ ሰውን ከመከራው ሊያወጣው የሚችል ሆኗል። የጥንቱ እምነት የቬዳ አምላክ ኢንዲራ ዛሬም ይወደዳል። ኢንዲራ ጋንዲ የተባለችው የህንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ስሟ የተሰጣት ከዚሁ በመነሣት ነው) ሺቫ ሌላው አምላክ ነው፣ ጸም ጸሎት ይደረግለታል። በዓላትም አሉት። ተከታዮቹም ብዙ ናቸው።

በሌላ በኩል ዛሬም በላሞች ይመለካል። ላም አትመታም ስጋዋም አይበላም ቅዱስ ናትና። ስለሆነም ዛሬም እንደልቧ ከተማ ውስጥ እየተዘዋወረች ስታስቸግር ትታያለች።

ሌላው ዓይነት አምልኮ በውሃ ማምለክ ነው። ውሃ ያነጻል፣ ስለሆነም በውሃ መታጠብ በተለይም ደግሞ (ቀደም ሲል እንዳየነው) ጋንጀስ በተባለው ጅረት ውሃ መታጠብ ከሃጢያት ያነጻል። ስለዚህ ጋንጀስ ወንዝ ዳርቻ መሞት ማለት መታደል ነው።

ሰው ሲሞትም አስከሬኑ በእንጨት ክምር ውስጥ ተደርጎ መቃጠልና ቅሪቱ ወደ ጋንጀስ ወንዝ መበተኑ ታላቅ ዕድል ነው።

እነዚህ ዓይነት እምነቶች በርካታ ተከታዮች ያሏቸው ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ አናሳ ተከታዮች ያሏቸው ብዙ አሉ። ከፍ ብለን የተመለከትነው የዮጋ ፍልስፍና ተከታዮች አንዱ አናሳ ክፍል ናቸው። የእነዚህ መለያ ምልክት በአንገታቸው የብረት ቀለበት ማጥለቃቸውና በባላገር ያሉት ሰዎች በሚተኙበት ጊዜ ጭንቅላታቸውን አፈር ውስጥ መቅበራቸው ነው። በስነ ስርዓት ሲቆሙም ሁለት እጆቻቸውን ወደ ሰማይ በማንሣት ነው።

ሌላው በብዙዎቻችን ዘንድ የሚታወቀው አናሳ ቡድን ሲክ (Sikh) የሚባለው ክፍል ነው። እነዚህ ሰዎች ጸጉራቸውን አይላጩም፣ አይቆርጡም፣ ራሣቸውን እንደቄስ በንጹህ ጥምጥም ሸፍነው ይሄዳሉ። አለባበሳቸውም ባህላዊ ደንብ አለው። ለመለያ ምልክትም በእጃቸው ላይ ልዩ የብረት አምባር ያጠልቃሉ። በታሪክ እንደተመዘገበውም ሲክ የጠሩ ዘር ናቸው።

እንግዲህ በዚህ ዓይነት ሂንዱይዝም አንድ ወጥ ሃይማኖት አይደለም። እርግጥ መሰረታዊ የሆኑ አንድ ዓይነት እምነቶች አሉት። እነዚህንም ለማጠቃለል፦

ሀ- በጥንታዊ የእምነትና ስነ ምግባር መመሪያ መጽሐፍ (ቬዳስ) ማመን፣

ለ- በመልሶ መወለድ (ሳምሳራ) ማመን፣

ሐ- ብራህማ ሁሉን አቀፍ ሁሉ-ገብ መንፈስ መሆኑና እንደአጠቃላይ ነፍስ የሚቆጠር መሆኑ፣

መ- ሕይወትን ሁሉ በማክበር በሌላው ላይ ጉዳት ላለማምጣትና ሰላማዊ ኑሮ ለመኖር መጣር የመሣሉት ናቸው።

እስከቅርብ ጊዜ ድረስ የጎሣዎች በአራት ምድብ ተከፍሎ መፈጠር በሰፊው ይታመንበት የነበረ ቢሆንም ዛሬ እምነቱ እየተለወጠ መጥቷል። እስከዛሬም ይህ ጥንታዊ ሃይማኖት አለም አቀፍ ይዘት ያጣው በዚሁ የጎሣ ጥያቄ ችግር ነው። ከህንድ በቀር ሌላ ዘር የሆነ ሰው አማኝ አባል ሊሆንበት የማይችበት ሁኔታ ነው።

አሁን ግን የህንድ መንግሥት ይህንን የጎሣ ልዩነት ለማሻሻል ብርቱ ጥረት እያደረገ ነው። ለምሣሌ የሱድራ ጎሣ እንደማንኛውም የህንድ ዜጋ ከሌሎች ጋር በእኩል ደረጃ በሆቴል የመብላት፣ በትራንስፖርት የመጓዝ፣ ንግድ የመነገድ፣ በአጠ ቃላይ በማህበራዊ ኑሮ የመሳተፍ መብቱን ማስከበር የመንግሥት ግዴታ ነው። የሃይማኖት ሊቃውንትም ቢሆኑ እምነቱን ለማሻሻል የራሣቸውን ጥናት እያካሄዱ ነው። የጥንቱን የሃይማኖት መጽ ሐፍት እንደገና በማጥናትና በመመርመር ከውስጡ ትምህርታዊ የሆነውን ያስቀራሉ፣ እንደዘመኑ ሁኔታም ያብራራሉ። ለምሣሌ ከፍ ሲል በመግቢያ ርዕሱ ላይ የተጠቀሰው መመሪያ በወቅቱ የተሰጠው ለቫዝያ ወታደር ሲሆን ይዘቱ መደባዊ ነበረ። ይህ መመሪያ ግን በአጠቃላይ መልኩ ዛሬም ለሰዎች ሊያገለግል ይችላል። ስለዚህ በዚህ መልኩ ይወሰዳል ማለት ነው።

እንዲሁም ዛሬ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሐዋሪያዊ ተግባር በማከናወን ላይ ያለው የተሻሻለው አንዱ የሂንዱይዝም ሃይማኖት ክፍል "ራማ ክሪሽና" በሚል ሥም ተለይቶ የሚታወቅ ሲሆን ይህም ሃይማኖት ፍልስፍናውን (ወይም እምነቱን) እንደሚ ከተለው ያስነብባል። ሃይማኖቶች ሁሉ (የአለፉትም ሆኑ የአሁኖቹ) ትክክለኛ ነበሩ ናቸውም። ማንም ሰው በኖረበት አካባቢ እና በኖረበት ዘመን የነበረው (ያለው) ሃይማኖት ለተጨባጭ እውነታ ትክክለኛ መግለጫ ነበረ (ነው)። ይህ እንግዲህ ያለፈውን እምነት ላለማውገዝ እና ብሎም በአግባቡ ለማደስ የታቀደ ነው። አሁን ይህ ሃይማኖት በጎሣ ልዩነት ማመንን በአፊሴል ትቷል፣ የሰውን እኩልነትና በራስ የመተማመንን መንፈስ ያስተምራል፣ ያራም ዳል፣ ለድሆች ሲል የእርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ድርጅ ቶችን በመደገፍ እንቅስቃሴ ያደርጋል።

በዚህ ዓይነት ሌሎችም የሃይማኖቱ ይዘቶችና አምልኮዎች እየተለዩ እየተስተካከሉና እየተሻሻሉ ለአሁኑ ትውልድ በሚበጅ መልኩ እየተዘጋጁ ነው።

ቡድሂዝም

የቡድሃ መንፈሣዊ አስተምሮት

ቡድሃ እውነታው ተገለጸለት። ከዚያም የመጀመሪያዎቹን አምስቱን ደቀመዛሙርቱን ሰብስቦ እንዲህ ሲል ነገራቸው÷

በዚህች ዓለም ላይ በአራት ክፍሎች ሊጠቃለሉ የሚችሉ እውነታዎች አሉ÷

1. መከራ የሰው ልጅ ዕጣ ፈንታ ነው።

ሕይወት በመከራ የተሞላች ነች። መወለድ መከራ ነው። እርጅና መከራ ነው። ሞት መከራ ነው በሽታም እንዲሁ ነው፤ ከተፋቀሩት ጋር መለያየት፣ የተመኙትን ለማግኘት አለመቻል የመሣሉ የመንፈስ ጭንቀቶችም ጭምር።

2. ለዚህ መከራ መነሻ ምክንያት አለው። ይህም ምክንያት ሰው ለመኖር ያለው ጉጉት ነው። በሌላ አነጋገር በምድራዊው ዓለም ውስጥ ስሜቱን ለማርካት እና ለድሎት ሲል ኑሮን ለማ መቻቸት ያደረበት ፍላጎት ወይም ግፊት ነው።

3. ይህ መከራ ደግሞ ሊወገድ የሚችለው የሰው ልጅ ይህን ጉጉት ሊቆጣጠር ሊያሸንፍና ሊያስወግድ ሲችል ብቻ ነው። ይህም ወደ ዘለዓለማዊ ሰላምና እርካታ (ኒርቫና) ያመራዋል።

4. ይህንን መከራ ለማስወገድም ስምንት መንታ መንገዶች ስለ አሉ እነሱን መከተል ነው። እነሱም÷

ሀ- ትክክለኛ አመለካከት÷ ይህም ከተራ ቁጥር 1 - 4 የተዘረዘሩት እውነታዎች መኖራቸውን መገንዘብ፣

ለ- ትክክለኛ አስተሳሰብ÷ ስጋዊ ፍላጎትን ተቆጣጥሮ ከራስ ወዳድነት ከክፉት ስራና ሌላውን ከመጉዳት መቆጠብ፣

ሐ- ትክክለኛ አነጋገር÷ ከስድብ፣ ከውሸት፣ ከብልግና÷ አነጋገር መራቅ፣

መ- ትክክለኛ ተግባር÷ ከስርቆት እና ከመሣሰሉት ከመጥፎ ተግባራት ሁሉ መራቅ፣

ሠ- ትክክለኛ አኗኗር÷ ሰውን በሚጎዳ ተግባር፣ ሴትና ባሪያን ለአገልግሎት በማቅረብ በመሣሉት ኑሮን ከመምራት መቆጠብ÷

ረ- ትክክለኛ ጥረት÷ ወደ መጥፎ የሚያመራ አስተሳሰብ እንዳይነሳ መጣር የተነሱትንም ቢሆን ማስወገድ፣ ጥሩ አስተሳሰብ እንዲፈልቅ መጣርና የተነሱትንም ማዳበር፣ ማጎልበት፣ በስራ ላይ ማዋል፣

ሰ- ትክክለኛ ግንዛቤ÷ የስጋ ደካማነትን በትክክል መገንዘብና የሚያድርበትን ፍላጎት አሊያም የተስፋ መቁረጥ ስሜት ለመቆጣጠርና ለማሸነፍ መቻል ደካማ ስሜትን በስ ሜትነቱ መገንዘብ፣ ንጹህ ሀሊናን ማዳመጥና መከተል፣

ሸ- ትክክለኛ ትኩረት÷ የመስከር፣ የመፍዘዝ፣ የመስነፍ፣ የመቅነዝነዝ፣ የመተንኮል የመሣሠሉትን መጥፎ ስሜቶች ለማስወገድ ተገቢውን ትኩረት መስጠት። እነዚህ መሰ ናክሎች ዓይነ ህሊና ይጋርዳሉ። ጥልቅ ዕውቀት ለመገ ብየት ጥበብ ለመቅሰም ወደ ዘላለማዊ ሰላምና ደስታ ለመዝለቅ እንቅፋት ይሆናሉ።

ቡድሃ ደቀመዛሙርቱ ይህንን እንዲገነዘቡ በሰፊው እንዲመ ራመሩበትና እንዲያዳብሩት ለሌሎችም እንዲያስተምሩ ዋቸውና ወደ ቅዱስነት መንገድ እንዲመሯቸው አስተማረ።

በአጭር ጊዜ ውስጥ የደቀመዛሙርቱ ቁጥር እየጨመረ እሰከ ሃምሣ ደረሰ። ከዚያም በለጠ። ቡድሃም ትምህርቱን እየጨመ ረላቸው ሄደ። ለአርባ አምስት ዓመታት በመዘዋወር ሰማንያ ዓመት ዕደሜ እስኪሆነውም በህዝብ መካከል እየተዘዋወረና እያስ ተማረ ኖረ።

ጉተማ

ጉተማ የተወለደው በ6ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ላይ ምናልባትም በ536 ዓመተ ዓለም አካባቢ ነው። ቦታው በሰሜን ህንድ በሂማላያ ተራራ ግርጌ ነው። እናቱ በወለደችው በሳምንቱ ስለሞተችበት በአክስቱ እና በእንጀራ እናቱ እጅ አደገ። ጉተማ የንጉስ ልጅ ነበረ። አባቱ የሻትሪያ (ጦረኛ መደብ) ወገን የሳኪያን ጎሣ በመሆኑና እነዚህም የጸሀይ ዝርያ ሆነው ስለሚቆጠሩ ጉተማም የሳኪያን ሊቅ፣ የጸሀይ ዝርያ የተባሉ ቅጽል ስሞች ነበሩት። ጉተማ በአስተዳደጉ በጣም እንክብካቤ የነበረው ልዑል ነበረ።

አባቱ ንጉሥ ሱዩዳና በምንም ዓይነት መንገድ ሕጻን ልጁ ሃዘን የተባለ ነገር እንዳያጋጥመው እና እንዳያውቅ ስለወሰነ በቤተ መንግሥቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ሁሉም ነገር እንዲሟላለት አደረገ። ልዑሉ ከግቦሃ፣ ከፈንጠዚያና ከፍጹም ደስታ በስተቀር አያውቅም ነበረ። ስለሆነም በዓለም ላይ ስቃይ በሽታ፣ ሞት የመሣሠሉት ክፉ ነገሮች መኖራቸውንም አላወቀም። በዚህ ሁኔታ ትዳር ይዞ ወንድ ልጅም ወልዶ እስከ 29 ዓመት ዕድሜው በፍጹም ተድላ እና ደስታ ኖረ።

በዚህ የተነሣ ለመጀመሪያ ጊዜ በውጪው ዓለም ያያቸው አራት ገጠመኞች ስሜቱን ክፉኛ ረበሹት። መጀመሪያ የታመመ ሰው አየ። ከዚያ ሽማግሌ አጋጠመው። ቀጥሎ ወደ መቃብሩ በመወሰድ ላይ ያለ አስከሬን አየ። ከዚያም በሽታ እርጅና እና ሞት የሰው ልጅ ዕጣ ፈንታ መሆኑን ተገነዘበ። በመጨረሻም በምናኔ ላይ ያለ ደሃ መነኩሴ ተመለከተ። ይህ መነኩሴ ዓለማዊውን ነገር ሁሉ ትቶ በድህነት ሲኖር እንዴት መንፈሳዊ

ሰላም እና ጸጋ ተቀዳጅቶ እንደሚኖር አስተዋለ። ጉተማም ሕይወቱን በዚህ መንገድ ለመምራት ወሰነ። በጾምና በጸሎት ስጋዊ ፍላጎቱን አድክሞ መንፈሱን ነጻ አውጥቶ ስለ ሕይወት ምስጢር ለማወቅ ተነሣሣ።

ስለሆነም ቤተመንግሥቱንና ቤተሰቡን ትቶ በመጥፋት ምናኔ ገባ። ለስድስት ወይም ለሰባት ዓመት በጾም በጸሎት አሳለፈ። የዚህን ዓለም ምንነት ለማወቅ፣ እውነታን ለመጨበጥ እና እውነተኛ ብርሃንን ለማየት ሰውነቱን ለስቃይ ዳረገ። ግን ምንም አልተጨበጠለትም። ይህ ሁሉ ጾም እና ጸሎት ይህ ሁሉ መከራ እና ስቃይ ምንም አላተረፈለትም።

ስለዚህ ጉተማ ሌላ መንገድ ፈለገ። ትንሽ ትንሽ ምግብ እየተመገበ ከሌሎች መናንያን ተለይቶ ብቻውን ለበርካታ ሳምንታት በአንድ በለስ ዛፍ ስር ተቀምጠ ያሰብ ገባ። በዚህ ጥልቅ አሳብ ላይ እያለ አንድ ቀን ንጋት ላይ በድንገት አንድ ነገር ተከሰተ።

ያለምንም አስተማሪ ያለምንም ረዳት ብቻውን በራሱ ጥረት ብርሃን በራለት። ከድንቁርና ወደ ዕውቀት፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ ከሚችነት ወደ ዘላለማዊ ህያውነት ተሸጋገረ። ይህ ክስተት በቅጽበታዊ ሁኔታ እንደ ነጸብራቅ በላዩ ላይ ረበበበት።

ከዚያን ዕለት ጀምሮ ጉተማ ቡድሃ ሆነ ቡድሃ ማለት በራሱ ብርታት ያወቀ የነቃ ህያው የሆነ ማለት ነው።

እንግዲህ ቡድሃ ይህንን የብርሃን መንገድ ለሌሎች ለማድረስ ተነሣ። እየዞረም ማስተማር ጀመረ።

መጀመሪያ የሄደው ቀድሞ ለ6 ዓመታት አብረውት ወደ ነበሩት አምስቱ መነኮሳት ነው። እሱ ጾሙን አቋርጠ መብላት ስለጀመረ ተጣልተውት የሄዱ ነበሩ። በኋላም ቀርቦ አስተማራቸው። እንዲህም አለ።

"የሞትን ሽረት አስተዋልኩ። የሃጢያትን ምንጭ አወቅሁ። ለሰው ልጅ በተንደላቀቀ ኑሮ መዋኘት ዋጋ የለውም። በስቃይና በመከራ ሰውነቱን መበደልም ጥቅም የለውም። ትክክለኛው ጎዳና መሃል መንገዱ ነው። እጅግም ለምድራዊ ምኞት ሳይገዙ እጅግም ራስን ሳያሰቃዩ መካከለኛ ኑሮ መኖር ነው"።

የደቀመዛሙርቱ ቁጥር ወደ ስድሳ አደገ። ትምህርቱም እየተሰፋፋ መጣ። ከዚህን ጊዜ ጀምሮ እስከዕለተ ሞቱ ድረስ ማራ (ሰይጣን) በሚል ስያሜ የሚታወቀው ውስጣዊ መንፈስ ይፈታተነው ነበረ። ቡድሃ ግን እስከ መጨረሻው ተቋቋመው።

ቡድሃ በእግሩ እየተዘዋወረ ሲያስተምር አንድ ወቅት በመንገድ ላይ 30 ጉልማሶች አጋጠሙት። "አንተ ሰው ሆይ አንዲት ሴት በዚህ ስታልፍ አይተህልን? አሉት። ወንዝ ውስጥ ገላቸውን እየታጠቡ ሳሉ አንዲት ሴት የአንዳቸውን ልብስ ሰብስባ ሰርቃ አምልጣ ነበርና። ቡድሃም ሲመልስ "እናንተ ሆይ ሴቲቱን ለምን ትሻላችሁ? ከእርሷ ይልቅ ራሳችሁን ብትፈልጉ ምንኛ በተሻለ ነበረ።" አላቸው ይህ መሰረታዊ ትምህርት

የሚያስገነዝበው ሰው ራሱን የሚያገኘው ራሱን ሲጥልና ምድራዊ ሃብቱን ንብረቱንና ፍላጎቱን ንቆ ትቶ ክቡር እውነታን ሲከተል ነው። ወዲያው ሰዎቹ ደቀመዛሙርቱ ሆነው ተከተሉት።

ቀጥሎም ቡድሃ ሌሎች አንድ ሺህ የብራህማ መነኮሳትን አስተምሮ አሳመናቸው። እነሱም እምነቱን ተቀበሉ። ንጉሥ ቢሣራ ይህንን ባየ ጊዜ ለሃይማኖቱ ማስፋፊያ ማዕከል የሚሆን ሰፊ ቦታ ሰጣቸው። የቡድሃም ተከታዮችና አማኞች እየበረከቱ መጡ።

የሃይማኖቱ ዓይነተኛ መለያዎች


ይህ ሃይማኖት ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋር ሳይጣላ በስምምነት ለመኖርና እነርሱን አቅፎ ለማደግ የቻለ ነው። ዋናው ትኩረቱ አማኞች ዘለዓለማዊ ሕይወት ሊያገኙ የሚችሉት ራሣቸው ህሊናቸውን መርምረው እውነትን ሲደርሱበት ነው በሚለው ላይ ነው። ሰው በሌላ ሰው አማካኝነት ወይም አማላጅነት አይድንም። የደህንነት መንገድ ቀጭን እና ቀጥታ ናት። እንደምንም ታግሎ በርትቶ ያችን ለመውጣት የራስ ትግልን ይጠይቃል። ሌላ አካል አይረዳም። ቡድሃ ራሱ ሊረዳ አይችልም። አንድን ሰው የሚያ ድነው የራሱ ተግባር ሆኖ ይህም በግል ጥረቱ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ስለጸሙና ስለጸለዩ የሚሆን አይደለም። ወሳኙ የሕይወት ተግባር ብቻ ነው።

ሌሎች ሃይማኖቶች መጸም መጸለይን ትኩረት ይሰጡታል። እግዚአብሔርን ማመስገንን አስፈላጊ ጉዳይ ያደርጉታል። የቡድሃ እምነት ተከታዮች በዚህ አያምኑም። በሌላ በኩል ግን ይህንን ከሚያደርጉት ጋርም ጥል የላቸውም አለአስፈላጊ አድርገው ይቆጥሩታል እንጂ አያጣላቸውም።

ስለሆነም ከሌሎች ጋር የሚያቃርን ነገር የላቸውም። በአካባቢው የነበሩ ሕዝቦች ይህንን ሃይማኖት ከራሣቸው ጋር ደምረው አብረው ማስኬድ ስላላስቸገራቸው ቅራኔ አልነበረም።

የብራህማን እምነት ተከታዮች በመልሶ መወለድ (ሳምሳራ) ያምናሉ። አንድ ሰው በህይወቱ ዘመን ሃጢያት ሰርቶ ከነበረ ያሃጢያቱ በምንም ዓይነት ዋጋ ሊከፈልበት ይገባል እንጂ በይቅርታ ወይም በመረሣት አይታለፍም። ግፈኛ ሰው ግፉን መክፈል አለበት። ስለዚህ ለግፍ ተመጣጣኝ ቅጣት እንዲያገኝበት በተገ ቢው ቅርጽ ተመልሶ ይወለዳል (ለምሣሌ ምቀኛ ከሆነ እንደ አይጥ ይወለዳል ሰነፍ ሰራፊት ከነበረም አህያ ይሆናል። ወዘተ...

በዚያ ኑሮው ለሃጢያቱ ዋጋ ይከፍላል። የተለያየ ሃጢያት ከሰራም በተለያየ ቅርጽ እየተወለደ ዋጋውን ሁሉ ይከፍላል። ከዚያም ተመልሶ የሰው ልጅ በመሆን ይወለድና ሌላ ዕድል ይሰጠዋል። አሁንም ዕድሉን ካበላሸ ዙሮሹ ይቀጥላል። ከዚህ ዙሮሽ የመከራ እና የስቃይ ሽክርክሪት



ጌታ ቡድሃ - ምህረት ወይም ይቅርታ የማይኖርበት ሁሉንም በስራው ብቻ በትክክል የሚዳኝ የቡድሂዝም አምላክ

ሊገላገል ያለው ዕድል ሰው በሆነ ጊዜ መልካም ሰርቶ ወደ ኒርቫና መሸጋገር ነው።

የቡድሃ ሃይማኖት ከዚህ ጋር ጥል አልነበረውም። ቡድሃ ራሱ ሲሞት አስከሬኑ በዚሁ ባህል መሠረት ተቃጥሎ ወደ ቅዱስ የጋንጀስ ጅረት ተበትኗል። ሌሎች የተለያዩ የቻይና የጃፓን እና የሌሎች አካባቢው እምነቶችም ከቡድሃ ፍልስፍና ጋር አብረው ኖረዋል። የቡድሃ ሃይማኖት ስለኒርቫና (መንግስተ ሰማያት) የሰጠው ዝርዝር መግለጫ የለም። ሞት የሌለበት፣ ፍስሃና ደስታ የሰፈነበት ሰላምና ጸጋ የነገሰበት ሁኔታ ነው፣ ከማለት በስተቀር ስለ አኗኗሩ ሁኔታ አልገለጸም። መንግስተ ሰማያት ውስጥ ምን እየተሰራ ይኖራል? እርስ በርስ መተዋወቅ መጫወት ይኖራል ወይ? ሌላስ ምንና ምን ይኖራል? ለሚሉት የሰዎች ጥያቄዎች ዝርዝር ሁኔታ ውስጥ አልገባም። እንዲያውም መልስ የሰጠው በሚከተለው ምሳሌያዊ አነጋገር ነበረ። አንድ ሰው በመርዛማ ቀስት ተወግቶ እያለ ወደ ሐኪም ቤት የሚሄድበትን መንገድ ጠይቆ ወደ ዚያው መሄድ እና ሕይወቱን ከሞት ለማዳን መቸኮል አለበት እንጂ ይህንን ትቶ ጠላቱ ማን እንደሆነ ትውልዱ ጎሣው የት እንደሆነ ከማን እና ከማን እንደተወለደ ለመመራመር ቅድሚያ መስጠት ቢከጅል ሕይወቱ ታልፋለች። ስለዚህ የዘለዓለም ሕይወት ለማግኘት የሚፈልግ ሰው በማይረቡ ጥያቄዎች ከመጨነቅ ይልቅ ትክክለኛውን ጎዳና ተከትሎ ወደዚያ ቢሄድ ይበጀዋል።

የእምነቱ አተረጓጎም ልዩነት

ቡድሃ የሰጠው አስተምሮት ሁሉ የተላለፈው በቃል ነበረ። ይህ እንግዲህ ከ2500 ዓመታት በፊት ነበረ። ቡድሃ እንደሞተ አምስት መቶ ያህል የሃይማኖት ሊቃውንት ተሰባስበው አስተምሮቱ ሳይበታተን እና ሳይረሳ ወይም ሳይበረዝ በፊት ተስማምቶ በአንድ መልክ ለማስቀመጥና ለትውልድ ለማቆየት ሲሉ የሚያስታውሱትን ሁሉ ደገሙ። ይህም ተጠናቅሮ በስተኋላ ቲፒታካ በተባለ መንፈሳዊ መጽሐፍ ተጠቃለለ። ይህ ቃል በተራ ትርጉሙ ሶስት ቅርጫቶች ማለት ሲሆን በመጀመሪያው የፅውቀት መያዣ ቅርጫት ውስጥ የተቀመጠው የገዳማት አሰተዳደርና የመነኩሳት ሥነ ምግባር መመሪያ ሲሆን በሁለተኛው ውስጥ ደግሞ የቡድሃ አስተምሮት እና በኋላም ደቀመዛሙርቱ የጨመ ሩበት ነበረ። ሶስተኛው የመንፈሳዊ ቃላት ትርጉምና ማብራሪያ ነው። ይህ ጥንቅር ነው የቡድሃ እምነት መሰረታዊ ሰነድ የነበ ረው።

በዚህ መጽሀፍ ውስጥ ከሰፈሩት ትምህርቶች ውስጥ የሚከተሉት ዋንኛ ሀሳች ተዘርዝረው ይገኛሉ።

1- አትግደል

2- የራስህ ያልሆነውን አትውሰድ

3- የሰው ሚስት አትሻ

4- አትዋሽ

5- የሚያሰክር መጠጥ አትውሰድ

እነዚህ ህጎች መከበር ያለባቸው መሆኑን ቡድሃ ደንግጓል።

ከጥቂት ዘመናት በኋላ ሰዎች ጽድቅን ማግኘታቸውን እርግጠኛ ለመሆን ባደረባቸው ጉጉት የተነሣ እነዚህን ህግጋት የበለጠ እንዲከብዱ አደረጓቸው። ለምሣሌ አትግደል የሚለውን ህግ በተሟላ መልኩ ለመፈጸም በማሰብ ጥቃቅን ህዋሳት እንኳ እንዳይገደሉ ወሰኑ። ስለሆነም ውሃ እንኳን ለመጠጣት በቅድሚያ እንዲጠለል ተደረገ። (በውስጡ ጥቃቅን ህዋሳት ሊኖሩ ስለሚችሉ)።

እንዲሁም እርሻ ማረስ ተከለከለ። ምክንያቱም ማረሻው መሬቱን በሚያርስበት ወቅት በአፈር ውስጥ የሚገኙት ትላትሎችና ሌሎች ነፍሣት ሊገደሉ ይችላሉ በሚል ስጋት።

የራስ ያልሆነውን አትውሰድ የሚለው ተባብሶ ጭራሽ ንብረት አይኑርህ ወደሚለው ተለወጠ።

የሰው ሚስት አትሻ የሚለው ህግ ጭራሹን የግብረ ስጋ ግንኙነትን እንዲከለክል ተቀየሰ።

የሚያሰክር መጠጥ አትጠጣ የሚለውም እንዲሁ ጠግቦ መብላትን ጭምር በመከልከል ሰው በቀን አንድ ጊዜ ብቻ መመ ገብ እንደሚገባው ተደነገገ።

ይህ ዓይነት በጊዜ ሂደት አዳዲስ ጭማሪዎችን አክሎ ህግጋ ትን የማጠንከር አዝማሚያ በሌሎች ሃይማኖቶች አልፎ አልፎ ታይቷል። የቡድሃ እምነት ተከታዮች ከሂንዱይዝም የወረሱትን አንድ አስተምሮት እንዲሁ አክርረውታል። ይህም ሕይወት ያላቸ ውን ሁሉ በእኩል ደረጃ ማፍቀር እና ለጋስ መሆን የሚለው ነው። አንዱን ከሌላው አስበልጠ መውደድ አድሎአዊነት ነው። ስለዚህ አባትን ወይም ልጅን አብልጠ ማፍቀርን እንዲሁም ሌላ ውን ጥፋተኛ ወይም ግፈኛ ነው ብሎ በማሰብ መጥላትን፣ ማራ ቅን፣ ማግለልን፣ ይከለክላል። ሁሉንም በእኩል ማፍቀር ያስፈ ልጋልና። በዚህ የተነሣ አማኞች ሁሉ ገለልተኛ ተመልካች እን ዲሆኑ አስገድዷል። ለምሣሌ አንድ ጉልበተኛ ሰው ደካማውን ቢደበድበው ለደካማው የሚራራ፣ የሚያደላ እና ጣልቃ የሚገባ የለም። የእርሱ መደብደብ መሆን ያለበት በመሆኑ ነው ይባላል።

በዚህ ዓይነት የቡድሃ አስተምሮት ያለ አግባብ እየተለጠጠ እና መስመሩን እየሳተ መጣ። ስለሆነም በአማኞች መካከል አለመ ግባባት እየተፈጠረ በመሄድ በኋላም ሃይማኖቱ ለሁለት ተከፈለ።

መንፈሳዊ ጉባዔዎች እና የሃይማኖቱ ተሃድሶ

በሰዎች መካከል የከረረ የሃሳብ ልዩነት ሲከሰት አንዱ መፍቻ መንገድ ጉባኤ መጥራት ነው። በዚህ መሠረት በሃይማኖት በኩል ያሉትን አለመግባባቶች ለመፍታት መንፈሳዊ ጉባኤዎችን ያካሄዳሉ። የቡድሂዝም

ሊቃውንት 2ኛው ጉባኤ ቡድሃ ከሞተ ከአንድ መቶ ዓመታት በኋላ እንዲሰበሰብ አስፈለገ። የዚህ መንፈሣዊ ጉባኤ መጠራት ምክንያት በርካታ የሃሣብ ልዩነቶችን ለማስታረቅ እና የጋራ ስምምነት ላይ ለመድረስ ሲሆን በወቅቱ ጎልቶ የወጣው ልዩነት ስለ ቡድሃ ተፈጥሮ ጥያቄ ነው። ቡድሃ እንደተራ ሰው ተወልዶ የኖረና ብዙ መከራ ያየ በኋላም እንደማንኛውም ሰው የሞተ ነበረ። የእርሱ አስተምሮትም ሰዎች ስለ ኒርቫና እንዲያውቁና ደግ እንዲሰሩ ነበረ እንጂ ራሱን ከሌሎች በተለይ አድርጎ የሚያይ አልነበረም።

ሰዎች ግን በስተኋላ በዚህ ሊረኩ አልቻሉም። ቡድሃን እንደ ተራ ሰው አድርገው ሊቆጥሩት አልፈለጉም። ስለሆነም አንድ ቡድን በእምነቱ እየተለየ መጣ። በዚህ ቡድን እምነት መሰረት ቡድሃ በሶስት ደረጃ መታየት ይገባዋል። እነዚህም፤

1ኛ- በሰው መሃል ኖሮ እንደሰው ለመታየት ሲል በለበሰው ስጋ መሰል አካል፣

2ኛ- እውነተኛ እሱነቱ የሚገለጥበት ሁኔታ ወይም ቅርጽ፣

3ኛ- በመንግሥተ ሰማያት ሲቀመጥ በታላቅ ጸጋና ሞገስ ለጻድቃን የሚታይበት፣ ደስታና ፍቅር የሰፈነበት ሁኔታ ናቸው። ጉባኤው ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ እነዚህንና ሌሎችንም ልዩነቶች ሊያስታርቅ ባለመቻሉ ሃይማኖቱ ለሁለት ተከፈለ። እነዚህም አንደኛው ሂናያ የተባለውና ሁለተኛው ማሃያና የተባለው ናቸው።

ከዚህ ጉባኤ በኋላ እሰከዛሬ ሌሎች አራት ጉባኤዎች ተካሄደዋል። ሶስተኛው ጉባኤ የተካሄደው ከሁለተኛው በኋላ 120 ዓመት ቆይቶ (በ3ኛው ዓመተ ዓለም) ሲሆን አራተኛው ደግሞ በ100 ዓመተ ምህረት ነበረ። ስድስተኛ በ1956 ዓ.ም. በበርማ አገር ሲካሄድ የሃይማኖቱን 2500ኛ ዓመት ለማክበር ጭምር ነበረ።

በነዚህ ጉባኤዎች ሂደት ሊቃውንት እየመከሩ ሃይማኖቱን በየደረጃው አድሰውታል። ይህም ከዘመኑ ጋር እንዲሄድ አስችሎታል።

የሃይማኖቱ መስፋፋት

የቡድሂዝምን ሃይማኖት ዓለም አቀፋዊ ሊያደርጉት ያስቻሉት ብዙ ምክንያቶች ነበሩ። በመጀመሪያ ደረጃ ቀድሞ በቡድሃ ተሰ ጥተው የነበሩት ትዕዛዛት እንዲጠናከሩ እና እንዲከብዱ በመደረጋቸው የተነሳ አንድ አማኝ ሊጸድቅ የሚችለው የምናኔ ኑሮ ሲኖር ብቻ ነበረ። ይህም በቀን አንድ ጊዜ ብቻ እንዲ መገብና ኑሮውን በምጽዋት እንዲኖር የሚያስገድድ ስለሆነ ከባድ ነበረ።

አሁን ግን ማሃያና የተባለው ክፍል ነገሮችን ቀለል በማድረግና ያለአግባብ የከበዱ ናቸው ያላቸውን በመተው ሰዎች ሰርተው ሊኖሩ እንዲችሉ ፈቀደ። ይህ በሰፊው ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነትን አስገኘ።

እንዲሁም ቀደም ሲል ተንሰራርቶ የነበረው የሂንዱይዝም እምነት ሰዎችን ብራህማን፣ ሻትሪያ፣ ቫዝያ፣ ሱድራ እያለ በ4 መደብ በመመደብ አንዱን ጭሎ ሌላውን ተጭሮ አድርጎ ነበረ። አሁን ስልጣኔ እያደገ ሲመጣ ተጨቋኝ ሕዝብ ሰርቶ የማግኘት ዕድል ስለነበረው "ሁል ጊዜ በተዋራጅነት እና በባርነት ስታገለግል መኖር አለብህ" የሚለውን ሃይማኖት መቀበል አቃ ተው። ስለሆነም ሁሉንም በእኩልነት የሚያየውን የቡድሂዝምን ሃይማኖት ወደደው።

በ324 ዓመተ ዓለም በጦርነት የፖለቲካ ስልጣንን ሊቀዳጅ የቻለው የአንድ ክልል ስርወ መንግሥት ሰረመሠረቱ የድሃ ዘር ስለነበረና ይህ ደግሞ የሂንዱ ሃይማኖት የማይፈቅደው ስለነበረ አዲሶቹ ገዢዎች የቡድሂዝምን ሃይማኖት መርጠውና ተቀብለው በግዛታቸው አስፋፉ። በተለይ ሃይማኖቱ "ክፉን በክፉ አትመ ልሱ፣ መከራንም ችላችሁ ተቀበሉ" በማለት ስለሚያስተምር የገ ዥ መደቡ ይህንን ትምህርት ወደደው። ሃይማኖቱም እንዲስፋፋ ድጋፉን ቸረው።

ከዚያም ቀስ በቀስ እምነቱ ወደ ሩቅ ምስራቅ ተሰራጨ። በወቅቱ ህንድ ሰፊ የንግድ ግንኙነት ስለነበራት መነኮሣቱ ነጋ ዴውን እየተከተሉ ወደ ቻይና፣ ኮሪያ፣ ኢንዶኔዥያ እና ጃፓን ዘለቁ።

ሃይማኖቱ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ሌሎችን ሃይማኖቶች የማይጋፉና የማይጻረር በመሆኑ ጎን ለጎን ኖረ። ስለሆነም ዛሬ ቡድሃ ካስተማረው ውጭ ሌሎችም እምነቶች ታክለውበት የተለ ያየ መልክ ይዞ ይኖራል።

በቡድሃ አስተምሮት መሠረት ሰው ከሃጢያቱ የሚነጻው በራሱ እና በራሱ ብቻ ጥረት ነበረ። ከጊዜ በኋላ ሰዎች ይህ እየከበዳቸው ስለመጣ ሽክሙን የሚያቀልላቸው መንገድ ፈለጉ። ስለዚህ ቡድሃ ከተራ አስተማሪነት ወደ አምላክነት እንዲሸጋገር መረጡ። ዛሬ ቡድሃ ራሱ ይመለክበታል። ሌሎችም ህዝቦች ይህንን እምነት እየተቀበሉ ሲሄዱ የእነሱንም አማልክት በዚሁ ሃይማኖት ውስጥ እየጨመሩ ታቀፉ። ከሞት በኋላ መንግሥተ ሰማያት ሲገቡ ብዙ የተመኙትን ሊያገኙ የሚችሉበት ቦታ እንዲሆንላቸው ፈለጉ።

ሃጢያተኞችም በተዘዋዋሪ መንገድ ሳይሆን በቀጥታ እንዲ ቀጡ፣እንዲሰቃዩ፣ማድረግ እንደሚገባ በመምረጥ በቡድሃ ትምህ ርት ውስጥ ያልነበረውን ገሃነም እሣት ጨመሩበት። ዛሬ የመን ግሥተ ሰማያት ጭሎ ሆኖ የሚታወቀው ታላቁ አሜታባ ሲሆን ምድሪትን የፈጠረው ደግሞ አዲ ቡድሃ ነው ይባላል። ሌሎች ቡድሃዎችም አሉ።

በአንዳንድ አካባቢ የነበሩ ሕዝቦችም ቀደም ሲል የነበ ራቸውን የጥንቆላ የመተትና የመሣሠሉትን ድርጊቶች ጨመሩበት። መናፍስትን በመሳብ፣ድግምትን በመድገምና ከታብ በማጻፍ ከበሽታ የሚፈወሱበትንና ችግራቸውን የሚፈቱበትን መንገድ አብረው አመቻቹ። በዚህ ሁኔታ

ሃይማኖቱ ምድራዊንና መንፈሳዊውን ሕይወት እያቃና እንዲያግዝ ተደራጀ።

በሌላ በኩል የዓለም ሊቃውንት ለዚህ ሃይማኖት ትኩረት በመስጠት እያጠኑት ነው። በሳይንሱ ዓለም ከሆነ እውነታ ማለት በተጨባጭ የሚታየው ዓለም ነው፤ በስሜት ሕዋሶቻችን (ዐይን፣ጆሮ. . .) ልንረዳው ልንዳስሰውና ልንገነዘበው የምንችለው ነው። የቡድሂስት ሃይማኖት ግን የሚያስተምረው አምስቱ ሕዋሳቶቻችን ከሚያውቁልን እዉነታ ውጭ የሆነ ሌላ ፍጹም ሌላ እውነታ አለ የሚል ነው። በጋራ አመለካከታቸው ግን የሰው ልጅ በዝግመተ ለውጥ መሠረት ይሻሻላል፡ በሚለው ሳይንሳዊ አስተሳሰብ መሠረት በቡድሂዝም ዕምነትም ሰው ራሱን ወደ ተሻለ ደረጃ ከፍ ለማድረግና ተራ አካላዊ ሞትን አሸንፎ ወደ ሌላው ሰላማዊና ጸጋ የተሞላበት ዓለም ለመሸጋገር ራሱን ውስጡን መመርመርና የሕይወት ትርጉምን ከራሱ ውስጥ መፈለግ አለበት ስለሚባል ይህ አስተሳሰብ የሊቃውንትን ትኩረት ስቧል።

በተጨማሪ ዛሬ ቡድሂዝም በተለያየ መልኩም ቢሆን በከፊል ህንድ፣ በደቡብ ምስራቅ እስያ አገሮች እና በቻይና ይታመ ንበታል። እነዚህ አገሮች ደግሞ አብዛኛውን የዓለም ህዝብ የያዙ ክፍሎች ናቸው። ስለሆነም ይህ ሃይማኖት እያደረ ትኩረት ማግኘቱ የሚያስገርም አይደለም።

አይሁድነት

መሠረታዊ እምነት

የአይሁድነት መሠረታዊ እምነትን በአራት ክፍሎች ማስቀመጥ ይቻላል። ይህም÷

1ኛ- በእግዚአብሔር ስለማመን 2ኛ- ስለነቢያት 3ኛ- ስለ ሰው ልጅ የመጨረሻ ዕድል እና 4ኛ- ትንቢት ናቸው። በዝርዝር ሲቀመጡ÷

1ሀ. እግዚአብሔር አለምን የፈጠረ ነው።

ለ. እግዚአብሔር አንድ ነው ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም።

ሐ. እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ነው።

መ. እግዚአብሔር መንፈስ ነው፣ በቅርጽ፣በጊዜ፣ በቦታ የተወሰነ አይደለም.

ሠ. ከእግዚአብሔር በስተቀር በሌላ አታምልኩ።

2ሀ. የእግዚአብሔር ቃል በነቢያት አማካኝነት ለሰው ልጅ ይገለጻል።

ስለሆነም ነቢያት የገለጹልን የእግዚአብሔርን ቃል ነው።

ለ. ሙሴ ታላቅ ነቢይ ነው። የሙሴ መጻህፍትም የእግዚአብሔር ቃል ናቸው።

አስርቱ ትዕዛዛትም በቀጥታ የወረዱልን ናቸው።

ሐ. ሙሴ የሰጠን ቃል (መጻህፍቱ) የማይሻር የማይለወጥ የማይቀየር ዘለዓለማዊ ህግ ነው።

3ህ. ለእግዚአብሔር የሚሣነው የለምእና ሰራችንን ሁሉ ያውቃል።

ለ. እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው እንደሰራው ይሰጠዋል። ደጉን ይክሣል፣ክፉውን ይቀጣል (በነፍሣቸው)።

4ህ. ከንጉስ ዳዊት የሚወለድ ታላቅ መሲህ ይመጣል።

ለ. የፍርድ ቀን ሲመጣ ሙታን ከመቃብር ይነሣሉ።

የአብርሃም ታሪክ

የእብራዊያን ታሪክ የሚጀምረው በአብርሃም ነው። ለማለት ይቻላል። ይህ ሰው ከ4 ሺህ ዓመታት በፊት የኖረ አስተዋይ ሰው ነበረ። የጥንት ሰዎች ለአምላኮቻቸው በመስዋዕትነት ያቀርቡ የነበረው ልጆቻቸውን ጭምር ሲሆን ምናልባት ለመጀመሪያ ጊዜ የተተወው በአብርሃም ሳይሆን አይቀርም። በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ አብርሃም የበኩር ልጁን ይስሃቅን ሊያርድ ሲል እግዚአብሔር በምትኩ በግ አቀረበለትና ይህ እንዲታረድ አደረገ፡ ተብሎ ተጽፏል። የይስሃቅ ከመስዋዕት መዳን በሰው ልጅ ታሪክ አንድ ዋና እርምጃ ነው። አብርሃም የጣኦት አምልኮን በመቃወም በአንድ እግዚአብሔር ማመን እንደሚገባ ያስተማረ የመጀመሪያ ሰው ነው። ዝርዝር ታሪኩ እንደሚከተለው ነው። አብሮሃም ከአባቱ ከታራ ጋር በዑር ከተማ ይኖር ነበረ። አባቱ ጣኦት እየሰራ በመሸጥ ሲተዳደር አብርሃም ደግሞ በኤፍራጥስ ወንዝ አካባቢ ከብቶች እያገደ እና አባቱንም በስራው እየረዳው አደገ።

አብርሃም ሰዎች ለጣኦት ሲሰግዱ እያየ ይገርመው ነበረ። ሟች አባቱና እሱ እየጠረቡ የሰሩትን እንጨት ማታ ሰዎች ሲሰግዱለት እያየ ተገረመ። አንድ ቀን የሰራቸውን ጣኦታት ሁሉ አንዱን ብቻ አስቀርቶ ሌሎቹን ሰባበራቸው። ከዚያም አባቱን በመፍራት የሰባበረበትን መሣሪያ ለቀሪው ጣኦት አስያዘው በአባቱ ሲጠየቅም "ጣኦታቱ ተጣልተው ይኸኛው ሌሎቹን ሰባበራቸው" አለ። አባቱ ግን አላመነም። ገቢው ስለቀረበትም ተናደ እነዚህ ግውዝ ነገሮች ናቸው! ምን ይሰራሉ? ይህ የአንተ ሥራ መሆን አለበት ብሎ ጮኸበት። አብርሃምም ሲመልስ "ታድያ ሃይል ከሌላቸው ለም፥ ለእነርሱ ትሰግዳላችሁ?" ብሎ አፋጠጠው። በዚህ የተነሣ የአካባቢው ሕዝብ ስለጠላው አብርሃም ሸሽቶ ተሰደደ። ወደ ፍልስጥኤም አገርም (ከነዓን) ተሻግሮ ኖረ። የከነዓን ሰዎችም ይህን ስደተኛ ዕብሪ አሉት። (ትርጉሙ ተሻግሮ የመጣ ለማለት ነው) ቤተሰቦቹም ዕብራውያን በመባል ታወቁ።

የአብርሃም የልጅ ልጅ (የያዕቆብ ልጅ) ይስሀቅ ወይም እስራኤል ተባለ። እስራኤል አስራ ሁለት ወንዶች ልጆች ስለነበሩት እና እነዚህም

በብዛት ስለተዋለዱ ለከብቶቻቸው ግጦሽ ለም መሬት ለማግኘት ሲሉ እየተዋጉ እያሸነፉና እየተስፋፉ ሄዱ። እነሱም እስራኤላውያን ይባላሉ።

ሆኖም በአንድ ወቅት ድርቅና ረሃብ በከነዓን ስለ ደረሰ ወደ ግብጽ ተሰደዱ። የያዕቆብ አንዱ ልጅ (ዮሴፍ የሚባል) ወደ ግብጽ አገር ተሸጠ እዚያም ባለስልጣን እስከ መሆን ደርሶ ነበር። በታሪክ እንደተዘገበው ዮሴፍ ንጉሡ ፈራያ ባየው ህልምና እሱም በተረጎመው መሠረት በግብጽ ለመጪዎቹ ሰባት ቀጭን ዘመናት የሚሆን እህል በብዛት እንዲከማች አስደርጎ ስለነበረ በንጉሡ (ፈራያ) ዘንድ ተሰሚነት ነበረው። ስለዚህ ዕብራዊያን (እሥራኤ ላዊያን ጭምር) ከችግሩ ዘመን ጀምሮ ወደዚያው በመሰደድ ብዙ ዘመናት ኖሩ።

በኋላ ግን ቁጥራቸው በዝቶ ግብጾችም ስለጠሏቸው ወደ አገራቸው መመለስ ግድ ሆነባቸው።

የሙሴ ታሪክ

ዕብራዊያንን ከግብጽ መርቶ ያወጣቸው ሙሴ ነበረ። ሙሴ ራሱ ተወልዶ ያደገው በግብጽ ነበረ። ሆኖም ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ግብጻዊ ዕብራውያን ባሮቹን በግፍ ሲያሰቃያቸው አይቶ በመናደድ ስለገደለው በዚህ የተነሣ አገሩን ጥሎ ወደ ምድያን አገር ተሰደደ። እዚያም በጎች ሲጠብቅ ኖሮ በአንድ ወቅት እግዚአብሔር እንደታየውና ዕብራውያንን ከግብጽ እንዲያወጣ እንዳዘዘው አስታወቀ። በዚህም መነሻ ብዙ ውጣ ውረድ ደርሶባቸው ወደ 600,000 ሰዎችን መርቶ በተአምር አወጣቸው። ዝርዝር ታሪኩ በመጽሐፍ ቅዱስ (ኦሪት ዘፀአት) ተቀምጧል።

የሙሴ ስም በአለም ታሪክ ታዋቂነት ያገኘው በዚህ ድርጊቱ ብቻ አይደለም። ሙሴ ደራሲ ነበረ። አምስት መጻህፍትን ጽፏል። እነዚህ በእብራይስጥ ቋንቋ የተጻፉት መጻህፍት በጥቅል ስማቸው "ቶራ" ይባላሉ። ቶራ የአይሁዳዊያን የተቀደሰ መጽሀፍ ነው። ከአምስቱ ዋንኛው "ኦሪት ዘፍጥረት" የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው ምዕራፍ ሲሆን ይህ ስለ ዓለም አፈጣጠር ስለ አዳምና ሔዋን፣ስለ ገነት እና ሲኦል የሚያስረዳ ነው። ዓለም የተፈጠረችው በስድስት ቀናት ሲሆን መጀመሪያ ሰማይና ምድር ተፈጠረ። ቀጥሎም ዕጽዋት ከዚያም ተንቀሳቃሽ ሕያዋን (ወፎች፣አሣዎች፣እንስሳት) ከዚያም የሰው ዘር ተፈጠሩ።

አዳምና ሔዋን የመጀመሪያዎቹ ሁለት ሰዎች ነበሩ። ለእነሱ ስለተሰጠ የኦሮ ህግ ስለደረሰባቸውም መርገምት ሙሴ በሰፊው ጽፏል።

ሙሴ "ኦሪት ዘሌዋውያን" በተሰኘ መጽሀፍ ውስጥ እስራኤላዊያን የሚተዳደሩበትን ህግጋት አስቀምጧል። እነዚህ ከእግዚአብሔር በእርሱ በሙሴ በኩል የተላለፉ ትዕዛዛት መሆና ቸው በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ተቀምጧል። ተጨማሪ ሃይማኖታዊ ስነ ምግባር (የጸሎት፣የአለባበስ፣ የአመጋገብ) "በኦሪት ዘዳግም" ውስጥ በዝርዝር

ተቀምጧል። የእስራኤላውያንን ታሪክ የሚያስረዳው ክፍል ደግሞ በ"አሪት ዘጉልቁ" ውስጥ ሰፍሯል። የሙሴ መጽሀፍት የእግዚአብሔር ቃል መሆናቸው የአይሁዳውያን ዕምነት መሰረት ነው። በተለይ "አስርቱ ትዕዛዛት" በ"አሪት ዘጸአት" እንደተቀመጠው ሙሴ ከ3ሺ ዓመታት በፊት ከሲና ተራራ ይዞት የወረደው የእግዚአብሔር ቃል የሃይማኖቱ የማዕዘን ድንጋይ ነው። ትዕዛዛቱም 1/ ከይሆዋ በስተቀር ሌሎች አማልክት አይኑሀ በጣኦት አታምልክ፣

2/ ሰንበትን አክብር የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አትጥራ። አባትና እናትህን አክብር፣ አትግደል፣ አታመንዝር፣ አትስረቅ፣ በሃሰት አትመስክር፣ የባልንጀራህን ሚስት አትመኝ የሚሉ ናቸው።

ሙሴ ከጻፋቸው መጻህፍት በተጨማሪ ሌሎች በብሉይ ኪዳን ተጠቃለው ያሉ መጻህፍት አሉ። ከነኝህ አንደኛው ክፍል በመን ፈሳዊያን የተጻፈ ስብስብ ሲሆን መንፈሳውያኑም ሳሙኤል፣ሩት፣ ዕዝራ፣ነህምያ፣አስቴር፣ኢዮብ እና መክብብ ናቸው።

በንጉስ ሰለሞን የተጻፉት መጽሀፈ ምሣሌ፣መሃልየ መሃልይ (የመዝሙሮች ሁሉ መዝሙር) እና የንጉስ ዳዊትም መዝሙር (መዝሙረ ዳዊት) ዋንኛ ሰነዶች ናቸው።

በተጨማሪም ነቢያት በየዘመኑ እየተጥኑ ብዙ አስተምረዋል፣ አስጠንቅቀዋል፣ ተንብየዋል፣ይህም የእግዚአብሔር ቃል ተደርጎ ስለሚወሰድ ተቀባይነት አለው። ከነቢያቱም ኤልያስ፣ ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል፣ እና ዳንኤል በታላቅ አክብሮት ሲታዩ ሚልኪያስ፣ ዘካርያስ፣ዕንባቆም፣ ናሆም፣ ሚኪያስ፣ ዮናስ፣ የመሣሉት በአገ ራችንም የተለመዱ ስሞች አሉ።

የእነዚህ ሁሉ ጽሁፍ ተጠናቅሮ ብሉይ ኪዳን ይባላል። የእነዚህ ሁሉ መጻህፍት ይዘት በተለይ የሚያተኩረው በእስራኤል ሕዝብ ላይ ነው። እንደመጽሀፍቱ አቀራረብ "እግዚአብሔር የዳዊትን መንግሥት መሰረተ (መጽሀፈ ሳሙኤል ካልእ 7፣8-16)፣ እስራኤልን (ያዕቆብን) ባርኬያለሁ። 12 ነገዶች ይወልዳል፣ታላቅ ሕዝብም እንዲሆን አደርገዋለሁ (ዘፍጥረት 17፣20) ከአብርሃም ጋር እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ሲገባ "ወንድ ሁሉ ይገረዝ . . . ወገንህን እንዳውቅ (ዘፍጥረት 17፣10-14) እንዲያውም በአዲስ ኪዳንም አይሁዶች አሁንም ቢሆን ከአባቶቻቸው የተነሣ በእግዚአብሔር ዘንድ እጅግ የተወደዱ ናቸው) ሮሜ 11፣28-29)።

ስለዚህ አይሁዳውያን ከአባቶቻቸው ባገኙት ትምህርት መሰ ረት ራሣቸውን የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ አድርገው ይቆጥራሉ። ይህ እርግጥ ሁል ግዜ አላደላቸውም። እንዲያውም መከራ ስቃይና ስደት ዕጣ ፈንታቸው ሆኖ ኖሯል። ግን ይህም ቢሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን በማመን እንዲያውም የበለጠ እንዲሰባሰቡና እንዲበረቱ ረድቷቸዋል።

የአይሁዶች ታሪክ የዓለም ታሪክ ሆኗል። ኢትዮጵያም ጭምር ከእስራኤል ታሪክ ጋር ትስስር አላት። የአይሁድነት ሃይማኖትም የሕዝቡን የዕለት ዕለት ኑሮ ጭምር የሚገዛ ነው።

ስለዚህ ታሪካዊ አመጣጡ የሃይማኖቱን ይዘት ስለሚወስነው ለበለጠ ግንዛቤ እንዲረዳ በአጭር በአጭሩ ይቀመጣል።

የአይሁድነት ታሪካዊ አመጣጥ

ዛሬ በእስራኤላውያን እና በፍልስጤማውያን መካከል ያለው ትግል ትላንት የተጀመረ አይደለም። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የአብርሃም ነገዶች ወደ አካባቢው ወጥተው ከሰፈሩ በኋላ ዕብራ ውያን ነገዶች ሆነው መስፋፋት ጀመሩ። በኋላም ከፊሎቹ ወደ ግብጽ ሄደው ቆይተው በመቶ ሺ የሚቆጠሩት ሲመለሱ እነዚህም ከብቶቻቸውን እየነዱ ስለመጡ የግጦሽ መሬት አስፈለጋቸው። ስለዚህ በግድ መቀማት ተያያዙት።

የእስራኤላውያን ሃይማኖት መሰረቱ በአንድ እግዚአብሔር ብቻ ማመን ነው። በዚህ ረገድ ከፈጣሪያቸው ጋር ልዩ ቃል ኪዳን ገብተዋል። የአብርሃም ልጆች ቃል ኪዳናቸውን ጠብቀው ህጉን ካከበሩ እሱም እግዚአብሔር ነገዳቸውን እንደሚጠብቅ ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል። (በመጽሀፍ ቅዱስ እንደተቀመጠው)።

ይህ በእንዲህ እንዳለ አሁን እስራኤላውያን የፍልስጤማውያንን ለም መሬት ለራሳቸው ለማግኘት አስመኛቸው። ስለዚህ ጦርነት ጀመሩ። ለዚህም እግዚአብሔር ከጎናቸው ቆሞ እንዲረዳቸው አስፈላጊ ሆነ።

ሙሴ ከሞተ በኋላ በመሪነት የተመረጠው ኢያሱ ነበረ። እሱም የጦር መሪ ነው። "በመጽሐፈ ኢያሱ" እንደሚነበበው እስራኤላውያን በአምላካቸው ፈቃድና ድጋፍ በፍልስጤማውያን ላይ ጦርነት አወጁ። ሕዝቦችን ፈጁ፣ የአካባቢውን አገሮች እና ከተሞች አጠፉ፣ አቃጠሉ፣ ለማስረጃ ያህል ከመጽሀፍ ቅዱስ ከመጽሀፈ ኢያሱ አንዳንድ አንቀጾችን እንመልከት።

"እግዚአብሔር ኢያሱን አለው÷ ኢያሪኮንና ንጉሥዋን . . . በእጅህ ሰጥቼአለሁ" መጽሀፉ ኢያሱ 6፣2 "ስለሆነም ከተማይቱን ወሰዱ በከተማይቱም የነበሩትን ሁሉ ወንዱንና ሴቱን ሕጻኑን ሽማግሌውን በሬውንም በጉንም አህያውንም በሰይፍ ስለት ፈጽመው አጠፉ"። መጽሀፈ ኢያሱ 6÷21

በሌላ ቀንም እንዲሁ ሆነ። "እግዚአብሔርም ኢያሱን አትፍራ አትደንግጥ . . . በኢያሪኮ እና በንጉሥዋ እንዳደረግህ እንዲሁ በጋይ እና በንጉሥዋ ታደርጋለህ" መጽሀፈ ኢያሱ 8÷1-2። ከዚያ በኋላ "የጋይም ሰዎች በእስራኤል መካከል ሆኑ። እስራኤላውያንም ከበቡአቸው። አንድም እንኳ ሳይቀር ሳያመልጥ ገደሉ አቸው። መጽሀፈ ኢያሱ 8÷22።

በዚህም ዓይነት እስራኤላውያን በጠረኛነት ብዙ ቦታዎችን ያዙ። ሕዝቦችንም በመጋዝና በሳንጃ ሳይቀር አረዱአቸው። ከተ ማዎችንም እንዳሉ አወደሙ። እርግጥ ያስተረፉአቸውም ነበሩ። ለምሣሌ በሊባኖስ ተራራ የሚኖሩ ሰዎችን፣ ፍልስጤማውያንን፣ ሶዶናውያንን፣ ከነዓውያንን ትተዋል። ይህ የሆነው ግን ከርህራሄ በመነጨ አልነበረም። "መዋጋትን ያላወቁን እስራኤላውያን በእነርሱ ይፈትናቸው ዘንድ፣ በፊትም ሰልፍን ያለመዱ የእስራኤል ልጆች መዋጋት ያውቁና ይማሩ ዘንድ እግዚአብሔር ያስቀራቸው" ናቸው። መጽሀፈ መሳፍንት 2ኛ፣1-3

በዚህ ዓይነት እስራኤላውያን የፍልስጤማውያንን ለም የእርሻ መሬቶች በመንጠቅ ከዘላንነት ኑሮ ተላቀው ባለመሬት ሆኑ። አምላካቸውም በዚህ ስራቸው ከጎናቸው ሆኖ እንደረዳቸው ያስተምራሉ።

እስራኤላውያን የግብርና ኑሮ ሲጀምሩ የጠር መሪዎቻቸው የነበሩት እንደ መሳፍንት ሆነው አስተዳደሯቸው። በኋላም አስራ ሁለት የእስራኤል ነገዶች አንድ መንግሥት መሥርተው ንጉስ ሳኦል የመጀመሪያው ንጉሥ ሆነ። ቀጥሎም ንጉስ ዳዊት ነግሶ በ1000 ዓመተ ዓለም ኢየሩሳሌምን ዋና ከተማው አደረገ። አገሪቱንም ገነባ። ሃይማኖቱንም በማጠናከር መዝሙረ ዳዊትን ተቀኘ። በመጨረሻም ንጉስ ሰለሞን አገሪቱን ደረጃ በደረጃ ለከፍተኛ ስልጣኔ አደረሰ። የሳባ ንግስትም የእስራኤልን ስልጣኔ ልታይ የሄደችው በዚህ በሰለሞን ዘመነ መንግሥት ነበረ።

ንጉስ ሰለሞን ከሞተ በኋላ ግን በሰሜን ከፍለ አገር የሚኖሩት ወገኖች የደቡብን ሰዎች "በእኩልነት አላስተዳደሩንም" በሚል ተቃውሞ አንስተው ጦርነት አካሄዱባቸው። አገሪቱንም ለሁለት ከፈሏት። የሰሜኑ ክፍል እስራኤል ሲባል የደቡቡ ክፍል ይሁዳ ተባለ። የይሁዳ አንበሳ የዚህ የይሁዳ ነገድ አርማና የዳዊት ዘር ምልክት ሆነ።

(የዚህ አንበሳ ዝርያ ከሌሎች ለየት ያለ ነበረ። አሁን ግን ወደመጥፋቱ ተቃርቧል ይባላል።)

ከዚህ መከፋፈል በኋላ ሃይላቸው ስለተዳከመ የውጭ ወራሪ ሃይልን ለመከላከል አቅም አጡ። ወዲያው እስራኤል በሰሜን በኩል በአሶራውያን ሕዝብ ተማርካ ተወሰደች፣ ጠፉች። ከ160 ዓመት በኋላ ይሁዳ በምስራቅ በኩል በባቢሎን ጦረኞች ተያዘች። (በ597 እና በ588 ዓ. ዓለም) በዚህ ዓይነት ሁለቱም ተሸንፈው ተግዘው በባርነት ስር ወደቁ።

ዛሬ ዕብራውያን በሁለቱ ትናንሽ አገሮች ስም እስራኤላውያን ወይም ይሁዳውያን (አይሁዶች) በመባል ይታወቃሉ።

ንጉስ ሰለሞን በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1004 ዓ.ዓለም የእግዚአብሔር ማደሪያ እንዲሆን በኢየሩሣሌም ያሰራውን ቤተ መቅደስ (የሙሴን ጽላት ያኖረበትን) ይሁዳ ስትሸነፍ የባቢሎን ንጉስ ነቡከደነጸር በእሣት አቃጥሎ አጠፋው። ይህም በ586 ዓመተ ዓለም ነበረ።

ይህ ክስተት አይሁዶችን ግራ አጋባቸው። እነሱ እንደዚህ ለባርነት የተዳረጉት የመረጣቸው አምላካቸው የት ሄዶ ነው? ቃል ኪዳኑንስ ለምን አልጠበቀም? ለዚህ መግለጫ አጡ። በኋላ ግን ጥፋት አጥፍተው ለቅጣት የተደረገ መሆኑን አሰቡ። የተመረጡትም ለድሎት ሳይሆን ትዕዛዙን እና የዓለም መከራን ለመሸከም እንደሆነ ተቀበሉት። በያሉበትም አምላካቸውን ማሰብ አልተዉም። ይልቁንም አምላካቸው ስልጣኑ በፍልስጥኤም አገር ብቻ ተወስኖ የእነሱ አምላክ ብቻ ተደርጎ መወሰዱ ትክክል እንዳልሆነና ለሁሉም ዓለም መሆን እንደሚገባ አሰቡ። በዚህም ሃይማኖቱ ዓለም አቀፍ እንዲሆን ጥርጊያ መንገድ ተከፈተ።

በ538 ዓ. ዓለም ንጉስ ቂሮስ የተባለ የፋርስ (ዛሬ ኢራን) ንጉስ ባቢሎንን በጦርነት አሸንፎ ሲወር አይሁዶችን ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ነጻ ለቀቃቸው። ስለሆነም ተመልሰው መቅደሳቸውን እንደገና አድሰው መጽሀፈ ኦሪትን አጠናቅረው ሃይማኖታቸውንም አጠንክረው (ለምሳሌ ግዝረትን አክብረው) ተቀመጡ።


ነገር ግን የአይሁዳውያን ስቃይ በዚህ አላበቃም። መጀመሪያ ታላቁ እስክንድር ቀጥሎም የሮም መንግሥት ከምዕራብ አኳያ እየመጡ በመስፋፋት የእነሱንም አገር ወረሩ። እንደገና ግዞትና ባርነት ዕጣ ፈንታቸው ሆነ። በማያውቁት ሕዝብ፣ በማያውቁት ቋንቋና ባህል ውስጥ ሲሰቃዩ ብዙ ትውልድ አሳለፉ። በ132-135 ዓ.ም. አካባቢ ጭራሹን ነቅለው ከአገራቸው ለቀቁ፣ ተበታተኑ። ዛሬ አይሁዳውያን በመላው አውሮፓ በሰሜን አሜሪካ፣ በሩሲያ እና በሌሎች አካባቢዎች ተሰራጭተው ይኖራሉ።

መቸም አገር የሌለው ሰው አገሩ ገንዘቡ ነውና አይሁዳውያን ወደ ንግድ መስክ በመሰማራት ትኩረታቸው በገንዘብ ላይ ሆነ። ስለዚህም በዜጎች ዘንድ መጠላትን አተረፈላቸው። በኋላም በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የጀርመኑ መሪ ሂትለር ብዙዎቹን በመርዝ ጢስ ፈጃቸው። (ስድስት ሚሊዮን ገደማ)። እርግጥ ለዚህ ፍጅት ምክንያት የሆነው የኢኮኖሚ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ይበልጡን የሃይማኖታቸው ልዩ መሆን ነው። በሰፊው አውሮፓ ክርስቲያን ሕዝብ መሃል የአይሁዶች መገኘት ችግር ማስከተሉ በወቅቱ ግልጽ ነበረ።

ጦርነት ካከተመ በኋላ አይሁዳውያን አገር አልባ በመሆናቸው የደረሰባቸውን ግፍና መከራ በመመልከት እንደገና የራሳቸው አገር እንዲኖራቸው ታስቦ በ1948 ዓ.ም. የፍልስጥኤም ክልል ተሰጣቸው።

ችግሩ በዚህ አልተፈታም። ፍልስጥኤማውያን መሬታቸው ለአዲስ መጤዎች እንዲሰጥና እነሱ እንዲፈናቀሉ የተወሰነውን ውሣኔ አልተቀበሉም። ስለሆነም በአረቦች ጉረቤቶቻቸው (ግብጽ፣ ሶሪያ፣ ሳውዲት አረብ . . . ወዘተ) በመረዳት የመረረ የትጥቅ ትግል ጀመሩ።

አይሁዳውያንም ከአገሮቹ እየተሰባሰቡ ወደ አገር በመግባትና ጠንካራ ቴክኖሎጂ በመገንባት አገራቸውን ለመመከት ታጥቀው ተነሱ።



የአይሁዳውያን መቅደስ አርማ እና ባለስድስት ሜዶ "የዳዊት ጋሻ"

በ1956 ዓ.ም እና በ1967 ዓ.ም. በእስራኤልና በአረብ አገሮች መካከል ከባድ የሞት ሽረት ጦርነቶች ተደርገው እስራኤል እንደገና አሸነፈች። ግዛቷንም ከእጥፍ በላይ አስፋፍታ ያዘች።

ሆኖም እስራኤል ዘላቂ ሰላምን በመምረጥ ድርድር አድርጋ እነሆ ዛሬ በጦርነት የያዘቻቸውንም መሬቶች በከፊል መልሣ በማስረከብ ከአረብ ጎረቤቶቿ ጋር ለመኖር ስትሞክር ሃይማኖቷን ልምዷንና ባህልዋን ግን ባለመተው ነው።

ታልሙድ

ይህ የአይሁዳውያን የመንፈሳዊ ህግጋት ጥንቅር መጽሀፍ ነው የተጻፈው ከ200-300 ዓ.ም ውስጥ ነው። በዚያን ጊዜ የክርስትና ሃይማኖት ራሱን ከዚህ ሃይማኖት ለይቶ እና አግልሎ ነበረ። በአውሮፓ የተበታተኑት ሕዝቦች እየተጉላሉና ብቸኝነት እየተሰማቸው ስለሄደ አንድ የጋራ መግለጫቸው የሆነ የኑሮ መመሪያ ማጠናቀር አስፈላጊ ሆነ። ስለዚህም ታልሙድ ተጻፈ። ታልሙድ የሃይማኖት የህግ የባህል ሁሉ መመሪያ ሆነ። መጀመሪያ በእብራይስጥ ቋንቋ የተጻፈው ሰንድ ሚሽናህ የሚባለው የኦሪት ህግጋት አተረጓጎም ሲሆን ገማራ የተባለው በሌላ ቋንቋ የተጻፈው ደግሞ የዚሁ የተሻሻለ አተረጓጎም ነው። መጽሀፉ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን ሀጎችንና ሥነ ሥርዓትን የያዘው ክፍል ሃላካህ ሲባል የቀረው እና የጥንቱ የእነሙሴን ታሪክ የሚተርከው ክፍል በሃጋዳ ውስጥ የተጠቃለለ ነው። በተጨማሪም ሚድራሽ የተባለ ጥንታዊ ሰንድ ይኖራል።

ታልሙድ ሁሉንም የአማኞችን የሕይወት ዘርፍ የሚዳስስ ነው። የተከለከለ የምግብ ዓይነት፣ የአለባበስ ሥርዓት፣ የጸሎት፣ የበዓላት አከባበር፣ የግዝረት፣ የአስተጣጠብ . . . ወ.ዘ.ተ. ስርአቶችን ሁሉ ይወስናል። ታልሙድ ወንዶችንና ሴቶችን በእኩልነት አያስቀምጥም። ለምሣሌ ሴቶች ለምስክርነት ፍርድ ቤት አይጠሩም። እንዲሁም ሴቶች ለባሎቻቸው መታዘዝ ግዴታቸው ነው። (ይህ በሌሎች ሃይማኖቶችምአለ) ታልሙድ ለሌሎችም ዝርዝር መመሪያዎችን ያስቀምጣል። ሆኖም ዛሬ አንዳንድ መመሪያዎች እየተሻሻሉ እንዲሄዱ ተደረገዋል።

በዓላት

የአይሁዳውያን በዓላት አከባበር በብዙ መንገድ ከአገራችን አከባበር ጋር ተመሳሳይነት አለው።

አዲሱ ዓመት በመስከረም ወር ውስጥ ይጀመራል። ይህ ቀን በዓል ነው። ሮሽ ሃሻና ይባላል። ይህ የፍርድ ቀን ነው። እግዚአብሔር የየአንዳንዱን ሰው ያለፈ ዓመት ሥራ (ክፉውንም ደጉንም) በሕይወት መጽሀፍ ውስጥ የሚመዘግብበት ዕለት ነው።

የሚቀጥለው በዓል ከአስር ቀን በኋላ የሚመጣው ዮም ኪፑር ነው። ይህ የጸምና ጸሎት ቀን ነው። በመካከሉ ባሉት ቀናት ውስጥ ሰዎች ከጸለዩ ሱባኤ ከገቡ፣ ለድሃ ከመጸወቱ እግዚአብሔር በሮሽ ሃሻና የመዘገበውን ፍርድ ሊያሻሽልላቸው ወይም ይቅርታ ሊያደርግላቸው ይችላል። ዮም ኪፑር ግን የመጨረሻው ዕድል ሰለሆነ 24 ሰዓት ይጸማል። ምኩራብ ውስጥ ይጸለያል። ከመንፈሳዊ መጽሀፍ ይነበባል። ሰው ሁሉ የበደለው ካለ ቀርቦ ይቅርታ ለማግኘት ይሞክራል። እግዚአብሔርም በዚህ የመጨረሻ ቀን የሚሻሻለውን አሻሽሎ መጽሀፉን ይዘጋል። የመጽሀፉን መዘጋት እና የጸም ጸሎቱን መጨረሻ ለማብሰር በየምኩራብ ደወል ይደወላል።

እንደገና ከአምስት ቀን በኋላ የዳስ በዓል ይከበራል። (ሱኮት ይባላል)። ይህም ከአምስት እሰከ ዘጠኝ ቀን ይዘልቃል። ሰዎች ዳስ (ጎጆ) ሰርተው ከቤታቸው ወጥተው እዚያ ውስጥ ይቀመጣሉ። ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብጽ አውጥቶ ወደ ፍልስጥኤም ሲመራቸው ያለቤትና ያለመጠለያ በየበረሃው የተንከራተቱበትን የስደትና የመከራ ዘመን በማስታወስ የሚከበር በዓል ነው። ዛሬም አገር እና ቤት የሌላቸውን ሌሎች ወገኖቻቸውን ያስታውሱበታል፣ ያስቡዋቸዋልም። የመጨረሻው ቀን ታላቅ ክብረ በዓል ሆኖ ይውላል።

በ6ኛው ወር ፑሪም ይከበራል። በመጽሀፈ አስቴር እንደተዘገበው የፐርሺያ (ኢራን) ፕዚን ግፈኛውን ሃማንን ያሸነፉበት ጊዜ ስለሆነ በታላቅ ደስታ ይከበራል። አስቂኝ ልብስ ይለበሳል፣ የምግብ ስጦታ ይበረከታል፣ ለደህ ይዘከራል፣ ያንዕለት እስኪሰክሩ መጠጣት የተለመደ ነው።

ሃኑካ እንደ ክርስቶስ ልደት በታህሣሥ ወር የሚከበር ነው። እስራኤላውያን የሃይማኖት ነጻነታቸውን መልሰው የተጎናጸፉበት ቀን እንደሆነ ይቆጥሩታል። ሶሪያ እስራኤልን አሸንፋ በምትገዛበት በድሮው ዘመን ሃይማኖታቸውን ትተው የአሸናፊውን ወገን እንዲከተሉ ስትል ቤተመቅደሳቸውን ዘግታ ለሶስት ዓመት አግዳ ነበረ።

በኋላ ግን በይሁዳ ማካቤ የጦር መሪነት ተዋግተው ቤተ መቅደሳቸውን አስለቀቁ። ከዚያም አጽድተው እና አዲስ መሰውያ ሰርተው ሚኖራ የተባለ ባለ ዘጠኝ ሻማ መቅረዝ ሰቅለውና አብርተው የሃይማኖት ነጻነታቸውን አረጋገጡ። ስለዚህ በዓለ ብርሃን (ሃኑካ) ይባላል። እንደ ገና በዓል ስጦታ ይለዋወጣሉ። ልዩ ምግብ ያዘጋጃሉ የደስታ የፈንጠዝያ ምሽት ያዘጋጃሉ።

ሌላው ትልቁ በዓል የቂጣ በዓል ነው። እንደሚታወቀው በክርስትና እምነት መሠረት እየሱስ ክርስቶስ የቂጣ በዓልን ከ12ቱ ደቀመዛሙርቱ ጋር ሲያከብር ይህ የመጨረሻው እራት ነበረ። ስጋ ወደሙን የሰጠውም በዚህ እራት ላይ ነው። በአይሁዶች ታሪክ ውስጥ ይህ በዓል እስራኤላውያን ለረዥም የስደት ጉዞ በመዘጋጀት በአስቸኳይ ከግብጽ እንዲወጡ ሙሴ በሰጠው መመሪያ መሠረት እንጀራ ለመጋገር ሊጡ እንኳ እስኪቦካ ባለመጠበቅ ጭነው በመነሣት ቂጣ እየበሉ የተጓዙበትን ለማስታወስ ነው።

የግብጹ ንጉስ እስራኤላውያንን ከባርነት ነጻ አለቃቸውም ስላለ እግዚአብሔር የግብጻውያን የመጀመሪያ ልጅ ሁሉ እንዲሞት መልአከ ሞትን ሲልክ በሙሴ ትዕዛዝ እስራኤላውያን በግ አርደው ደጃፋቸውን የመስዋዕት ደም ቀብተውት ኖሮ ያን ሌሊት የሞት መልአክ ምልክቱን በማየት እያለፋቸው ሄደ። ንጉሡ በዚህ የሞት መቅሰፍት ደንግጠ ነጻ ለቀቃቸው። ስለዚህ በዓሉ የይለፍ (ፓስ ኦቨር) በዓል ይባላል። ልዩ እራትም ይዘጋጅለታል። የሙሴን ታሪክ ለማስታወስም ሃጋዳ መጽሀፋቸው ይነበባል። ይህ በዓል በዓለም ዙሪያ ያሉ አይሁዳውያን ሁሉ በያሉበት በየቤታቸው በአንድ መንፈስ የሚያከብሩት ስለሆነ ያለፈ ታሪካቸውን የሚያስቡበትና የአንድነት መንፈሣቸውን በየጊዜው የሚያድሱበት ትልቅ በዓል ነው።

የጴንጤቆስጤ በዓል ከቂጣ በዓል በኋላ በሃምሣኛው ቀን የሚውል ነው። በግሪክ ቋንቋ ጴንጤቆስጤ ማለት 50 ቀን ማለት ነው። ይህ ቀን ሙሴ እግዚአብሔር የሰጠውን ትዕዛዛት ከሲና ተራራ ላይ ይዞ ወርዶ ለእስራኤል ልጆች ያበረከተበት ዕለት ነው። አማኞች በዋዜማው ሌሊቱን ሁሉ በምኩራባቸው አድረው በጸሎት እና ቅዱስ መጽሀፍትን በማንበብ ያነጋሉ። ይህም ትዕዛዛቱን ለመቀበል ዝግጁ መሆናቸውን ለመግለጽ ነው። እሰከ ጴንጤቆስጤ ድረስ ያሉት 50 ቀናት ግን ጋብቻ የማይከናወንባቸው ጊዜያት ናቸው።

ሰንበት

ይህ በሳምንቱ መጨረሻ ላይ ቅዳሜ ቀን የሚከበር በዓል ነው። ከሙሴ አስርቱ ትዕዛዛት ውስጥ ቀደም ባሉት ሕብረተሰቦች ዘንድ አዲስ የሆኑት ሁለቱ ትዕዛዛት 1ኛ ጣኦታትን ወይም አማልክትን ትተህ በአንድ እግዚአብሔር ብቻ አምልክ የሚል ሲሆን 2ኛ ሰንበትን አክብር የሚለው ነው። በአዲስ ኪዳንም እንደሚታየው ሰንበት ቅዳሜ ነው። ምክንያቱም እየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለው (ስቅለት) ሰንበት ሳይገባ ሆኖ ከሙታን የተነሳው (ፋሲካ) ደግሞ ሰንበት ማግስት ነው።

አይሁዳውያን ሰንበትን በጣም ያከብራሉ። ስራም አይሰሩም። ይህም ማለት ለምሣሌ ምግብ አያበስሉም፣ እንጨት አይቆርጡም፣ እሳት አይለኩሱም፣ ሽክም አይሸከሙም፣ ረዥም መንገድ አይሄዱም፣ . . . ወ.ዘ.ተ. በዚህ ቀን ሰዎች ብቻ ሳይሆን እንስሳትም ዕረፍት ያገኛሉ።

በዓሉ የሚጀመረው ዓርብ ማታ ነው። ቀናት የሚቆጠሩት ከምሽቱ ጀምሮ እስከሚቀጥለው ምሽት (24 ሰዓት) ነው። ስለዚህ ዓርብ ልዩ ምግብ ተዘጋጅቶ ሁለት ሻማ ተለኩሶ ወይን ጠጅ በዋንጫ ተቀድቶ ሰንበት ከመግባቱ በፊት ዝግጅት ሁሉ ይጠናቀቃል። አባት ከጸሎት ሲመለስ ልጆቹን መርቆ ባለቤቱን አወድሶ ምግቡን ባርኮ በስነ ስርዓት ይመገባሉ። ማግስቱም እንዲሁ ይሆናል። ቀኑ የጸሎት የመዝሙር የዕረፍት ቀን ሆኖ ይውላል። ማታ ሶስት ከዋክብት ለመታየት ሲበቁ ቀኑ እንደመሸ ተወስዶ መብራት ይበራል፣ አዲሱ የሥራ ቀንም ይጀመራል።

ምኩራብ

ይህ የአይሁዳውያን የመሰብሰቢያ እና ጸሎት የማድረሻ ቦታ ነው። በጥንቱ ዘመን ንጉሥ ሰለሞን ለሙሴ ጽላቶች ማስቀመጫ ትልቅ ቤተመቅደስ አሰርቶ ነበረ። ይህ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ10ኛው ምዕተ ዓመት ነው። ይህንን መቅደስ ለመሥራት ሲባል ብርቅ ድንቅ ዕቃዎች ከዓለም ዙርያ (አፍሪካ፣እስያ፣እና አውሮፓ/እንዲሰባሰቡ ታዞ ስለነበር ነጋዴዎች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የሰለሞንን ዜና ያበሰሩት በዚያ አጋጣሚ ነው ይባላል።

ይህ ታላቅ ቤተመቅደስ በ6ኛው ምዕተ ዓለም በነቡከደነጾር ፈረሰ ተቃጠለ። አይሁዳውያንም ተሰደዱ። ከዚያ ከተመለሱ በኋላ (በ538 ዓ.ዓ) ቤተመቅደሳቸውን እንደገና አድሰው ቢሰሩትም እንደገና ደግሞ በ70 ዓ.ም. በሮማውያን ተቃጥሎ ጠፋ።** እነሱም ወደ አውሮፓ ፈለሱ። ስለዚህ ቤተመቅደስ ባልነበራቸው ጊዜ በምኩራብ መሰባሰብ ጀመሩ።

በቀድሞ ዘመን ምኩራብ ሲገነባ ዋናው መድረክ (መሰዊያ)መሃል ቦታ ላይ ሆኖ ሕዝቡ ዙሪያውን ይቆማሉ። ይህም በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉም ሰው በእኩልነት ስለሚታይ አንዱ ከፊት ሌላው ከኋላ የሚቆምበት ሁኔታ እንዳይኖር። ታስቦ ይመስላል። ስለዚህ የቅዱስ መጻህፍት ንባብ እና ሥነ ሥርዓት ሁሉ የሚከናወነው መሃል መድረኩ ላይ ነው። (እንደዛሬው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን)።

በኋላ ግን ምናልባት የአውሮፓውያንን ባህል በመያዝ መድረኩን ወደፊት ለፊት እልፍ በማድረግ ሰዎቹ ቀሳውስቱን እንደባለሥልጣን ወይም ባለሙያ አድርገው ፊት ለፊት እንዲመለከቱ ተደረገ።

ዛሬ ምኩራብ ሲገነባ ታቦቱ የተቀመጠበት ቦታ ከሰዎቹ አቀማመጥ ሲታይ ወደ ኢየሩሳሌም አቅጣጫ ይሆናል። ሕዝቡም ጸሎቱን ሲያደርስ ወደዚሁ ወደ ኢየሩሳሌም አቅጣጫ ይሆናል። ማለት ነው። (ሙስሊሞች ወደ ሜካ አቅጣጫ እንደሚሣለሙ ዓይነት)። የወንድና የሴት መግቢያ እና መጸለያ የተለያዩ ናቸው።

የጸሎት ሥነ ሥርዓት በቁም የሚከናወን ነው። መዝሙር፣ ቅዳሴ፣ የመጽሀፍ ንባብና ማሳረግ ሁሉ የሥነ ሥርዓቱ አካል ናቸው። የሰንበት ጸሎት ከ2.30 እሰከ 3 ሰዓት ሲፈጅ በሌሎች ቀናት ግን ከአንድ ሰዓት አይበልጥም።

** ስለሰለሞን መቅደስ ቦታ ታሪክ አባሪ (ገጽ 42) ይመልከቱ።

አባሪ

የሰለሞን መቅደስ መዘዝ

ንጉሥ ሰለሞን ለእግዚአብሄር መቅደስ ትሆን ዘንድ መርጠ የቆረቆራት ቦታ ረዥም ታሪክ ያላት ናት። ለምሣሌ ዛሬ በዚያ ቦታ ላይ ቆሞ የሚገኘው መስጊድ ነው። የአለቱ ላይ ጣሪያ Dome of the Rock በመባል ይታወቃል። የኡመር መስጊድ በመባልም ይጠራል።

የዚህ ዓለትማ ቦታ ማዕከል የሰለሞን መቅደስ ቅድስተቅዱሳን መሆኑ ይታመናል። በእየሱስ ዘመን ይህ ማዕከል በትክክል የት ቦታ እንደነበረ በፍርስራሹ ውስጥ የማይታወቅ ስለነበረና ቅድስተ ቅዱሳን ደግሞ ከሊቀ ካህናት በስተቀር ማንም ተራ ሰው ሊረግጠውና ሊረማመድበት የማይፈቀድ ቅዱስ ቦታ ስለሆነ ንጉሱ ሄሮድስ ዙሪያውን ግንብ አስገንብቶ አጠቃላይ ቦታውን ለሕዝብ ዝግ አደረገው። እስከዛሬም በዓለም ዙሪያ ያሉ አይሁዳውያን በሚሰግዱበት ጊዜ አቅጣጫቸውን ወደዚህ አድርገው ነው።

በኋላ ሙስሊሞች እየሩሳሌምን ሲይዙ በቦታው (ወይም በአካባቢው) መስጊድ ሰሩ። በቅዱስ ቁርዐን እንደተገለጸው ነቢዩ መሐመድ በ621 ዓ.ም. አካባቢ ወደ መንግስተ ሰማያት ወጥቶ የተመለሰው በዚህ ቅድስተ ቅዱሳን በኩል ተወስዶ በማረግ ነው። (የሰው ዘር ከአዳም ውድቀት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር የሚገናኝበት በዚህ ምርጥ ቦታ በኩል ስለሆነ ነቢዩ መሐመድም ወደ ሰማይ የተወሰደው በዚሁ ተገቢ መንገድ ነው ተብሎ ይታመናል።)

ስለሆነም ቦታው ቅዱስ ነውና ለመጀመሪያ አንድ ዓመት ገደማ ሙስሊሞች ሲሰግዱ አቅጣጫቸውን (ቂብላ) ወደዚህ ቦታ አድርገው ነው። ይህ በኋላ ቢቀርም በ690 ዓ.ም. አብዱልማሌክ መስጊድ አሰርቶበት በቅድስና ይዞት አቆይቶታል። እንደገና ደግሞ በመስቀል ጦርነት አማካኝነት ክርስቲያኖች በ1099 ዓ.ም. እየሩሳሌምን ከሙስሊሞች አስለቀቁ። መስጊዱንም አፈራርሰው ቤተ ክርስቲያን ተከሉ አሁንም እንደገና በሰላዲን መሪነት ሙስሊሞች በ1193 ዓ.ም. ሲያሸንፉ ቤተ ክርስቲያኑ ፈርሶ በቦታው ላይ መስጊድ ተሰራበት። በ1453 ታላቋ የክርስቲያን ማዕከል የሆነችው ቁስጥንጥኒያ ራሷ ስትወድቅም የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ አከተመለት።

በ1967 ዓ.ም. አይሁዳውያን በ6 ቀኑ ጦርነት ሙስሊሞችን ሲያስለቅቁም አንዱ ትርፋቸው ይህን ቅዱስ ስፍራ ማስመለስ ነበረ። (በደስታ ስሜት አልቅሰውበታል)። ግን በመስጊዱ ላይ ጥፋት አላደረሱም። ሆኖም ዛሬም አክራሪ አይሁዳውያን ይህንኑ መስጊድ በሃይልም ቢሆን አፈራርሰው መቅደሳቸውን ለ3ኛ ጊዜ ሊገነቡበት ያደባሉ። በዓለም ዙሪያ ያሉ ሙስሊሞች ደግሞ ይህ ከሜካ እና ከመዲና መስጊዶች ቀጥሎ ዋንኛ ቅዱስ ቦታቸው ስለሆነ ዝም ብለው አያዩም።

ስለዚህ ሰለሞን የቆረቆራት ቦታ ታሪክ አሁንም መጨረሻ ያገኘ አይመስለኝም።

ማጠቃለያ

የአይሁዳውያን ዕምነት ከአራት ሺህ ዓመታት በፊት በአብርሃም የተጀመረ ነው። ይህ ዕብራዊ ምሁር ለጣኦት መስገድ እና ልጁን ለመሰዋት ከተወ ወዲህ የእርሱ ዘር በተለይም 12ቱ የእስራኤል ነገዶች በአንድ እግዚአሔር ብቻ የማምለክ እምነታችውን ይዘው ዘልቀዋል።

ከዚህ ሃይማኖት የመነጩ በርካታ ሃይማኖቶች ዛሬም አንዳንድ ከዚያ የተወረሱ የሚመስሉ ባህርያትን ያንጸባርቃሉ።


ለአይሁዳውያን ሃይማኖት ቅርጹን የሰጠው ሙሴ ነው። የሃይማኖቱ መሠረት የሆኑት አስርቱ ትዕዛዛትም በሙሴ በኩል የወረዱ ናቸው። ከእነኝህም የመጀመሪያው ትዕዛዝ ጣየታትን የሚያስወግድ በመሆኑ ለሰው ልጅ የባህል ዕድገት መሰረት የጣለ ነው።

“ሰንበትን አክብር” የሚለውም ትዕዛዝ ሰድስት ቀናት ደክሞ በሰባተኛው ዕረፍት ማድረግ ለሰዎች ቀርቶ ለእንስሳትም የጠቀመ ነው።

የአይሁዳውያን ሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓት በአገራችንም ይታወቃል። ቤተ ክርስቲያን ተሂዶ ሲጸለይ ሴትም ሆነ ወንድ መከናነብ እንዳለባቸው በተለይ ሴቶች ፀጉራቸውን መሸፈን ያለባቸው መሆኑ፣ ቤተ ክርስቲያን መግቢያ በር የተለያየ መሆኑ፣ጽላቶች (ታቦት) የቤተ ክርስቲያን መሰረታዊ መሆን ወ.ዘ.ተ. ።

አንዳንድ ክስተቶች ምናልባት በእርግጠኛነት ላይወሰዱ ይችላሉ። እነዚህም ለምሣሌ 1ኛ- አይሁዳውያን በፀሎት እንዲሰባሰቡ ስለሚፈልጉ ለመጸለይ ቢያንስ ዘጠኝ ሰዎች እንዲሰበሰቡ ስለሚሹ ይህ ዘጠኝ ቁጥር ለባሃይ አማኞች ወሳኝ ቁጥር መሆኑ 2ኛ- እግዚአብሔር የእሥራኤልን ነገድ ለመጠበቅ ቃል የገባው ለ12ቱ ነገዶች በመሆኑ እየሱስም ይህን ትንቢት ለመፈጸምና አሪትን ለማደስ ሲል 12 ደቀ መዛሙርትን መርጠ በመሾም በመላው ዓለም እንዲያስተምሩ ማድረጉ አንዳንድ ክስተቶች ናቸው።

የአይሁዳውያን ሃይማኖት ትልቁ ነጸብራቅ ግን መሢህ ወደፊት ይመጣል የሚለው እምነት ነው። እግዚአብሔር አንድ አገልጋዩን እንደሚልክላቸው በትንቢተ ኢሣያስ ተጽፏል። እንደገናም በትንቢተ ዳንኤል በህልም መልክ ተነግሯል። መሢህ መቸ እና እንዴት እንደሚመጣ በትክክል የታወቀ ባይሆንም አመጣጡ “ለዘመንና ለዘመናት ለዘመንም እኩሌታ ነው፤የተቀደሰውም ሕዝብ ሃይል መበተን በተጨረሰ ጊዜ ይህ ሁሉ ይፈጸማል” ተብሎ ተጽፏል።



በሰለሞን መቅደስ ቦታ ላይ ያለው ባለወርቅ-ቅብ የኡመር መስጊድ

ዛሬ እስራኤላውያን ከዓለም ዙሪያ ተሰባስበው ከሁለት ሺ ዓመታት ስደትና መከራ በኋላ አንድ መንግሥት ለመመስረት መብቃታቸው ለዓለም መጨረሻ መቃረብ እንደ አንድ ምልክት ይወሰዳል ተብሎ ይታመናል። በየቦታው የሚታየው እልቂት ረሃብ ቸነፈር በሽታ እና እርስ በርስ ግድያ (ጦርነት) ሌላው ምልክት ሆኖ ይወሰዳል።

በአጠቃላይ ይህ ጥንታዊ ሃይማኖት ለሰው ልጅ የኑሮ መመሪያ እና አስተሳሰብ አስተዋጽዖ በማድረግ ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውቷል። ዛሬም ቢሆን በዓለም ላይ እስከ 15 ሚሊዮን ተከታዮች ያሉት ሲሆን በመካከለኛው ምሥራቅ የሚጫወተው ፖለቲካዊ ሚና የዓለምን ትኩረት እንደገዛ ነው።

የክርስትና ሃይማኖት

የናዝሬቱ እየሱስ

እየሱስ በትውልድ አይሁዳዊ ነበረ። ከንጉሥ ዳዊት ዘር የተወለደ ለመሆኑ በማቴዎስ ወንጌል መጀመሪያ ምዕራፍ በዝርዝር ቀርቧል። ንጉሡ ዳዊት የአብርሃም 14ኛ ትውልድ ሲሆን እስከ ዮሴፍ (የድንግል ማርያም እጮኛ) ሃያ ስምንት ትውልድ እንደሆነ ያስቀምጣል።

የእየሱስ እናት ማርያም እራስዋ ለእናቷ ብርቅዬ ልጅ ነበረች። እናቷ ሃና ልጅ ስላልነበራት ለእግዚአብሔር ተስላ ማርያምን ወለደች። ስለዚህም በደንቡ መሠረት ማርያም ለቤተ እግዚአብሔር እንድታገለግል ሃና ወስዳ ለቀሳውስቱ አበረከተቻት። ማርያም መቅደስ የገባችበት ቀን ዛሬም ይዘከራል። ማርያም አድጋ ዮሴፍ እጮኛዋ ሆነ። ከዕጮኛዋ ጋር እንዳለችም ኢየሱስን አርግዛ ወለደች። መጽሐፍ ቅዱስ (ማቲዎስ ወንጌል) እንደሚገልጸው

"እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ጸንሳ ተገኘች።"

እየሱስ የተወለደው በቤተልሔም ከተማ ነው። እናቱ ከዮሴፍ ጋር ከናዝሬት ከተማ ተነስታ ወደ ቤተልሔም ሄዳ ሳለ በእንግድነት ማደሪያ ቦታ አጥታ በበረት

ግርግም ውስጥ እንዳደረች ሕጻኑን ወለደች። ከዚያም ዮሴፍ ወላጁን ከነ ህጻኑ ይዞ ወደ ግብጽ እንደሸሹና ከዚያም ቆይተው ተመልሰው ናዝሬት ከተማ መኖር እንደጀመሩ ተዘግቧል።

እየሱስ በህጻንነቱ በጣም ብሩህ እና አስተዋይ ነበረ። በአይሁዳውያን ልምድ መሰረት በየሳምንቱ መጨረሻ ምኩራብ እየሄደ ይጸልያል። የሃይማኖት መጻህፍት ሲነበቡ ይከታተላል፣ ይወያያል። አንዳንዴም የነቢያትን መጻህፍት ሲያነብ በግልጽ ሊረዳ በመቻሉ ከተቀመጠበት

እየተነሣ ለሌሎች ያስረዳል፣ ያብራራል። እየሱስ የማስረዳትና የማስተማር ከፍተኛ ተሰጥኦ እንደነበረው ገና በልጅነቱ ግልጽ ነበረ።

እየሱስ አስራ ሁለት ዓመት ከሞላው በኋላ ለሚቀጥሉት አስራ ስምንት ዓመታት ስለ አስተዳደጉ የተዘገበ ነገር የለም። በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈው "እየሱስ በጥበብ እና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር" የሚል ብቻ ነው። ዮሴፍ በዚህ መካከል ሞቶ ስለነበረ ማርያም ከናዝሬት ከተማ በመውጣት ልጇን ይዛ ወደ ትውልድ ስፍራዋ ወደ ቃና ዘገሊላ መመለሷን እዚያም ልጇ በአናጢነት ስራ ላይ ተሰማርቶ ቤተሰቡን ይረዳና ያስተዳድር እንደነበር ይገመታል። ቤተሰቡ ማለት እናቱ ማርያም እና እንዲሁም አራት ወንዶችና ከሁለት ያላነሱ ሴቶች (ማር፡ 6፣3) ሊሆኑ ይችላሉ።

እየሱስ ስለ ቅዱሳን መጻህፍት በይበልጥ የተከታተለውና በየጉባኤው እየቆመ ሃሳቡን መግለጽና ማስረዳት የደረሰው በዚሁ በቃና ዘገሊላ መንደር ነበረ።

እየሱስ ሰላሣ ዓመት በሞላው ጊዜ በአካባቢው ዝናው ይነገርለት ወደ ነበረው ዮሐንስ የተባለ ሰው ሔዶ ሊገናኘው ወስኖ የአናጢነት ስራውን ትቶ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ ሄደ። ዮሐንስ በትንቢተ ዳንኤል የተነገረውን የመሢህ መምጣት በእርግጠኝነት ወስዶ ይሰብክ ያሳምን ነበረ። ሰዎችም አምነው ከሃጢያታቸው መንጻታቸውን ለማስመስከር ሲፈቅዱ በውሃ ያጠምቃቸው ነበረ። እየሱስም በትንቢተ ዳንኤል ወትሮም ይመስጥ ስለነበረ (በልጅነቱም ያንን ደጋግሞ ማንበብ ይወድ ነበረና) ወደ ዮሐንስ ቀርቦ በመጠየቅ በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ ተጠመቀ።

ከዚያ በኋላ እየሱስ የአናጢነቱን ስራ ትቶ ወደ ይሁዳ ምድረ በዳ ሄደ። ለአርባ ቀናት በብቸኝነት በጸም እና በጸሎት አሳለፈ። ከዚያም በኋላ እየተዘዋወረ በቃና ዘገሊላ በናዝሬት በእየሩሣሌም በቅፍርናሆም በሰማርያ እና በቢታንያ ማስተማር ጀመረ። ተከታዮችም አገኘ።

የእየሱስ ትምህርት ወዲያው ከፈሪሳውያንና ከካህናት ያቃርነው ጀመረ። በፈሪሳውያን እምነት መሰረተ እግዚአብሔር የተቀየማቸው የሙሴን ህግ በሚገባ ስላላከበሩ በመሆኑና ወደ ባቢሎንም ተግዘው በስደት ሲሰቃዩ የኖሩት በዚህ ጥፋታቸው በመሆኑ አሁን ወደ አገራቸው ከተመለሱ ዘንድ ህግጋቱን አጥብቀው ለመያዝ ነበረ። ከዚያ ውጭ ማሰብና መስራት ፍጹም ሃጢያት እንደሆነ ያስተምራሉ።

የእየሱስ ትምህርት ግን ከዚህ ለየት ያለ ሆነ። ዝነኛ የሆነው የተራራ ስብከት እንደምሣሌ ሊጠቀስ ይችላል።

በኦሪት ህግ ውስጥ "በውሸት አትማል፣ አታመንዝር፣ አትግደል፣ ባልንጀራህን ውደድ፣ ጥርስህን ያወለቀ በጥርሱ መውለቅ ይቀጣል" ይላል። የኢየሱስ ትምህርት ግን "ጽድቃችሁ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም" በማለት ይጀምርና፣

አትግደል ይፈረድብሃል ተብሏል፤ እኔ ግን እላችኋለሁ መግደል ቀርቶ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ይፈረድበታል።

አታመንዝር ተብሏል፤ ግን ወደሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያንጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል። . . . ያለዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል፤ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል።

በውሸት አትማል ተብሏል፤ መሃላዎችንም ለጌታ ስጥ ተብሏል፤ እኔ ግን እላችኋለሁ ከቶ አትማሉ ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን።

ጥርስ የሰበረ በጥርሱ ይቀጣል ተብሏል፤ እኔ ግን ክፉውን አትቃወሙ ጠላቶቻችሁን ውደዱ እላለሁ" በማለት ያስተምር ነበረ። በአጭሩ ኦሪት ስለሕግ ሲያስተምር እየሱስ ግን ስለ ፍቅር አስተማረ።

ፈሪሳውያን ይህንን የኦሪትን ሕግ የመለወጥ አዝማሚያ አልወደዱለትም። በእየሱስ አስተምሮት የተነሣ ስልጣናቸውም ሆነ በሕዝብ ዘንድ የነበራቸው ተሰሚነት እየቀነሰ መጣ። ስለዚህ ይህንን ሰው ማጥፋት ተገቢ ሆኖ አገኙት። ስለሆነም መክረውና ዘክረው፤ ምክንያት ፈልገው እና አግኝተው፣ እየሱስን ከሰው ለፍርድ አቀረቡት። "የኦሪትን ህግ አላከበረም (ለምሣሌ ሰንበትን እንደ አይሁዶች አጥብቆ ማክበር) ከዚያ በተጨማሪ የእግ ዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሎ ያሳስታል" በማለት ወነጀሉት፣ በስቅላት እንዲቀጣም አስፈረዱበት።

በዋዜማው የአይሁዳውያን የቂጣ በዓል ነበረና እየሱስ በባህሉ መሠረት ከደቀመዛሙርቱ ጋር አከበረ። ይህ ቂጣ መብላትንና ወይን ጠጅ መጠጣትን ያካተተ እራት ለእየሱስ የመጨረሻው እራት ነበረ። እሱም ይህንን በቅድሚያ ተረድቶት ነበረና እራታቸውን ሲበሉ እየሱስ ቂጣውን አንስቶ ባርኮ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና "እንካችሁ ብሉ፣ ይህ ስጋዬ ነው" አለ። ጽዋውንም አንስቶ "ሁላችሁም ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ሃጢያት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው" አለ። ይህ ስነ ሥርዓት ዛሬ ቁርባን በመባል የሚታወቅና በቤተ ክርስቲያን የሚከናወን ነው።

እየሱስ በዕለተ ዓርብ ተይዞ በመስቀል ላይ ተሰቀለ። ሰንበት ከመግባቱ በፊትም ተቀበረ። ነገር ግን እሁድ ጧት መቃብሩ ባዶ ሆኖ ተገኘ። በሌላ ቀንም እየሱስ ለእናቱ እና ለደቀ መዛሙርቱ በአካል ተገለጠ።

ደቀ መዛሙርቱ አስተማሪያቸው በመኖሩ ሐዘናቸው ወደ ደስታ ተለወጠ። ዜናውም በሰፊው ተሰራጨ። ክርስቶስ መሆኑንም አወቁ። ክርስቶስ ማለት በጽርዕ ቋንቋ "የተቀባ" ማለት ነው። ተከታዮቹም ክርስቲያኖች በመባል ይጠሩ ጀመረ።

ክርስቲያኖቹም የስቅለቱን ዕለት ለማስታወስ በሰንበት ማግስት እየተሰበሰቡ ይጸልዩ ነበረ። መጀመሪያ ቀሳውስቱን በመፍራት ስብሰባቸውን በድብቅ ያደርጉ ነበረ። በኋላ ግን ትምህርቱን በማስላስል በርካታ ሰዎች (በተለይም ድሆች) እያመኑ መጡ። ስለዚህም ስብሰባው በግልጽ እየሆነ

መጣ። በማህበርም ተደራጁ። አባል ለመሆን በመጀመሪያ መጠመቅ አስፈላጊ ነበር። እነዚህ አባላት በመረዳዳት በመተሳሰብ እና በመፋቀር እንዲያውም ንብረታቸውንም የጋራ በማድረግ ለሌሎች ልዩ አርአያ ሆኑ። በዚያን ጊዜ የነበራቸው እምነት እየሱስ ክርስቶስ በምጽአት ጊዜ ተመልሶ እንደሚመጣና ለሁሉም እንደስራው ፍርድ እንደሚሰጠው ነበረ። ስለ አመጣጡም ከተጻፉት መካከል "ጸሐይ ይጨልማል፣ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፣ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፣ የሰማያት ሃይላትም ይናወጣሉ በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ በብዙ ሃይልና ክብር በደመና ሲመጣ ያዩታል (ማር 13÷24-26) ይህም በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሚሆን ያስቡ ነበረ። 'እውነት እላችኋለሁ የሰው ልጅ በመንግሥቱ ሲመጣ እስኪያዩ ድረስ እዚህ ከሚቆሙት ሞትን የማይቀምሱ አንዳንድ አሉ" (ማቴ 16÷28)።

በዚህ የተነሣ ክርስቲያኖች ተግተው ይጸልዩና ይረዳዱ ነበረ። በአይሁዶች በዓል በጴንጤቆስጤ ዕለት በአገሩ ባህል መሠረት ክርስቲያኖችም ተሰብስበው ባህሉን ሲያከብሩ ዕለቱም እሁድ በመሆኑ በደንባቸው መሠረት ሲጸልዩ ሳለ አንድ ነገር ተከሰተ። "ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎ ንፋስ ከሰማይ ድምጽ መጣ ተቀምጠው የነበረበት ንም ቤት ሁሉ ሞላው እንደ እሣትም የተከፋፈሉ ልሣኖች ታዩዋቸው። በእያንዳንዳቸው ላይ ተቀመጡባቸው። በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፣ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።" (ሃዋ ሥራ 2÷2-4) ይህ ዛሬ በ"ሙሉ ወንጌል" አማኞችና በሌሎችም ዘንድ ልዩ ትኩረት የተሰጠው ነው። ከጴንጤቆስጤ በኋላ ደቀመዛሙርቱ ከመንፈስ ቅዱስ በተሰጣቸው ሃይልና ስልጣን ሐዋሪያት ሆነው ሊያስተምሩ ተነሱ፣ በዓለም ዙሪያ እስኪደርሱም መሰራጨት ጀመሩ። ዛሬ ክርስቲያን የሆነ ዜጋ የሌለው አገር ብዙም አይገኝም።

የክርስቲያንን እምነት ከጠባብ የአይሁዳዊነት አስተሳሰብ አላቆ ዓለምአቀፋዊ ይዘት የሰጠው ከሃያ ዓመታት በኋላ የተገኘው ትልቁ እና ዝነኛው ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ነው። ጳውሎስ በሮም አገዛዝ ምክንያት ከአገር ተሰደው ይኖሩ ከነበሩት አይሁዳውያን የተወለደ ሐቀኛ አይሁዳዊ ነበረ። ስሙም ሳውል ነበረ። ነገር ግን በሮማ ግዛት ተወልዶ ያደገ በመሆኑ ጳውሎስ የተሰኘ የሮማውያን ስም ተሰጠው። ጳውሎስ መጀመሪያ ጸረ-ክርስቲያን ነበረ። ወደ እየሩሣሌም ተጠርቶ የመጣውም ክርስቲያኖችን እንዲያጠፋ ነበረ። በኋላ ግን ራሱ አምኖ ተለወጠ። ሃይማኖቱንም በበለጠ ማስፋፋት ጀመረ። ከእየሩሣሌም ተነስቶ በቱርክ አልፎ በግሪክና በአካባቢው ያሉትን በርካታ አገሮች አዳርሶ በመጨረሻ እስከ ሮማውያን ዋና ከተማ ዘለቀ። በየሄደበት ቦታ ሁሉ ቤተክርስቲያን በማቋቋምና አማኞችን በማጥመቅ ሃይማኖቱን በእጅጉ አስፋፋ። በመጨረሻ ግን በሮማ ከተማ ቤተክርስቲያን ለማቋቋም ጥረት ሲያደርግ ተይዞና ተወንጅሎ ተገደለ። ቅዱስ ጳውሎስ በሕይወት ዘመን ከጻፋቸው መልዕክቶች አሥራ አራቱ በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ታቅፈዋል።

የመጽሀፍ ቅዱስ ክፍሎች

የክርስቲያኖች ሃይማኖት መነሻው ከእየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት ነው። እንዲያውም በአዳም ይጀምራል። ሙሴ እንደጻፈውና አይሁዳውያንም እንደሚያምኑት አዳም እግዚአብሔር የደነገገውን የአኗኗር ስነ ስርዓት በመጣስ (ከተከለከለችው ፍሬ በመብላት) ሃጢያተኛ ሆነ የአዳም ዘሮች መንግስተ ሰማያትን ለመውረስ ብቁ አልሆኑም። ምድርንም በከሏት። ስለዚህ የኖህ ውሃ ዋጋቸውን ሰጣቸው። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ዳግም የጥፋት ውሃ እንዳያመጣ ከኖህ ጋር ቃል ኪዳን ቢገባም የሰው ልጅ ከጥፋት መንገድ አልተመለሰም። ስለሆነም እግዚአብሔር አብርሃምን መርጠ ባረከው። ትዕዛዙንም እንዲፈጽም እና ዘሮቹም የተመረጡ ሆነው ከነሱ ዘር መሲህ እንዲመጣ ቃል ኪዳን ገባለት። 12ቱ የእስራኤል ነገዶችም በሙሴ መሪነት ከባርነት ወጥተው ወደ ቅድስት አገር እንዲመለሱ አደረገ። ንጉሥ ዳዊትንም ሰጣቸው። እሥራኤላ ውያን ግን ሕጉን አላከበሩም። በየጊዜው የተላኩላቸውንም ነቢያት ትምህርትና ማስጠንቀቂያ አልተ ቀበሉም። ስለሆነም ለባቢሎን ስደትና ስቃይ ተዳረጉ። ከዚያም ሲመለሱ አልተማሩም። ስለሆነም በመጽሀፈ አሪት በተሰጠው ተስፋ መሠረት እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ላከ። በልጁ ደም የሰው ልጆች ከሃጢያታቸው ይነጹ ዘንድ መንግሥተ ሰማያትንም ይቀዳጁ ዘንድ ቃል ኪዳኑን ጠበቀ። ትንቢትም ተፈጸመ። እየሱስ ክርስቶስ ስጋ ለብሶ ከድንግል ማርያም ተወለደ። እንግዲህ ይህ ሁሉ የተያያዘ ነው። ስለሆነም የክርስቲያኖች መጽሀፍ ቅዱስ ሰላሣ ዘጠኙን የኦሪትን መጻህፍት ጭምር ያቀፈ ነው። ይህ የኦሪት ስብስብ "ብሉይ ኪዳን" በመባል ሲታወቅ የእየሱስ ክርስቶስ እና ሐዋርያቱ አስተምሮት በኋላ የተጠናቀረው ስብስብ ደግሞ "አዲስ ኪዳን" ይባላል።

አዲስ ኪዳን አራት ክፍሎች አሉት÷

ሀ- አራቱ ወንጌላት÷ በአራቱ ሐዋሪያት በቅዱሳን ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ሉቃስና፣ዮሐንስ የተጻፉት ወንጌሎች ስለ እየሱስ ክርስቶስ ምድራዊ ሕይወትና አስተምሮት፣ ተአምሮች፣ስቅለትና ትንሣኤ የሚያስተምሩ ናቸው።

ለ- የሐዋርያት ሥራ÷ የመጀመሪያዎቹ ደቀመዛሙርትና ሌሎች ስላከናወኑት የስብከትና የጥምቀት ተግባሮች የሚያስረዳ በቅዱስ ሉቃስ እንደተጻፈ የሚታመንበት ነው።

ሐ- መልዕክቶች የቅዱስ ጳውሎስ አሥራ አራት መልዕክቶችና ሌሎችም በእነ ቅዱስ ጴጥሮስ የተጻፉ ሰባት መልዕክቶች፣

መ- ራዕይ÷ በቅዱስ ዮሐንስ እንደተጻፈው፣

እርግጥ ሌሎች ሐዋርያት የጻፏቸው መልክቶች ነበሩ። ነገር ግን የሃሣብ ድግግሞሽ ያሉባቸውን በመለየት ለሃይማኖቱ ግንዛቤ እነዚህ በቂ እንዲሆኑ ቅዱስ አትናቴዎስ ሃሳብ አቀረቡ። (ቅዱስ አትናቴዎስ

የመጀመሪያውን የኦርቶዶክስ ጳጳስ አባ ሰላማን ሾመው የላኩልን የእስክንድርያው ጳጳስ ናቸው።) ይህ ያቀረቡት የቅዱስ መጽሐፍት ሊስት በመንፈሳዊ ጉባኤዎች ጸድቆ ከዚያን ዘመን ጀምሮ ይሰራበታል።

የፈተና ወቅት

የክርስቲያን እምነት በታሪክ አጋጣሚዎች ጭምር በቀላሉ ሊሰፋፋ አልቻለም። ከመጀመሪያውም ቢሆን ሰፊው የአይሁ ዳውያን ዜጋ እየሱስን እንደመሲህ አልተቀበለም። እርግጥ አንድ ከእግዚአብሔር የተላከ ጀግና ወይም ዳኛ ወይም መሪ እንደ ሚመጣላቸው በትንቢት መጽሀፍት ተጽፏል (ለምሳሌ ኢሳ 7÷14 እና ሚክ 5÷2)። በዚህ ዘመን ደግሞ እስራኤል ወይም ፍልስጥኤም በሮማውያን ቅኝ ግዛት ስር ወድቃ ነበር። የሮማ መንግሥት ግሪክን፣ ቱርክን፣ ሊባኖስን፣ አርመንንና ግብጽን ሌሎችንም በርካታ አገሮች ያጠቃለለ ግዙፍ መንግሥት ስለነበረ ይህን በሃይል ተጋፍቶ ለማሸነፍ ለአይሁዳውያን ፍጹም የማይ ታለም ሆነባቸው። በዚያ ላይ የሮማ አገዛዝና የወታደሮቹ ጭካኔ የሚያስመርር ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር ለዚህ አንድ መፍትሄ እንዲልክላቸው ይመኙና ይጸልዩ ነበረ።

ግን እየሱስ እየዞረ ያስተምር የነበረው እንደ ተራ ሰው ነበረ። አስተዳደጉም ሆነ አለባበሱ ከሌሎች ምንም ያልተለየ ስለነበረ የእነሱ መሲህ በዚህ መልኩ ይመጣል ብለው አላመኑም። ስለዚህ አልተቀበሉም።

ከእየሱስ ስቅለት እና ቀብር በኋላ መቃብሩ ባዶ ሆኖ ሲገኝ ደቀመዛሙርቱና ሌሎችም ተከታዮቹ የሞራል ብርታታቸው ጠነከረ። በኋላም ትምህርቱ በእነ ቅዱስ ጳውሎስ አማካኝነት መስፋፋት ጀመረ። አህዛብም ተቀበሉት። ለዚህ አንድ ዋና ምክንያት ሃይማኖቱ ለተጨቋኞች መከራ ምላሽ ሆኖ መገኘቱ ነው። ትናንሽ መንግሥታትና ህዝቦች ይህንን የሮማ መንግሥት የመከራ ቁንበር ከጫንቃቸው ላይ አውርደው ለመጣል አልተቻላቸውም። ስለሆነም ተስፋ መቁረጥ ጀመሩ። የሞራል ውድቀት ሰፈነ። የሚያደርጉት ጠፋቸው። በዚህን ጊዜ ነበረ የክርስቲያን አስተምሮት ደርሶላቸው በሚቀጥለው ዓለም ዘለዓለማዊ ሕይወት ለማግኘት እንደሚቻል የተሰፋ ጭላንጭል ያሣያቸው። ሃይማኖቱን በቅድሚያ ከተቀበሉት መካከል ጭቁን ባሮችና ጭቁን ወዝአደሮች ነበሩ። የወንድማማችነትንና የእኩልነትን ስሜት ለሁሉም ሰዎች በእኩል ደረጃ ያሳናጸፈው ይህ አዲሱ እምነት ነው። ስለዚህም ተወዳጅነትንና ተቀባይነትን አገኘ። አማኞችም በረከቱ።

በዚሁ አንጻር ደግሞ የሮማ መንግሥትም ተቃውሞ እየከረረ መጣ። ሮማውያን ነገስታቶቻቸውን (ቄሣሮችን) እንደ አምላካቸው ያህል ያመልኩ ነበረ። ጣዖታትም የራሣቸው ነበሩአቸው። ስለዚህ የክርስቲያኖች አስተምሮት አልተስማማቸውም። በዚህ የተነሣ ክርስቲያኖችን በግልጽ አደባባይ ለተራቡ አራዊት በመጣልና በማቃገል ጨዋታ እያስበሏቸውና በሌላ የተለያየ ዘዴም እያሰቃዩዋቸው ይዝናኑ ነበር። በዚህ ዓይነት በርካታ ክርስቲያኖች በሃይማኖታቸው ጽናት የተነሣ መራራ ጽዋ ተቀብለዋል። ሐዋሪያውያ

ቅዱስ ጴጥሮስ ተዘቅዝቆ እንዲሰቀል የተደረገው በዚህ ጊዜ ነበረ። ቦታውም ዛሬ የካቶሊክ ማዕከል የርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ቤት የቅዱስ ጴጥሮስ ቤተክርስቲያን (ባሲሊካ) ነው።

የክርስቲያን ሃይማኖት አዲስ ምዕራፍ የተከፈተለት በ313 ዓ.ም. ቆስጠንጢኖስ (የእሌኒ ልጅ) ሲነግስ ነበረ። ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ይሆንን ሃይማኖት በመዋጋት ችግሩ እንደማይፈታና ክርስቲያኖችም በመከራው እንደማይበገሩ በመረዳት ከዚህ ይልቅ ሃይማኖቱን ቢቀበለው ሰፊው ጭቁን ህዝብም በቀላሉ እንደሚተባበርለትና መንግሥቱም እንደሚጸና ተረዳ። ስለሆነም ራሱ ንጉሡ ክርስትናን ተቀበለ ይባላል። ሌሎችም ሹማምንት እንዲቀበሉት አበረታታ። በዚህም ክርስትና የንጉሠ ነገሥቱ ግዛት ብሔራዊ ሃይማኖት እንዲሆን አደረገ። ከዚህ በኋላ ክርስቲያኖች መከራና ስቃይ፣ግርፊያ እና እስራት ቀረላቸው። ሃይማኖቱንም አስፋፉ።*

የሃይማኖቱ መከፋፈል

የክርስትና እምነት በቀላሉ ዓለም አቀፋዊ አልሆነም። በሂደት ላይ በርካታ መሰናክሎች አጋጥመውታል። አንዳንዶቹን በቀላሉ የፈታ ሲሆን ሌሎቹ ግን ሊፈቱ ባለመቻላቸው ሃይማኖቱ እንዲከፋፈል ግድ ሆኗል። ዛሬ ከሁለት መቶ በላይ የተለያዩ የክርስቲያን እምነቶች እንዳሉ ዘገባዎች ይገልጻሉ።

በመጀመሪያ ተነስቶ የነበረው ጥያቄ ክርስትያንነት ከአይሁድነት የመነጨና ከኦሪት ትንቢት ጋር የተያያዘ መሆኑ ነው። ኦሪት ደግሞ የእስራኤላውያን እምነት ነው።

እግዚአብሔር ምርጫውን ያደረገው ቃልኪዳንም የገባላቸው በተለይ ለእነሱ ለአብርሃም ልጆች ነው። ለምሣሌ ግዝረትን ያዘዘው የእነሱን ወገን ከሌላው ለመለየት ነው። ስለዚህ ይህ ሃይማኖት አይሁዳውያን ላልሆኑ ወገኖች አልታሰበም የሚል ነው። በአዲስ ኪዳንም እንኳ ስለ እሥራኤል ልጆች ምርጥነት መላልሶ ይናገራል። ቅዱስ ጳውሎስ ግን ይህንን ችግር ሲፈታ እንደሚከተለው አስቀመጠው። "እርግጥ አይሁዳውያን ተመርጠው ነበረ። የተመረጡት ግን ለድሎት ሣይሆን ለአገልግሎት ነበረ። እነሱ ይህንን ባለመረዳታቸው እግዚአብሔር በሥልጣኑ ይህን ሃላፊነት ለአዲሶቹ ለቤተ እሥራኤል ልጆች ማለትም ለቤተክርስቲያን ልጆች (ለአማኞች) ሰጥቷል። ስለዚህ አህዛብም አይሁድም ሁሉም ዜጎች የቤተ ክርስቲያኑ አባል እስከሆኑ ድረስ ይህንን ባለቤትነት ይወርሣሉ።

በዚህ ዓይነት ሌሎችም በርካታ ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቷቸዋል። ነገር ግን አንዳንድ በወቅቱ ግልጽ ያልሆኑና ከርከር የፈጠሩ ጥያቄዎችም ነበሩ። ከእነዚህ ዋነኛው ስለምስጢረ ስላሴ ነበረ። በዚህ አርዕስት ላይ የነበረው ከርከር ብዙ ጊዜ የፈጀና ረጅም ታሪክ ያለው በመሆኑ ለግንዛቤ እንዲረዳ ከፊሉን በአጭሩ እንመልከት።

---

*ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ጴርሱልጣንን ለአብርሃና አጽብሃ የመለሰ ነው (ንጉሥ ሰለሞን ለንግሥት ሳባ ሰጥቷት ሰለነበረ።)

ምስጢረ ስላሴ

በክርስትና እምነት ውስጥ ትልቁ ምስጢር ምስጢረ ሥላሴ ነው። ይህም ሥላሴዎች ሶስትም አንድም ናቸው የሚል ነው። ሊቃውንት ይህ ንን ለመረዳትና ለማስረዳት ሲሉ ብዙ ተወያይተውበታል። ባለመስማማትም ተከራክረውበታል። አንዳንዴም ወደ ልዩነት አምርተዋል። መሠረታዊ ጥያቄው "ስላሴዎች ሶስት ከሆኑ እንዴት አንድ ይሆናሉ? አንድ ከሆኑስ እንዴት ሶስት ይሆናሉ?" የሚል ነው።

በመጽሀፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት እየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። እንዲሁም "እናቱ ማርያም ከመንፈስ ቅዱስ ጸንሣ ተገኘች (ማቴ፣1፣18)። ሌሎችም ምዕራፎች ስለ እየሱስ ክርስቶስ ስለ መንፈስ ቅዱስና ስለ እግዚአብሔር በሰፊው ይጠቅሳሉ።

በዚህ መሰረት አብ፣ወልድ፣መንፈስ ቅዱስ አሉ ማለት ነው። እነዚህ ሶስት ናቸው። በሌላ በኩል ግን እግዚአብሔር አንድ ነው።

እንግዲህ ይህ አባባል ግልጽ ስላልሆነ ሊቃውንት ለበርካታ ዓመታት ተከራክረውበታል። ተጣልተውበታል፣ ለጊዜው ልዩነ ትም ፈጥረውበታል።

በታሪክ እንደ ተመዘገበው አንዳንድ ጎላ ብለው የታዩት ክስተቶች የሚከተሉት ናቸው። በአራተኛው ምዕተ ዓመት (319 ዓ.ም) በሮማ ቅኝ ግዛት ሥር በነበረች በእስክንድርያ ግብጽ የቤተክህነት አለቃ የሆነ አንድ ቄስ አርዮስ የሚባል ነበረ። በአርዮስ ትምህርት መሠረት እየሱስ በእግዚአ ብሔር የተፈጠረ እንጂ ራሱ እግዚአብሔር አይደለም። እርግጥ በምድር ላይ በሚኖርበት ዘመን ስነምግባሩ ፍጹም በእግዚአብሔር መንገድ ነበረ። ሰውንም እንዲሁ አስተማረ። ግን ፍጡር መሆኑ አይካድም አለ።

ይህ አስተምሮት ከባድ ተቃውሞ ገጠመው። የአርዮስ ደጋፊዎች በግብጽና በተለይም በእስክንድሪያ በርካታ ስለነበሩ በነዚህና በሰፊው ተቃ ዋሚ ወገን መካከል የከረረ ጥል ተደረገ። ብዙ ረብሻና ሁከትም ተፈጠረ።

የሮማ መንግሥትም ሊናጋ ሆነ። በዚህ ስጋት የተነሣ የሮማ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ አንድ ታላቅ ጉባኤ ጠራ። ይህም የኒቂያ ጉባኤ የተሰኘ በ325 ዓ.ም. የተሰበሰበው የመጀመሪያ የክርስቲያን መንፈሣዊ ጉባኤ ነው።

ይህ ጉባኤ አርዮስን አወገዘ። እየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ አምላክ መሆኑን በድንጋጌ አረጋገጠ። እየሱስ "እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ አለ" (ዮሐ 14÷10) ብሎ በገለጸው መሰረት አንድ አካል መሆናቸው የታመነ መሆኑ ጠቅላላ ስምምነት ላይ ተደረሰ።** ከዚያ ወዲህ እስከዛሬ አርዮስ ማለት የተወገዘ ከሃዲና ሃጢያተኛ ተደርጎ በክርስቲያኖች ዘንድ ይወሰዳል።

** የኒቂያ ጉባኤ ዛሬም ጎልቶ የሚታየው ክርስቲያኖች በእምነት ልዩነት ከመፍጠራቸው በፊት በጋራ ስምምነት የደረሱበት የመጨረሻ ስነዳቸው የዚህ ጉባኤ ስምምነት በመሆኑ ነው። ከዚህም በላይ እየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንጂ ተራ ሰው አለመሆኑን ያጸደቁበት ነው። ሰነዱ ዛሬ ጸሎተሃይማኖት በመባል የሚታወቀው የሃይማኖት መግለጫ ሲሆን ዝርዝሩ በከፊል በሚከተለው ገጽ በአባሪ የተሰጠው ነው።

አባሪ

ፀሎተ ሃይማኖት (የኒቂያ የሃይማኖት መግለጫ)

ሰማይንና ምድርን በፈጠረ፣የሚታዩትንና የማይታዩትን ጭምር ሁሉ በሠራ በሃያሉ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን

እንዲሁም እርሱ ብቻ የአብ ልጅ በሆነ ዓለም ሳይፈጠር ከአብ በተወለደ፣ከብርሃን በተገኘ ብርሃን፣ከእውነተኛ አምላክ በተገኘ እውነተኛ አምላክ፣ በተፈጠረ ሳይሆን በተወለደ፣ በህልውናው ከአብ ጋር አንድ በሆነ፣ ሁሉ በርሱ በሆነ (አማካኝነት የተፈጠረ) ስለ እኛ ስለ ሰዎች እና ስለ ደህንነታችን ሲል ከሰማይ ወርዶ በመንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማርያም ሥጋ ነስቶ ሰው በሆነ፣ በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን ስለ እኛ በተሰቀለ፣ መከራ በተቀበለ፣ በሞተ በተቀበረ፣በቅዱሳት መጻህትም እንደተጻፈው በሶስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ በተነሣው፣ ወደ ሰማይ በወጣው እና አሁንም በአብ ቀኝ በተቀመጠ፣ በህያውያንና በሙታን ላይ ፍርዱን ሊሰጥ ዳግመኛ በክብር በሚመጣው፣ ለመንግሥቱ ፍጻሜ በሌለው በአንድ ጌታ በእየሱስ ክርስቶስ እናምናለን።

እንዲሁም ከአብ (እና ከወልድ)* በሚሰርጽ ከእነሱም ጋር በእኩልነት በሚሰገድለትና በሚከበር፣ በነቢያት በተናገረ ጌታና ህይወት ሰጪ በሆነ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን። የሁሉም በሆነች በአንዲት ቅድስት ሀዋርያዊ ቤተክርስቲያንም እናምናለን።

ለሃጢያት ማስተሰሪያ የምትሆንን (የተደረገችን) አንዲት ጥምቀት እንቀበላለን። የሙታንን ትንሣኤና ወደፊት የሚመጣውን ዓለም ህይወትም እንጠባበቃለን። አሜን።

የእየሱስ ክርስቶስን አምላክነት የተጠራጠሩ የነበሩትን ያህል ደግሞ በሌላ በኩል እጅግ አጥብቀው ያራመዱም ነበሩ። የሶሪያው ኤጲስቆጶስ አቡልናርዮስ እንዳስተማረው እየሱስ ክርስቶስ ፍጹም እግዚአብሔር እንጂ የሰው ባህርይ የለውም። መለኮት ወርዶ ስጋ ለበሰ እንጂ ሰው ሆኖ አልተፈጠረም አለ። ይህም በቁስጥንጥኒያ ጉባኤ በ381 ዓ.ም. ተወገዘ። ስለዚህ እየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መሆኑ ተደነገገ። በሌላ አንጋገር ሰብዓዊነቱም ሆነ መንፈሳዊነቱ በተሟላ ሁኔታ መሆኑ በቅዱስ ጎርጎሪዮስ ዘናሳንሱስ መሪነት በተካሄደው በዚህ ጉባኤ ተደነገገ።

አሁንም ትንሽ ቆይቶ አለመስማማት ተፈጠረ። ንስጥሮስ (የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ) ስለ መንፈሳዊነትና ሰብዓዊነት ውህደት

ለማስረዳት በመሞከር እንደሚከተለው አስተማረ። "እግዚአብሔር አዳምን ሲፈጥረው እስትንፋስ ሰጠውና ለቀቀው። አዳምም ነጻ ግለሰብ

---

[1] *"እና ከወልድ" የሚለው በሶስተኛው ፓራግራፍ የገባው ሐረግ በ325 ዓ.ም. ከተደረገው የኒቂያ ስምምነት በኋላ በካቶሊክ የተጨመረ ነው።

ሆነ። ሙሉ የሰብዓዊነት ባህርይ ነበረው። እየሱስ ግን እንደ አዳም ሙሉ ሰብአዊ ባህርይ ቢኖረውም እግዚአብሔር ግን አብሮት ነበረ እንጂ እስትንፋስ ሰጥቶት አልተለየውም። ስለዚህ ማርያም እየሱስን በማህጸኗ ተሸከመች እንጂ የክርስቶስ እናት አያሰኛትም። እም አምላክ ልትባልም ከቶ አይቻልም አለ።

ይህ እንደገና እየሱስን ሁለት ባህርያት ሊያሰጠው ሆነ። ስለዚህ የኤፌሶን ጉባኤ በ431 ዓ.ም. ተጠርቶ ይህንንም አወገዘ። ማርያምም እመ አምላክ ወላዲተ አምላክ ልትባል እንደሚገባት ተደነገገ። የእስክንድሪያው ፓትርያርክ ቅዱስ ቄርሎስ እንዳስረዱት ሁለቱ ባህርያት አንድ ናቸው እንጂ እንደ ሁለት አይታዩም። እንዲያውም እግዚአብሔር ተወለደ፣ስቃይና መከራ ተቀበለ፣ ሞተ፣ ተነሣ፣ ለማለት እንኳን ይቻላል። እስከዚህ ድረስ አንድ ናቸው አሉ።

ከዚህ በኋላ ነበረ ክርስቲያኖች እርስበርሳቸው ሊለያዩ የበቁበት ጉዳይ የተነሳው። አቡነ አውጣቂ (ከቁስጥንጥኒያ) የንስጥሮስን አቋም ተቃውሞ ሲነሣ እንድያውም ወደ ተቃራኒው ወገን ዘለቀ። እርሱ እንዳለው እየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባህርያት አሉት የተባለውን ፍጹም ባለመቀበል "ከሁለት ባህርያት ቢነሣም በኋላ ሰብአዊነቱ በአምላክነቱ ስለተዋጠ ክርስቶስ ራሱ ከእግዚአብሔር ነው፤ ገላጭ ባህርዩም ይኸው ነው" አለ። ግን ይህ ደግሞ በሰብዓዊነቱ ላይ የተመሠረተውን የእየሱስን ስቃይና መከራ ለመንፈሣዊ ባህርይ መስጠት ስለሚሆንና ይህም ስለማያስኬድ ተቀባይነት ሊያገኝ አልቻለም። ስለሆነም በ451 ዓ.ም በተካሄደው የኪልቄዶን ጉባኤ ላይ ተወገዘ።

ነገር ግን የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ዲዮስቆሮስ በዚህ ቢስማማም የአውጣቂ አመለካከት እውነት ያለበት በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ሊወገዝ አይገባውም አለ። እዚህ ላይ ልዩነት ተፈጠረ፣ እምነቱም ለሁለት ተከፈለ። ዲዮስቆሮስ የራሱን እምነት እውነተኛና ትክክለኛ ነው በማለት "ኦርቶዶክስ" (በግሪክ አጠራር ትክክለኛ) ብሎ ሲሰይመው የቀሩትን ወገኖች ንስጥሮሳውያን አላቸው። የቀሩት ግን አብዛኛው ወገን በመሆናቸው የተነሣ የራሣቸውን እምነት "ካቶሊክ" (በግሪክ አጠራር ሁሉን አቀፍ) በማለት ሰየሙ። እነሱም በበኩላቸው ተቃዋሚዎቹን (ኦርቶዶክስ ነን ባዮችን) ያዕቆባውያን ወይም ሞኖፊሳይት) (ባለአንድ ባህርይ አማኞች) አሏቸው። ሞኖፊሳውያን በመባል የሚታወቁት የኢት ዮጵያ፣ የግብጽ፣ የአርመን፣ የሶሪያና የህንድ ቤተክርስቲያኖች ናቸው።

ነገር ግን ዛሬ የታሪክ ምሁራን እንደሚነግሩን ለዚህ አለመ ግባባት ምክንያት የሆነው የግሪክ ቋንቋ አተረጓጎም እንጂ የዲዮስቆሮስ እና የቄርሎስ አመለካከት እስከዚህ ልዩነት ኖሮት አይደለም ይባላል። የሁለቱንም አመለካከት በትክክል የሚያስ ቀምጠው "ተዋህዶ" የሚለው የአማርኛ ቃል ነው። ዛሬ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አውጣቂንም በማውገዝ ያስቀመጠችው ቀኖና "ቃል ከሰማይ ወረደ፣ ስጋ ለበሰ፣ ስለ ሃጢያታችንም ተሰቃየ፣ ተወገረ፣ በኋላም ተነስቶ (ከሙታን)

አረገ" የሚል ነው። ተዋህዶ የሚገልጸውም መለኮት ከስጋ ጋር መዋሃዱን ነው።

የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ከግሪክ (ባይዛንታይን) ቤተክርስቲያን ጋር የተለያየችውም በዚሁ ጊዜና ሁኔታ ነበረ። በኋላም የግሪክ ቤተክርስቲያን ከሮማው ቤተክርስቲያን ጋር አብረው ሆነው ሶስት ጉባኤዎችን (ሲኖዶስ) በማካሄድ የጋራ ውሣኔዎች አጽድቀዋል። ከዚያ በኋላ ደግሞ ልዩነት ስለተፈጠረ እነሱም ተለያይተዋል። የሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንም በራሷ ተጨማሪ 14 ጉባኤዎች (እስከ 1965 ዓ.ም) አካሂዳ ያወጣቻቸውን ድንጋጌዎች ሌሎች ዛሬ አይቀበሉም። (ለምሣሌ የሮማ ጳጳስን የበላይነት)።

የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት በኢትዮጵያ

አጀማመር፡

የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ የደረሰው በ34 ዓ.ም ገደማ ነበረ። በመጽሀፍ ቅዱስ ሐዋ 8÷27-39 እንደተጻፈው የኢትዮጵያ ንግሥት ሕንደኬ በጅሮንድ የነበረው ጃንደረባ ሊሰግድ ወደ እየሩሳሌም ሄዶ በሚመለስበት ጊዜ ሐዋርያው ፊልጶስ መንገድ ላይ አግኝቶት ስለ ወንጌል ሰበከለት። ጃንደረባውም ተቀበለ። ስለሆነም ወንዝ አጠገብ ሲደርሱ ጃንደረባው ምስጢረ ጥምቀትን ለመፈጸም በማሰብ "እነሆ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድ ነው?" አለ ፊሊጶስም ሲመልስ "በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዶልሃል" አለው። በዚህም ጃንደረባው "እየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ" አለ። ስለሆነም በሐዋርያው ፊሊጶስ እጅ ተጠመቀ። የመጀመሪያ ኢትዮጵያዊ ክርስቲያንም ሆነ። ከዚያም ወደ አገሩ ከተመለሰ ጀምሮ ክርስትናን ለሕዝቡ ስለ አስተማረ ሃይማኖቱ ወደ ኢትዮጵያ ሊገባ ችሏል።

ሃይማኖቱ የመንግሥት ድጋፍ አግኝቶ በሰፊው ሊሰራጭ የቻለው ግን በ330 ዓ.ም ገደማ ነው። መረጳዎስ የተባለ ትውልዱ ግሪክ የሆነ የጢሮስ (ሶሪያ) ነጋዴ በቀይ ባህር ሲጓዝ አዱሊስ ወደብ አካባቢ ስለሞተ (ወይም ስለተገደለ) አብረውት የነበሩት ሁለት ክርስቲያን ወጣቶች (ፍሬምናጦስ እና አድዮስዮስ) ዛፍ ስር ቁጭ ብለው ሲያለቅሱ የአዱሊስ ሰዎች አግኙአቸው። ከዚያም ወስደው በባህር ነጋሹ አማካኝነት ወደ አክሱም ንጉሥ አደረሷቸው። ንጉሡም ከራሣቸው ሁለት ልጆች (ኢዛና እና ሳይዛና) ጋር በቤተመንግሥት ተቀምጠው እንዲያድጉና እንዲ ማሩ አደረጉ። ስለሆነም ሊቀካህናት እንበረም (በጊዜው የአይሁድ እምነት ባለሟል የነበሩ) ለሰባት ዓመታት የግዕዝ ቋንቋና ትምህርትም አስተማሯቸው።

ንጉሡ ሲሞቱ መጀመሪያ ንግሥቲቱ በኋላም ሁለቱ ልጆቹ ለአቅመ አዳም ሲደርሱ በትረሥልጣኑን ተረክበው አገሪቱን በአሪት ህግ መሠረት

ሲያስተዳድሩ ከቆዩ በኋላ የክርስትና ሃይማኖት በአገሪቱ ሊስፋፋ እንዲችል ጳጳስ ከእስክንድሪያ እንዲላክላቸው ፍሬምናጦስን ከወንድሙ ጋር ላኳቸው።

የእስክንድሪያው ሊቀ ጳጳስ አትናቴዎስ በጣም ታላቅ ሰው ነበሩ። የአርዮስን ትምህርት ያወገዙ መሪ ከመሆናቸውም በላይ የሐዋርያትን ስራዎችና መልዕክቶች ሰብስበው ከወንጌላት ጋር ሃያ ሰባቱ መጽሀፍት አንድ ላይ መጽሀፍ ቅዱስን ያሟላሉ በማለት በ367 ዓ.ም ጽሁፍ አቅርበው ይኸው ተቀባይነት አግኝቶ ሲሰራበት ያለ ነው።

አቡነ አትናቴዎስ የፍሬምናጦስን መልዕክት ተቀብለው ካሰቡበት በኋላ ጥያቄውን በሙሉ ልብ በመቀበል ጳጳስ እንዲላክ ወሰኑ። ሆኖም ለሥራው ቀናነት ሲባል የኢትዮጵያን ቋንቋ እንዲሁም ባህልና አኗኗር የሚያውቅ ሰው ቢመደብ ተገቢ በመሆኑ ፍራምናጦስ ራሱ ተመልሶ እንዲያስተምር አግባቡት። ስለሆነም እሱን አሰልጥነው መጀመሪያ የድቁና ማዕረግ ከዚያም ክህነት በመስጠት በኋላም ሚመተ ጵጵስና ሰጥተው ወደ ኢትዮጵያ መለሱት። አድዮስዮስ ግን ወደ ትውልድ አገሩ ዘለቀ።

የፍሬምናጦስ የጵጵስና ስሙ "አባ ሰላማ" በሚል ስለ ተሰየመ አባ ሰላማ የክርስትና ሃይማኖትን ማስተማር እና ማስፋፋት ቀጠሉ። በጊዜው አገሪቱን ይመሩ የነበሩትን ኢዛና እና ሳይዛና ወንጌል አስተምረውና አጥምቀው አብርሃ እና አጽብሃ ብለው በክርስትና ስማቸው ሰየሙዋቸው።

ነገስታቱ አብርሃ እና አጽብሃ መኳንንቶቻቸውና ባለ ሥልጣኖቻቸው ሁሉ እንዲጠመቁ አደረጉ። የክርስትና ሃይማኖት ትምህርትም በሰፊው እንዲዳረስ አዘዙ። አባ ሰላማም ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጌልን ከግሪክ ወደ ግዕዝ ተረጉሙ። የቀድሞ አስተ ማሪያቸውን ሊቀ ካህናት እንበረምን ወንጌል አስተምረውና አጥ ምቀው የኤጲስ ቆጶስነት ማዕረግ ስለ ሰጧቸው አሁን ሁለቱ በመተባበር ትምህርቱን በሰፊው ማስፋፋት ቀጠሉ። ይህ እንግዲህ ከ325 ዓ.ም ጀምሮ ነው።

በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን የሆነችው በአክሱም ከተማ የተመሰረተችው ጽዮን ማርያም ናት። ከዚያ በኋላ ሌሎች በየቦታው ተቋቋሙ። ዛሬ በዓለም ዙሪያ የታወቁት ቤተክርስቲያኖች ማለትም በ12ኛው ክፍለ ዘመን በቅዱስ ላሊበላ ዘመን ከአለት የተፈለፈሉት ሕንጻዎች የዚህ ዕድገት ቅጥያ ናቸው።

በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ክልል ሰፊ ስለነበረ ሁለቱ ነገሥታት ተስማምተው አብርሃ ከአክሱም ሆኖ እንዲያስተዳድር አጽብሃ ደግሞ ወደ ሸዋ ዝቅ ብሎ ደቡቡን ክፍል እንዲያስተዳድር ሆኖ በዚህ ሁኔታ ተስማምተው ኖሩ። ዛሬ በአዲስ አበባ የሚገኘው የካ ሚካኤል ታቦት በ1878 ዓ.ም ከዋሻ ሚካኤል የተዛወረ ቢሆንም ዋሻ ሚካኤል ራሱ አጽብሃ በዚያን ዘመን ያሰራው ቤተ ክርስቲያን ነው ይባላል። የአጽብሃ ግዛት እስከየመን ይዘልቅ ስለነበረ ክርስትና ሃይማኖትም እዚያ ድረስ ተስፋፋ ነበረ።

እንዲያውም ክርስትናን ወደ ሳውዲት አረብ ለማዳረስ በአጼ ካሌብ ተሹሞ የመንን ያስተዳድር የነበረው አብርሃ በ570 ዓ.ም አካባቢ ወደ ሜካ ከተማ ዘምቶ ነበረ። ግን ሜካ ሊደርስ ጥቂት ሲቀረው በወታደሮቹ መሃል የፈንጣጣ በሽታ ስለተነሣበትና አብዛኛው ሰራዊት ስላለቀበት ራሱም አብርሃም ስለሞተ ዘመቻው ዳር ሣይደርስ ቀረ።(ከበላይ ግደይ" የኢትዮጵያ ስልጣኔ" ገጽ 125 የተገኘ) በዚህ አጋጣሚ በመጠቀም ፋርሶች በ578 ዓ.ም በየመን ላይ ወረራ አንስተው በቁጥጥራቸው ስር ሊያውሏት ቻሉ። ኢትዮጵያም የባህር ማዶ ግዛቷን አጣች።

ከዚያ በኋላ ነቢዩ መሐመድ መድረክ ላይ ብቅ ስላለ በጥቂት ዓመታት ውስጥ መላው የቀይ ባህር አካባቢና ሰሜን አፍሪካ በእስልምና ሃይማኖት ስር ዋሉ። ኢትዮጵያም ከውጭው ዓለም ጋር የነበራት ግንኙነት ተቋረጠ። "የጨለማ ዘመን" የተባለውም ሰፈነ። ይህ ከ7ኛው ምዕተ ዓመት እስከ 13ኛው ምዕተ ዓመት የዘለቀ ነበረ። በዚህን ጊዜ ከእስክንድሪያ ጋር ያለውም ግንኙነት በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ነበረ። ለምሣሌ በአንድ ወቅት ሁለት ግብጻዊያን የሃሰት ደብዳቤ ይዘው "የኢትዮጵያ ፓትርያርክና ረዳቱ ሆነን ተሹመን መጥተናል" በማለት ባለሥልናትን አታለውና አሳምነው አቡነ ጴጥሮስን አስወርደው ነበረ። ይህንን ሲሰሙ የእስክንድሪያ መንፈሣዊ መሪዎች ተቀይመው ዳግም ፓትርያርክ ተሹሞ እንዳይላክልን ስለወሰኑ ለ60 ዓመታት ታግዶ እንደነበረ ይነገራል። ይህ እንግዲህ የግንኙነት አለ መኖር ያስከተለው ችግር ነበረ።

ከዚህ በተጨማሪ በኢትዮጵያ የነበሩ ፈላሾች ከክርስትያኖች ጋር አለመግባባት ስለነበራቸውና ከአክሱም አካባቢ ተባረው ስለነበረ በስተኋላ ከእስራኤል እየፈለሱ ያመጡ አባላት ተጨምረው በቁጥርም በመሣሪያም ሊያጠናክሯቸው ስለቻሉ ጦርነት ተነስቶ ፈላሾቹ በንግሥት ዮዲት መሪነት አሸንፈው ስልጣን ያዙ። ከዚያም በኋላ ዝነኛዋን የጽዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያንና ሌሎችንም በርካታ አብያተ ክርስቲያናት አቃጥለውና አጥፍተው ለአርባ ዓመታት ገዙ። በዚህ ወቅት የኦርቶዶክስ ሃይማኖት አማኞች ብዙ መከራ ደረሰባቸው። በርካታ ቅዱሳት መጽሀፍትም ወደሙባቸው።

ያም ሆኖ ግን የኦርቶዶክስ ሃይማኖት እንደገና አንሰራርቶ የበላይነቱን ጨበጠ። እየተጠናከረም ሄደ። በ15ኛው መቶ ዓመት አጼ ዘርዓያዕቆብ ሲነግሱ የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን በተጠናከረ መሰረት ላይ አቆሙት።

ይህም እስከ ግራኝ ወረራ ድረስ ቀጠለ። በኋላ ግን የቱርክ (አቶማን) መንግሥት በ1516 ዓ.ም ግብጽን በቁጥጥራቸው ሥር በማዋልና ከዚያም የጂሃድን ጦርነት ወደ ደቡብ በማስፋፋት በ1527 ዓ.ም በግራኝ መሐመድ የጦር መሪነት የኢትዮጵያን ሶስት አራተኛ ክፍል ያዙ። ይህም እንደገና ለበርካታ አብያተ ክርስቲያናት መቃጠልና መውደም ምክንያት ሆነ። ቀሳውስትና መነኮሳትም ተጨፈጨፉ።

ይህ ሁኔታ ያሣዘናቸው የፖርቹጋል ክርስቲያኖች ለዕርዳታ በመድረስ በመሣሪያና በሰው ሃይል እንዲሁም በታክቲክ ተጠቅ መው ጦርነቱን አሸነፉ። በዚህም መሃል ግራኝ መሐመድ በ1543 ዓ.ም ተገደለ። ኦርቶዶክስ ሃይማኖት እንደገና ማንሰራራት ጀመረ። ነገር ግን የፖርቹጋል የክርስትና ሃይማኖት ካቶሊክ ስለነበረ እነሱ ደግሞ ሃይማኖታቸውን ለማስፈን ፈለጉ። ስለሆነም እንደገና ተከታዮቻቸውን አበራክተው የእርስ በርስ ጦርነት ተጀመረ። ንጉሡ ሱሰንዮስም ከእነሱ ወገን ሆነ። በዚህ የተነሣ የኦርቶዶክስ ቀሳውስት እና ተከታዮቻቸው ከፍተኛ መሰዋዕትነት ከፈሉ። ሆኖም በትግሉ አሸንፈው ንጉሱን አስወርደው አጼ ፋሲልን አንግሰው (በ1632 ዓ.ም) እየሱሳውያንን (ጄሱትስ) ከአገር አስወጡ።

ከዚያ ወዲህ የነገሱ ነገስታትም ሃይማኖቱን ጠብቆ ለማቆየት አልቦዘኑም። ለምሣሌ ንጉስ ሣህለ ሥላሴ ፈረንጆች (ሚሲዮ ናውያን) ወደሸዋ እንዳይገቡ ባህረ ነጋሹን አዘው ነበረ። አጼ ዮሐንስና አጼ ቴዎድሮስም አህዛብ ሁሉ ክርስትና እንዲነሣ መመሪያ ሰጥተው ነበረ ይባላል። አጼ ምኒልክም የሐረር ታሪክ እንደገና ሊደገም እንደሆነ ጥቆማ ስለደረሳቸው ግብጽ ሐረርን በወለጋ በኩል ከግዛቷ ከሱዳን ጋር አገናኝታ እስልምናን ለማ ጠንከር ያላትን ዕቅድ ለማክሸፍ ዘመቻ ጀመሩ። የኦርቶዶክስ ሃይማኖትንም ወደ ደቡብ እንዲስፋፉ ዕድል ሰጡ። ሆኖም የሐዋርያዊ ተልዕኮው ብቃት የነበረው በፕሮቴስታንት ሚሲዮኖች እጅ ስለነበረና ለነገሥታቱም ቢሆን ለአገራቸው ዕድገትና ለጦር መሣሪያ ማግኘት፣ ለትምህርት መስፋፋትና ለህክምና አገልግ ሎትም የፈረንጆች አስተዋጽኦ ወሳኝ ስለነበረ ሁኔታዎችን አቻ ችሎ መያዝ የሚመረጥ ሆነ። ይህ በአጼ ቴዎድሮስ ጊዜ ከዚያም በነአጼ ምኒልክና ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ጎልቶ የታየ ነው።

ዛሬ በኢትዮጵያ እስከ 20 ሺ ቤተ ክርስቲያኖች እንደሚኖሩ ሲገመት የምዕመናን ቁጥርም ምናልባት ወደ 26 ሚሊዮን ይደርሳል። ሆኖም ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋር ያለው ምዕመናንን የማበራከት ትግል ቀላል አይደለም። እርግጥ የራሷ የዕድገት ሂደት አልተቋረጠም። ለምሣሌ ጥንት ከ325 ዓ.ም ጀምሮ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ከእስክንድሪያ (ግብጽ) እየተሾመ ይመጣ እንደነበረ ይታወሳል። ይህ ለ1660 ዓመታት ቀጥሎ በ110ኛው ፓትርያርክ አቡነ ቄርሎስ ጊዜ አክትሟል። አቡነ ባስልዮስ ተተ ክተው ለ8 ዓመታት ከሰሩ በኋላ በ1959 ዓ.ም የመጀመሪያ ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ ሆነው ሊቀቡ በቅተዋል።

ዛሬ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ራሷን ችላ የምትተዳደር ከመሆኑም በላይ በሌሎች አገሮችም አብያተ ክርስቲያናትን በመክፈት ሐዋርያዊ አገልግሎት ታበረክታለች። ለምሣሌ በጃማይካ፣ በዩናይትድ እስቴት፣ በኒውዮርክ፣ በካናዳ፣ በጅቡቲ፣ በሱዳን፣ በኬንያ፣ በጀርመን፣ በእንግሊዝ፣ በሰዊድን፣ እና በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ኦርቶዶ ክስ ተዋህዶ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ። ቁጥሳትም ከዚሁ እየተሾሙ ይላካሉ።

አእማደ ምስጢራት (በተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን)

አእማደ ምስጢር ማለት የሰው ልጅ በተለይም ያመነ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጸጋን እንዲጎናጸፍ ሲባል የሚደረግለት ቅዱስ ሥነ ሥርዓት ነው ሊባል ይቻላል። በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ውስጥ ሰባት ዋና ሥነ ሥርዓቶች አሉ። ዝርዝራቸውም እንደሚከተለው ነው።

1= ምስጢረ ጥምቀት

ማንም ሰው ወደ ክርስትና ሃይማኖት ለመግባት በቅድሚያ መጠመቅ አለበት። ከሌላ ሃይማኖት የተመለሱ አዋቂዎች በማንኛውም እድሜአቸው ይጠመቃሉ። ሕጻናት ከሆኑ ወንዶች በአርባ ቀን ሴቶች በሰማንያ ቀን ይጠመቃሉ። ስነ ስርዓቱ ክርስትና አባት በሚሆነው ሰው የህጻኑን አውራ ጣት በመያዝ ይጀመራል። ቄሱ የጸሎት ስነ ስርዓት ያካሂዱና አዲስ በሰየሙለት የክርስትና ስም በመጥራት ልጁን "በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅሀለሁ" በማለት ሦስት ጊዜ ያጠምቁታል።

እየሱስ ክርስቶስ ዮርዳኖስ ወንዝ ወርዶ በመጥምቁ ዮሐንስ ሲጠመቅ መንፈስ ቅዱስ እንደወረደበት ሕጻኑ ወይም ተጠማቂው መንፈስ ቅዱስ ያድርበታል። ሦስት ጊዜ የሚጠመቀው በሦስቱ ሥላሴዎች ስም ሲሆን በተጨማሪ ቅዱስ ጳውሎስ እንደሚያስረዳው ከክርስቶስ መሞት መቀበርና ትንሣኤ ጋር እንዲመሳሰል ነው።

2= ምስጢረ ቁርባን

እየሱስ ክርስቶስ በቂጣ በዓል ምሽት ከ12ቱ ደቀ መዛሙርቱ ጋር የመጨረሻ እራት የተባለውን በሚበላበት ጊዜ ቂጣውን እና ወይን ጠጁን አንስቶ እና ባርኮ ተራ በተራ ሰጣቸው። "ይህ ስጋዬ ነው ይህም ደሜ ነው ስጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘለ ዓለም ህይወት ያገኛል"። ስለዚህ በዚህ ቃል ኪዳን መሰረት ካህናት ሕብስትና ወይን ከስንዴ እና ከዘቢብ በልዩ ሁኔታና ሥነ ሥርዓት አዘጋጅተው ሲያቀርቡ ይህ በጌታ ፈቃድ ስጋ ወደሙ ወደ መሆን ይለወጣል። ቆራቢ ይህንን ሲቀበል "የክርስቶስን ስጋ ወደሙ ወሰደ" ማለት ነው። ይህም 1ኛ/ እየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ሲል በመስቀል ላይ መስዋዕት መሆኑን ለማስታወስ 2ኛ/ ሃጢ ያታችንን ይቅር እንዲለንና 3ኛ/ የዘለዓለም ህይወት እንዲሰጠን በማለት ነዉ።

3= ምስጢረ - ሜሮን

ይህ ከክርስትና ወይም ከጥምቀት በኋላ የሚሰጥ ነው። ቄሱ ዘይቱን ይባርካሉ፣ ከዚያ የተቀባዩን ግንባር በመስቀል ምልክት የዐይን ሽፋል፣ አፍንጫ፣ ከንፈር፣ ጆሮ፣ ጀርባ፣ መዳፍ፣ ደረት፣ ጉልበት እና ውስጥ እግር ይቀባሉ። በዚህ ሥነ ሥርዓት አማካኝነት የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በተቀባዩ ላይ ያድራል፣ በጥምቀት የተሰጠውንም አዲስ ሕይወት ያረጋግጥለታል

ከዚህ ስነ ስርዓት በኋላ ሕጻኑ በአዲስ መታቀፊያ ይጠቀለላል። ቄሱም እጃቸውን አናቱ ላይ በመጫን ይባርኩታል። ቁርባንም ይሰጠዋል። በአንገቱ ይታሰርለታል።

4= ምስጢረ ንስሃ

አንድ አማኝ የሰራውን ኃጢአት ወይም ጥፋት ለነፍስ አባቱ (ነፍስ አባት ከሌለውም ለቄስ) በመናዘዝ/ በቄሱ አማላጅነት ኃጢአት እንዲሰረይለት የሚደረግበት ስነ ስርዓት ነው።

በኦርቶዶክስ ሃይማኖት መሠረት ማንም ቤተሰብ የነፍስ አባት ይይዛል። ይህም አባት ምስጢርጠባቂ ይሆናል። የኑዛዜ ወረቀትም ይፋ እስኪሆን ድረስ በአደራነት የሚሰጠው ለነፍስ አባት ነው።

አንድ አማኝ ንስሃ ከመግባቱ በፊት ስለሰራው ኃጢአት መፀፀትና ዳግመኛ ላይሰራው መወሰን አለበት። የሰረቀው ዕቃ ካለው ለባለቤቱ መመለስ፣ የበደለው ሰው ካለ ሄዶ ይቅርታ መጠየቅ አለበት። ንስሃ መግባት ምንግዜም ይቻላል።

ለተፈፀመ ሃጢያት ዋጋውን መክፈል ግዴታ ስለሆነ ቄሱ በአጥፊው ምዕመን ላይ እንደ ጥፋቱ ብዛትና ክብደት አይተው የገንዘብ ቅጣት ወይም ለተወሰኑ ቀናት ጾም ወይም ለተወሰነ ቁጥር መስገድ ወይም ሁለት ሶስቱን በማጣመር ይፈርዳል። ያንን መፈፀም ግዴታው ይሆናል።

5= ምስጢረ ተክሊል

ይህ ሥነ ሥርዓት አንድ ወንድና አንድ ሴት ባልና ሚስት ሆነው እንደ አንድ አካል የሚቆጠሩበት የጋብቻ ስነ ስርዓት ነው። የእየሱስ ክርስቶስ ትምህርት አንድ ወንድ ለአንድ ሴት ነው። ይህም በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ጋብቻ መሆን አለበት። ባልና ሚስት ታማኝ ለመሆን፣ ወልዶ ለማሳደግ፣ በክፉም ሆነ በደግ፣ በሃብትም ሆነ በድህነት፣ በህመምም ሆነ በደህንነት፣ ሞት እስኪለያቸው ሊፋቀሩና ሊረዳዱ ቃለ መሃላ ይገባሉ። ሊፋቱ የሚችሉት አንዳቸው ሲሞቱ፣ ሲያመነዝሩ፣ ወይም የአእምሮ ሕመምተኛ ሲሆኑ ነው።

በዚህን ጊዜ ተበዳዩ ነጻ ተደርጎ እንደገና ሊያገባ ይችላል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ግን 2ኛው ጋብቻ በተክሊል ሳይሆን በጸሎትና በቁርባን ብቻ ይከናወንለታል።

የሥነ ሥርዓቱ ቅደም ተከተል እንደሚከተለው ይሆናል÷

ሀ) ቀለበት ተባርኮ ይደረግላቸዋል

ለ) ቅበዓ ቅዱስ ይቀባሉ

ሐ) ካባ ላንቃ ይደረብላቸዋል

መ) የተክሊል ዘውድ ይጫንላቸዋል

ሠ) የቅዳሴ ሥነ ስርዓት ተካሄዶ ሥጋ ወደሙ ይቀበላሉ

6) ምስጢረ ቅብዓ ቅዱስ

ይህ በከባድ ሕመም ላይ ላሉ ይሰጣል። ብዙውን ጊዜ በሞት አፋፍ ላይ ለሚገኙ ወይም ከባድ ቀዶ-ጥገና ሊደረግላቸው ላሉ ሰዎች ይሰጣል። ዓላማው መንፈስ ቅዱስ ነፍስና ስጋውን እንዲያድነው፣ ካልሆነም ነፍሱን እንዲያጸድቀው ነው።

እርግጥ ቅብዓ ቅዱስ ለሀሙማን ብቻ የተወሰነ አይደለም። በምስጢረ-ክህነት ጊዜ ለቄስ ለጳጳስ ለንጉሥ . . . ይቀባል። ቅባቱ የሚዘጋጀው በልዩ ሥነ ሥርዓት ነው። ይህም የራሱ ደንብና ሥርዓት ያለው ነው። ቄሱ ይህንን ቅባት በስርዓቱና በጸሎት በጥንቃቄ ያዘጋጃል። ከዚያም ባለጉዳዩን ግንባሩን እጁን ይቀባል።

ከዚህ ስነ ስርዓት ጋር አብረው የሚሄዱ ለምሣሌ በቅድሚያ ጠበል መርጨት እና ጸሎት ማድረግ በኋላም ስርዓተ ቁርባን ማከናወን ይፈጸማሉ።

7- ምስጢረ ክህነት

የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ማዕከል ቤተክርስቲያን ናት። የቤተክርስቲያን ባለሟሎችና አገልጋዮች ምዕመናንን ለማስተማር፣ለመምራት፣እና መንፈሳዊ ደህንነታቸውን ለመጠበቅ ሃላፊነት አለባቸው። ጋብቻ ማስፈጸም፣ንሰሃ መቀበል፣ ስርዓተ ፍታት (ለሞተ ሰው) ማከናወን፣ጥምቀት መስጠትና ማሞንከስ የመሣሠ ሉትን ማህበራዊ መንፈሳዊ ተግባሮች ያከናውናሉ። የቤተ ክርስ ቲያንን አስተዳደርም ይቆጣጠራሉ። ይፈጽማሉ። ይህንን ሃላፊነት ሊቀበል የሚችል ባለሙያ የሚመረጠው በከፍተኛ ጥንቃቄ ነው።

ምስጢረ ክህነት የሚሰጠው ለጳጳስ ለኤጲስ ቆጶስ ለቆሞስ ለቄስ እና ለዲያቆን ነው። መለስተኛ ስርዓት ለበታች ሹማምንትም ሊሰጥ ይችላል።

ይህ ስልጣን የመስጠት ስርዓት የሚታሰበው በበዓለ ሃምሳ (ጰንጠቆስጤ) ዕለት መንፈስ ቅዱስ ቤሐዋርያቱ አናት ላይ ወርዶ ከዚያ በኋላ እየዞሩ እንዲያስተምሩና እንዲያጠምቁ ሥልጣን የሰጣቸውን በማስታወስ ነው። በዚሁ መንፈስ ባለሥልጣኑ በተሿሚው አናት ላይ እጁን (መዳፉን) ይጭንበታል። በዚህም ሁኔታ ጸሎት ይጸለያል። የእግዚአብሔር ረድኤት እንዲወርድለትና የተወሰነለትን ሃላፊነት በብቃት ሊያከናውን እንዲችል የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ እንዳይለየው ይለመንለታል። ይህም ሁሉ በስርዓተ ቅዳሴ ውስጥ ይከናወናል። ተሿሚውም እጁን ቅብዓ ቅዱስ ይቀባል። ለተግባሩ ማከናወኛ የሚጠቀምባቸውንም ዕቃዎች (ለምሣሌ ጽዋ፣ ልብስ፣ ጻህል፣ ማቁረቢያ፣ ወዘተ. . .) ይረከባል። ማህበራዊ ሃላፊነቱም ለሰፊው ምዕመናን አገልግሎት መስጠት በመሆኑ በጣም ከባድ ነው።

በዓላት

የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት የሚያከብራቸው በዓላት በትንሹ በአምስት ሊመደቡ ይችላሉ። እነሱም÷

1ኛ- በእየሱስ ክርስቶስ ስም (ገና፣ ጥምቀት፣ስቅለት. . .)
2ኛ- በድንግል ማርያም ስም (አስተርዕዮ፣ ፍልሰታ፣ በዓታ)
3ኛ- በመላዕክት ስም (ሚካኤል፣ ገብርኤል፣ ኡራኤል. . .)
4ኛ- በጻድቃንና በሐዋርያት ስም (አቡነ ተክለሃይማኖት፣ አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ፣ ቅዱስ ዮሐንስ. . .)
5ኛ- በሰማዕታት ስም (ቂርቆስ፣ እስጢፋኖስ፣መርቆሬዎስ. . .)

የኢትዮጵያ ወራት ያሏቸው ቀናት ሁሉ ለአንዳንድ ምክንያቶች በመታሰቢያ ተይዘዋል። በወር ውስጥ ሰላሣ ቀናት አሉ። እያንዳንዱ ቀን የራሱ መታሰቢያ አለው። እርግጥ ከእነኝህ ውስጥ የሚከበሩ በዓላትም አሉ። በነዚህ በዓላት ዕለት ሥራ መሥራት ግዴታ እንዳይሆን ሕግ ያስከብራል። አንዳንድ በዓላት (ለምሣሌ ፋሲካ) በቤት ውስጥ በቤተዘመድ እና ጎረቤት መካከል የሚከበሩ ሲሆን አንዳንዶቹ (ለምሣሌ ጥምቀት) በሕዝባዊ አጀብና ጭፈራ፣ በእልልታና ዝማሬ ይከበራሉ።

የወር ቀናቱ መታሰቢያነት አንዳንድ የክብረ በዓላት ቀናት እና ምክንያቶቹ በሚቀጥለው ገጽ ተጠቃቅሰዋል። (ገጽ 66 ይመልከቱ)

<u>ማሳሰቢያ÷</u> ፋሲካ (ትንሣኤ) ሁል ጊዜ እሁድ ላይ ማረፍ ስላለበት ከዚህ ጋር የተያያዙ በዓላት የወር ቀናቸው በየዓመቱ ይለዋወጣል። እነዚህም በዓላት ደብረ ዘይት (የጸም አማካይ) ሆሣዕና (የትንሣኤ ዋዜማ እሁድ) ስቅለት (ስግደት)፣ ዕርገት (ከፋሲካ በኋላ በ40ኛው ቀን) ጰራቅሊጦስ እንዲሁም ጾመ ነነዌ ናቸው።

የጸም ጊዜያት

ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኘው በጸሎት ነው። በሚገባ ለመጸለይ ደግሞ ስጋዊ ፍላጎትን አድክሞ መንፈሳዊ ስሜት እንዲበረታ ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህም ጾም ዋና መሣሪያ ነው።

በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ህግ መሠረት የጸም ጊዜያት ከዓመቱ ቀናት ግማሹን ያህል ይሸፍናሉ። ዋናው የአጿጿም ዘዴ ቅዳሴ እስኪያበቃ ድረስ (ስለ ሰዓቱ ገጽ 72 ይመልከቱ) እህል ውሃ ከመቅመስ መቆጠብና ከዚያም በኋላ ቢሆን ሥጋ-ነክ የሆኑና እንዲሁም ቅቤ እንቁላል ዓይብ ወተት አለመመገብ ነው። አብዛኛው ሕዝብ ግን ጠሙን ሳይውል ሥጋ እና የወተት ዘር የሆኑትን መጾም ብቻ ይበቃዋል።

የጸም ጊዜያት ብዙ ናቸው። በመጀመሪያ ረቡዕና ዓርብ ይጸማሉ። ረቡዕ አይሁዳውያን በጌታ ተሰብስበው እየሱስ ክርስቶስን እንዲሞት ውሳኔ የደረሱበት ቀን ሲሆን ዓርብ ደግሞ ውሣኔያቸውን ተግባራዊ ያደረጉበት ዕለት ነው።

ሌላው ጾም የገና ጾም ነው። ይህ ከህዳር 15 ቀን እሰከ ታህሳስ 28 ቀን 44 ቀናት የሚዘልቅ ሲሆን የሚጾመውም ነቢያት (እና ኤልያስ) መድሀን እንዲመጣ ለ44 ቀናት ያህል የጾሙት ነው። (የነቢያት ጾም ወይም ጾመ ነቢያት ይባላል)።


ጾመ ነነዌ የ3 ቀን ጾም ስትሆን ዮናስ የነነዌ ከተማ እንደ ሰዶምና ገሞራ እንዳትቃጠል ህዝቡን እንዲጸልዩ ባዘዘውና ከተማዋ በተረፈችበት ምክንያት ሲሆን ምዕመናንም ጸሎታቸው ተሰምቶ እንዲድኑ ይህች ጾም የሁዳዴ ጾም ከመግባቱ ሁለት ሣምንት ሲቀረው የምትጾም ናት። (ሰኞ፣ማክሰኞ እና ረቡዕ)።

የሁዳዴ ጾም (አቢይ ጾም) 55 ቀናት ይረዝማል። እሁድ ቅበላ ሆኖ በ8ኛ ሳምንት (56ኛው ቀን) እሁድ ፋሲካ ይሆናል። የጾሙ ምክንያት÷

1ኛ/ 40 ቀናት እየሱስ የጾመው ሲሆን 2ኛ/ የስምንት ቀን ጾመ ሕማማት (ጌታ የተሰቃየበት) ነው። (ፈሪሳዊያን አድማውን ጀምረው እስከጨረሱ) 3ኛ/ ሰባት ቀን ጾመ-ሕርቃል የባይዛንታይን ንጉሥ ሙስሊሞችን ከእየሩሣሌም ለማስለቀቅ የጾመበት፣ በ614 ዓ.ም (ከመስቀል ጦርነት በፊት)።

ጾመ ሐዋርያት ከጰንጠቆስጤ (ማለትም ከፋሲካ በኋላ 50 ቀናት ቆይቶ) ጀምሮ እስከ ሐምሌ 4 ቀን የሚጾም ነው። ሐዋሪያት መንፈስ ቅዱስ ከወረደላቸው ቀን ጀምሮ እየተዘዋወሩ ማስተማር እስከጀመሩበት ጊዜ ድረስ የገቡት ሱባኤ (ጾም) ነው።

ጾመ ፍልሰታ ነሐሴ 1-15 ቀን የሚጾም ሲሆን የድንግል ማርያምን ዕጣፈንታ (ከሞት በኋላ) ለማወቅ የተወሰደ ጾም ነው። ወደ ሰማይ ማረጓየተገለጸው ነሐሴ 16 ቀን ነበረ።



1. እየሩሳሌም
   - የሰለሞን መቅደስ የነበረበት
   - የኦማር መስጊድ የሚገኝበት
   - የእየሱስ ሞት (እና ትንሳዔ) የተፈጸመበት

2. ቤተልሄም
   - እየሱስ የተወለደበት

3. ሄብሮን
   - አብርሃም ይስሐቅና ያዕቆብ የተቀበሩበት

4. ናዝሬት
   - እየሱስ ያደገበት

5. ሃይፋ
   - የኤልያስ ዋሻ
   - የባሃኡላህ መካነ መቃብር
   የቂብላ አቅጣጫ፤ የሃጂ ጉዞ
   (ልዩ ቦታው ኤክር - ባጂ

6. የጎላን ኮረብታ
7. ሊባኖስ
8. ሶሪያ
9. ጆርዳን (ዮርዳኖስ)
10. የገሊላ ባህር
    እየሱስ ውሃ ላይ የተራመደበት
11. ጨው ባህር (ሙት ባህር)
12. የይሁዳ ምድር
13. የሰማሪያ ምድር
14. የገሊላ ምድር
15. ደብረዘይት ተራራ
    እየሱስ ያረገበት
16. የሳይናይ በረሃ (ግብጽ)
17. ሜዲተራኒያን ባህር

የአራት ሃይማኖቶች ታሪካዊ ቦታዎች የሚገኙባት እሥራዔል

የመታሰቢያና የበዓላት ቀናት

የወር ቀን	መታሰቢያነቱ	የክብረ-በዓል ቀን	የመታሰቢያነቱ (ክብረ በዓሉ) ምክንያት
1	ልደታ፣ራጉኤል	መስከረም 1	ራጉኤል የተሾመበት ቀን።
		ግንቦት 1	ቅድስት ማርያም የተወለደችበት ቀን።
2	ቅ/ዮሐንስ መጥምቁ	መስከረም 2	ቅዱሱ ራሱ የተቆረጠበት ቀን።
3	በዓታ	ታህሣሥ 3	ማርያም በስለት ስለተሾኘች ቤተመቅደስ በመግባቷ (በ3 ዓመቷ) መታሰቢያ።
4	ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ	ጥር 4	ሐዋሪያው ያረገበት።
5	አቦ	መጋቢት 5	አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ያረፉበት።
		ሐምሌ 5	ጴጥሮስ ወጳውሎስ የተገደሉበት።
6	እየሱስ፣ቁስቋም	ጥር 6	እየሱስ ግዝረት የተቀበለበት።
		ሕዳር 6	ማርያም ከግብጽ ስደት ስትመለስ ያረፈችበት ቦታ (ቁስቋም)
7	ስላሴ	ጥር 7	የባቢሎን ሕንጻ የተደረመሰበትና የሰዎች ቋንቋ የተለያየበት
		ሐምሌ 7	ስላሴዎች ለአብርሃም ተገልጠው ያስተናገደበት (በቤቱ)
8	አባ ኪሮስ	ሐምሌ 8	ዕረፍታቸው ነው
		ሕዳር 8	ኪሩቤል
9	ስለስቱ ምዕት	ሕዳር 9	318ቱ የኒቂያ ጉባዔ አባቶች መታሰቢያ
10	መስቀለ እየሱስ	መጋቢት 10	እሌኒ (የቆስጠንጢኖስ እናት) መስቀሉን አስቆፍራ ያገኘችበት
		መስከረም 10	ግማደ መስቀሉ ኢትዮጵያ የገባበት ቀን
11	ሃና	ሕዳር 11	የማርያም እናት የሞተችበት ቀን
		ጥር 11	ጥምቀት
		ግንቦት 11	ቅዱስ ያሬድ የተሰወሩበት
12	ሚካኤል	ሕዳር 12	ሊቀ መላዕክትነት የተሾመበት (ሳጥናኤል ሲሻር)
		ጥር 12	እየሱስ ውሃውን ጠጅ ያደረገበት (ቃናዘገሊላ)
13	ሩፉኤል	ታህሣሥ 13	ሩፉኤል ተአምር የሰራበት እና ጳጉሜ 3 ቀን የተሾመበት
		ነሐሴ 13	ደብረ ታቦር
14	አቡነ አረጋዊ	ጥቅምት 14	ጻድቁ የተሰወሩበት ቀንና ደብረ ዳሞ ገዳም በዓል
15	ቂርቆስ	ጥር 15	ሰማዕቱ ያረፉበት ቀን
16	ኪዳነ ምህረት	የካቲት 16	ድንግል ማርያም ከልጇ ቃል ኪዳን የተቀበለችበት ቀን

		ነሐሴ 16	ድንግል ማርያም ያረገችበት
17	እስጢፋኖስ	መስከረም 17	እሌኒ ቁፋሮ ያስጀመረችበት (ጎልጎታ) እና ግሸን የተባለችው ቦታ ተገኝታ ግማደ መስቀሉ የገባበት ቀን
		ጥቅምት 17	ሰማዕቱ ያረፉበት (በሃዋሪያት ዘመን የኖሩ)
18	አቡነ ዮስጣዎስ (ዝርወተ ዐጽመ ጊዮርጊስ)	መስከረም 18	ጻድቁ ያረፈበት
		ጥር 18	ፋርሶች አጥንቱን ከስክሰው እና ፈጭተው ተራራ ላይ ሲበትኑት ጥር 18 ቀን
19	ገብርኤል	ታህሣሥ 19	2ኛ ሆኖ የተሾመበትና ለማርያም ለማብሰር የተመረጠበት
20	ሕንጸታ	ሰኔ 20	የመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን የታነጸችበት በቅ/ጳውሎስና ቅ/በርናባስ
21	ማርያም	ጥር 21	የአረፈችበት ዕለት (አስተርእዮ) በኋላ በነሐሴ 16 አረገች
22	ኡራኤል	ሐምሌ 22	መልአኩ የተሾመበት
23	ጊዮርጊስ	ሚያዝያ 23	ሶስት ጊዜ ሞቶ ተነስቶ በ4ኛው ያረፈበት (የ7 ዓመት ተጋድሎ ፈጽሞ)
24	አቡነ ተክለ ሃይማኖት	ነሐሴ 24	ያረፉበት
25	መርቆሬዎስ	ሕዳር 25	ሰማዕቱ ያረፉበት
26	ዮሴፍ	ሐምሌ 26	የማርያም እጮኛ ጻድቅ ያረፉበት እንዲሁም የአቡነ ሰላማ መታሰቢያ ቀን
27	መድሃኔ ዓለም	መጋቢት 27	ስቅለት
28	አማኑኤል	ታህሣሥ 28	ማርያም ከሕዝብ ቆጠራ ስትመለስ ቤተልሔም የገባችበት
29	በዓለ እግዚአብሔር	ታህሣሥ 29	እየሱስ የተወለደበት ገና (ልደት)
30	ማርቆስ	ሚያዝያ 30	ሐዋርያው ያረፈበት
		ሰኔ 30	መጥመቁ ቅዱስ ዮሐንስ የተወለደበት

የጾም ቀናት

የጾሙ መለያ ሥም	የጾሙ ብዛት	የጾሙ ምክንያት
አቢይ ጾም (ሁዳዴ)	55 ቀናት	40 ቀናት ኢየሱስ የጾመበት 8 ቀናት ስለ ሀማማት፣ 7 ቀናት ጾመ ሕርቃል። (ኢየሩሳሌምን ከሙስሊሞች ለማስለቀቅ አስቀድሞ የጾመበት ከመስቀል ጦርነት በፊት) 614 ዓ.ም።
ጾመ ሐዋርያት	በአማካይ 40 ቀናት /ከጴንጤ ቆስጤ እስከ ሐምሌ 4 ቀን ጭምር/	ሐዋርያት ከዕርገት በኋላ በ10ኛው ቀን መንፈስ ቅዱስ ወረደላቸው (ጴንጤቆስጤ ቀን) ከዚያም ሊያስተምሩ ከመሰማራታቸው በፊት 40 ቀናት ጾሙ ጸለዩ።
ፍልሰታ	15 ቀናት	ድንግል ማርያም ጥር 21 ቀን ስትሞት መጨረሻዋን ለማወቅ አስከሬኗ ለማግኘት ሐዋሪያት ነሐሴ 1 ቀን ሱባዔ ገቡ። ነሐሴ 14 ቀን አስከሬኗ ተመልሶ ወረደላቸውና ቀበሩዋት። ነሐሴ 16 ቀን ማርያም እንደገና በአካል አረገች።
ጋድ (ለውጥ) ወይም ገሐድ (ግልጽ)	1 ቀን	ገና ወይንም ጥምቀት ዓርብ ሮብ ላይ ከዋለ በዚህ የደስታ ቀን ስለማይጾም በምትኩ በዋዜማው ይጾማል። እንዲሁም ገሐድ (ግልጽ) የክርስቶስ ልደት ጥምቀትና መለኮት ግልጽ የሆነበት ቀን በዋዜማው ጾም ተዘጋጅቶ ለመቀበል ሲባል ይፈጾማል።
የገና ጾም (ጾመ ነቢያት)	44 ቀን	መድኅን እንዲመጣ ነቢያት በተሰፋ 44 ቀን ጾሙ ትንቢቱ ለመፈጸሙ እምስክርነት የሚጾምበት ነው። ከህዳር 15 - ታህሣሥ 28 ቀን።
ጾመ ነነዌ	3 ቀን	ነነዌ እንዳትጠፋ ዮናስ "ንሰሐ ግቡ" ብሎ 3 ቀን ስለ ተጾመ ዛሬም ንስሃ ለመግባት ከሁዳዴ በፊት 3 ቀን ይጾማል።
ረቡዕና ዓርብ ጾም		ረቡዕ እየሱስ እንዲገደል ፈሪሳውያን ካህናት ሴራውን የጨረሱበት ሲሆን ዓርብ ደግሞ ስቅለቱ የተፈጸመበት ዕለት ነው።

የፋሲካ ቀን አወሳሰን ስሌት

የፋሲካ ቀን ሁል ጊዜ እሁድ ላይ መዋል አለበት። እንዲሁም ቅበላ፣ደብረዘይት፤ (እኩለ ጾም) ሆሳዕና እርገት ሐሁድ ላይ ይው ላሉ። በዚህ የተነሳ የበዓላቱ ዑደት በየዓመቱ ዞሮ ሲመጣ የወሩ ቀናት መስተካከል አለባቸው። ለዚህም ቀመር አለው። ዛሬ ብዙ ሰው ፋሲካ (እና ቅበላ) የሚውሉበትን ቀን ለማወቅ በካሌንደር መጠቀም ግዴታው ነው። ነገር ግን ቀመሩን ሲያውቅ እራሱ ተምኖ ሊደርስበት ስለሚችል ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል።*

1- እሰከዛሬ (ወይም እስከተፈለገው ዓመተ ምህረት) ድረስ ያሉት ዘመናት ይደመሩና በአስራዘጠኝ ይከፈላሉ። ዓለም ከተፈ ጠረ እስከ ክርስቶስ ልደት ድረስ 5500 ዓመታት ስለሆነ ከዚያ ወዲህ ካለው ዘመን ጋር ይደመራል። ለምሣሌ 1988 ዓ.ም ብን ወስድ 5500+1988=7488 7488÷19=394 ቀሪ 2 ይሆኖል።

2- ቀሪው ተረፈ ዘመን ይባላል። ከዚህ ላይ አንድ ቁጥር ተቀንሶለት የሚገኘው አሃዝ ወንበር ይባላል። ይህ በአስራ ዘጠኝ ይባዛል። ስለዚህ ለ1988 ዓ.ም ወንበሩ 2-1=1 ነው። 1×19=19 (19 መጥቅዕ ይባላል)።

ይህ ብዜት ከሰላሳ ቁጥር ከበለጠ በተደጋጋሚ ሰላሳ ቁጥር እየገደፉ ቁጥሩ ከ30 በታች እንዲወርድ ማድረግ ነው። ለምሣ ሌ 45 ሲመጣ 45-30=15 ይሆናል። 68 ቢመጣ 68-30-30=8 ይሆናል።

3- የዓመቱ መጀመሪያ ቀን (መስከረም 1 ቀን) የሚውልበት ዕለት በቅድሚያ መታወቅ አለበት። ከዚያም መጥቅዕን በመውሰድ መስከረም 19 ቀን የሚውልበት ዕለት ይሰላል። ለ1988 ዓ.ም መስከረም 1 ቀን ማክሰኞ ስለሚውል መስከረም 19 ቀን ቅዳሜ ይውላል።

4- እያንዳንዱ የሳምንት ቀናት ተውሳክ አለው። ይህም በዓላቱ እሁድ ላይ እንዲውሉ ለማስተካከል የሚጠቅም ቁጥር ነው። ተደማሪ የሚሆኑት ቁጥሮች የሚከተሉት ናቸው።

ቀን	ተውሳክ	ቀን	ተውሳክ
ቅዳሜ	8	ረብዕ	4
እሁድ	7	ሐሙስ	3
ሰኞ	6	ዓርብ	2 ናቸው።
ማክሰኞ	5		

5- መስከረም 19 ቀን ቅዳሜ ላይ ስለዋለ የቅዳሜ ተውሳክ (8 ቁጥር) ይደመርበትና ይህ በጥር ወር የነነዌ ጾም የምትውልበትን ቀን ይሰጠናል።

19+8 = 27

ስለዚህ የነነዌ ጾም ጥር 27 ቀን ይውላል።

* ይህ በከፊል በአቶ መሠረት ስብሐት ለአብ የተገለጸልኝ ነው።

ቁጥሩ ከ30 ከበለጠ 30 ገድፎ ቀኑ በየካቲት ወር ይውላል ማለት ነው ለምሳሌ፡- ጥር 35 ከመጣ (35-30=5) ነነዌ ጾም የካቲት 5 ቀን ይውላል።

በዚህ መሠረት ለ1991 ዓ.ም ብናሰላ (5500+1991)÷19=394 ቀሪ 5፣ ወንበር 4

4×19 = 76 76-(30×2)=16

መስከረም 16 ቅዳሜ ይውላል።

16 + 8 = 24 ነነዌ ጥር 24 ቀን ይውላል።

6- ነነዌ ከታወቀ ለሌሎች (የተያያዙ ስለሆኑ) ማስላት ነው። ለምሳሌ ነነዌ ሰኞ ስትገባ ልክ ከሁለት ሣምንት በኋላ አቢይ ጾም ይገባል። ከዚያም 55 ቀናት ከተጾመ በኋላ ስምንተኛው ሳምንት እሁድ ፋሲካ ይውላል።.....ወዘተ።

በዚህ መሠረት ለ1988ዓ.ም ጾመ ነነዌ ጥር 27

ቀን (ሰኞ)

አቢይ ጾም መግቢያ የካቲት 11 ቀን (ሰኞ)

እኩለ ጾም መጋቢት 8 ቀን (እሁድ)

ፋሲካ ሚያዝያ 6 ቀን(እሁድ) ይውላሉ።

7- የጾም ቀናቱ የሚወሰኑባቸው የጊዜ ገደቦች አሉ። ለምሳሌ ፋሲካ በግንቦት አይውልም። ቅበላም በጥር አይደርስም። ስለሆነም ገደቦቹ የሚከተሉት ናቸው።

ጾመ ነነዌ ጥር 17 ቀን እሰከ የካቲት 21 ቀን

አቢይ ጾም (ሁዳዴ) የካቲት 1 ቀን እሰከ መጋቢት 5 ቀን

ፋሲካ (ትንሳኤ) መጋቢት 26 ቀን እስከ ሚያዝያ 30 ቀን ይሆናሉ።

<u>ማስታወሻ፡-</u> እነዚህን ገደቦች ለመጠበቅ ሲባል መጥቅዕ ከመስ ከረም 14 ማነስ የለበትም። ይህ ሲሆን ወደ ጥቅምት ተዛውሮ ይሰላና ጾመ ነነዌ በየካቲት ይውላል።

ለምሳሌ ለ1989 ዓ.ም ቢሰላ እንደሚከተለው ይሆናል።

መስከረም 1 ቀን 1989 ዓ.ም ረቡዕ ይውላል።

5500+1989 = 7489

7489÷19 = 394 ቀሪ 3፣ ስለዚህ ወንበር 2

2×19=38፣ 38-30=8

መስከረም 8 ቀን ረቡዕ ሆኖ 8+4(ተውሳክ)=ጥር 12 ቀን መስከረም 8 ከ 14 ያነሰ ነው፣ ጥር 12 ቀንም ከገደቡ በታች ነው።

ስለዚህ መስከረም 8 ቀርቶ ጥቅምት 8 ተወስዶ ይሰላል።
ጥቅምት 8 ቀን ዓርብ ነው
8+2 (የዓርብ ተውሳክ) =10
ጸመ ነነዌ የካቲት 10 ቀን ይውላል።

ቤተክርስቲያን

በብዛት የሚገኙት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያኖች በክብ ቅርጽ የሚሰሩ ናቸው። ከውጭ ሲገቡ የሚገኘው ክፍል ቅኔ ማህሌት ይባላል። ምዕመናን ጫማቸውን አውልቀው ደጃፉን ተሳልመውና አደግድገው ይገባሉ። ይህ ክፍል መሪ ጌታዎች፣ ደብተራዎችና መዘምራን ዜማ የሚያዜሙበት ነው። በዚህ ክፍል ሰዎች በተወሰነላቸው ቦታ ዙሪያውን ሲቆሙ ወንዶች በግራ ክንፍ (በሰሜን) ሴቶች በቀኝ ክንፍ (በደቡብ) ይሆናሉ። መካከሉ በመጋረጃ ይለያል።

ቀጥሎ ያለውና ወደ ውስጥ የሚገባው መካከለኛ ክፍል ቄሶች ቁርባን የሚያቆርቡበት ሰዓታት የሚቆሙበትና ሌሎች ስነ ስርዓቶችን የሚያካሂዱ በት ክፍል ነው። ይህ ቅድስት ይባላል።

ሶስተኛውና ዋናው በመካከል የሚገኘው ክፍል ታቦቱ ያለበት ክፍል ነው። ይህ መቅደስ ይባላል። ከሀጋዊ ቀሳውስትና ዲያቆናት በስተቀር ወደዚህ ክፍል መግባት ፍጹም የተከለከለ ነው። ዲያቆናትም ቢሆኑ ታቦቱን* አይነኩም። አረማውያን ከነኩት በጳጳስ ይባረካል (ለምሳሌ ተሰርቆ ከነበረ)። የዲያቆን አንድ ተግባር ስጋ ወደሙን አዘጋጅቶ ማቅረብ ነው። ይህ የሚዘጋጀው ቤተልሄም ተብሎ በሚጠራ በስተምስራቅ አቅጣጫ በሚገኝ ቤት ውስጥ ነው። የካህናት ወደ ቤተክርስቲያን መግቢያና መውጫ በር በዚሁ አቅጣጫ ያለው ነው። የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስ ቲያን የራሷ የሆነ መንፈሳዊ ዜማዎች አሏት። ከእነዚህም ዋና ዋናዎቹ ሶስት ሲሆኑ እነዚህም በዝነኛው በቅዱስ ያሬድ የተደረሱና የተቃኙ ናቸው። ከእነኚህ "ግዕዝ" የሚዜመው በአዘቦት ቀንና በጸም ጊዜ ሲሆን ዕዝል ለክብረ በዓላት ጊዜ ነው። አራራይ ከሁለቱም ጋር ይጣመራል።

የቤተክርስቲያን ዜማዎችም ሆኑ የመዘምራን ሽብሸባ ሲከና ወኑ በተለያዩ መሣሪያዎች ታጅበው ነው። እነዚህም ጸናጽል፣ ከበሮ፣ቃጭል፣ መቋሚያ፣ እና ጽንሐ (ጽና) ናቸው። ከቤተክርስቲያኑ ውጭ ትልቅ ደወል (በደወል ቤት ውስጥ ወይም በረኸም ዛፍ ላይ) ተሰቅሎ የሚገኝ ሲሆን ይህ ጥሪ ለማድረግ፣ የቅዳሴን ጊዜ ለማስታወቅ እና ለመሳሰሉት ተግባራት የሚያገለግል ነው።

*አሪት ዘፀአት 25፡10-22 እንደሚያዘው ታቦት የሚሰራው 2½×1½×1½ ክንድ ኩብ ከሆነ የግራር እንጨት ሳጥን ሆኖ ውስጥና ውጪው በወርቅ የተለበጠ ሲሆን ከዳኑም የስርየት መክደኛ የተሰኘ 2½×1½ ክንድ የሆነ ወርቅ ሆኖ በግራ ቀኙ የመልአክ (ኪሩቤል) ቅርጽ ይኖረዋል። በውስጡ ሙሴ ከሰማይ የተቀበለው አስርቱ ትዕዛዛት ጭምር በጽላት ይኖራሉ።

ሌሎችም እንደግምጃ ቤት የመሳሰሉት ቤቶች በቤተክር ስቲያን ዙሪያ ይገኛሉ። ይህ በአጠቃላይ በትልቅ ግንብ ወይም አጥር ይከበባል። ከዚያ ውጭ ከተቻለ የመቃብር ቦታዎች ይመደባሉ።

ሥርዓተ ቅዳሴ

ይህ ሥርዓት መጀመሪያ ሐዋርያት ሲሰሩበት የነበረና ሰለስቱ ምዕትም በንቂያ ጉባዔ ላይ ተስማምተው ያስቀመጡት ሥርዓት ነው።* ለሥርዓቱ ዝርዝር ይዘት "መጽሐፈ ቅዳሴ ዘደብረ ዓባይ" (1984) ይመልከቱ። በዚህ ሥርዓት መጀመሪያ የጥሪ ደወል ይደወላል። ዲያቆኑ መብራት ይዞ ይደውላል። ከዚያም ካህናትና ሌሎች ሹማምንት እንዲሁም ምዕመናን መግባት ይጀምራሉ። ሲገቡም በሥርዓቱ እያማተቡ ነው። ይህም እጃቸውን (ጣቶቻቸውን) በመስቀል ቅርጽ አድርገው ከግንባር ላይ በማሳረፍና ከዚያም እጁን ወደ ደረት በማውረድ ቀጥሎም በትከሻ ላይ ከግራ ጎን ወደቀኝ ጎን በማምጣት ነው። ይህ ድርጊት ተጨማሪ ምሣሌነት አለው። ይህም ጌታችን ከሰማይ ወደ ምድር ወረደ፣እኔንም ከግራ ጎን (ከሃጢያት) ወደቀኝ ጎን (ጽድቅ) አዛወረኝ ማለት ነው።

ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ስግደት ይደረጋል። የስግደቱም ምሣሌ መሬት ነክተው ቀና ሲሉ እንደዚህ አፈር ነበርኩ አሁን ሰው አደረግከኝ ስለዚህም ክብር ምስጋና ይድረስህ ማለት ነው።

ከዚያም ካህናቱ ዲያቆናቱ እና ሌሎችም ባለሞያዎች የስራ ድርሻቸውን ለመሥራት ይዘገጃጃሉ። (ልብስ መቀየር፣ ዕቃ ማቀራረብ፣ ማጠን፣ . . .) ምዕመናን የግል ጸሎት በማድረስ ይቆያሉ።

ከዚያም ቅዳሴ ይጀመራል። ቅዳሴ ማለት ቁርባኑን ለማዘጋጀት እና ለማቅረብ የሚካሄድ ሥነ ሥርዓት ነው። የአጀማመሩ ሰዓት እንደ ሁኔታው ይለያያል። ሀ/ በጾም ቀናት ከቀኑ በሰባት ሰዓት ይጀመራል።

ለ/ በአዘቦት ቀን ሟች በ1፡30 ተጀምሮ በሶስት ሰዓት ገደማ ያበቃል። (ይህ የሰለስት ቅዳሴ ይባላል)።

ሐ/ በሰንበት ቀን ከሟቹ በ12 ሰዓት ይጀመራል። ይህ በእሁድ ቀናትና ዕርገት በመሣሉት ዘጠኝ ዓበይት በዓላት ነው።

መ/ ለገና፣ ለጥምቀትና፣ ለፋሲካ ዕለቶች በእኩለ ሌሊት ይጀመራል።

ቅዳሴ ሲጀመር ምዕመናን ይሰግዳሉ። ቆይቶም ካህኑ "ተነሱ ጌታን አመስግኑ" ብሎ ጥሪ ያስተላልፋል። ሁሉም ይነሣሉ። እንደገናም መጋረጃው ከመከፈቱ ቀደም ሲል ምዕመናን ተዘጋጅተው እንዲጠባበቁ ዲያቆኑ እንዲሰግዱ ያስታውቃል። የዚህ አምልኮ ስነ ስርዓት ዝርዝር እንደሚከተለው ነው። [1]

በቅዳሴ መጽሀፍ እንደተቀመጠው መጀመሪያ በአራራይ ዜማ መወድስ ይጀመራል። (ይህ በየቀኑ የሚከናወን ነው።) ከዚያም እንደ በዓልነቱና

[1] ለሥርዓቱ ዝርዝር ይዘት "መጽሐፈ ቅዳሴ ዘደብረ ዓባይ" (1984) ይመልከቱ።



ታቦት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ (ኢትዮጵያ) ልዩ መለያ ነው ::

ማስታወሻነቱ እየተመረጠ ዕዝል እና ግዕዝ የሚፈራረቁበት ቅዳሴ ይከናወናል። ቁርባን ማቅረቡ ዋናው ሥነስርዓት ነው። ይህም በሚከተለው ዓይነት ይከናወናል።

የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሥርዓተ ቅዳሴ ከጥንት ጀምሮ በሐዋሪያት ሲሰራበት የነበረና የኒቂያ ጉባኤ ያጸደቀው ሥርዓት ነው። ሥርዓቱ ከካቶሊክ ለየት ከሚያደርገው አንዱ ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያ (ለምሳሌ ፒያኖ አኮርዲዮን) መጠቀም ክልክል መሆኑ ነው። ዜማው ግን በጣም ደማቅና እጅግ የሚመስጥ ነው። ሥነ ሥርዓቱም ይበልጡን የሚካሄደው በመቅደስ ውስጥ ነው። መቅደሱ በትልቅ መጋረጃ (መንጠላዕት) የተጋረደ ሲሆን ከህጋዊ ካህናት በስተቀር ምዕመናን እንዲገቡ ፈጽሞ አይፈቀድም።

ካህኑ ሲገባ ልብሱን ወገቡ በታች ዝቅ አድርጎ በትከሻው ላይ ትምህርተ መስቀል አጣፍቶ ይገባል። ይሳለማል። ይሰግዳል። ይጸልያል። በዕለቱ የሚሰራባቸውን ንዋየ ቅድሳት አንድ ባንድ ይባርካል። እነዚህም ጻህል (ህብስቱን ማስቀመጫ) ማህፈድ (መሸፈኛ) ጽዋ (ወይን መያዣ) መሶበ ወርቅ ዕርፈ መስቀል የመሣሉት ናቸው። የተለያዩ አልባሳትም ይጭናሉ።

በስርዓተ ቅዳሴ ጊዜ ለሚከናወን ተግባር ሁሉ የተወሰነለት ጸሎት አለው። ለምሳሌ ካህኑ መቅደስ ሲገባ ጸሎተ ንሰሐ ይደግማል። መዝሙረ ዳዊትም ይከተላል። ወደ መጋረጃው ውስጥ ሲገባ የሚጸለየው የጉርጎሪዮስ ጸሎት ነው። ከስግደት በኋላም የባስልዮስ ጸሎት ይቀጥላል። በታቦቱ ፊት ሲሰገድ የሚጸለየው የዮሐንስ ጸሎት ነው። እነዚህ በደንቡ ተዘግበውና ተጠንተው የታወቁ ናቸው።

በዚህን ጊዜና ከዚህም በኋላ እሰከ ሥነ ሥርዓቱ ማብቂያ ድረስ ምዕመናን በጸሎት እና በጸጥታ ሥነ ሥርዓት ይቆያሉ። መሣቅ ወይም ጮክ ብሎ መናገር ማለት የጸሎትን ስነ ስርዓት አለመጠበቅና ለእግዚአብሔር ቤትም ክብር አለመስጠት ሆኖ ስለሚወሰድ አጥፊው ከቤተክርስቲያኑ እንዲወጣ ይደረጋል። ቄስ ቢሆን ግን በአንድ ቀን ሱባዔ (ጾም) ይቀጣል።

በቅዳሴው ሥርዓት ከጸሎት በተጨማሪ ከመጽሀፍ ቅዱስ ብዙ ምንባብ ይኖራል። ረዳት ቄስ (ንፍቅ ቄስ) ጧፍ በማብራት መቅደሱንና ቅድስቱን ደጃፎቹንና አካባቢውንም እየዞረ በጽና ያጥናል። አካሄዱም በዘፈቀደ ሳይሆን ስርዓት አለው። ይህም ከመቅደሱ በምዕራብ በር ወጥቶ "በየማዕዘኑ እያጠነ በደቡብ በር ዞሮ ተመልሶ በምዕራብ በር ይገባል። በስነ ሥርዓቱ ሂደት የዲያቆን ተግባር ሕዝቡን ለጸሎት መጋበዝ፣ በጸሎት መምራት እና ማዜም እንዳሁም ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን ማበርከት ነው።

የቅዳሴው ሥነ ሥርዓት የሚጀምረው ህብስቱንና ወይኑን ከቤተልሄም በማምጣት ነው። በዚህን ጊዜ ትልቁ ደወል አምስት ጊዜ ይደወላል። ምዕመናን ይሰግዳሉ። ቀደም ሲል ቀሳውስት ወደ ቤተ ክርስቲያን

እንዲመጡ ለመቀስቀሻ ሶስት ጊዜ አስር አስር ማለትም 30 ጊዜ ይደወላል) (ሶስት ጊዜ አራት አራት ሊደወልም ይችላል)። የቤተክርቲያን በርም የሚከፈተው ያን ጊዜ ነው። በኋላ ህብስቱና ወይኑ ወደ መቅደስ እንደደረሱ ካህኑ (መሪው ቄስ) በታላቅ አክብሮትና ጥንቃቄ በታጠበ እርጥብ እጁ ህብስቱን አንስቶ ይባርካል። ለንፍቅ (ረዳት) ቄስም ያሣልፋል። ረዳት (ንፍቅ) ቄስም በአክብሮት በማህፈድ ተቀብሎ በመሸፈን መልሶ ያቀርባል። ቄሱም ተቀብሎ ታቦቱን ይዞራሉ። ሕብስቱንም በጻህል ውስጥ ያኖሩታል። ቀጥሎም ረዳት ቄሱ ወይኑን በጽዋ ይጨምራል። ይዞትም ሶስት ጊዜ ታቦቱን ይዞራሉ። በዚህን ጊዜ ሁሉ ተገቢው ጸሎት እየተካሄደ ይሆናል። ከዚህ ሥነ ሥርዓት በኋላ ቄሱ ህብስቱንና ጽዋውን የጌታችን ስጋ ወደሙ እንዲሆኑ መጀመሪያ አንድ በአንድ በኋላም አንድ ላይ ይባርካቸዋል። ምዕመናንም ጸሎቱ እንዲደርስ አሜን በማለት አብረው ይጸልያሉ።

አቡነ ዘበሰማያትም ይደገማል። የምስጋና ጸሎት (ስብሃት) በማድረስም ምዕመናን ይሳተፋሉ። ይህም በአማርኛ ሲነገር፤ ቄስ ይላል÷

"አንዱ አብ ቅዱስ ነው፣ አንዱ ወልድ ቅዱስ ነው፣ አንዱ መንፈስ ቅዱስ ቅዱስ ነው" ምዕመናንም ይላሉ።" አብ በእውነት ቅዱስ ነው።

ወልድም በእውነት ቅዱስ ነው።

መንፈስ ቅዱስም በእውነት ቅዱስ ነው።

ቀጥሎም ቄሱ ሁሉንም ይባርካል። ከዚያም ስግደት ይኖራል። መሪ ዲያቆን ለጌታ እየሱስ ክርስቶስ የምልጃ ጸሎት ያቀርባል። ይህ ወደ ሰላሳ ዓይነት የሚሆን ምልጃ ህብረተሰቡን ሁሉ የሚያስታውስ ይሆናል። ለምሣሌ በስደት ላይ፣ በብሄራዊ ግዳጅ ላይ፣ በህመም ላይ ያሉትን ሁሉ እንዲሁም አለቆችን፣ መንፈሳዊ አባቶችን ፓትሪያርኩን፣ የአገር መሪዎችን ኢትዮጵያን ጭምር በጸሎት ያስታውሣል። ምዕመናንም መሬት ላይ እንዳጎነበሱ በምልጃ ጸሎቱ ይሳተፋሉ።

ቀጥሎም ካህናቱ ከመጋረጃው ውጭ ወጥተው በዜማ እየተቀባበሉ የምስጋና ጸሎት ያደርሣሉ። (ሽብሸባ) ክርስቶስ ስለ ሰራልንም ስራ ያመሰግናሉ። ከዚያም ከመጽሀፍ ቅዱስ ጥቅሶች እየተመረጡ ይነበባሉ። እነዚህም

1ኛ- ከጳውሎስ መልዕክቶች፣

2ኛ- ከአራቱ ሐዋሪያት መልዕክቶች (ጴጥሮስ፣ዮሐንስ፣ያዕቆብና ይሁዳ)

3ኛ- ከሐዋሪያት ሥራ

4ኛ- ከመዝሙረ ዳዊት ከእያንዳንዳቸው እየተመረጠ ይነበባል። ከዚህ በኋላ ከወንጌል ይነበባል። ደወል ሶስት ጊዜ ይደወላል። ምዕመናን ወንጌልን በየተራ ይሳለማሉ።

ከአሁን በኋላ ለቁርባን ዝግጅት ምዕመናን በቅድሚያ ንሰሃ እንዲገቡ ይነገራል። በቂም በቀል ወይም በሃጢያት ሆኖ ቁርባን መቀበል አይገባምና ምዕመናን ተንበርክከው ቄሱ በሕዝቡ ስም የንሰሃ ጸሎት ያቀርባል። እግዚአብሔር ንሰሃ ለገባ ሰው ይቅርታ እንደሚያደርግ በመጽሐፍ ተጽፏልና። ቀጥሎ የምስጋና ጸሎት (ስብሃት) ይደገማል። ጸሎተ ሃይማኖት እና የሐዋርያት አመክንዮ ይቀጥላል። ካህናት ሰላምታ ይሰጣጣሉ (እጅ በመንሳት) ምዕመናንም እንዲሁ እርስ በርሳቸው ጎንበስ በማለት ሰላምታ ይለዋወጣሉ።

በዚህም ጊዜ ከአስራ አራቱ የምስጋና ቅዳሴዎች (የማርያም የሐዋርያት...) ለበዓሉ ነክ የሆነ ወይም አግባብ ያለው ተመርጦ ይቀደሳል። ከዚያም "እግዚኦ" ይባላል። ቄሱ እና ምዕመናን በመቀባበል አርባ አንድ ጊዜ እግዚኦ ማህረነ ክርስቶስ ይላሉ። ይህ በዜማ የሚሄድ ነው። አባባሉም፡

1ኛ- ቄሱ አንዴ በማከታተል 3 ጌዜ፣ ምዕመናን 3 ጊዜ

2ኛ- ቄሱ አምስቴ በመደጋገም በእያንዳንዱ 3 ጊዜ

(ድምር 15 (ምዕመናንም እንዲሁ 15 ጊዜ

3ኛ- ቄሱ ሁለት ጊዜ፣ መዕመናን ሁለት ጊዚ።

4ኛ- ቄሱ አንድ ጊዜ በረዥሙ ያዜማሉ (ድምር 41 የጌታ ግርፋት ምሣሌ ነው።

በዚህን ጊዜ ትልቁ ደወል ሰባት ጊዜ ይደወላል። በመጨረሻ ም ቁርባኑ ደግሞ ተባርኮ እና ምዕመናኑም አቡነዘበሰማያት ደግመው ስጋ ወደሙ (ቁርባኑ) ከመቅደሱ ሊወጣ ይዘጋጃል።

በዚህን ጊዜ ከቅኔ ማህሌት ሆነው መሪ ጌታዎችና መዘምራን ቅኔ ይቀኛሉ ክብርይእቲ ያወርዳሉ ይባላል።

ቤተመቅደሱ ይከፈታል። በሮቹ ወለል ተደርገው ይከፈታሉ። በዚህ ጊዜ ሰው ሁሉ ይሰግዳል። ደወልም ሶስት ጊዜ ይደወላል። እርገትም ይወርዳል። (ማለትም ስጋ ወደሙ ከመቅደሱ ይመ ጣል)። ቆራቢዎችም ለመቁረብ ይቀርባሉ። ድያቆን በየተራ ያቆርባቸዋል። የቁርባኑ ሥነ ሥርዓት ይቀጥላል። ቆራቢዎችም ህብስቱን ይቀበላሉ። ወይኑንም በእርፈመስቀል (ማንኪያመሰል) በአፋቸው ይቀበላሉ። የአቀራረቡ ቅደም ተከተል እንደሚከተለው ይሆናል፡ መጀመሪያ አቁራቢው ቄስ ራሱ ይቆርባል፣ ቀጥሎም ረዳቱ ይቆርባል። ከዚያም ጳጳሳት (በቦታው ካሉ) ቀሳውስት ዲያቆናት፣ ይቆርባሉ። ቀጥሎም የተጠመቁ ወንዶች ህጻናትና ሴቶች ህጻናት ከዚያም የቀሳውስት ሚስቶች እና መነኮሳት ቆርበው የቀሩት ወንዶችና ሴቶች ይቀጥላሉ።

ካህኑ በሚያቆርብበት ጊዜ "ስጋንና ነፍስን ደመነፍስንም ለማከበር የሚሆን የጌታችን የእየሱስ ክርስቶስ ስጋ ይህ ነው።" ሲል ቆራቢው ሲቀበል "አሜን" ይላል። ረዳቱም ሲያቆርብ "የሕይወት ጽዋ ከሰማይ

የወረደ የክርስቶስ ክቡር ደሙ ነው" ሲል ቆራቢውም ተቀብሎ "አሜን ወአሜን" ይላል።

ይህ በሚሆንበት ጊዜ በቅኔ ማህሌት መሪጌታው ዝማሬ ይቀኛሉ። ያዜማሉ። በመሃሉ ክብርይእቲ ያወረደው ይቀርብና ለመሪው ቅኔውን ያበረክታል። በዚህን ጊዜ ሁሉ ቅኔው በመቋሚያ ይዘመምና ከበሮ ይመታል፣ጸናጽል ይጸነጸናል። (ይጸፋል)።

ቀዳሾችም ቤተመቅደስ ውስጥ የነበሩት ወጥተው ይቆማሉ። ውዳሴ ማርያም ይደገማል። መልክዓ ማርያም፣ በመጨረሻም መልክዓ እየሱስ ይደገማል።

ይህ ሁሉ እስኪሆን ቁርባኑ ይ ጥላል። ቆራቢዎች ጥቂት ከነበሩም አቁራቢዎች ስራቸውን አጠናቀው ወደ ቤተመቅደስ ተመ ልሰው ይቆያሉ።

ሁሉም ካበቃ በኋላ ቄሱ ይባርካሉ። የኡዛዜ ጸሎት ይሰጣል (ማኅረጊያ)። በመጨረሻም ዲያቆኑ ምዕመናንን ያስናብታል።

<u>ማስታወሻ፡-</u> አንድ ቆራቢ ከቆረበ በኋላ ለዚያን ዕለት እጅ እግሩን መታጠብ የለበትም። እንዲሁም ምራቅ መትፋት፣ ደም መድማት፣ ጥፍሩን መቁረጥ፣ ጸጉር መላጨት፣ መሳደብ፣ መጣላት፣ ግብረስጋ ግንኙነት መፈጸም፣ እና የመሳሰሉትን የሚያረክሱ ተግባራት መፈጸም አይገባውም።

ከጥንት ሲያያዝ የመጣልን ታሪክዊው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተርስቲ ያን የቅዳሴና የቁርባን ስርዓት በአጭሩ ይህንን የመሰለ ነው።

<u>የካቶሊክ ሃይማኖት</u>

<u>የኦርቶዶክስና የካቶሊክ መለያየት ታሪክ</u>

በነዚህ ሁለት ታላላቅ ሃይማኖቶች መካከል የተፈጠረው አለመግባባት በ5ኛው መቶ ዓመት በኬልቄዶን ጉባኤ በተዋህዶ ቤተክርስቲያንና በሌሎች መካከል እንደተከሰተው ዓይነት በአንድ ምክንያትና ወቅት አልነበረም። ብዙ ምክንያቶች ነበሩት። ለብዙ መቶ ዓመታትም የተራዘመ ነበረ።

ለልዩነቶቹ መነሻ ምክንያት ከሆኑት አንዱ ፖለቲካዊ ነው ለማለት ይቻላል። ይህም የሮማውያን መንግሥት መፈራረስ ነው። ታላቁ የሮማውያን መንግሥት ከምዕራብ አውሮፓ እስከ ምስራቁ ተንሰራፍቶ እስከኖረበት ዘመን ድረስ ክርስቲያን ሃይማኖትን በማዕከላዊነት መምራት ቀላል ነበረ። ለምሳሌ፣ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ባለው ሥልጣን በመታገዝ በተለያዩ ጊዜያት መንፈሳዊ ጉባዔዎችን እየጠራ ሲያስማማ ቆይቷል። በኋላ ግን በ476 ዓ.ም አካባቢ ሃያል የነበረው መንግሥት እየደከመ ሄደ ፈራረሰና ተበታተነ። ትናንሽ አገሮች ነጻነታቸውን አገኙ። የሮማ ቄሣሮች

ከዙፋናቸው ከመንበራቸው ስለወረዱ በነሱ ምትክ ትናንሽ ሕዝባዊ አገዛዞች ተመሰረቱ።

በዚህ ሂደት መካከል የሮማ ጳጳሳት ለቀድሞ ቄሳሮች ተገዢ መሆኑ ቀርቶላቸው ራሣቸውን ችለው መንፈሣዊ ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ አመቺ ሁኔታ ተፈጠረላቸው።

በምሥራቅ አውሮፓ ግን ነገሥታት ጉዟዎች ራሳቸውን ችለው ነበሩና በፓለቲካው አስገዳጅነት ጳጳሳቱን በስራቸው እንዳደረጉ ቀሩ። በዚህ የተነሣ ምዕራቡ ክፍል ራሱን ሲችልና በአንድ ወጥነት የሚያስተዳድረው መንፈሣዊ መሪ ሲኖረው የምስራቁ ክፍል ግን በነገሥታቱ የፖለቲካ አመራር ስር ስለሆነ የፓትሪያርኮች ነጻነት በአንጻራዊ መንገድ ውሱን ሆነ። ለምሣሌ ርስተ ጉልታቸው ተወሰደባቸው። አንዳንድ የእምነት አሰራሮችም ለገዢው መደብ በሚያመች መልኩና ስልጣንን በማይቀናቀን መልኩ እንዲስተካከሉ ወይም እንዲታገዱ ተደረጉ።

በዚህ ሳቢያ የምስራቁ እና የምዕራቡ ክፍሎች የተለያየ አመለካከት እያደረባቸውና አንዱ የሚያደርገው መሻሻል ለሌላው አልጥመው እያለ ሄደ። በሁለቱ መካከል ልዩነት እየተፈጠረና እየሰፋ ሄደ። መሪ መሆን ያለበት ማን እንደሆነ ስምምነት ስላልነበረ ነገሮች እየከረሩ ሄዱ። ለምሣሌ ቻርለማኝ ወይም ታላቁ ቻርለስ ንጉሠ ነገሥት ሆኖ ሲነግስና (በ800 ዓ.ም) አቡነ ሊዎ 3ኛ ዘውድ ሲጭንለት አቡኑ የምሥራቁን ክፍል አላማ ከረም። በኋላ ደግሞ የቡልጋሪያ ንጉሥ ቦሪስ (852 - 889) የክርስቲያን እምነት ተቀብሎ ሊጠመቅ ሲፈልግ የምስራቁ እንዳያጠምቀው ሲል የምዕራቡ ክፍል ተቃወመ። በዚህ የተነሣ አንዱ የሌላውን ድክመት በማመልከት ንጉሡን ወደራሣቸው ለመሳብ ዘመቻ ጀመሩ።

በኋላም በ1054 ዓ.ም ተወጋገዙ።* ልዩነቶቻቸውንም በዝርዝር እየጻፉ መወነጃጀል ጀመሩ።

አንዳንድ ልዩነቶቻቸው የሚከተሉትን ይመስሉ ነበረ።

1- የካቶሊክ ቄስ ሚስት ማግባት የለበትም፣ ድንግላዊ ሆኖ መኖር አለበት። የኦርቶዶክስ ቄስ ግን ሚስት ያገባ ወይም ያላገባ ሊሆን ይችላል። ሚስት ካገባ ግን ምስቲቱ ቀድሞ አግብታ ባሏ የሞተባት መሆን የለባትም። እንዲያውም ፈት (ባል የፈታች) መሆን የለባትም። የሚያ ገባትም ከመቀሰሱ በፊት ይሆናል።

2- ጥምቀት (ክርስትና) በካቶሊክ ዘንድ ከአንገት በላይ ራስን በመጠመቅ ሊያበቃ ይችላል። ይህ ለአዋቂዎች እንዲያመችና ስራውን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለሰፊው ሕዝብ ለማዳረስ ተብሎ የታሰበ ነው ይባላል። አዋቂዎች ልብሣቸውን እንዲያወልቁ አይገደዱም ማለት ነው። ኦርቶዶክስ ግን የሚቀበለው ልብስን አውልቆ ሙሉ ጥምቀት ነው።

---

* ይህ ግዝት ከ900 ዓመታት በላይ ጸንቶ ሲቆይ በ1965 ዓ.ም ተነስቷል፣ የሮማው አቡነ ጳውሎስ 6ኛ እና የግሪኩ ፓትሪያርክ አቴናጎራስ በስምምነት አነሱት።

3- ጾምን በተመለከተ በካቶሊኮች ዘንድ ስጋ ከመብላት መቆጠብ ነው። እንደእኛ ከሆነ ወተት እና እንቁላልም ክልክል ነው። ጾምም ዓርብ እና ረቡዕ እሰከ ግማሽ ቀን ነው። ግን በምዕራቡ ባህልና የስልጣኔ ሂደት የተነሣ ለረዥም ሰዓታት ምግብ እንዳይቀመስ መከልከል ከባድ ስለሆነ ለሁሉም በሚያመች መልኩ ቀላል በማድረግ ጾም በፍል ሰታ (15 ቀን) እና የስቅለት ዕለት እንዲሁም ረቡዕና ዓርብ እንዲሆንና ይህም ቢሆን ጠም መዋል ሳይሆን ሶስት ጊዜ ይበላ የነበረው ሁለት ጊዜ (ቁርስና ግማሽ ምሣ ግማሽ እራት) እንዲሆን ነው። የቀረውን በገንዘብ አስቦ መመጽወት ይቻላል። ኦርቶዶክስ ግን ይህንን ፈጽሞ አልተቀበለም። ጾም የጸሎት አስፈላጊ ቅደመ ሁኔታ ስለሆነና ስጋዊ ስሜትን አድክሞ መንፈሣዊ ስሜትን ስለሚያጠነክር መላላት የለበትም ባይ ነው።

4- ቁርባን በሚከናወንበት ጊዜ በካቶሊክ አመለካከት ወይን በሁሉ ቦታ እና ጊዜ ላይገኝ ላይሳካ ስለሚችል ስጋ ወደ ሙን ለቄሶች ብቻ አድርጎ ለሰፊው ቆራቢ ግን ከብዛቱ የተነሣ ሀብስቱን ማዳረስ ብቻ በቂ ይሆናል። ከተቻለ ግን በአገራችን እንደሚደረገው ሁሉ ሀብስቱን በወይን ውስጥ ነክሮ ማቀበሉ በቂ ነው። ለብዙ ምዕመናን በአንድ ማንኪያ ቁርባን መስጠቱ የሃይጂን ጥያቄም ያስነሣል ይላሉ። በኦርቶዶክስ አመለካከት ግን ቁርባን ከተባለ ሁሉንም ሰው በተሟላ ስርዓት ማስተናገድ ይገባል እንጂ መከፋፈልም ሆነ መለወጥ አይገባም።

ከእነዚህ ሁሉ ልዩነቶች ግን የማይታረቅ መስለው የታዩት የሚከተሉት ናቸው።

ሀ- የካቶሊክ ጳጳስ ቀኖናን በተመለከተ የሚሰጠው የግል ውሣኔ የተሳሳተ ሊሆን አይችልም። ይህ ድንጋጌ በ1870 ዓ.ም በመጀመሪያው የቫቲካን ጉባኤ የተሰጠ ነው። እየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሳለ ስልጣኑን ያወረሰው ለጴጥሮስ ስምአን ስለሆነ (በዚህ አለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሰራለሁ የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ ማቴ 16÷18-19) በዚሁ ሥልጣን ተዋረድ የሮማው ጳጳስ በምድር ላይ የክርስቶስ እንደራሴ ነው። ባለሙሉ ሥልጣን ሆኖም ይወሰዳል። እርግጥ ካርዲናሎች በአማካሪነት ደረጃ ሊኖሩት ይችላል። የመጨረሻው ሥልጣን ግን የእርሱ ብቻ ነው። ማዕረጉም ርዐሰሊቃነ ጳጳሳት ነው።

በኦርቶዶክስ አሰራር ግን ፓትርያርክ ሰው ነው። ሰው ደግሞ በማንኛውም ነገር ሊሳሳት ይችላል። ስለዚህ ከባድ ውሣኔዎች በመንፈሳዊ ጉባኤ (ሲኖዶስ) መወሰን አለባቸው።



በቫቲካን (ሮም) የሚገኘው ቅዱስ ጴጥሮስ ካቴድራል የካቶሊክ ማዕከል ነው ::

በዚህ የተነሣ ካቶሊኮች ቤተ ክርስቲያንን እንደ ዓለም አቀፍ አሃዳዊ መንግሥት በመቁጠር የሮማ ጳጳስ የሁሉም ጳጳሳትና ምዕመናን የበላይ ነው ሲሉ ኦርቶዶክስ ግን እያንዳንዱ አማኝ የአምላክን ህግ የመጠበቅና የቤተ ክርስቲያንን ህልውና በዲሞክራሲያዊ መንፈስ የመጠበቅ ሃላፊነት አለበት ይላሉ።

ለ- ከፍ ሲል በተጠቀሰው አመለካከት በመነሣት የሮማው ጳጳስ ሊዎ በ1854 ዓ.ም ያወጁት ድንጋጌ ነበር። ይህም ማርያም ንጽህት ነች ከአዳም የተወረሰ ስጋዌ ሃጢያት የለባትም በዕለት ከዕለት ኑሮዋም ቢሆን ለሃጢያት አልተጋለጠችም የሚል ነው። ጳጳሱ ይህን ለመወሰን መብታቸው ነው። ምዕመናን ሁሉ መቀበል ይገባቸዋል። የኦርቶዶክስ ምዕመናን ግን በራሳቸው የግል እምነት ካልሆነ በስተቀር የሮማው ጳጳስ ውሣኔን በውሣኔነቱ አይቀበሉም።

ሐ- በኦርቶዶክስ እምነት መሰረት መንፈስ ቅዱስ ከአብ ይሰርጻል እየሱስ ክርስቶስ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተነገረው ከማርያም የተጸነሰው በመንፈስ ቅዱስ ሃይል ነው። ይህም መላው ክርስቲያን ሕዝብ በዝነኛው የኒቂያ ጉባኤ የተቀበለውና የተስማማበት ነው። የካቶሊክ እምነት ተከታዮች ግን መንፈስ ቅዱስ ከአብ "እና ከወልድ" ይሰርጻል ይላሉ። በዚህ እምነት መሠረትም በስተኋላ በኒቂያው ጉባኤ ሰነድ ላይ "እና ከወልድ" የሚል ተጨማሪ ሃረግ በመጨመር አስተካክለውታል። (ገጽ 54 ይመልከቱ)

በነዚህና በሌሎች ጥቃቅን ምክንያቶችም ጭምር በሁለቱ እምነቶች መካከል ልዩነቶች እየሰፉ ሄዱ። በመጨረሻም በ1204 ዓ.ም የስግደት ዕለት ቅራኔው ተባባሰ። የታላቁ ምሥራቅዊ የኦርቶዶክስ ማዕከል የሆነችው ቁስጥንጥኒያ ከተማ ተቃጠለች። ተዘረፈች። ይህ የሆነው በአረማውያን ሳይሆን ከምዕራብ አውሮፓ በመጡ ክርስቲያን ወታደሮች ነበረ። ጉዳዩ እንደሚከተለው ነው።

የእስልምና ዕምነት ተከታዮች ከሳውዲት አረብ (ሜካ) እየተ ስፋፉ መጥተው ወደ እየሩሣሌም ተቃረቡ። የምዕራብ አውሮፓ ክርስቲያኖች ይህች የእየሱስ ክርስቶስ አገርና የክርስቲያን ታሪክ መሰረት የሆነች ቦታ በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ሥር ስትወድቅ ለማየት አልፈለጉም። ስለዚህ ወዶ ዘማች ሁሉ ከመላው አውሮፓ እየተውጣጡ ወደ ምስራቅ ዘመቱ ጳጳሳቱም "በዚህ ዘመቻ የተሳተፈ ሰው ሃጢያቱ ይሰረይለታል" ብለው አስታወቁ። ስለሆነም ዘመቻው በ1095 ተጀምሮ በስፋት ቀጠለ። ጦርነቱም ለብዙ ዓመታት (እስከ 1396) ተካሄደ። ይህ በታሪክ "የመስቀል ጦርነት" በመባል የሚታወቀው ነው። በአነሳሱ መጀመሪያ ሙስሊ ሞች በ637 ዓ.ም እየሩሣሌምን ያዙ። የመስቀሉ ጦርነት ቀጥሎ በ1099 ዓ.ም ክርስቲያኖች አሸለቀቁ።

ነገር ግን እንደገና ሙስሊሞች በመሪያቸው በሳላዲን አማካኝነት በ1187 ዓ.ም መልሰው እየሩሳሌምን ወረሩ። ጦርነቱም ቀጠለ። በዚያን ዘመን ወደ መካከለኛ ምስራቅ የሚደረገው ጉዞ በእግር ስለነበረ ወታደሮቹ በየመንገዱ በክርስቲያን ወን ድሞቻቸው እየተቀለቡና እየተረዱ ይጓዙ ነበረ። በዚህ ረገድ ትልቅ የሞራል ድጋፍም ያኖኑ ነበረ። ነገር ግን ጦርነቱ እየተራዘመ በመጣ ቁጥር በድጋፍ ሰጪዎች አመለካከት ከጥቅሙ ጉዳቱ እያደላ መጣ። ወዶ ዘማቾቹ የምሥራቁ ሃይማኖት ከእነሱ የተለየ መሆኑን በማሰብ ወደ ጥላቻ እና ከምጽዋት እና ዕርዳታ ይልቅ ወደማስገደዱ ወደማራቆቱ አዘነበሉ። በነዋሪዎቹ ዘንድ ምሬቱ እየጨመረ መጣ። በመጨረሻም በ1204 ዓ.ም የስግደት ዕለት ወታደሮቹ በስካር ተነሳስተው የቁስጥንጥንያን ከተማ ዘረፉ። እስልምናን እንዋጋለን ብለው የተነሱት ወታደሮች በክርስቲያኑ ሕዝብ ላይ ተነስተው በከፋ ጭካኔ ጨፈጨፉት። ከተማዋንም አቃጠሉ። ቁስጥንጥንያ ለሺ ዓመት ያህል የስልጣኔና የባህል ቅርስ ማዕከል የሆነችና የተከበረች ከተማ ነበረች። ታድያ ለሶስት ቀናት ያለማቋረጥ ተደባየች የቤተ ክርስቲያን አቢያተመጻሕፍትተቃጠሉገዳማት እና መኖሪያ ቤቶች ሳይቀሩ ተደመሰሱ።

በዚህ በሰካራም ወታደሮች በተፈጸመ ግፍ እና ስቃይ የተነሳ በሁለቱ ሃይማኖቶች መካከል ቅራኔው ተባባሰ። ቂሙም ስር ሰደደ። ከዚያ ወዲህ ሁኔታውን ለማርገብ ጥረት ቢደረግና ለምሳሌ በ1439 ዓ.ም በፍሎሬንስ ከተማ የስምምንት ጉባኤ ቢካሄድም የእስልምና ሃይማኖት እያየለ መጥቶ የቀረውንም ምስራቅ አውሮ ፓን ጭምር ስላጥለቀለቀው ጥረቱ እዚያ ላይ ተገታ። ቁስጥ ንጥኒያም በ1453 ዓ.ም በሙስሊሞች ተያዘች። ስሟም ኢስታ ንቡል ሆነ። ስለዚህም ዛሬ በግሪክ ኦርቶዶክስና በሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያናት መካከል ልዩነቱ እንዳለ ነው።*

የካቶሊክ ሃይማኖት በኢትዮጵያ

የሮማውያን ካቶሊክ ሃይማኖት መጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ የገባው ግራኝ መሐመድ እስልምናን በጀመረ ማግስት ነበረ። አጼ ልብነ ድንግል የግራኝን ጦር ለመቋቋም አልቻሉም። ወታደሮቻቸው በጦርና በጎራዴ በጋሻ እና በጥቂት ጠመንጃዎች በመዋ ጋት በቱርክ በፋርስና በሳውዲት አረብ ወታደሮች የታገዘን እና በመድፍ ጭምር የታጠቀን የግራኝ ጦር ሊመክቱ አልቻሉም። ስለሆነም የክርስቲያን ወገን በመፈለግ የፖርቹጋል መንግሥት እንዲረዳቸው ጥያቄ ላኩበት። ግን ጥያቄው ደርሶ ጦሩ እስኪመጣ ድረስ ሰድስት ዓመት ፈጀ። በዚያን መሃል እጣቸው ተሸንፈው እና ወደ ሰሜን ግዛታቸው አፈግፍገው በኋላም ደብረ ዳሞ ገዳም ገብተው ሲኖሩ ሞቱ።

---

* የሩስያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከቁስጥንጥኒያው ቤተ ክርስቲያን መለያየቷን በ1996 አስታወቀች። ግን ይህ የሺ ዘመን አንድነትን ያፈረሰው ልዩነት በእምነት ልዩነት ሳይሆን በፖለቲካ ምክንያት ነው።

ልጃቸው አጼ ገላውዴዎስ በ18 ዓመታቸው ከእናታቸው ጋር በመተጋገዝ ሲዋጉ የፖርቹጋል ወታደሮች ደርሰውላቸው በ1541 ዓ.ም ግራኝን አሸንፈው አባረሩ። የፖርቹጋል ወታደሮች ካቶሊካዊ ስለነበሩ የካቶሊክ ሚሲዮኖች ጥቂቶቹ አብረዋቸው መጥተው በኋላም ሌሎቹ ተጨምረው ወደ አገር ውስጥ ገብተው ያስተምሩ ጀመር። እነዚህ ሚሲዮኖች እየሱሳውያን (ጂዙትስ) ይባላሉ።

እየሱሳዊያኑ እምነቱን ማስፋፋት ጀመሩ። እንዲያውም ከድል በኋላ ይህ መንግሥት ካቶሊካዊ እንዲሆን ውል አለን በማለት እምነቱ ብሔራዊ እንዲደረግ ጠየቁ። ይህ በወቅቱ ተቀባይነት ቢያጣም በስተኋላ የነገሰው አጼ ሱስንዮስ ከሮማ ጳጳስ ተሹሞ በተላከው የስፓኝ ተወላጅ አቡነ አልፎንስ ሜንዲዝ ትጋትና ብርታት የካቶሊክን ሃይማኖት አምኖ ተጠመቀ። ከዚያም በኋላ ሕዝቡ እንዲቀበለው በአዋጅ ታዘዘ። በዓላት ሁሉ እንዲለወጡ ካህናት እንደገና እንዲጠመቁ ግዴታ ሆነ። በንጉሡ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መሰረት ይህ ታላቅ የአውሮፓ ሃይል ብዙ ድጋፍ እንደሚሰጥና የስልጣኔ በር እንደሚከፍት አምነው ነበረ ተብሎ ይገመታል።

ነገር ግን እንዳሰቡት ሳይሆን ቀረ። ሕዝቡ በተቃውሞ ተነሣ የጳጳስ ግዝትም አላገደውም። "ለሃይማኖታችን እንሞታለን" በማለት ተነሳ። ነገር ግን የንጉሡንና የጳጳሱን ሃይልና ትጥቅ ሊመክቱ አልቻሉም። ስለ ሆነም በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ኦርቶዶክስ ምዕመናን አለቁ። ተጨፈጨፉ። የቀሩት ተሰደዱ። አገሪቱ ተበጠበጠች።

በዚህ የከፋ ብጥብጥ የተነሣ አጼ ሱስንዮስ ስልጣናቸውን ለቀቁ። "ፋሲል ይንገስ ሃይማኖት ይመለስ" የሚል አዋጅ አሳውጀው በትረ መንግሥቱን ለልጃቸው ለቀቁ። አጼ ፋሲልም እየሱሳውያንን በ1632 ዓ.ም ከአገር አስወጥተው ሰላምን አሰፈኑ።

እርግጥ የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በኋላም ቢሆን ጥረቱን አላቋረጠችም። በየጊዜው ሚሲዮኖች ለመግባትና ለማስ ተማር ሙከራ ያደርጋሉ። ነገር ግን ሕዝቡ ስላልረሳው ሚሲዮ ናውያኑ "በተያዙ ቁጥር" በድንጋይ መወገርና በሞት መቀጣት ይደርስባቸው ነበረ። ከዚህ የተነሣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሃይማኖት መለወጥን በተመለከተ አንድ ሰው "ሰለመ" ከሚባል ይልቅ "ኮተለከ" ቢባል በአንዳንድ ኦርቶዶክስ ምዕመናን ዘንድ እንደ ከባድ ክህደት ተደርጎ ይወሰድ ነበር።

ይህ የእርስ በርስ ጠርነት መነሻ በመሆን ከዚያ በኋላ ኢትዮ ጵያውያን እርስ በርሳቸው ባለመተማመናቸው የተነሣ አገሪቱ ወደ አስከፊው የመሣፍንት ዘመን የዘቀጠችበት እና ያላሰለሰ የእርስ በርስ ብጥብጥ እና ዕልቂት የነገሠበት፣ የአክሱም መንግሥት ስልጣኔ ደብዛው የጠፋበት የጭለማ ዘመን ውስጥ እንደገባች ይታወቃል።

ከዚህ በኋላ አጼ ቴዎድሮስ መሳፍንቱን በሃይል ካስታገሱ በኋላ ሰላምንና አንድነትን ወደ ማምጣት ተቃረቡ። በዚህም ጊዜ የሮማ

ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሌላ ሙከራ በማድረግ ሚሲዮ ኖች ላከች። ከነዚህ መሃል የታወቀው አባ ያዕቆብ የተባለ ሚሲ ዮናዊ ሲሆን እሱም ትልቅ አስተዋጸኦ አድርጓል። በአካባቢው ሕዝብ ቋንቋ ማለትም በአማርኛ በማስተማር የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን ባለመጋፋትና የሕዝቡን ባህልም አክብሮ በመያዝ እንደማንኛውም የአካባቢው ቄስ በድህነት እየኖረ አስተምሯል። በርካታ ተከታዮችንም አፍርቷል። ይህም እስከ 12,000 ምዕ መናን ሊደርስ እንደቻለ ተዘግቧል በስተኋላ ግን ለምዕመናኑ መንፈሳዊ አመራር ለመስጠት እንዲያስችል በማሰብ የሮማ ቤተ ክርስቲያን ለቄሱ የጵጵስና ማዕረግ በመስጠት በሰየመችው ጊዜ ይህ ሰበካ እዚህ ደረጃ መድረሱን መንግሥት ሲያይ ብርቱ ተቃ ውሞና ችግር ገጠመው ሆኖም አቡነ ያዕቆብ የመጀመሪያው የካቶ ሊካዊ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ በኢትዮጵያ መሆናቸው ነው።

የጣሊያን ወረራ በመጣበት ዘመን ደግሞ የካቶሊክ እምነት ሌላ ምዕራፍ ተከፈተለት። ሚሲዮኖች መግባት ጀምሩ፣ቤተ ክርስቲያ ናትም ተስፋ ሃይማኖቱም በሰፊው መታወቅ ጀመረ። ነገር ግን እንደገና "የእየሱስ አካላዊ ባህርይ አንድ ነው ወይስ ሁለት ነው?" በሚል ክርክር አለመግባባት ተከስቶ እየሱሳውያን ከአገር እንዲወጡ ተደርገው ነበረ።

ዛሬ ግን ሃይማኖቱ ሰፊ ተቀባይነት አግኝቷል። ትምህርት ቤቶችንም (እስከ 2ኛ ደረጃ ድረስ) በመክፈትና በማስተማር፣ የተጎዱ ወገኖችንም በመርዳት ትልቅ አስተዋጽኦ እያደረገ ነው።

የቤተ ክርስቲያን ቅርጽና ሥነ ሥርዓት

ሀ- ቅርጽ

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከኦርቶዶክሱ ቤተ ክርስቲያን በጣም ይለያል። የውስጥና የውጭ ክፍል የሚባሉ የሉትም። ሁሉም ክንውን በግልጽ ፊት ለፊት የሚታይ ነው። በአዳራሹ ግራና ቀኝ መቀመጫዎች ይኖሩና በመካከል ቀጥ ብሎ ወደፊት የሚቀጥል መተላለፊያ መንገድ ይኖራል። በስተመጨረሻው ከፍ ብሎ መሰ ዋዕ የሚታይበት መድረክ ይኖራል። ይህም ግራና ቀኝ ጥቂት መቀመጫዎች ሊኖረው ይችላል። መስዋዕ የሆነው አግድም የተዘረጋ ቀጭን ረዥም ጠረጴዛ ነው። እንደ ጥንቱ እምነት ከነ በረ መስዋዕት የሚቃጠለው ወይም የሚቀርበው በዚህ ላይ ነበረ። አሁን ግን እየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጅ ሃጢያት ሲል ራሱን መስዋዕት ስላደረገ ሌላ መስዋዕት ማቅረብ አስፈላጊ አልሆነም።

አሁን የሚያሰፈልገው በክርስቶስ አምኖ ስለሃጢያታችን ተጸጽቶ እና በደልን ይቅር ብሎ ቁርባን መውሰድ ነው። ከመስዋዕ በስተኋላ ህብስት ይኖራል። ይህ ህብስት ከተቻለ በወርቅማ ነገር ከተሰራ ዕቃ ውስጥ ተደርጎ በቁልፍ በተቆለፈ ጠንካራ ሳጥን ውስጥ የተቀመጠ ነው። ሳጥኑ በመስቀል

ቅርጽ ተሰርቶ ፊት ለፊት በተሰቀለ ካቢኔት ውስጥም ሊሆን ይችላል። ይህ በአግባቡ ከተባረከ የጌታችን የእየሱስ ክርስቶስ ስጋ ወደመሆን ይቀየራል። ስለዚህ ያንን አጠናቆ የበላ "ስጋዬን የበላ የዘላለም ሕይወት ያገኛል"። በሚለው ቃል ኪዳን መሰረት እንደሚፈጸምለት ይታመናል። የጌታን ስጋ በዚያ መኖር ለማብሰር ሻማ ወይም ሌላ መብራት በቦታው ላይ ሊበራ ይችላል። ከበላዩም የክርስቶስ ስቅለት መስቀል በጉልህ እንዲታይ ይደረጋል። እንግዲህ በቁርባን ስነ ስርዓት ጊዜ ቄሱ የደንብ ልብሱን ለብሶ በታላቅ ስነ ስርአት እና ጸሎት ቀርቦ ህብስቱን አንስቶ እና ባርኮ ሲበላ ቆረበ ማለት ነው። ወይን አብሮ ስለሚኖር ይህንንም ከተቀበለ ስጋ ወደሙ ተቀበለ ያሰኛል።

ወደ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሲገባ ሁልጊዜ በሩ ላይ ውሃ ይኖራል ይህ ሲባረክ የተቀደሰ ስለሚሆን ምዕመናን ሲገቡ ያንን ጠበል በእጃቸው አጥቅሰው ያማትባሉ (ከግንባራቸው ላይ በመጀመር በደረታቸው ላይ የመስቀል ምልክት ይሰራሉ)። ቤተክርስቲያን ውስጥ በግራና በቀኝ ጎኖች ሰባት ሰባት ስዕሎች ወይም ቅርጾች ይኖራሉ። እነዚህ 14ቱ እየሱስ ክርስቶስ ከጲላጦስ ቤት እስከስቅለቱ ቦታ ድረስ መስቀሉን ተሸክሞ የተጓዘውን ጉዞ በ14 ምዕራፍ የሚገልጹ ናቸው።

አስራ አራቱን ምዕራፎች የሚገልጹት ስዕሎች የሚያመለክቱት የሚከተሉትን ነው።

1- እየሱስ የሞት ፍርድ እንደተፈረደበት
2- እየሱስ መስቀሉን ለመሸከም ሲቀበል
3- እየሱስ መስቀሉን እንደተሸከመ ሲወድቅ
4- እየሱስ ከቅድስት እናቱ ጋር ሲገናኝ
5- ቀሬናዊው ስምኦን እየሱስን ሲረዳ
6- ቬሮኒካ የተባለች ሴት የእየሱስን ፊት ስትጠርግለት
7- እየሱስ ለሁለተኛ ጊዜ ሲወድቅ
8- እየሱስ የእየሩሳሌምን ሴቶች ሲመክር
9- እየሱስ ለሶስተኛ ጊዜ ወደቀ
10- እየሱስን ልብሶቹን ሲገፉት
11- እየሱስ በመስቀል ላይ ተቸነከረ
12- እየሱስ ሞተ
13- እየሱስን ከመስቀል አውርደው ለእናቱ ሰጧት
14- እየሱስ ተቀበረ

ምዕመናን ይህንን የእየሱስን ጉዞ አብረው እንደሚጓዙ በማሰብ በየምዕራፉ (በየስዕሉ) ቆም እያሉ ጸሎት ያደርሳሉ። (በተለይ በ 40 ቀን የጾም ወቅት እና ዓርብ በየሳምንቱ)

ለ- ስርዓት ቅዳሴ

እዚህ ላይ አብዛኛውን ጊዜ የሚካሄደውን ስርዓተ ቅዳሴና የሐዋርያት የቁርባን ጸሎት (አኮቴተ ቁርባን የሃዋሪያት) እንከታተላለን።

የቅዳሴ ስነ ስርዓት እሰኪ ጀመር ድረስ ጸሎት ከዳዊት መዝሙሮች ይወሰዳል። መሪ ካህኑም ከመቅደስ ሆኖ ስነ ሥርዓ ቱን ይመራል ይቆጣጠራል።

ከጸሎት በኋላ ሀብስቱንና ወይኑን በመንበሩ (መስዋዕ) ላይ ያዘ ጋጃል። ቀጥሎም ከምዕመናን ጋር በመቀባበል የምስጋና ጸሎት ያደርሳሉ። ከጸሎቶቹም መካከል የሚከተለው ይገኝበታል።

ካህን "አንዱ አብ ቅዱስ ነው አንዱ ወልድ ቅዱስ ነው አንዱ መንፈስ ቅዱስ ቅዱስ ነው"። ሕዝቡ "በእውነት አብ ቅዱስ ነው፣ በእውነት ወልድ ቅዱስ ነው፣ በእውነት መንፈስ ቅዱስ ቅዱስ ነው።" ሌሎች ካህኑ ለሚላቸውም ህዝቡ "አሜን" በማለት ይመልሣል።

ከዚያም ሀብስቱና ጽዋው በስርዓቱ ከለበሰ (ከተሸፈነ) በኋላ ዲያቆኑ በምልጃ ጸሎት ይመራል። ይህም ሰላሳ አካባቢ የሚሆን የምልጃ ጸሎት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የሚያቅፍ ይሆናል። ለምሣሌ ርዕሰ ልቃነ ጳጳሳት እና ጳጳሳት (በስም እየተጠቀሱ) ካህናት፣ ዲያቆናት፣ ባልቴቶች፣ ደናግል፣ ሕዝበ ክርስቲያን፣ መኳንንት፣ ባለሥልጣናት፣ መንገደኞች፣ ሃዘነተኞች፣ ረሃብተኞች እስረኞች፣ ሕመምተኞች፣. . . ወዘተ ሁሉ ይጸለይላቸዋል። ስግደትም ሊኖር ይችላል።

ምዕመናን ተቀምጠው የመጽሀፍ ቅዱስ ንባብ (አግባብ የሆነው ተመርጠ) ይነበባል። በመጨረሻም የእየሱስ ክርስቶስ ዜና ቅዱስ ወንጌል ይደመጣል። ጸሎተሃይማኖትም ይደገማል።

ካህኑ ቁርባኑን ለማቅረብ ሲዘጋጅ ንስሃ ግቡ በማለት እጁን ይታጠባል። ካህናቱም ሕዝቡም ስለሰላምና ፍቅር ጸልየው ቅዱስ ሰላምታ ይሰጣሉ።

ከዚያም ለዕለቱ አግባብ ያለው የቁርባን ጸሎት (የሐዋሪያት፣ የእየሱስ ክርስቶስ የቅዱስ ጎርጎርዮስ . . .) ተመርጠ ይወሰዳል። የዘወትር የቁርባን ጸሎት ግን የሐዋሪያቱ ነው። በዚህም ካህኑ ዲያቆኑና ሕዝቡም ምስጋና ያቀርባሉ። ሞትና ትንሣኤውን በማሰብ ሀብስቱንና ጽዋውን የእየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም እንዲያደርገው እነሱንም ለቁርባን ብቁ እንዲያደርጋቸው ይጸልያሉ።

የቅዱስ ባስልዮስ የንስሃ ጸሎትም ይጸለያል። ካህናትና ሕዝቡ እየተቀባበሉ በዜማ 12 12 ጊዜ እግዚኦ ማህረነ ክርስቶስ ይላሉ። ንስሃ ጸሎቱ ይቀጥላል።

ከዚያም ካህኑ ለራሱ ከቆረበ በኋላ (ሀብስቱን ቀጥሎም ወይኑን በመቀበል ለምዕመናን ቁርባን ያቀርባል። ሲያቀብልም ሀብስቱን ወይኑ ውስጥ በመንከር (በማጥቀስ) በየአፋቸው ማቀበል ነው። ሕዝቡም

ሕጻናትንና ልጆችን በማስቀደም ወንዱም ሴቱም እኩል በመሰለፍ በስነ ስርዓት ይቀበላሉ።

ካህኑ ሲያቆርብ "የክርስቶስ ቅዱስ ስጋና ክቡር ደም" ሲል፣ ቆራቢ "አሜን" ብሎ ይቀበላል።

በመጨረሻም ስለተሰጣቸው ጸጋ የምስጋና ጸሎት አድርሰው ካህኑ ቡሪኬ ካደረሱ በኋላ ዲያቆኑ "በሰላም ሂዱ" በማለት ምዕመናንን ያሰናብቱታል።

አዕማደ ምስጢራት

በካቶሊክ ሃይማኖት መሠረት ሰባት አዕማደ ምስጢራት አሉ። እነኝህም ከኦርቶዶክሱ ምስጢራት ጋር ተመሣሣይ ናቸው።

ምስጢረ ጥምቀት

ስጋ የለበሰ ሁሉ ሃጢያተኛ ነው ይህ ከአዳም የወረስነው ሃጢያት ነው። ስለዚህ ከዚህ የተወረሰ ሃጢያት ለመንጻት እና ከክርስቲያን ቤተሰብ ለመቀላቀል የመጀመሪያው እርምጃ መጠመቅ ነው።

አንድ ህጻን አንድ ወር ሳይሞላው በፊት ክርስትና ሊነሳ ይችላል። ግን ወንድ በ40 ቀን፣ ሴት በ80 ቀን ሊነሱም ይችላሉ። የክርስትና አባት (ወይም ለሴት ልጅ ከሆነ የክርስትና እናት) ተመርጠ ቤተ ክርስቲያን ይሄዱና ደጃፉ ላይ ባለው ውሃ ህጽኑን ያጠምቁታል። ይህም ማለት ክርስትና አባቱ ሕጻኑን ይዞት ቄሱ በሕጻኑ ራስ ላይ ሶስት ጊዜ ጠበሉን ያፈሱታል። የክርስትና ስሙንም እየጠሩ "በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅሃለሁ" ይሉታል። ከዚያም ሜሮን ወስደው ራሱ ላይ በመስቀል ቅርጽ ይቀቡታል። ከዚያም ስለ በዓሉ ክብር ስጦታ እና መስተንግዶ በወላጆች ቤት ሊደረግ ይችላል።

ምስጢረ ቁርባን

ልጆች ከሰባት ዓመት ጀምሮ ሊቆርቡ ይችላሉ። በመጀመሪያ ለጥፋታቸው ንሰሐ ይገቡና በኋላም ስጋ ወደሙን ይቀበላሉ። ይህ እንደ ኦርቶዶክስ አሰራር ተራ በተራ ወደ ቅድስት እየተጠሩ ገብተው እንደቆሙ ሳይሆን በመሰውያው አጠገብ ሄደው ከተቻለ ተንበርክከው ይቀበላሉ። ይህም በመካከላቸው ለሚገኘው እየሱስ ክርስቶስ ክብር ነው። በተረፈ ግን ለቁርባኑ የሚሰጠው ትርጉም ተመሣሣይ ነው።

ምስጢረ ንስሃ

ይህ በየሁለት ወሩ ወይንም ባነሰ ጊዜ ዘወትር መከናወን ያለበት ነው። ቄሱ ቁጭ ባሉበት ቦታ ልጁ (ምዕመኑ) ይቀርብና ይንበረከካል። አንዳንድ ጊዜ በመካከላቸው ከለላ (መጋረጃ ወይም ግድ ግዳ) ይኖርና በመስኮት (ቀዳዳ) ይገናኛሉ። ልጁ (ምዕመኑ) ቀርቦ ያማትብና ቄሱ እንዲባርከው ይጠይቃል። ሃጢያቱንም ይናዘዛል። ቄሱም አዳምጠ ለወደፊት ሁኔታው

እንዳይደገም የሚ ያስወግድበትን ዘዴ ይመክረዋል። ስለ ጥፋቱም ቅጣት ይወ ስንበታል። ይህም ለተወሰነ ጊዜ ደጋግሞ እንዲጸልይ ሊሆን ይችላል።

ከዚያም ቄሱ "በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ሃጢያትህን ይቅር ብያለሁ" በማለት ባርኮ ያሰናብተዋል።

ምስጢረ ሜሮን

ይህ ከ12 ዓመት ዕድሜ በኋላ የሚሰጥ ነው። አንድ ሰው በራሱ ፍላጎት ከልቡ አምኖበትና ትርጉሙንም ተረድቶ የእግ ዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም፣ ትዕዛዛቱን ለመቀበልና ቃሉን ለሌሎች ወገኖች ለማዳረስ አስፈላጊም ከሆነ የ"ክርስቶስ ወታደር" ሆኖ ለመታገል ሲዘጋጅ ለዚህ ተግባር የመንፈስ ቅዱስ ሃይል እንዲያድርበት የሚደረግ ስነ ስርዓት ነው።

ይህ ስነ ስርዓት በማንኛውም ቄስ የሚከናወን ሳይሆን በጳጳስ ወይም በተመሣሣይ ባለሥልጣን ነው። ሰውየው በመሠውያው አጠገብ ተንበርክኮ ይቆምና ጳጳሱ እጁን በሰውየው እራስ ላይ ያሣርፋል፤ ብሎም ይጸልይለታል። በዚህም የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ያስተላልፍለታል።

ከዚያም ግንባሩ ላይ በሜሮን የመስቀል ምልክት ይቀባዋል። ይባርከዋ ልም። በመጨረሻም ጉንጩ ላይ በትንሹ መታ መታ ያደርገዋል። ይህም የክርስቶስ ወታደር እንደመሆኑ መጠን ለከባድ ትግልና ፈተና ሊጋለጥ እንደሚችልና ዝግጁ እንዲሆን ለማስታወስ ነው።

ምስጢረ ተክሊል፣ ምስጢረ ክህነትና ምስጢረ ቅብዓ ቅዱስ

እንደ ቅደም ተከተላቸው ለጋብቻ፣ ለቅስና ሹመት እና ለደከሙ ሀሙማን የሚሰጡ ናቸው። ጋብቻን በተመለከተ የባልና ሚስት መፋታት በፍጹም አይፈቀድም። ጋብቻ አይፈርስም። በዚህ መሃልም የወሊድ ቁጥጥር በተፈጥሮዋዊ መንገድ (የኡደትን ወቅት በመጠቀም) ካልሆነ በስተቀር በመድሃኒት ወይም በሌላ መከላከያ ለመጠቀም ተገቢ አይደለም። ሕይወት ክቡር ስለሆነ በጤንነት ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ውርጃ በፍጹም አይፈ ቀድም።

የፕሮቴስታንት ሃይማኖት

የካቶሊክና የፕሮቴስታንት እምነቶች መለያየት

ምዕራብ አውሮፓ በሙሉ ካቶሊክ ነበረ። ጣሊያን፣ ጀርመን፣ እንግሊዝ፣ ስዊድን፣ ፈረንሣይ፣ ስፓኝ . . . ወዘተ በአንድ እምነት ሥር ነበሩ፤ የሮማው ጳጳስ የሁሉም መንፈሳዊ መሪ ነው። በካቶሊኮች አመለካከት አንድ ወጥ መሆን ጠቃሚ እና አስፈላጊ ነው። የሃሳብ ልዩነት ወደ መከፋፈል ስለሚያመራ አንድ መሪ ብቻ መኖሩ አመራሩን በአንድ ዓይነት ስለሚያደ ርገው አንድነትን ይጠብቃል። ይህ ባልከፋም ነበረ። ነገር ግን ሌሎች ሁኔታዎችም ነበሩ።

1- የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በላቲን ቋንቋ ብቻ ስለሆነ የሌሎች አገሮች ሕዝቦች መሳተፍ አልቻሉም። ሊገባቸውም አልቻለም። እንዲሁም ማንም ተራ ሰው መጽሀፍ ቅዱስን እንዳስመለከተው አይተረጉምም። የቀሳውስቱን አተረጓጎምና መመሪያ ብቻ መቀበል አለበት።

2- ስልጣን እየተማከለና እየበዛ ሲሄድ በከፍተኛ ሥልጣን ላይ ያሉ ቀሳውስት ተግባራቸውን በመርሣት ምድራዊ ሆኑ። ከፖለቲካ መሪዎች ጋር በመተባበርም ለአንዳንድ ቅሬታ ተጋለጡ። በሌላ በኩል ደግሞ ተራ ቄሶች ግንዛቤያቸው ዝቅተኛ እየሆነ ምዕመናኑን መምራት እየተሳናቸው ሄደ። ከዘመኑ የሳይንስ ዕድገት ጋርም ሊያጣጥሙት ቸገራቸው። ስለሆነም "መሬት ክብ ናት ትዞራለች" ብሏልና ይገደል እየተባለ ችግር መጣ። እነ ጋሊሊዮ የታሰሩትና እነ ብሩኖ የተቃጠሉት በዚሁ ጊዜ ነበር።

3- እነዚህ መነሻ ምክንያቶች ሲሆኑ ለእምነቶች መለያየት ወሳኝ የሆኑት ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ- አቡነ ሊዎ አስረኛ በሮማ የሚገኘውንና የዓለም የካቶሊክ ማዕከል የሆነውን የቅዱስ ጴጥሮስ ካቴድራልን ትልቅ አድርጎ ለማሰራት ተነሳ። ግን ገንዘብ አልነበረውም። ስለዚህ የገንዘብ ማግኛ ዘዴ አሰበ። የሚከተሉት ዘዴዎች ጥቂቶቹ ነበሩ።

1. ሃጢያተኛ ነፍስ በገሃነም (ፐርጋቶሪ) ተቃጥላ ሃጢአቷን ስትጨርስ መንግስተ ሰማያት ትገባለች። የዚህን ስቃይ ዘመን ለማሣጠር ከተፈለገ ገንዘብ በመክፈል ቤተ ክርስቲያን እንድት ጸልይለት ለማድረግ ይቻላል።

2. ቀደም ሲል የኖሩት ጻድቃን የሰሩዋቸው ደግ ስራዎች እና አገልግሎቶች ተጠራቅመው የሌሎቹን ሃጢያት ለመፈወሻ ይውላሉ (ለቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ከተከፈለ)

ለ- የመስቀልን ጦርነት ለማካሄድ ሲባል የዘመተ ሁሉ ይጸድ ቃል በማለት ጳጳሱ የደነገጉት ስርዓት ጥርጣሬ አስነሳ።

ሐ- ከካቶሊክ እምነት ያፈነገጡትን ለመቅጣት ሲባል ዘግሬት ኢንኩዚሽን የሚባል ችሎት (ፍርድ ቤት) በተለያዩ አገሮች አቋቋሞ ሰዎች ቡዳ መተተኛ ሰላቢ ይመስላሉ ወይም ናቸው ያሏቸውን ጭቁኖችንና እንዲሁም ከሀዲያንን ሁሉ እየሰበሰቡ ማቃጠል ጀመሩ። በዚህ ዓይነት በአውሮፓ ብቻ ከ100 ሺ በላይ ሕዝብ አልቋል ይባላል።

በነዚህ ምክንያቶች የተነሣ ቅሬታው እየበረከተ መጣ። ስለሆነም ጀርመናዊው ቄስ ማርቲን ሉተር የተቃዋሚዎች መሪ ሆኖ ተነሣ። ተቃዋሚ ከሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ፕሮቴስታንት የሚል ስም ተሰጣቸው።

ማርቲን ሉተር ሃይማኖቱን በሚመስለው መልኩ እንደሚከተለው አሻሽሎ ማስተማር ጀመረ።

1- የእምነት መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው። ቤተ ክርስቲያን የምትደነግገው ህግ ወይም ቄሶች የሚያወጡት የተለየ ደንብ አስገዳጅነት አይኖረውም። ማንም ምዕመን መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ ሊረዳው ይችላል። ጸሎቱንም በቀጥታ ለአምላኩ ሊያቀርብ ይችላል። አማላጅና ነፍስ አባት አያስፈልግም።

2- ጽድቅ በገንዘብ አይገዛም። ሰውን የሚያድነው እምነቱ ነው። የሰው ልጅ ሁሉ ከአዳም ጀምሮ ሃጢያተኛ ነው። ይህን ሃጢያቱን በራሱ ስራ ብቻ ሊድን ከቶ አይችልም። ስለሆነም እየሱስ ክርስቶስ ከሰማይ ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በ.ሥቀል ላይ ደሙን ዋጅቶ አስተስርዮለታል። አድኖታል። አሁን ማመን ብቻ በቂ ነው ቀሪው ከዚያ ይከተላል። በሌላ አነጋገር እምነት ከተግባር ይቀድማል ይወስናልም።

3- "ዳግም መወለድ" ያስፈልጋል (በጥምቀት)።

በእነዚህ ትምህርቶች መሠረት ገንዘብ በመመጽወት ወይም በመክፈል ጽድቅ እንደማይገኝም ታመነ። የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ስነስርዓቶች (ዜማ፣ቅዳሴ) ሁሉ ግዴታነታቸው ቀረ።

ይህ የማርቲን ሉተር አስተምሮት በሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በብርቱ ተወገዘ። ስለሆነም ሉተር ተይዞና ታስሮ እንዲቀርብና ፍርዱን እንዲቀበል በ1520 ዓ.ም ትዕዛዝ ተላለፈ። ነገር ግን የሉተር ተከታዮች ተከላከሉለት። እሱም የተቃውሞ መግለጫውን በበለጠ በማብራራት አስተምሮቱን ገፋበት። ስለሆነም ልዩነቱ እየሰፋ እና ስር እየሰደደ ሄዶ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተለይቶ በእግሩ ቆመ።*

ይህ ሁኔታ ለአገር አስተዳደር ችግር እያስከተለ መጣ። ለምሳሌ የጀርመን ግዛት አንድነት አደጋ ላይ ሊወድቅ ሆነ። በሃይማኖት ልዩነት የተነሣ ቡድኖች ለሁለት ስለተከፈሉ ጉዳዩ አሳሳቢ ሆነ። ስለዚህ ማርቲን ሉተር ከሞተ በኋላ ሁለቱን ሃይማኖቶች አቀራርቦ ለማስማማት ከፍተኛ ጥረት ተደረገ። ዝነኛውና ረዥሙ (ሲቋረጥና ሲቀጥል የቆየ) የትሪንት ጉባኤ (1545 - 1563) የዚህ ውጤት ነበረ። ለፕሮቴስታንት ሃይማኖት መነሻ የነበሩ የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር ድክመቶች ተገምግመው እንዲሻሻሉ ተደረገ። ያለ አግባብ ገንዘብ መሰብሰብና የቀሳውስት ዋልጌነት ጉቦኝነት፣ጠጪነት፣ የመሳሰሉ ሁሉ ጥብቅ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ተደረገ። ይህም ትልቅ መሻሻልን አስከተለ። በምዕመናን ዘንድም አክብሮትን አሰገኘ። ሆኖም የሚከተሉት መሰረታዊ የሆኑ የካቶሊክ እምነቶች ሊቀየሩ የሚችሉ አልነበሩም።

---

* ከማር ቲን ሉተር ቀደም ባለ ጊዜ(በአጼ ዘረዐ ያዕቆብ ዘመን) አስጢፋኖስ የተባለ ታሪካዊ ሰው በኢትዮጵያ ተነስቶ ተመሣሣይ ትምህርት ጀምሮ ነበረ። ተከታዮችም አፍርቶ ነበረ። ግን ለማርያም እና ለቅዱሳን አትስገዱ የሚለው መልዕክቱ ከባድ ተቃውሞ ስለገጠመው ከነተከታዮቹ ተገደለ።

1- የሃይማኖት መሰረት መጽሀፍ ቅዱስ ብቻ ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን አባቶች የጻፏቸው መጻህፍት ጭምር መሆኑ፣

2- መጽሀፍ ቅዱስን የሚተረጉመው ማንም ሰው እንደፈለገው እንደመሰለው ሳይሆን ቤተ ክርስቲያንና መሪዎቿ ብቻ መሆናቸው፣

3- ሰዎች ጽድቅ የሚያገኙት በእምነት ብቻ ሳይሆን በደጋግ ስራዎቻቸው ጭምር መሆኑ

4- ካህናት ሙሉ ጊዜአቸውንና ጉልበታቸውን ለእግዚአብሔር ስራና ለምዕመናን ሊያውሉ እንዲችሉ በድንግልና መኖር እንዳለባቸው፣

5- አእማደ ምስጢራት በቁጥር ሰባት መሆናቸው ናቸው።

እነዚህ እና ሌሎችም የካቶሊክ ሃይማኖት መሰረታዊ እምነቶች በምንም ዓይነት በፕሮቴስታንት አማኞች ዘንድ ተቀባይነት ሊያገኙ አልቻሉም። ስለዚህ ልዩነታቸው ጸና።

የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ይዘት

የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ራሱ በአንድ ወቅት ቢመሰረትም በተለያዩ የጎረቤት አገሮች የነበረው አመለካከት አንድ አልሆነም። የጀርመን የስዊትዘርላንድና የእንግሊዝ አመለካከት የተለያየ ሆነ። ከፊሉ በእምነት ብቻ መዳን ይቻላል ሲል ከፊሉ ደግሞ እምነት በተግባር መተርጎም አለበት አሉ። ሆኖም እምነት የሁሉም መነሻ መሰረት መሆኑ አልተካደም። በዚህ ረገድ በሁሉም ዘንድ ተወ ዳጅ ሆኖ ዘወትር የሚጠቀሰው የመጽሀፍ ቅዱስ ጥቅስ ዮሐ 3፤16 ነው። "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ህይወት እንዲኖረው እንጅ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና" ስለዚህ በእየሱስ ክርስቶስ ያመነ ይድናል ማለት ነው።

ይህንን መሰረት አድርጎ በመያዝ የፕሮቴስታንት ትኩረት እምነቱ ላይ ነው። የእምነቱም ፍሬ ዘር÷

1- በሶስቱ ስላሴዎች (በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ) ማመን፣

2- የሰው ልጅ ሁሉ በውርስም በገቢርም ሃጢያተኛ መሆኑ፣

3- እየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጅ ሲል ደሙን ያፈሰሰ ቤዛ ያደረገ መሆኑ፣

4- ጽድቅ የሚገኘው በመጀመሪያ በክርስቶስ በማመን መሆኑ ናቸው። ይህም ምህረቱ በስጠታ የተገኘ እንጂ የበጎ ስራ ዋጋ አይደለም።

በዚህ የተነሣ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሚካሄደው እጅግ የደመቀ ስነ ስርዓት አልአስፈላጊ ሆኖ ታየ። የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን በውስጡ ቅርጻ ቅርጽ አይሰቀልም። የመላዕክትና የጻድቃን ምስሎች አይታዩም።

ቀድሞ በላቲን ብቻ ይከናወን የነበረው የቅዳሴ ስነ ስርዓትም አጠር እና ቀለል ተደርጎ በየአገሩ ቋንቋ እንዲከናወን ተደርጓል። ጸምን በተመለከተ ግዴታ መሆኑ ቀርቷል። ደህንነት የሚገኘው በእየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ እንጂ በጸም አይደለም። ከአፍ የሚወጣ እንጂ ወደ ሆድ የሚገባ አያረክስም ተብሏል። ምጽዋት መስጠትም ለጽድቅ አይቆጠርም። ጽድቅ የሚገኘው በእምነት ነው። ነገር ግን ይህ ሁሉ ለውጥ ቢደረግም ሃይማኖቱ በአንድነቱ አልዘለቀም። የተለያዩ የፕሮ ቴስታንት ሃይማኖቶች የተለያዩ አመለካከቶችን ማንጸባረቃቸውም አልቀረም። እነዚህ ዛሬ ከሁለት መቶ በላይ ናቸው። በኢትዮጵያ ከታወቁት ዋና ዋናዎቹ ሃይማኖቶች በአጀማመሩ ቀዳሚነቱን ስፍራ የያዘችው መካነ እየሱስ ቤተ ክርስቲያን ናት።

መካነ የሱስ ቤተ ክርስቲያን

መካነ የሱስ ቤተ ክርስቲያን የሉተርን እምነት በመከተል የዘለቀችና ዛሬም ሉተራን በሚል መለያ የምትታወቀው ናት። በተጨማሪም ሰፊ የሐዋሪያዊ ተልዕኮ ታካሂዳለች። የመካነ የሱስ ሃይማኖት መግለጫ በአራት ክፍሎች ይመደባል። እነዚህም÷

ሀ- የሐዋሪያት የሃይማኖት መግለጫ እና የኒቂያ የሃይማኖት መግለጫ፣

ለ- የአትናቴዎስ የሃይማኖት መግለጫ፣

ሐ- ያልተለወጠው የኦግስቡርግ የሃይማኖት መግለጫ (1530 ዓ.ም)

መ- የማርቲን ሉተር ካቴክዝሞች

እነዚህን መግለጫዎች መቀበል መካነ የሱስን በአንድ መመሪያ ስር እንድትጓዝና እንዳትከፋፈል ረድቷታል። በመካነ የሱስ እምነት መሰረት የጸጋ መሳሪያ (ወይንም አእማደ ምስጢራት) የሚባሉት ሶስት ናቸው። እነዚህም÷

ሀ- የእግዚአብሔር ቃል (መጽሀፍ ቅዱስን መማር)

ለ- ጥምቀት

ሐ- ቁርባን ናቸው።

ጥምቀት ማለት እኛ ለሃጢያት መሞታችንና በጌታ እየሱስ ክርስቶስ መነሣታችንን ደህንነትን በጸጋ የተቀበልንበት ወደፊት ከሃጢአት ተጠብቀን ትክክለኛ አኗኗርን ለመኖር ጸጋ የምንቀበልበት ነው። አዋቂዎች ሲጠመቁ ክርስቶስን አምነው ተቀብለው የሚያደርጉት ሲሆን ሕጻናት ግን ለወላጆቹ ሃላፊነት በመስጠት ልጆቹ የክርስትያን ሕይወት እንዲመሩ እንዲያዘጋጇቸው ነው። ስለሆነም ክርስትና ለሕጻናትም ለአዋቂዎችም ይሰጣል። በዚህም ጊዜ የክርስትና አባትና እናት ይኖራሉ። ቄሱም በተጠማቂው እራስ ላይ ውሃ በማፍሰስ ሲያቆርብ "በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅሃለሁ" ይላል። ከዚያም ለክርስትና አባት/እናት ይሰጣል። አንድ

ጊዜ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ለተጠመቀ ሰው ወይም ሕጻን ዳግም ጥምቀት መስጠት አስፈላጊ አይሆንም።

ቅዱስ ቁርባን የጌታችን የእየሱስ ክርስቶስ ስጋ ወደሙ ነው። ስለሆነም ይህንን ጸጋ በመቀበል የጌታን ምህረት እናገኛለን። ደህንነትንም እንቀበላለን። ስለሆነም ቋሚ ቆራቢ በመሆን በየጊ ዜው (ለምሣሌ በየወሩ) ለመውሰድ ይቻላል የቁርባን ስነ ስርዓት ቀላልና ለሁሉም በሚገባው መልክ እንዲያውም ሕዝቡ ተሳትፎ በሚያደርግበት አኳኋን በአጭሩ የሚካሄድ ነው። ዝርዝሩ እንደሚከተለው ነው።

የኢትዮጵያ መካነ የሱስ ቤ/ክ የእሁድ ቅዳሴና ቅዱስ ቁርባን ስነ ስርዓት

ቤተክርስቲያኑ ከመምጣታቸው በፊት ቄሱና ረዳቶቹ በዝግጅት ክፍል ሆነው ህብስቱንና ጽዋውን አዘጋጅተው ቅደመ ዝግጅት ጸሎት አድርሰው ከዚያም በስነ ስርዓት ይገባሉ። ስነ ስርዓቱንም መምራት ይጀምራሉ።

1- ቄሱ ይላሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አንድ አምላክ አሜን፣

2- መዝሙር ከመዝሙር መጽሀፍ መርጠው ያስታውቁና በህብረት ይዘመራል፣

3- "የእግዚአብሔርን ቃል እንስማ" በማለት ከመጽሀፍ ቅዱስ ጥቅሶች ስለንሰሃ መግባት ያስተምራሉ።

4- ጸሎት ያደርሳሉ። ከሕዝቡም ጋር "ቅዱስ ቅዱስ" ይላሉ።

5- ምዕመናን ቆመው(ወይም አጎንብሰው) የሃጢያት ኑዛዜ የንስሃ ጸሎትም ይደረጋል። "ሃጢያታችንን ይቅር በለን" ለማለት።

6- ቄሱ ከተንበረከከበት ተነስቶ "እግዚአብሔር ሃጢያታችንን ይቅር እንደሚለን ቃል በገባልን መሠረት የሃጢያት ስርየት እንዳገኛችሁ አስታውቃችኋለሁ አሜን ይላሉ"።

7- "ስብሃት ይደገማል (በጋራ)። ምስጋና ለእግዚአብሔር ለማቅረብ (ስለተሰጠው ይቅርታ)። ከዚያም እንደወቅቱ የተመረጡት መዝሙሮች ይዘመራሉ። ጸሎት ይደረጋል ከሐዋሪያት መልእክት ይነበባል። መዘምራንም የዕለቱን መዝሙር ይዘምራሉ።

8- የኒቂያ የሃይማኖት መግለጫ ወይም የአትናቴዎስ የሃይማኖት መግለጫ በምዕመናን በቃል ይገለጻል።

9- ጸሎት ትምህርት መዝሙር እንደአስፈላጊነቱ ይቀርባል።

10- ቄሱ ወደ ጌታ ማዕድ ይጋብዛሉ። የቤተ ክርስቲያኒቱ ቆራቢ አባላት ወደ ጌታ ማዕድ ቅረቡ ያላሉ። ቆራቢዎች ወደ መሠዊያው

እየቀረቡ ቅዱስ ቁርባንን ይቀበላሉ። የክር ስቶስ ስጋ ደም ስለ አንተ የተሰጠ እየተባለ ይሰጣቸዋል።

11- አቡነ ዘበሰማያት ይባላል።

12- ምዕመናን ቆመው ጸልየው "ለአምላክ ስብሀት ይሁን ሃሌ ሉያ ሃሌሉያ ሃሌሉያ በማለት ይፈጽማሉ። ቄሱም እግዚአብሔር ይባርካችሁ . . . ወዘተ በማለት ቡራኬ ሰጥተው ያሰናብታሉ።

13- የግል ጸሎት ያለው ወደ ኋላ ቀረት ብሎ ሊፈጽም ይችላል።

መካነ እየሱስ ሃይማኖትን ከሌሎች አብዛኞቹ የፕሮቴስታንት ሃይማኖቶች የሚለየው ቅዱስ ጥምቀት በጸጋ የደህንነት መቀበያ መንገድ ነው በማለትና ቁርባንም ለመታ ነቢያነት ብቻ ሳይሆን ለጽድቅም የሚቆጠር ጸጋ ነው በማለታቸው ነው። ቅዱስ ቁርባን የሚያቀርበውም ልብሰተክህኖ የለበሰ ባለሙሉ ሥልጣን ቄስ እንጂ ማንም አይሆንም። እርግጥ ቄስ ባልተመደበበት አዲስ ቦታ የበታች ሹማምንት ለጊዜው ሊወከሉ ይችላሉ።

ሌሎች የመካነ የሱስ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች

በመካነ እየሱስ ሃይማኖት መሠረት የጸጋ መሣሪያዎች ሶስት ቢሆኑም ቤተ ክርስቲያን ለምዕመናን በተጨማሪ ሌሎች አገልግሎቶችንም በመስጠት ትባርካለች። ለምሣሌ÷

ሀ- <u>የእምነት ማጽኛ</u>

ቀደም ሲል ተጠምቀውና አምነው በክርስቲያን መንገድ ሕይወታቸውን የሚመሩ ሰዎች ለቀና መንገዳቸው በአባላት ከተመሠከረላቸው እምነታቸው እንደጸና እንዲዘልቅ ይባረካሉ። ከዚያም ቆራቢ አባል ይሆናሉ።

ለ- <u>የግል ኑዛዜ</u>

ይህ ግለሰቦች የፈጸሙትን ሃጢያት ተናግረው ንስሃ የሚገቡበት ነው። ኑዛዜው የሚገለጸው ለቄስ ወይም ሃላፊነት ላለበት የቤተ ክርስቲያን አባል ሲሆን በምስጢር የሚያዝ ይሆናል። ኑዛዜውን የሰማው አካልም ግለሰቡ በእየሱስ ክርስቶስ የሃጢያት ስርየት ማግኘቱን ያስታውቃል። ዳግም እንዳይሳሳትም ምክር ይሰጠዋል።

ሐ- <u>የጋብቻ ስነ ስርዓት የቅስና ስነስርዓት፣ የምረቃና የፍታት ስነ ስርዓቶች</u> እነዚህ ለቆራቢ አባላት ይፈጸማሉ።

መካነ የሱስ በኢትዮጵያ

ዛሬ መካነ የሱስ በሚል የኢትዮጵያዊነት ስያሜ ዳብሮና ጎልብቶ የሚገኘው ሃይማኖት መሠረቱ የሉተራን እምነት ሲሆን ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አገሪቱ ገባ ተብሎ የሚገመተው በ1829 ዓ.ም ሳሙዔል ጎባት እና ክርስቲያን ኩግለር የተባሉ የጀርመን ዜጎች በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ድጋፍ ሰጪነት ወደ ጎንደር ሲላኩ ነው።

ይህ ዘመን በኢትዮጵያ ግጭትና ጦርነት የበዛበት ዘመነ-መሳፍንት በመባል የሚታወቀው ጊዜ ቢሆንም በአውሮፓ ግን ሰላም ሰፍኖ ሃይማኖታዊ ድርጅቶች የክርስቶስን ትምህርት ላልደረሳቸው ለማዳረስ ሰፊ እንቅስቃሴ የጀመሩበት ዘመን ነው።

በእንግሊዝ አገር በ1799 ዓ.ም ተቋቁሞ የነበረው የቤተ ክርስቲያን ሚሲዮናዊ ማህበር (ቸርች፣ሚሽነሪ፣ሶሳይቲ) በመሰረቱ ኤኢስ ቆጵስ (አንግሊካን) ነበረ። ወዲያው በ1804 ዓ.ም "የእንግሊዝና የውጭ አገር የመጽሀፍ ቅዱስ ማህበር" የተሰኘ ድርጅት ሲቋቋም የዚህ ድርጅት ዓላማ መጽሀፍ ቅዱስን በቀላል ወጪ በብዛት አሳትሞ እና በተለያዩ ቋንቋዎች ተርጉሞ ለዓለም ለማዳረስ ስለነበረ ሁለቱ ድርጅቶች ተባብረው እነሣሙኤል ጎባትን መልምለው ወደ ኢትዮጵያ ላኩ።

ሳሙኤል ጎባት ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣቱ በፊት በእስክንድሪያ (ግብጽ) ለሶስት ዓመታት ቆይታ አድርጎ አማርኛ ቋንቋን አጥንቶ ነበረ። ስለሆነም ጎንደር እንደገባ አዲስ ኪዳንን በከፊል ወደ አማርኛ ተረጎመ።

እርግጥ ከዚያ በፊት ምንም ጥረት አልተደረገም ነበር ለማለት አይደለም። አባ አብርሃም የተባሉ የጎጃም መነኩሴ መካከለኛውን ምስራቅ ተዘዋውረው የጎበኙ እና ጣልያንኛ፣ ግሪክ፣ ፐርሺያንኛ፣ እና ሌሎችንም ቋንቋዎች የሚናገሩ ሊቅ ስለነበሩ መጽሀፍ ቅዱስን በአስር ዓመት ጥረት ተርጉመው (1818) ለህትመትም አብቅተው ነበረ (1840)። በዚህ መሃል ወንጌል (በ1824) እና አዲስ ኪዳን በአጠቃላይ (በ1829) ተዘጋጅተው ቀርበው ነበረ። እንዲያውም ቀደም ሲል ሄይሊንግ የተባለ ጀርመናዊ ምሁር በ1647 ዓ.ማ የዮሐንስ ወንጌልን በከፊል ወደ አማርኛ ተርጉሞ እንደነበረ ተዘግቧል።

ቀዳሚ ሚሲዮናዊያኑ እና ተከታዮቻቸው ይህ እንደ ጥሩ መነሻ ቢያገለግላቸውም በ1856 ዓ.ም አካባቢ ድርጅታቸው አስራ ስምንት ግመል ጭነት ቅዱሳት መጻህፍትን በማስመጣትና ከህንድም በምጽዋ ወደብ ብዙ መቶ መጽህፍትን በማስገባት የክርስቶስ ቃል በሰፊው እንዲዳረስ አስደርጓል።

አጼ ቴዎድሮስም ሚሲዮናውያንን ተቀብለው በመልካም ሁኔታ ይዘዋቸው ነበረ። እንዲያውም አብረው ያስቀድሱ እንደነበረ ይነገራል። ፈረንጆች የፅደ ጥበብ ሥራ እንደሚችሉና ሕዝቡንም በመድሃኒትና በትምህርት ሊረዱ እንደሚችሉ ተስፋ በማድረግ አጼ ቴዎድሮስ ከሚሲዮኖች ብዙ ይጠብቁ ነበረ። ስለሆነም በአንድ ወቅት ሰብስበው ጋፋት ላይ መድፍ እንዲሰሩ አስደርገዋቸዋል።

በዚሁ ወቅት ሌሎች ሚሲዮናውያን በምጽዋ በኩል ገብተው በአካባቢውና በሰሜን አቅጣጫ ያሉትን ክልሎች ለማጥመቅ ጥረት አድርገዋል። እነዚህም የስዊድን ሚሲዮናውያን ሲሆኑ ጊዜውም በ1866 ዓ.ም ነበረ። አመጣጣቸውም ወደ ኦሮሞ ክልል ለመዝለቅ የነበረ ቢሆንም በቀላሉ ሊሳካላቸው አልቻለም።

ምክንያቱም በወቅቱ በአካባቢው የነበረው ሃይማኖት ኦርቶ ዶክስ ክርስቲያን በመሆኑ ነገሥታቱ (ለምሥሌ የሸዋ ንጉሥ አጼ ሳህለስላሴ) ሌላ የክርስትያን ሃይማኖት ደግሞ ማስተማሩን አልወደዱትም። በኋላም ቢሆን አጼ ምኒልክ ለምሣሌ "ማርያም አታማልድም" የሚለውን ትምህርት ባለመቀበላቸው ሙሉ ትብብር ሊሰጡ አልፈለጉም። ሆኖም የስዊድን ሚሲዮኖች በዚያው ጠረፍ አካባቢ ትምህርት ቤት ከፍተው ማስተማር ጀምረው ስለነበረ ይህ ጥረታቸው አንድ ጉልህ ውጤት አስገኘ። በትምህርቱ ዘልቀው ሊጠመቁ ከቻሉት ተማሪዎች መካከል የመጀ መሪያው "ሂካ" የተባለ ከወለጋ በባርነት ተፈናቅሎ የተወሰደ ልጅ ነበረ። ይህ የኦሮሞ ተወላጅ የክርስትና ስሙ ኦኒሲሞስ ተባለ። (ፊል፣11 ይመልከቱ) እሱም ወደ ስዊድን ተልኮ በበለጠ ከተማረ በኋላ በ1897 ዓ.ም መጽሀፍ ቅዱስን ወደ ኦሮምኛ ተረጎመ። ይህ የሶስት ዓመት ድካሙ ውጤት አግኝቶ በ1899 ዓ.ም በስዊዘ ርላንድ አገር ታተመ። እሱ እና ባልደረቦቹ በዚህ በመጠቀም ወደ ወለጋ ሄደው በነጆና በነቀምት አካባቢ እየተዘዋወሩ አስ ተማሩ።

በወለጋ አካባቢ ብዙ ስራ የሰሩት ግን የስዊድንና የጀርመን ቤተ ክርስቲያን ሚሲዮናውያን ናቸው። የኢትዮጵያ መሪዎች ከፈረንጆቹ በይበልጥ የሚፈልጉት ዕደ ጥበብ ዕውቀትና ህክምና መሆኑን በማስተዋል ጀርመኖቹ ሚሲዮናውያኑን በዚሁ መስመር አሰልጥነው ላኳቸው። ስለዚህ በንጉሥ ፈቃድ ወደ ወለጋ አልፈው ላሎ አይራ ወረዳ ውስጥ የመጀመሪያ ውን ሆስፒታልና ትምህርት ቤት ከፈቱ። ከዚያ ወዲህ በነቀምት በግምቢ እና በነጆ የተቋቋሙት ትምህርት ቤቶች ለአያሌ ምሁራን መፍለቅ መሰረት ሆነዋል። ለአገሪቱ ዕድገትም ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

ሃይማኖቱ በሰሜን ኢትዮጵያ እንዲሁም በወለጋ አካባቢ ከተስፋፋ በኋላ በአዲስ አበባም እንዲቋቋም ስለተፈቀደ ስደርኩ ይስት የተባለው ስዊድናዊ ቄስ በ1913 ዓ.ም ቦታ ገዝቶ ቤት ሰርቶ እያስተማረ ተቀመጠ። ይህ ቦታ ዛሬ በአዲስ አበባ መካነየሱስ ቤተ ክርስቲያን የቆመበት ቦታ ነው። የሰደርኩይስት አስተምሮትም የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን ብዙም የማይጋፋ ስለነበረ ዘለቄታ አገኘ። በ1921 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ሶስት ሙስሊሞች አምነው ሲጠመቁ አራት ኦርቶዶክሳውያን ተረጋገጡ። (ኮንፈርሜሽን ተቀበሉ) እነዚህ የመጀመሪያዎቹ የሃይማኖት ተከታዮች መሆናቸው ነው። ይህ ሥርዓት ወድያው በወለጋ ነጆ እናቦጂ በሌሎችም አካባቢዎች ቀጠለ።

በኋላም በተለያየ ቦታ የተተከሉት ቤተ ክርስቲያኖች አንድ የወል መጠሪያ ስላስፈለጋቸው "መካነየሱስ" የሚል ስያሜ አገኙ። ስሙን መጀመሪያ ያወጡት ቄስ ባድማ ያለው ነበሩ። ቄስ ባድማ ቀደም ሲል በወለጋ ቦጂ ከተማ ያገለግሉ የነበሩ ኦርቶዶክሳዊ ቄስ ነበሩ። በኋላ ግን ትምህርቱን ወስደው አመኑና ተቀበሉ። ከዚያም ወደ ጎጃም ተሻግረው ሲሰሩበት ከቆዩ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው ማስተማር ጀመሩ። ቤተ ክርስቲያንዋ አሁን ባለችበት ቦታ በ1951 ዓ.ም ስትመሰረት ስሟን መካነ እየሱስ ብለው የሰየሙ እሳቸው ነበሩ። የመጀመሪያዋ መሪም

ነበሩ። መካነ የሱስ የሚለው ስም ለሌሎችም ተመሳሳይ ቤተ ክርስቲያናት የወል መጠሪያ እንዲሆን በ1958 ዓ/ም በተካሄደው ጉባዔ ተወሰነ።

ዛሬ መካነ እየሱስ ቤተ ክርስቲያን ከአንድ ሚሊዮን ተኩል በላይ ተመዝግበው የሚታወቁ አባላት አሏት ። ዕድገቷም እየቀጠለ የሚሄድ ነው።

የፕሮቴስታንት ሃይማኖት አከፋፈል

ሁሉም ምዕመናን በየግላቸው መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ ለመገ ንዘብ ሃላፊነትም መብትም አላቸው። ስለዚህ የግድ ሁሉም አንድ ዓይነት አመለካከት እንዲኖራቸው አስገዳጅ ሁኔታ የለም። እርግጥ መካነየሱስ የሃይማኖት መግለጫ ስላላት በአንድ መንገድ እንድትሄድ አስችሏታል። ሌሎች ግን መጽሀፍ ቅዱስን ብቻ በመውሰድ በየግሳቸው የተለያየ አመለካከት ላይ ሊደርሱ ችለዋል። ማርቲን ሉተር እምነቱን ባወጀ ጊዜ ሌሎችም የየራሣ ቸውን አመለካከት እንዳዳበሩ ቀደም ሲል ተጠቅሷል። ለምሣሌ በስዊዘርላንድ እና በኋላም በስኮትላንድ የተደራጀው የፕሬሲቢቴሪያ እምነት ከሉተራን እምነት በመጠኑ ለየት ያለ ሆነ። እንደሚታወቀው የሉተር ቅድሚያ ትኩረት የነበረው የሮማ ቤተ ክርስቲያን የበላይ ጥርነት እንዲያከትምና እያንዳንዷ አገር በራሷ ቤተ ክርስቲያን እንድትተዳደር፤ በላቲን ቋንቋ የመጠቀም ግዴታም ቀርቶ ሁሉም በሚገባው በራሱ ቋንቋ ሊጠቀም እንዲችል ነበረ። እንዲሁም በወቅቱ የነበሩ አንዳንድ ከመጽሀፍ ቅዱስ ውጭ የተደነገጉ ህጎች እንዲሰረዙ ነበረ።

ከዚህ ከረር ያለ አቋም የያዙ የፕሬሲቢቴሪያ አማኞች የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን መተው ብቻ ሳይሆን ማደስ እና መቀየር አለብን ሲሉ ተነሱ። እንደ ሉተር "በእምነት ብቻ ይዳናል" የሚለውንም በማሻሻል እምነት ከተግባር ጋር ካልተዋሃደ በስተቀር ብቻውን አይጠቅምም። ሀብረተሰቡ ንም ሆነ በመጨረሻም አምላክን የሚያስደስተው በህጉ መሠረት መኖርና ትዕዛዙን መጠበቅ እንዲሁም የሰው ልጅን መርዳት ነው በማለት አስተ ማሩ። በተጨማሪም በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የሥልጣን ተዋረድ መዋቅር መኖር እንዳለበት ወሰኑ። ፕሬሲቢተር ማለት ትርጉሙ አበው ወይም መምህር ማለት ሲሆን ቤተ ክርስቲያን በአበው መመራት አለባት ለማለት ነው። ይህን ሃይማኖት የመሠረተው ካልቪን ይባላል።

ከእነኝህ ሁለቱ እምነቶች ለየት ያለው ሌላው የኤጲስ ቆጶስ ሃይማኖት (አንግሊካን) ከእንግሊዝ አገር የመነጨ ነው። የእንግሊዝ ንጉሥ ሄንሪ 8ኛ ከሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ለመለየት አላመነታም። ዱሮውንም ቢሆን የግል ጥል የነበረው ንጉሥ ሄንሪ ሚስቶች ማግባት ይወድ ስለነበረ ስድስት ገደማ ሚስቶች ነበሩት። የሮማው ጳጳስ ግን ይህንን ድርጊት ካለማጽደቃቸውም በላይ አወገዙት። ስለዚህ ንጉሡ ተገቢውን ዓመታዊ ግብር ላለመክፈልም ይፈልግ ነበረ። አሁን የአገሪቱ ርዕሰ ጳጳሳት ሲሞት ሌላው የሚቀባው በሮማው ጳጳስ መሆን ነበረበት። ንጉሡ ግን በራሱ

ሥልጣን ክራንመር የተባለውን ሾሞ የእንግሊዝ ምክር ቤትም ይህንኑ ምርጫውን አጸደቀለት (በ1533 ዓ.ም)። ምክር ቤቱም ሆነ ሕዝቡ የፕሮቴስታንትን እምነት ይገነዘባሉ። ግን ሙሉ በሙሉ አልተ ስማሙበትም። ለምሣሌ በአንድ በኩል በምዕመናን ሙሉ የነጻነት እምነትና የግል አመለካከት መብት ሲያምኑ በሌላ በኩል ደግሞ ርዕሰ ሊቀ ጳጳስ መኖር እንዳለበትና ሌሎች የበታች ሹማምንትም (እጨጌ፣ርዕሰ ደብር፣ቄስ፣ዲያቆን) በተዋረድ እየተሾሙ በሃላፊነት ቦታ ላይ እንዲመደቡ አስፈላጊ መሆኑን፤ በዚህም አሰራር ሃይማኖቱ አንድ ወጥ ሆኖ እንዲጠበቅ አስፈላጊ መሆኑን ይቀበላሉ። ይህ ሁለተኛው ሃሳብ በሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አሰራር መሰረት መሆኑ ነው። በዚህ የተነሣ የእንግሊዙ አዲሱ ሃይማኖት "መሃል መንገደኛ" ዓይነት ሆነ። እንደ ካቶሊክ በጳጳሱ እና በቤተ ክርስቲያኒቷ ሙሉ አገዛዝ ባያምንም እንደ ፕሮቴስታንት "ዘመናዊ" ሳይሆን የቅዳሴን ነባር ስርዓት የማርያምን ቅድስናና ስልጣን የመሳሰሉትን አክብሮ ያዘ።

ከዚያ ወዲህ በሌሎች ጥቃቅን ምክንያቶች የተነሣ የተለያዩ ሌሎች ሃይማኖቶች በየአገሩ ፈለቁ። ዛሬ ከሁለት መቶ ስልሳ በላይ የተለያዩ እምነቶች እንዳሉ ተዘግቧል። በዚያን ዘመን ከተጥሩት ጥቂቶቹ ለዓይነት የሚከተሉት ናቸው።

ሀ- <u>ሜቶዲስት</u>

ይህ ሃይማኖት በ1790 ዓ.ም በእንግሊዝ አገር የኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በነበሩ 14 አባላት የተመሰረተ ነው። በክርስቶስ ካመኑ ዘንድ ክስህተት መራቅ እና ራስን መቆጣጠር ተገቢ መሆኑን አሰመሩበት። ስለዚህ በተግባር ብቁ እንዲሆኑና የጻድቃን ኑሮ ለመምራት እንዲችሉ መጣር አስፈላጊ መሆኑን በማመን ለጸሎት እና ለተለያዩ ስራዎች ሁሉ ፕሮግራም አውጥተው በጥብቅ ተግባራዊ ማድረጉን መረጡ። በዚሁ መሠረት ደረጃ በደረጃ ወደ ብጽዕና ይደረሳል እንጂ በአንድ ጊዜ ተነስቶ ፃድቅ ለመሆን አይቻልም አሉ። ስለሆነም ስራቸውን ሁሉ በፕሮግራም መፈጸም ስለወሰኑና ስለተገበሩ ፕሮግራም አጥባቂዎች (ሜቶዲስት) ተባሉ። በአጭሩ የሜቶዲስት እምነት ከእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ጋር ተቀራራቢ ሲሆን ትኩረታቸው ግን "ቃሉን ሰምቶ ማመን ብቻ ሳይሆን በሚሲዮናዊ ስራ እና በአገልግሎት በተግባር መተርጎም ይገባል" በሚለው ላይ ነው።

ለ- <u>ማህበርተኞች (ኮንግሬጌሽናሊስትስ)</u>

የክርስቲያኖች ማዕከል ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሊሆን አይችልም። እየሱስ ክርስቶስ እንደተናገረው ሁለት ወይም ሶስት ወይም ከዚያ በላይ ከሆናችሁ እኔ በመካከላችሁ እሻለሁ (ማቴ፣ 18÷20) ባለው መሠረት ከሁለት በላይ እውነተኛ አማኞች ከተሰበሰብን የትም ቢሆን ጌታ እየሱስ ክርስቶስ በመካከላችን አለ። ብለው የሚያምኑ ናቸው። ስለሆነም ባለሥልጣኑ ቄስ ወይም ጳጳስ ሳይሆን ይኸው ጉባኤ ነው ይላሉ።

በዚህ የተነሣ የምዕመናኑ ጉባኤ እሱን ለሚመለከት ጉዳይ ሁሉ የበላይ ትዕዛዝን ሳይጠብቅ ራሱ የመወሰንና የመተግበር ሙሉ ሥልጣን አለው።

ሐ- አጥማቂያን (ባፕቲስት)

ልጆች በሀጻንነታቸው መጠመቃቸው ትክክል አይደለም። እየሱስ ክርስቶስን አውቀውና አምነው ተምረው በገዛ ፈቃዳቸው ሲቀበሉት ብቻ ነው። መጠመቅ ያለባቸው። መጥምቁ ዮሐንስ ያጠምቅ የነበረው አስተምሮ ካሳመነ በኋላ ነው። እየሱስ ክርስ ቶስም የተጠመቀው በሰላሣ ዓመቱ ነው። ስለዚህ ማንኛውም ሰው ከመጠመቁ በፊት መማርና ማመን ክርስቶስን መቀበል አለበት። ጥምቀት ደግሞ በመረጨት አያበቃም። ተጠማቂው ሙሉ በሙሉ መነከር አለበት። ይህም ሐዋሪያው ጳውሎስ እንዳስተማረው ጥም ቀት በጌታችን ሀ/ መወለድ፣ ለ/ መቀበር እና ሐ/ ከሙታን መነሣት ጋር ስለሚመሣሰል ውሃ ውስጥ መነከርና መውጣት የጥምቀት ህግ ነው።

በተጨማሪም "ምሰጢረ ቁርባን እና ምሰጢረ ሜሮን ለጨቅላ ህጻናት መሰጠት የለበትም፣ አያውቁምና" የሚል ጠንካራ አቋም አላቸው። ይህም ከፍ ሲል ከተጠቀሱት በርካታ ሃይማኖቶች የተለዩ ያደርጋቸዋል። ከዚያ በኋላ ግን በዚህ ላይ በመመሰረት በርካታ የጴንጤቆስጤ ሃይማኖቶች ተመስርተዋል።

የሐዋሪያዊ ተልዕኮ (ኢቫንጀሊዝም) መስፋፋት

ሐዋርያዊ ተልዕኮ መስፋፋት የጀመረው በይበልጥ በአሜሪካ (ዩናይትድ ስቴትስ) ነው። በሃይማኖት ነጻነት ምክንያት እና በሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች ከየአገሩ ተሰደው ወደ አሜሪካ የሄዱና የሰፈሩ ሕዝቦች በየመንደሩ በተሰባሰቡ ጊዜ የተለያየ ስሜት አደረባቸው። መጽሀፍ ቅዱስን ሁሉም የሚቀበሉ ቢሆንም የአተረጓጎም መብት ለግለሰቦች የተሰጠ በመሆኑ ነጻ አስተሳሰብ ሰፈነ። ከተለያዩ አቀራረቦች ውስጥ ገንነው የወጡት የእግዚአ ብሔርን ቃል በስሜትና በሙሉ ልብ መቀበልና መተግበር እውነት እንድትቀርብና እግዚአብሔርም ቃሉን በምድር ላይ እንዲያመጣ ያግዛል፣ ያፋጥናል የሚል እምነት ያስተማሩ ናቸው። እነዚህ አብዛኞቹ የጴንጤቆስጥ እምነት ተከታዮች ናቸው።

ለነዚህ እምነቶች አንዱ መሠረት የሜቶዲስት ዲሲፕሊናዊ ስርዓት ሲሆን የአጥማቂያንም የእምነት ቀዳሚነት በተጨባጭ መተግበር ሌላው ነበሩ።

ስለዚህ በብዛት በመሰብሰብና ተሰጥኦ ያላቸው ሰዎች እየተነሱ በስሜት በመስበክ (በዘመናዊ ሙዚቃ በመጠቀም ጭምር) እግዚአብሔርን በሙሉ ስሜትና ጉልሀ በሆነ መንገድ ማመስገንና መለመን ተገቢው ስርዓት ሆነ "ሰው ሁሉ ሃጢያተኛ መሆኑን መገንዘብ አለበት። ለሃጢያቱ ስርየት የሚያገኘው ደግሞ በሥ ራው ዋጋ አይደለም በእምነት ብቻ እንጂ፣ ይህ

ደግሞ ለፈለገ ሰው ሁሉ እግዚአብሔር የሚሰጠው ችሮታ ነው።" የሚለው ግንዛቤ ሰፈነ።

እርግጥ በዚህም ቢሆን አንዳንድ መጠነኛ የሃሳብ ልዩነት መከ ሰቱ አልቀረም። ለምሣሌ ዮሐንስ ቄስሊ ተነስቶ "እንዲያውም ፍጹም መንፈሳዊ መሆን ደረጃ ሊደረስ ይቻላል። ፍጹም ቅድ ስናም ሊገኝ ይችላል።" ሲል ሌሎች ደግሞ ሰው መንፈሳዊ ቢሆንም እንደ ቅዱስ መንፈስ ሊሆን ከቶ አይቻለውም። (ቆሮ፣ 1÷1) አሉ።

በልሳን መናገርንም በተመለከተ አንዳንዶች ይህንን ችሎታና ብቃት ያሳዩ ነበሩ። በበዓለ ሃምሣ እንደተከሰተው (ሐዋ፣ 2÷1-4) አንዳንዶቹ ይህ ጸጋ ተሰጣቸው። ሌሎች ግን ይህንን ጸጋ ያላዩት አላመኑትም። አንዳንዶቹ ይህ በሃዋርያት ጊዜ አስፈላጊ የነበረ ቢሆንም አሁን አስፈላጊ አይደለም እና አይኖርም ሲሉ አንዳን ዶቹ እንዲያውም ይህ የሰይጣን (እርኩስ መንፈስ) መሣሪያ መሆን አለበት አሉ። አብዛኞቹ ግን ይህ ጸጋ ሊኖር ቢችልም እንደ መብት ሳይሆን እንደስጠታ ሊታደል ይችላል በማለት ታገሱት። በዚህ የተነሳ በርካታ የተለያዩ እምነቶች ሊፈልቁ ችለዋል። በአገራችን ውስጥ ያሉት እንኳ ጥቂት አይደሉም።

በኢትዮጵያ የሚገኙ አንዳንድ የፕሮቴስታንት ሃይማኖቶች

ዛሬ በኢትዮጵያ በርካታ የፕሮቴስታንት ሃይማኖቶች አሉ ብለናል። እነዚህ ሃይማኖቶች አንድ የሚያደርጋቸው የጋራ እምነት ቢኖራቸውም የሚለያያቸው ደግሞ መጠነኛ ልዩነት አለ።

በእምነት ረገድ አንድ የሚያደርጋቸው በሚከተሉት ሶስት ነጥ ቦች መስማማታቸው ነው።

1- በእየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ማመን። ይህ ማለት የደህንነት መንገድ በክርስቶስ በኩል መሆኑን።

2- የመጨረሻው የሃይማኖት ባለሥልጣን ጳጳስ ወይም ቤተ ክርስቲያን ወይም ሌላ ነገር ሳይሆን መጽሀፍ ቅዱስ ብቻ መሆኑ።

3- ደህንነት በስራ የሚገኝ ሳይሆን በእምነት የሚገኝ ጸጋ መሆኑ ናቸው።

በተግባር አንድ ከሚያደርጋቸው ውስጥ ቤተ ክርስቲያናቸውን ለመደገፍ ሲሉ ከገቢያቸው አስራት መክፈላቸው እንዲሁም በዓላቱ (ገና፣ጥምቀት፣ፋሲካ) በአገራችን ካለንደር መሠረት መሆናቸው ዋናዋናዎቹ ናቸው። ሃይማኖቶቹን የሚለያያቸው አንዱ ቁና ነገር አመሰራረታቸው ነው። ይህም ከተለያዩ አገሮች በመጡ ሚሲዮናውያን በመሆኑ የተነሣ የማምለክ፣ የመቀደስ፣ የባህልና የአቀራረብ ልምዳቸው የተለያየ ነው። ለምሣሌ የአንዳንድ ቤተ ክርስቲያን መሰራች ሚሲዮኖውያንን ምንጭ እንመልከት።

ሃይማኖት	መስራች
ህይወት ብርሃን	የስዊድን ኤንጤቆስጥ
መሰረተ ክርስቶስ	የአሜሪካ ሜኖናይት ሚሽን ሆኖ በኋላ በራሳቸው የተደራጁ።
ሙሉ ወንጌል አማኞች	የስዊድንና የፊንላንድ ኤንጤቆስጥ ሚሽን ሆኖ በኋላ ግን ራሣቸውን ያቋቋሙ።
ቃለ ህይወት	ኤስ አይ ኤም (አሜሪካ)
አዲስ ኪዳን መጥምቃውያን	የደቡብ (ዩናይትድ ስቴትስ) ባፕቲስት
እምነት ክርስቶስ	ሜቶዲስት
ወንጌላዊት መጥምቃውያን	የስዊድን ሉተራን
ገነት ቤተ ክርስቲያን	የፊንላንድ ኤንጤቆስጥ
መጽሀፍ ቅዱስ መጥምቃውያን	ባፕቲስት ሚሽን
መጥምቃውያን ማህበር	ጄኔራል ባፕቲስት
ሉተራን ቤተ ክርስቲያን	የስዊድን ሉተራን ሚሽን

እነዚህ ሃይማኖቶች ዛሬ ከመካነ እየሱስ ጭምር በአንድ የጋራ ማህበር ስር የተደራጁ እና በርካታ የጋራ እምነት ያላቸው በመሆኑ ለእያንዳንዳቸው የእምነቱን ይዘት ማስቀመጡ ተደጋጋሚ ሥራ ስለሚሆን ከእነዚህ ውስጥ ተቀራራቢ የሆኑትን አንድ ላይ በመውሰድ አንዳንድ ገላጭ ባህርያቸውን ለማመልከት ይሞከራል።

1- ሙሉ ወንጌል እና እህት ቤተ ክርስቲያናት፣

ሀ- <u>እምነት</u>÷ ይህ ሃይማኖት ከሌሎች የፕሮቴስታንት ሃይማኖቶች ጠንከር ያለ ይዘት የሚኖረው በይበልጥ በሚከተሉት አራት ነጥቦች ላይ ነው።

ሀ- መጠመቅ በክርስቶስ መወለድ መሞት እና መነሣት ስለሚመስል ሙሉ በሙሉ በመነከር መሆን አለበት። ይህም ደግሞ ፊሊጵስ ለኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በፍጹም ልብህ ብታምን (ጥምቀት) ተፈቅዷል እንዳለው ሁሉ ጥምቀት ከእምነት በኋላ የሚመጣ ነው። ስለሆነም ለሕጻናት አይሰጥም።

ለ- በእየሱስ ክርስቶስ ካመኑ ዘንድ ቆራጥ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል። "በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ" ባለው መሰረት በቃልም በተግባርም ማስተማርና አርአያ መሆን ይገባል። ስለዚህ ለምሳሌ አባላት ከገቢያቸው እሰከ 10% ይከፍላሉ። በአጠቃላይ እምነት ይቀድማል፣ መጽሀፍ ቅዱስ በጥሞና መማርና ማጥናት ይከተላል መጠመቅ ይቀጥላል። ከዚያ አርአያ መሆን ይገባል።

ሐ- አንድ ሰው አምኖ በሚጠመቅበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ይወርድ በታል። በላዩ ላይም ያርፍበታል። ይህ እየሱስ ክርስቶስ አጽናኝ (መንፈስ ቅዱስ) እልክላችኋለሁ ባለው መሰረት ነው። ይህ ከሆነ በኋላ በሌላ ልሣን ሊናገሩ ይችላሉ። "መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር" በተባለው መሠረት አሁንም ከአምላክ ጋር ለመነጋገርም ሆነ ተርጉሞ ለሌሎች ለመንገር ላመኑና ለተጠመቁ ይቻላቸዋል።

መ- አማኞች በእየሱስ ክርስቶስ ስም አጋንንትን ሊያወጡ ይቻላቸዋል። ክርስቶስ ከሙታን ተነስቶ ካረገ በኋላ በሌላ ቀን ለደቀመዛሙርቱ ታይቶ እንደነገራቸው "ያመነ የተጠመቀ ይድናል . . . ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል። በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፣በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፣ . . . እጃቸውንም በድዊዎች ላይ ይጭናሉ፣ እነርሱም ይድናሉ።" (ማር 16÷ 16-18)። በዚህ እምነት መሰረት በቤተ ክርስቲያን በጸሎት ጊዜ ብዙ ትዕይንቶች ይታያሉ።

በኢትዮጵያ "ጴንጤ" በሚል መለያ የሚታወቀው ይህ ሃይማኖት በቀብር ጊዜ ሥነ ሥርዓቱን በመዝሙር እና በጸሎት ያከናውናል። ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ይነበባሉ ለቅሶ አይኖርም። ይህ ከኦርቶዶክስ ባህል ለየት ያለ በመሆኑ ትኩረትን ሳይስብ አልቀረም።

ከሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ጋር የሚመሳሰሉ ሀ) ሕይወት ብርሃን እና ለ) ገነት ቤተ ክርስቲያን አሉ። ከጥቃቅን ልዩነቶች በስተቀር አንድ ናቸው።

1-ለ. <u>ሙሉ ወንጌል በኢትዮጵያ</u>

ሙሉ ወንጌል ወደ ኢትዮጵያ የገባው በ1945 አካባቢ በገቡት የፊንላንድ ሚሲዮናውያንና በኋላም በ1961 በገቡት የስዊድን ሚሲዮና ውያን አማካኝነት ነው። አነሣሡ ጴንጤቆስጥ (በዓለ ሃምሣ) በመባል በዩናይትድ ስቴትስ በኋላም በአውሮፓ በተስፋፋው እምነት ነው። የዚህ እምነት ልዩ ባህርዩ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ነው። በዚህ የተነሣ በልዩ ልሳን የመናገርና ሀመምተኛ የመፈወስን እምነት ያስከትላል።

ይህ እምነት በኢትዮጵያ በተመሰረተ ጊዜ ከኦርቶዶክስ ሃይማኖት ጋር ከፍተኛ አለመግባባት ፈጥሯል። በዚህ የተነሣ መንግሥትም በየጊዜው ጣልቃ ገብቷል። ሃይማኖቱ በአዲስ አበባ በይፋ መንቀሳቀስ የጀመረው



ፕሮቴስታንት ከምግብ በፊት ፀሎት ያደርሳሉ ::

በ1967 ዓ.ም ገደማ ነው። ወጣቶች ቤት ተከራይተው የጸሎት ቤት በማድረግ "ልመና" እና መዝሙር የተቀላቀለበት እንቅስቃሴ ጀመሩ ይባላል። በትክክል ግን እግዚአብሔርን መፍራትና ማክበር ይገባል በሚል አቋም እየተንቀጠቀጡና እጃቸውን እየዘረጉ የሚጸልዩበት ሁኔታ ነው።

በ1970 ዓ.ም አካባቢ "የሙሉ ወንጌል ማህበር" ተቋቋመ። ግን ተጽዕኖ ስለበዛ ቤተክርስቲያኑ በዓመቱ እንዲዘጋ ሆነ። ወላጆችምልጆቻቸው ስለ እየሱስ ፍቅር በማለት ይሳሳማሉ በሚል ምክንያት ድርጊቶቻቸውንም አወገዙ። ድብደባ እስራትና ግርፋትም ተከተለ። አማኞች የቀብር ቦታ ተከለከሉ። በአንድ ወቅት (በ1992 ዓ.ም) በጨፌ ዶንሳ የተቀበረም አስከሬን ወጥቶ እስከመቃጠል ተደርሷል። በአጀማመሩ ጊዜ ሙሉ ወንጌል አማኞችን ያጋጠማቸው ችግር እስከዚህ ነበረ።

ሆኖም ሃይማኖቱ መስፋፋቱን አላቋረጠም። ዲሲፕሊኑም እንደተጠበቀ ይኖል። ስለሆነም ለምሣሌ አማኞቹ ዘፈን ስለማይፈቅዱ በሠርግ ላይ ጭምር መዝሙር በመዘመር ደስታቸውን ይገልጻሉ። አልኮል መጠጥም አይፈቀድም። ሱስ የሚያስይዙ ነገሮችም የተከለከሉ ሲሆኑ ሻይና ቡና ግን አስጊ ስላልሆነ ክልክል የለበትም። ይህ የአልኮል አለመፈቀድ ጉዳይ በሌሎች በርካታ ሃይማኖቶችም የሚኖ መሆኑ ግልጽ ነው።

2- <u>ቃለ ህይወት</u>

2ሀ. <u>እምነት</u>÷ ይህ ከሱዳን ኢንተሪየር ሚሽን (SIM) የፈለቀ ነው። በ1920ዎቹ ዓ.ም የገባ ይሆናል። ጥምቀት ከእምነት በኋላ ብቻ ነው። ከአመነ ግን መጠመቅ አለበት። ይህ ሲሆን በዚያው ጥምቀት ላይ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ይጀምራል። ግን ይህ ማለት ደግሞ በሌላ ልሳን መናገር መጀመር አለበት ማለት አይደለም። በልሣን መናገር መቻል እንደ ስጦታ እንጂ እንደ ምልክት አይወሰድም። በሙሉወንጌል የሚፈለገውንም ዓይነት ቆራጥ ውሣኔ አይጠይቅም። የቃለ ህይወት እምነት ዋና መሰረቱ የዘለዓለም ደህንነት የሚባለው ነው።

አንድ ሰው ወዳጆቹ ክርስቲያን ስለሆኑ ወይም እሱ ቤተክርስትያን ስላዘወተረ ብቻ ክርስቶስን ተቀብሏል ማለት አይደለም። አንድ ቀን በአንድ ወቅት ሕይወቱን መርምሮ ሃጢአቱን አምኖ ጌታ እየሱስ ክርስቶስን የተቀበለ እና በሃጢያቱ የተጸጸተ የተናዘዘ ዕለት ያን ጊዜ ክርስትያን ሆነ ማለት ነው። ዳግም ተወለደ ማለትም ነው። በመንፈስ ቅዱስ ታተመ ነው። (ኤፌ፣1÷13)። ስለዚህ ድኗል። ከዚያ በኋላ ደህንነቱን አያጣም። ዳግም ወደኋላ አይመለስም። ጥፋትም ቢያጠፋ፣ሃጢያትም ቢሰራ ጌታ እየሱስ ይገስጸዋል። ይመራዋል። ካልሆነም በምድራዊ ሕይወቱ ይቀጣዋል እንጂ እንደ አረማውያን በነፍሱ አይኮንነውም። አንዴ ድኗልና። በጎቼን ከእጄ ማንም አይነጥቃቸውም። (ዮሐ፣10÷29)።

ስለዚህ ደህንነት የሚመጣው በእምነት ጌታ እየሱስ ክርስቶስን በመቀበል ነው። በኤፌ፣2÷8-9 እንደተቀመጠው "ጸጋው በእምነት

አድኗችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም። ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።"

በቃለ ሕይወት እምነት መሰረት ቁርባን ለመታሰቢያነት እንጂ ለደህንነት የሚውል አይደለም። እየሱስ ክርስቶስ እንጀራውን አንስቶ ሰጣቸው ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት (ሉቃ፣ 22÷19) ስላለና ጳውሎስም በዚሁ መንፈስ ከአርባ ዓመታት በኋላ ሲያስተምር ቁርባን (የጌታ እራት) ለመታሰቢያነት ብቻ መሆኑን አስምሮበታል። በተጨማሪ በቃለ ሕይወት እምነት መሰረት "በስጋ ትንሳኤ" ያታመናል። ጌታ የተነሳው በሙሉ አካል ነው። የሃጥያት ዕዳ የተከፈለውም አንድ ጊዜ ነው። ስለዚህም በየጊዜው ደሙ አይፈስም። በየጊዜውም ስጋው አይቆረስም።

እርግጥ ለመታሰቢያ የሚሰጥ ቢሆንም ከእምነቱ በኋላ መሆን ይገባዋል። (ቆሮ 1፣ 11÷27-32) አለበለዚያ ዕዳ አለበት፣ፍርድም ይፈረድበታል

ጥምቀትንም በተመለከተ ሕጻናትን ማጥመቅ ትርጉም የለውም። "ያመነ የተጠመቀም ይድናል፣ ያላመነ ግን ይፈረድበታል" (ማር 16÷16) ይላል ስለዚህ ይህ ለሕጻናት አይሆንም አንድ ሰው የሚጠመቀው መጀመሪያ ውሃ ውስጥ እንደቆመ በእየሱስ ክርስቶስ ማመኑን ተጠይቆ ሲያምን ብቻ ነው። እርግጥ ጥምቀት ከእምነት በኋላ አስፈላጊ ነው። ምስክርነት መስጠት ነውና። ከዚህ በኋላ መንፈስ ቅዱስ የራሱን ስራ ይሰራል። ሰውዬውም እንደአገልግሎቱ እንደ ጸሎቱና ጥናቱ መጠን በመንፈስ ቅዱስ እየተሞላ ይሄዳል። ይህ ግን ስጦታ ነው እንጂ መብት አይደለም። በስጦታነቱ ግን በልሳን መናገር፣ ከበሽታ መፈወስ የሚችሉ አሉ። ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን እንደሌሎቹ አብዛኞቹ ከመካነ የሱስ ቤተ ክርስቲያን የሚለያት ቄስ አለመኖሩ ነው። መጋቢ (ፓስተር) ስላለ የጌታ እራትን የሚመግበው የሚያቀርበው እሱ ነው። የተለየ አልባሳት ሊኖረውም ላይኖረውም ይችላል መጋቢ ባልተኖም ጊዜ በምትኩ በሳል መንፈሳዊ ሰው ከምዕመናኑ መካከል እየተመረጠም ተግባሩን ሊያከናውን ይችላል። በአገራችን ሁኔታ ግን የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ስለማይታጡ ሰብሳቢያቸው የሆነ ወይም ሌላ የተመረጠ ሽማግሌ ስነስርዓቱን ያካሂዳል።

ስለዚህ ሚስጥረ ክህነት በአእማደ ሚስጥር (ሳክራመንት) መልኩ የለም። አንድ ሰው ብቃቱ የሚመሰክረው በስልጠና በአገልግሎት እና በምዕመናን ዘንድ ባለው አክብሮት ወይም ተወዳጅነት ስለሆነ በሚመረጥበት ጊዜ ከሳክራሜንት ቀለል ባለ ስነስርዓት ስልጣኑና ሃላፊነቱ ይሰጣቸዋል። በአገልግሎት ላይ ሳሉ መዘምራን ጋውን (የደንብ ልብስ) ይለብሳሉ። ወደፊት ግን ለስነስርዓቱ ክብር ብቻ ጠቃሚ መስሎ ስለታየ መጋቢ (ፓስተር) እንዲለብስ ተወስኗል ይባላል።

2ለ. <u>የቤተ ክርስቲያን ስነስርዓት</u>

1፣ <u>የጌታ እራት ማቅረብ</u>

የዚህ ስነስርዓት በጣም ቀላል እንዲሆን ተደርጓል። ዝርዝሩ እንደሚከተለው ነው።

3- ጾም

ጾም ከጸሎት ጋር ይካሄዳል። የጾም ቀን በቅድሚያ ይነገራል። በዚያን ዕለት የቻለ ሁሉ ጾሙን ይመጣል። እስከ ቀን ወይም ከቻለ እስከ ማታ በጸሎት ይቆያል። ከዚያም ሲወጣ ሂዶ ይመገባል ማለት ነው። ጾም የሚጠየቀው የጋራ (ለምሣሌ ብሔራዊ) ችግር ሲደርስ ነው። ይህ በአማካይ በዓመት ሶስት ጊዜ ያህል ሊጠየቅ ይችላል።

4- በልሣን መናገር

በቃለ ሕይወት እምነት መሠረት በልሣን መናገር ከጌታ የሚሰጥ ስጦታ ነው። ምዕመናን ተሰብስበው በጸሎት ላይ ባሉ ጊዜ ድንገት በመሃል አንዱ ተነስቶ በልሣን መናገር ይጀምራል። ይህ በሚሆንበት ወቅት አንዳንድ ጊዜ ራሱ ባለቤቱ ትርጉሙን ይገልጸዋል። ብዙውን ጊዜ ግን ከተቀመጡት ሰዎች መካከል አንዱ የተገለጸለት ወይም ትርጉሙ የገባው ብድግ ብሎ ትርጉሙን ያስረዳል። የሚተረጉመው ከሌለ ግን መልዕክቱ ለሕዝብ ሳይሆን ለራሱ ለተናጋሪው መሆኑ ታውቆ እንዲቀመጥ ይደረግና ስነስርዓቱ ይቀጥላል።

የዚህ በልሣን የመናገር ክስተት ጥቅሙ የግለሰቡን እምነት ለማጠናከር ይረዳዋል። ለቤተክርስቲያን ወይም ለተሰበሰበው ሕዝብ የሚሆን መልዕክት ሆኖ ከተገኘም ይህም ለሁሉም እምነቱን ያጠናክርለታል።

2-ሐ. ቃለ ህይወት በኢትዮጵያ

ይህ እምነት መሠረቱ ሱዳን ኢንቲሪየር ሚሽን (S.I.M) ነበረ። ሚሽኑ የተመሠረተው ሶስት ሚሲዮናውያን ከዩናይትድ ስቴትስ በ1893 ዓ.ም ክርስቶስን ለማስተዋወቅ ሲሉ ከሥልጣኔ ርቀው በጨለማ ወደ ተቀመጡት ወደ አፍሪካውያን ለመሄድ ተነሳስተው በጀመሩበት ወቅት ነው። የሃይማኖቱ ስም ባፕቲስት ሲሆን በደቡብ ዩናይትድ ስቴትት ዳብሮ የነበረ ጥምቀት አጥባቂ ሃይማኖት ነበረ። ከሶስቱ አንዱ ብቻ (ዶክተር ሮውላንድ ቢን ግሃም) ግባቸውን ከፍጻሜ ሊያደርሱ በቁ። በዚህ ስራቸው በአውሮፓ ዝናቸውን ሰምተው የተማረኩት በኢትዮጵያ በህክምና ስራ ላይ ተሰማርተው የነበሩት ዶ/ር ቶማስ ላምቢ በዚህ ወንጌላዊ ተልዕኮ ለመተባበር ቆርጠው ተነሱ። ስለዚህ በ1928 ዓ.ም አንድ ቡድን በመምራት 60 በቅሎዎች ጭነት ይዘው ለብዙ ሣምንታት በእግር እና በበቅሎ እየተጓዙ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ አመሩ። በቀን 25 ኪሎ ሜትር ገደማ በመጓዝና በየመንገዱም የህክምና አገልግሎት በመስጠት ስለወንጌልም በማስተማር በሁለት ሣምንት ሆሳዕና ደረሱ። ከዚያም ወደ ሲዳሞ እና ጋሞጎፋ ዘለቁ። በየሄዱበት ሁሉ ጣቢያ እያቋቋሙና ሰውን እያስተማሩ ካጠመቁት ደቀመዛሙርቶቻቸው መካከል በፊት ጠን ቋሮች ባለዛርና ባርያ-ፈንጋዮች የነበሩ ሁሉ ይገኙባቸዋል። ቡድኑ በየጊዜው ከባድ ፈተና ገጥሞት እንደነበረ ይነገራል። ለምሣሌ "ባሪያዬን ነጻ ትወጣለህ

እያልክ ትመክራለህ" በመባል ዶክተሩ በጥፊ የተመቱበት ጊዜም ነበረ። አዲስ አማኞችም ቢሆኑ መቀበሪያ ቦታ እስከማጣት እስከ መገረፍ መሰደድና መዘረፍ ድረስ መከራ እና ስቃይ ተቀብለዋል።

በዚህ ዓይነት በብዙ ትግል ወንጌልን አስተማሩ። በኋላም ቀስ በቀስ ደቀመዛሙርቱ ራሳቸውን ችለው ያስተምሩና ያጠምቁ ጀመር። የራሳቸውን የጸሎት ቤትም ከፈቱ። የገንዘብም ምንጭ እንዳይደርቅ የአገሩ ዜጋ አስተዋጽኦ አደረገ። በዚህ ዓይነት በግሩ ቆመ። ስር ሰደደ። ተበራከተ።

ለቤተ ክርስቲያኑ ስም ባስፈለገ ጊዜ የሱዳን ኢንቲርየር ሚሽን እነዚህን በየቦታው የተበታተኑ ቤተ ክርስቲያናትን ለማገናኘት እያሳተመ ያሰራጭ የነበረው መንፈሳዊ ጽሁፍ ስለነበረውና የመጽ ሄቱም ስም ቃለ ሕይወት ስለነበረ ይኸው የአካባቢው ቤተ ክርስቲያን መለያ እና የወል መጠሪያ እንዲሆን ተወሰነ።

ዛሬ ቃለ ህይወት ቤተ ክርስቲያን በሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች ይገኛል። አባላቱም ከሚሊዮን በላይ ይቆጠራሉ።

መሰረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን

መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የተመሰረተው በ1950ዎቹ ዓመተ ምህረት በናዝሬት ከተማ ነው። ቀደም ሲል ወደዚያ ከተማ መጥተው በሃይለማርያም ማሞ ሆስፒታል ይሰሩ የነበሩ የውጭ አገር ዜጎች በሃይማኖታቸው ሜኖናይት ስለነበሩ በትርፍ ጊዜያቸው መጽሐፍ ቅዱስን ያስተምሩ ነበረና በርካታ አማኞችን ሊያፈሩ በቁ። በኋላም አዲሶቹ አማኞች መጽሐፍ ቅዱስን በጥሞና በማጥናት በተለይም እየሱስ ክርስቶስ በበዓለ ሃምሳ ዕለት ለሐዋርያቱ ያወረደውን ጸጋ በማጤን (ሐዋ፡ ምዕራፍ 2) እነሱም በእምነታቸው ጸንተው ከጸለዩ ይህ ጸጋ ለእነሱም ሊደርስ እንደሚችል በማመን ተግተው ይሰሩና ይጸልዩ ነበረ ይባላል። በኋላም በልሣን መናገር ሕሙማንን በጸሎት ሃይል መፈወስ ተጅላቸው በዚህን ጊዜ የውጭ አገር ዜጎቹ ይህንን ክስተት በመጠራጠር "የእርኩስ መንፈስ አስተዋጽኦ ሳይኖርበት አይቀርም" በማለት ራቋቸው ይባላል። ኢትዮጵያውያኑም ለራሳቸው የጸሎት ቤት የሚሆን ተከራይተው ሃይማኖቱን በራሳቸው አሰፋፋት በመጨረሻም የውጭ አገር ዜጎቹ አምነውበት መልሰው እንደተቀላቀሏቸው ይታወቃል። ይህ ሃይማኖት በሂደት ብዙ ፈተና አጋጥሞት የነበረ ቢሆንም ዛሬ በኢትዮጵያ ካሉት ትላልቅ የፕሮቴስታንት ሃይማኖቶች አንዱ ነው።

መሠረተ ክርስቶስ ከሙሉ ወንጌል ጋር ብዙ ተቀራራቢነት አለው። ለምሳሌ ጥምቀትን በተመለከተ ይህ ለሕጻን የሚሰጥ ሳይሆን ለአዋቂ ሰው ሆኖ ይህም ቢሆን በእየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት አምኖና ንስሃ ከገባ በኋላ በውሃ ውስጥ በመጥለቅ የሚጠመቅበት ሚስጥር ነው። እርግጥ የተጠመቀ ሰው የመንፈስ ቅዱስ ሙላት እንደሚያገኝ ቢታወቅም ይህ ሙላት የሚገለጠው በልሳን ለመናገር በመቻል ብቻ አይደለም ፣ ሌሎች በልሳን የተ

ናገሩትን ለመተርጎም በመቻል ወይም የታመመን ሰው በጸሎት ብርታት በመፈወስ ወይም ተአምራትን በመሰራት ችሎታ ሊገለጥ ይችላል።

ቅዱሳት ምስጢራትና የክርስትና ስርዓቶች

መሠረተ ክርስቶስ ቅዱሳት ምስጢራት ብሎ የሚቀበላቸው ሶስት ናቸው። እነዚህም እየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር ሳለ የፈጸማቸው ሲሆኑ እነሱም 1ኛ/ ቅዱስ ጥምቀት 2ኛ/ የጌታ እራት ሲሆኑ 3ኛው/ የእግር መተጣጠብ ስርዓት ነው። ሌሎች የክርስቲያን ተግባራት በክርስትና ሥርዓት ስር የሚጠቃለሉ አሉ እነዚህም 1ኛ/ ሕሙማንን በጸሎት ሊፈወሱ እንዲችሉ የእምነት ጸሎት ማድረግ (ማር፡ 16፣17-18) 2ኛ/ጋብቻ አንድ ለአንድ ብቻ ሲሆን ይህም ሞት ካልሻረው ወይም በምንዝርና ካልሆነ በስተቀር ፍቺ የሌለበት፣ እግዚአብሔር የመሰረተውና, የቀደሰው, የሁለት ምዕመናን አንድነት ስለሆነ ቅዱስ ስርዓት መሆኑ (ማቴ 19÷3-9)።

3ኛ. ክርስቲያን እህቶች (ሴቶች) በህብረት ጸሎት ጊዜ ጸጉራቸውን መሸፈን የሚገባቸው መሆኑ (1 ቆሮ 11÷1-16)።

4ኛ. ለእየሱስ እንደተደረገው ሁሉ ሌሎች ወላጆችም ለተወለዱ ሕጻናት (እሰከ ሁለት ዓመት ዕድሜ ላሉ) የሚያከናውኑት ስርዓት ነው። ይህም ለእግዚአብሔር ባርኮትና ጥበቃ ሕጻናትን ለጌታ አሳልፎ በመስጠት ሕጻናትን በእግዚአብሔር መንገድ እንዲያሳድጉ ወላጆች ቃል የሚገቡበት ስርዓት ነው።

ክርስቲያናዊ ስነምግባርን በተመለከተ ከሌሎች ጎላ ብሎ የሚታየው የመለየት ጉዳይ ነው። ክርስቲያን በቅድስና መኖር አለበት። ከዓለማዊነትና ለዓለም ከሚመቹ ከንቱ ነገሮች ተለይቶ ለእግዚአብሔር ክብር በእየሱስ ክርስቶስ የጽድቅ ኑሮ መኖር ይገባል። (ሮሜ 12÷1-2 እና 2ኛ ቆሮ 6÷14-18)።

በአጠቃላይ መሠረተ ክርስቶስ በአብ ወልድ መንፈስቅዱስ የሚያምን፣ መጽሐፍ ቅዱስን (66ቱን መጻሕፍት) በሚቀበል። በመንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚያምንና ስለደህንነት የተሰጠውን ትምህርት በአትኩሮት የሚከታተል ስለቤተክርስቲያን ስለመላ እክትና ሰይጣን ተግባር የሚያውቅ ነው። በተለይ ደግሞ ከፍ ሲል የተጠቀሱት ሀ) እግር መተጣጠብ ለ) ጸጉር መሸፈን፣ ሐ) ልጆችን ለጌታ አደራ መስጠትና) በቅድስና ተለይቶ መኖር ጉዳይ ሃይማኖቱ ቸል የማይላቸው ናቸው።

3- ሌሎች ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያኖች

ወንጌላዊት መጥምቃውያንና መጽሀፍ ቅዱስ መጥምቃውያን እንዲሁም መጥምቃውያን ማህበር፥ በባፕቲስት ሚሲዮኖች የተቋቋሙ ናቸው። እነዚህም ከሌሎች ጋር በጋራ ከሚያምኑት በተጨማሪ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ያጣኘ ሰው ደህንነት እንዳጣኘ ሲያምኑ በአዲስ ልሣን የመናገርን

አስፈላጊነት አይቀበሉም። በኦፊሴላዊ ክህነትም አያምኑም። ጥምቀት ከእምነት በኋላ (ለአዋቂ ብቻ) የሚሰጥ መሆን አለበት በሚለው ከመካነ የሱስና ከሉተራን ቤተ ክርስቲያን ይለያሉ። ቁርባንም እንዲሁ ለመታሰቢያ ብቻ ስለሆነ የጌታ እራት መታሰቢያ ሆኖ ይወሰዳል።

ከፍ ሲል የተጠቀሱት የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያናት በተጨማሪ አንድ የሚያደርጋቸው÷

- የጸሎት መጽሐፍ አለመኖሩ፣
- ለስግደት መንበርከክ ግዴታ አለመሆኑ፣
- ሻማ መብራት መኖር አስፈላጊ አለመሆኑ፣
- መዝሙረ ዳዊትን ማዜም አለማስፈለጉ፣
- ክርስትና አባት (እናት) አለመኖሩ ናቸው።

መካነ የሱስ ሉተራንና ቃለ ህይወት የመሳሰሉት ቤተ ክርስቲያኖች ግን በዚህ "መሻሻል" ውስጥ አይጠቃለሉም።

ማጠቃለያ፡- የፕሮቴስታንት ሃይማኖት በተለያየ አናሳ ክፍሎች (ሴክት) ቢከፋፈልም የእምነቱ መሰረት አንድ ነው። ይህም ዛሬ ነባር ከሆኑት የኦርቶዶክስና የካቶሊክ ሃይማኖቶች የበለጠ ዕድገት እያሣየ ነው። እርግጥ በአጠቃላይ ምዕመናን ቁጥር አንጻር ሲታይ በጣም ትንሽ ነው። ሆኖም ዕድገቱ ፈጣን ነው። ለዚህ በርካታ ምክንያቶች አሉት። ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል፡-

1- የእምነቱ ይዘት ቀጥታ እና ቀላል ነው። እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን ስነ ስርዓት ግልጽና ሁሉም ሰው ሊከታተለውና ሊሳተፍበት የሚችል ነው። ስለዚህ የሁሉም አብሮ መዘመር "አብሮ መጸለይና መወዛወዝ" የመሳሰሉ ማህበራዊ ተግባሮች እምነቱን ግልጽና ህያው አድርገው ያቀርቡለታል።

2- በልሣን መናገርን ማየቱ ልዩ መንፈሳዊ ስሜት ያሳድራል። በእምነቱ መዳን ከክፉ ደዌ መፈወስ የመሳሰሉትን ሲመሰክሩ ማየት ደግሞ እምነቱን በበለጠ ያጸናል።

3- ሃይማኖተኛ የሆነ ሰው ከመጠጥ ሱስ ስለሚታቀብ እንዲሁም ሃሺሽ ከመሳሰሉት ዕጾች ሱስ ስለሚላቀቅ የቤተሰብ ጥል ይቀንሳል፣ ማህበራዊ ኑሮው ይጎለብታል፣ሃላፊነት የበለጠ ይሰማዋል። ስለሆነም የሃይማኖቱ ተወዳጅነት እየጨመረ መጥቷል።

4- ሌሎች የክርስትና ሃይማኖቶች

ከፍ ሲል ከተዘረዘሩት 12 የፕሮቴስታንት እምነቶች ውጭ በመሆን በየራሳቸው የተደራጁ ሌሎች በርካታ ሃይማኖቶች አሉ። ከእነሱም አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

1/ አድቨንቲስት (ሰባተኛው ቀን አክባሪ) ቤተ ክርስቲያን

የዚህ ሃይማኖት ጉልህ መለያ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ/ አድቨንቲስቶች እንደሰንበት አድርገው የሚያከብሩት ቅዳሜን እንጂ እሁድን አይደለም። ለዚህም ጠንካራ ምክንያት አላቸው።

"እግዚአብሔርም ሰባተኛውን ቀን ባረከው ቀደሰውም" ይላል ኦሪት ዘፍጥረት። ከአሰርቱ ትእዛዛትም አንደኛው "የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ" ይላል። ይህ ትዕዛዝ ከጥንት የኦሪት ዘመን ጀምሮ ሲከበር የቆየ ነበረ። ግን ይህ ሰባተኛው ቀን እሁድ አይደለም። ይህ በአዲስ ኪዳን የተረጋገጠ ነው። ለምሳሌ እየሱስ ክርስቶስን ከመስቀል አውርደው ለተከታዮቹ የሰጡት ሰንበት ሳይገባ በፊት ነበረ። (ሰቅለት ዓርብ ቀን ይውላል።) ከሰንበት ማግስትም እነ ማርያም መግደላዊት በማለዳ ወደ መቃብሩ ሄዱ ግን መቃብሩን ባዶ ሆኖ አገኙት (ትንሳዔ እሁድለት ይውላል።) ስለዚህ ሰንበት ማለት ቅዳሜ መሆኑ አያከራክርም።

"ግን በትዕዛዙ መሰረት ሰንበት ለምን አይከበርም?" ሲሉ አድቨንቲስቶች ዓለምን ይጠይቃሉ። እየሱስ ክርስቶስ ሞትን ሽሮ በድል አድራጊነት ያረገበት ቀን እሁድ ስለሆነ በምትኩ ይህ ቀን እንዲከበር ሆኗል የሚል መልስ ይሰነዘራል። ግን እየሱስ ኦሪትን አልሻረምና አሰርቱ ትዕዛዛቴን ጠብቁ፣ ህግን ሁሉ የሚጠብቅ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል። ወደ ህይወት መግባት ብትወድ ግን ትዕዛዙን ጠብቅ" የሚሉ ጥቅሶች አሉ።

በቅዳሜ ምትክ እሁድ እንዲከበር የተደነገገው በላውዶቂያ ጉባኤ (364ዓ.ም) ሲሆን ይህም እንደገና የሮማ ጳጳስ ባለው ሙሉ ሃይማኖት-ነክ ስልጣን መሠረት በ1910 ዓ.ም አጽድቆታል። ግን አድቬንቲስቶች የሮማ ጳጳስ ውሣኔንም አይቀበሉም።

ለ/ ሞት እና ትንሣኤን በሚመለከት እንዲሁም ስለ ሲኦልና ገሃነም ያላቸው አመለካከት ከኦርቶዶክስም ሆነ ከካቶሊክ ለየት ያለ ነው። ለምሣሌ በኦርቶዶክስ እምነት መሠረት ሰው ሲሞት ነፍስ ከስጋ ተለይታ ትሄዳለች። በአድቬንቲስት እምነት ግን ነፍስ ማለት ስጋ እና እስትንፋስ በአንድነት ነው።

ስለዚህ ሰው ሞተ ሲባል ሁለቱም ስጋ እና እስትንፋስ ማለት ስለሆነ ነፍስ ሞተች እንደማለት ያስቆጥራል። አዳም ሲፈጠር ህያው ነፍስ ሆነ ተብሎ ተጽፏል። በኋላም በተሰጠው ማስጠንቀቂያ ከዚህ ዛፍ በበላህ ቀን ትሞታለህ ተብሏል። ምክንያቱም ሐጢያት የሰራች ነፍስ እሷ ትሞታለችና።

ግን ሞት ምንድነው ለሚለው ጥያቄ መልሣቸው "እንቅልፍ" ነው። ይኸውም እንቅልፍ የያዘው ሰው በኋላ እንደሚነቃ እንዲሁም ሙታን ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ ይነሣሉና።

ሲኦል እና ገሐነም ዛሬ የሉም። በጥንቱ እስራኤል ሶኦል (ሼዖል) ማለት የመቃብር ቦታ ሲሆን ገሐነም (ሄሎም) የቆሻሻ ማቃጠያ ቦታቸው ነበሩ። ስለዚህ ዛሬ ሲኦል ወይንም ገሐነም ተልኮ የሚቃጠል ሰው የለም።

በአጠቃላይ ሰው ሲሞት ከመኖር ወደ አለመኖር ይለወጣል። በክርስቶስ ዳግም መነሳት ሁሉም ተነስተው እንደስራቸው ፍርዳቸውን ይቀበላሉ።

ሐ- በሰማይ መቅደስ አለ። ሙሴ በምድር የሰራው መቅደስ የሰማዩ መቅደስ ምሳሌና ጥላ ነው። (ዕብ 9÷23-24) ክርስቶስ ከሙታን ከተነሣ ጀምሮ እስክ 1844 ዓ.ም በቅዱስ ቦታ ሆ ከዚያ ወዲህ በቅድስተ ቅዱሳን ሆኖ እያማለደን ነው። (ዕብ 8÷1-2)። በምድራዊው መቅደስ ካህናት መስዋዕት በመስጠት ያማልዳሉ። ደም ሳይፈስ ስርየት የለም። (ዕብ 9÷22) ምክንያቱም የሃጢያት ዋጋ ሞት ነው። ስለዚህ ሃጢያተኛ መሞት አለበት። ወይም የእርሱ ምትክ መሞት አለበት። ክርስቶስ አንዴ ለሰው ልጅ ሲል ሞቷል። ስለዚህ አሁን የማማለዱን ተግባር መቀጠል ብቻ ነው። እሱ በቅድስት ቅዱሳን ሊቀ ካህን በመሆኑ በእርሱ በኩል ወደ አብ የሚመጡትን ሁሉ ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል። (ዕብ 7÷25) በሌላ አንጋገር በእርሱ በኩል ካልሆነ ወደ አብ የሚመጣ የለም።

በመጨረሻም ከቅድስት ቅዱሳን ወጥቶ በስርየት ቀን ለመጨረሻ ፍርድ ሊሰጥ ይመጣል። አሁን ይህ ቀን ሰለተቃረበ ሊቀካህናችን ወጥቶ ከመምጣቱ በፊት ሃጢያታችንን በመናዘዝ የዘለዓለም ደህንነት ለመቀበል መዘጋጀት ይኖርብናል።

እርግጥ የምጽአት ቀን መቃረብ በሁሉም ክርስቲያኖች ዘንድ የሚታመን ነው። በአጭር ጊዜ የፍርድ ቀን እንደሚመጣና ለዚህም ዝግጁ ሆነን መቀመጥ እንዳለብን ሁሉም ያስተምራሉ።

በተጨማሪም ሰውነታችን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ወይም መቅደስ ስለሆነ በቅድስና በንጽህናና በአክብሮት ይዘን መጠበቅ አለብን። ይህ ሁሉም ክርስቲያን የሚስማማበት ነው።

በአድቬንቲስት እምነት መሰረት እግዚአብሔር ለጥንቱ እስራኤላውያን የምግብ ዓይነትም ደንግጎላቸዋል። ይህም ለሰውነታቸው ጎጂ የሆነውን እንዳይመገቡ ነው። ዛሬም ቢሆን በምንመገበው ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉ (1 ቆሮ 1÷31) ተብሏል። በዚህ መሰረት የሚያሰክር ወይም ሱስ የሚያስይዝ ምግብ መጠጥ መውሰድ አይገባም። ሰው 1- አልሚ ምግብ (ኑትሪሽን) 2- የሰውነት እንቅስቃሴ 3- ውሃ 4- የጸሃይ ብርሃን 5- ጠባይ (ቴምፐራመንት) 6- አየር 7- ዕረፍት 8- እምነት (በእንግሊዝኛ ምህጻረ ቃል NEWSTART) ካጣ ወይም ካለው በሕይወቱ ውስጥ ምንም ዓይነት ጉዳት አይደርስበትም።

ከዚህ በተረፈ ግን አድቬንቲስቶች የጴንጤቆስጤን በሌላ ልሣን የመናገር ችሎታን የማረጋገጥ አስፈላጊነት አያምኑበትም። የሃይማኖቶች

አንድነትም ሊመጣ የሚችለው ሌሎች ሃይማኖቶች ትዕዛዛቱንና ሌሎችንም ትክክለኛ አመለካከታችንን ሲቀበሉ ብቻ ነው ይላሉ።

2- የጄሆቫ ምስክሮች (የያህዌህ ምስክሮች)

ይህ ሃይማኖት መጀመሪያ የተመሠረተው በዩናይትድ ስቴትስ አገር በ1872 ዓ.ም ነው። መስራቹ ቻርለስ ራስል (1852-1916) የሚባል ነበረ። የተነሳሳበትም ዓላማ መጽሀፍ ቅዱስን ብቻ መነሻ በማድረግ በሌሎች ሳይመራ አንድ ሰው ራሱ አንብቦ አጥንቶ እና ተመራምሮ ትክክለኛው ውሣኔ ላይ ለመድረስ ይችላል የሚል ስለነበረ ዓለም አቀፍ የመጽሀፍ ቅዱስ ተማሪዎች ማህበር ተቋቋሞ ጥናቱ ተጀመረ።

የሃይማኖቱ ስም መነሻ የሆነው ጄሆቫ ወይም በትክክለኛው አጠራር ያህዌህ የተባለው ስም እግዚአብሔር ራሱ ለሙሴ በኮረብ ተራራ ላይ በተገለጠለት ጊዜ ስሜ ያህዌህ ነው ብሎ ባስታወቀው መሠረት ነው። ይህንን ትክክለኛ ስም ይዞ በመነሣት ነው አማኞቹ እግዚአብሔር ስለሰራቸው ስራዎች በምስክርነት ለመናገር ሲሉ ይህንን ስያሜ የወሰዱት።

የዚህ እምነት ተከታዮች ከሌሎች የክርስትያን እምነቶች የሚለዩበት መሰረታዊ እና ጥቃቅን ልዩነቶች አሉ። ለምሣሌ፡-

1- ተዋህዶ እምነትን በተመለከተ አብ የዓለም ሁሉ ፈጣሪ መንፈስ ነው። መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የእርሱ ሃይል ነው። ወልድ ግን መጀመሪያ (ማለትም ከአዳም በፊት) በአብ የተፈጠረ መንፈስ ነበረ።

2- ሰው ከነአካሉ ነፍስ ይባላል እንጂ ነፍስ ከስጋ ውጪ አይደለም። ሰው ሲሞት ነፍስ ሞተች ይባላል። በሞት ጊዜ አካል ቢፈርስም በትንሣኤ ጊዜ ነፍስ ሌላ ተመሣሣይ አካል ለብሳ ትነሣለች። ነፍስ ደግ የሰራች ከነበረች ወይም ክፉ የሰራችው ባለማወቅ ከነበረ ትናሣኤ ታገኛለች ሃጢያተኛ ከነበረች እንደሞተች ትቀራለች።

3- "ገሃነም እሣት" ማለት "እሣቱ የማይጠፋበት ትሉ የማያንቀላፋበት" የሚባል ነገር የለም። ይህ ምሣሌያዊ አነጋገር ነው። ገሃነም የገባች ነፍስ ማለት ተመልሣ አትነሣም ማለት ነው።

4- መንግሥተ ሰማያትን የሚወርሷት 144,000 ሰዎች ብቻ ናቸው። እነዚህ ለአንድ ሺ ዓመታት ከክርስቶስ ጋር ይነግሣሉ። ካህናትና ነገስታት ይሆናሉ። ከዚያ ዘመን በኋላ ከአብ ጋር ይሆናሉ። ለእርሱም ተገዢ ይሆናሉ።

ክርስቶስም ሥልጣኑን ለአብ ያስረክባል። ይህ ከፍርድ ፍጻሜ በኋላ ነው።

5- ክርስቶስ ሞቶ መነሣቱ እርግጥ ነው። ነገር ግን ስጋው (አካሉ) ወደ ሰማይ አላረገም። ምድር ላይ ቀርቷል። እርግጥ መቃብሩ ባዶ መሆኑ

ተረጋግጧል። ታድያ ስጋው የት ደረሰ? ለሚለው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ "ሰዎች እንዳያመልኩበት አምላክ ራሱ አጥፍቶታል" የሚል ነው።

6- መስቀል ሊመለክበት አይገባም። እየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት እንጨት ዛሬ እንደምናውቀው ዓይነት መስቀል አልነበረም። ቀርጹ በ"ፐ" መልክ ነበረ። ምልክቱ የዛሬው ዓይነት መስቀል እንዲሆን ስምምንት የተደረሰው ከዚያ በኋላ በመንፈሳዊ ጉባኤ (ኒቂያ) የተወሰነ ነው።

ስለዚህ የዛሬው መስቀል ቅርጽም ሆነ ትርጉም ተቀባይነት የለውም። ልናመልክበትም አይገባም።

7- በመንፈስ ቅዱስ ስም ተአምር እንሰራለን፣የታመመ እናድናለን፣ደቂ እንፈውሳለን የሚለውን አባባል የጄሆቫ (ያህዌህ) ምስክሮች አይቀበሉም። እየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሳለ ተአምር የሰራው እና ከዚያም በኋላ ሰልጣኑን ለሐዋርያቱ ሰጥቶ ተአምር የሰሩት ሰዎች እንዲያምኑ ለመርዳት ሲል ነበረ። ይህም ትንቢት እስኪሟላ ድረስ ብቻ ነበረ። ከዚያ ወዲህ ትንቢት ተጽፏል (በ98 ዓ.ም)። መጽሀፍ ቅዱስም ተሟልቷል። አሁን በዚያ ላይ ለመጨመር አይቻልም። ስለዚህ ተአምር መሥራት አልአስፈላጊ ሆኗል። (በዕምነቱ መሠረት 4ቱ ወንጌሎች የተጻፉት ሀ/ ማቴዎስ በ41 ዓ.ም ለ/ ሉቃስ 56-58 ዓ.ም ሐ/ ማርቆስ በ60 - 65 ዓ.ም. መ/ዮሐንስ በ98 ዓ.ም ነበሩ)።

8- ሰዎች ሲሞቱ ሃጢአን እንደሞቱ ይቀራሉ፣ጻድቃን ግን በምጽዓት ጊዜ ይነሣሉ። ከዚያም ክርስቶስ ለአንድ ሺ ዓመታት ይገዛል። በዚህን ጊዜ ሰዎች አካላዊ ፍጽምና ያገኛሉ። የመንፈስም ፍጽምና ያገኛሉ። ሰይጣንም እንዳይፈታተናቸው ታስሮ ይቆያል።

ከአንድ ሺ ዓመታት በኋላ ሰይጣን ይፈታል። ለአጭር ጊዜ ይፈታተናቸዋል። ከዚያም የመጨረሻው ፍርድ ይሰጣል። ሃጢያት የሰሩ ሁለተኛ ሞት ይሞታሉ። ሰይጣንም አብሮ ይጠፋል። ከዚያም ዘለዓለማዊ የደስታ ህይወት በምድር ላይ ይሰፍናል። ሰው ከአንበሣ፣በጎች ከነብሮች፣ጅብም ከአህያ ተስማምተው ፍጥረታት በሙሉ በጸጋ እና በደስታ የሚኖሩበት ዘመን ይጀመራል።

የእየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት በጣም በአጭር ጊዜ የሚጠበቅ ነው። እንዲያውም መሰራቹ ቻርለስ ራስል እንደተነበየው በመጽሀፍ ቅዱስ ንባብ መሰረት በስሌት ተደርሶበታል የሚባለው እየሱስ ክርስቶስ ከአምላክ በተሰጠው ሥልጣን ከ1914 ዓ.ም ጀምሮ ንጉስ ሆኖ እየገዛ ነው። በዚህ በ1914 ዓ.ም ከነበሩት ሰዎች ውስጥ የአሁኑ ክፉ ዓለም እስከሚጠፋ ድርስ የማይሞቱ አሉ ተብሏል። በዚህ መሰረት የመጨረሻው ቀን በጣም ተቃርቧል ይባላል።

ዛሬ የጄሆቫ (ያህዌህ) ምስክሮች ለመንፈሳዊ ተግባር እንጂ ለዚህ ዓለም ግዴታዎች ቁብ የላቸውም። ለምሣሌ በወታደራዊ አገልግሎት ለመሰማራት ወይም ዘመቻ ለመሄድ መንግስቶች የሚያውጁትን አዋጅ

አይቀበሉም። አያምኑበትም። "ሰይፍ የሚያነሱ ሁሉ ይጠፋሉና ሰይፍህን ወደ ስፍራው መልስ" (ማቴ 26÷52) ስለሆነም በጦርነት ጊዜ ብዙ ችግር ላይ ሲወድቁ ይታያል። እነሱም ግን በጽናት ይቋቋሙታል።

በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ለምሳሌ ነፍሱ ደሙ ያለችበትን ስጋ አትብሉ (ዘፍጥ 9÷4) በሚለውና በመሣሉት መሠረት የዚህ ሃይማኖት አማኞች ለታመመ ሰውም ቢሆን ደማቸውን አይለ ግሱም። እነሱም ቢታመሙ ወይም ደም ቢፈሳቸው የሌላ ሰው ደም እንዲሰጣቸው አይፈቅዱም።

ሃይማኖቱ ቀሳውስት ወይም መንፈሳዊ ባለሥልጣናት የሉትም። አማኞች ግን በስብሰባ ቦታ ብቻ ሳይሆን ከቤት ወደ ቤት እየተዘዋወሩ በየሠፈሩ ውስጥ እንዲያስተምሩ ይጠበቅባቸዋል።

ግን በ1914 ዓ.ም የነበረ ትውልድ ሳያልፍ በፊት ዓለም ታልፋለች የሚለው ትምህርታቸው ባለፉት ዘመናት ተከታዮ ቻቸውን ለማዘጋጀትና ለማነሳሳት በጣም የረዳ ቢሆንም ጊዜው እየራቀ ሲሄድ ተቀባይነቱ እየቀነሰ መምጣቱ ግድ ይሆናል።

3- አዲሱ የሐዋሪያት ቤተ ክርስቲያን

ይህ ቤተ ክርስቲያን የተጀመረው በ19ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በ1832 ዓ.ም አካባቢ ነው። በ1835-1838 ዓ.ም መካከል ባሉት ዓመታት በተካሄደው ጥናት አንድ የሃይማኖት መግለጫ ወጣ። በዚህም መሰረት በእየሱስ ክርስቶስ ጊዜ የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን በሐዋሪያት ትመራ ነበረ። እየሱስም ስልጣኑን የሰጠው ለሐዋሪያት ነው። "አብ እንደላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ"። አላቸው። ይህንንም ብሎ እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ። "ሃጢያታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል። የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል።" አላቸው። (ዮሐ 20÷21-23)

ስለዚህ "የቀድሞይቱን የሐዋሪያት ቤተ ክርስቲያን የመሰለች በሐዋሪያት የምትመራ አዲሲቱ ቤተ ክርስቲያን እንድትኖር ይገባል።" በሚል እምነት ተነስተው ተደራጁ። የጀርመን (ፕሩስያ) ንጉሥ ፍሬድሪክ ዊሊያም አራተኛ ይህንን መግለጫ አምኖ በመቀበል ሃይማኖቱን በአገሪቱ እንዲስፋፋ ተባበረ። ስለሆነም የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በሐዋሪያ መመራት አለበት የሚለው አስተምሮት ተስፋፍቶ ዛሬ በሁሉም አህጉሮች በ170 ሀገሮች ወደ ስድስት ሚሊዮን ያህል ተከታዮች አሉት ይባላል።

ዋናው ሐዋሪያ አንድ ሆኖ በስሩ ለየክልሉና ለየወረዳው ሐዋሪያት ይሾማሉ። ዛሬ በዓለም ላይ በዋናው ሐዋሪያ አመራር ሰጭነት 18 የክልል ሐዋሪያቶች አሉ። በእነዚህ በእያንዳንዱ ስር የአውራጃ ወይም የወረዳ ሐዋሪያ ይኖራል። በስሩ ተጨማሪ ሐዋሪያቶች ኤጲስቆጶሶች (አቡኖች) ሽማግሌዎች ወንጌላውያንና ካህናት እንዲሁም ዲያቆናትና ምክትል ዲያቆናት ይኖራሉ። ሐዋሪያት ሁሉ (ዋናው ጭምር) በጉባኤው እየታየ እንደብቃታቸው የሚሾሙና ሲያስፈልግም በጡረታም የሚገለሉ ይሆናሉ። አመራሩ እንግዲህ በማዕከላዊነት የሚመራ ነው። ለምሳሌ በየቤተ ክርስቲያኑ የሚሰጠው የሰንበት ሰበካ ወይም ትምህርት በቄሱ ፍላጎት

የሚመረጥ ሳይሆን ከበላይ በተላለፈ መመሪያ መሠረት ስለሆነ በዕለቱ በዓለም ዙሪያ የሚሰጠው ትምህርት አንድ ነው።

ቅዱሳን ምስጢራት

አዲሲቱ የሐዋሪያት ቤተ ክርስቲያን ሶስት ቅዱሳን ምስጢራት ትሰጣለች።

1- ቅዱስ ጥምቀት፡- ይህ እንደገና በክርስቶስ ለመወለድ የሚደረግ የመጀመሪያ እርምጃ ነው። ከአዳም የተወረሰውን ሃጢያት ለማስወገድ የሚቻለው በጥምቀት ነው። ጥምቀት በቄስ ወይም ከዚያ በላይ ስልጣን ባለው ሰው ሊሰጥ ይችላል። ጥምቀቱ በመነከር አይደለም። ራስ ላይ ውሃ በማፍሰስም አይደለም። መስቀሉን ወይም ጣቱን) ውሃ ነክሮ ግንባር ላይ በማፍሰስ (በማስነካት) ነው። ውሃው በቅድሚያ ይባረካል። ቄሱ ይህን ውሃ በስመ እግዚአብሔር አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ እባርካለሁ፣ በዚህም ሰው ላይ የማጠብ ሃይል ያለውን የሰማይ ቅዱስ ውሃ አወርዳለሁ" ሲል ይባርካል። ከዚያም የሰውየውን ግንባር በማስነካት "በስመ እግዚአብሔር አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አጠምቅሃለሁ።" በማለት ያጠምቃል።

ጥምቀት ለህጻናትም ይሰጣል። (በወላጆቻቸው አቅራቢነት) መሰጠትም አለበት። የተጠመቁና ያልተጠመቁ በአንድ ላይ መኖር አይገባምና። ልጆች በኋላ ሲያድጉ (14-15 ዓመት ዕድሜ ሲሆናቸው) የአንድ ዓመት የእምነት ማጽኛ ትምህርት ይሰጣቸውና ምርቃት (ኮንፈርሜሽን) ይቀበላሉ። ይህ ሙሉ ሃላፊነትን (ከወላጅ ሃላፊነት ነጻ መሆንን) ያጎናጽፋቸዋል። ለማስተማርም ብቃት ይሰጣቸዋል።

2- ቅዱስ ጎትመት

ሰው ከመንፈስና ከውሃ ካልተወለደ በስተቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም (ዮሐ 3÷5) በተባለው መሠረት ቅዱስ ጥምቀትን የወሰደ ሰው በቅዱስ ጎትመት የተሟላ ማድረግ አለበት። ቅዱስ ጎትመት በሐዋሪያ ብቻ የሚሰጥ ነው። ሌላ ማንም አገልጋይ ሊሰጥ አይበቃም። ሐዋሪያው እጁን በተቀባዩ ራስ ላይ በመጫን ጸሎት ያደርጋል። በዚህም ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ይወርዳል። ሐዋርያው ሲናገር "አንተ ከእግዚአብሔር አብ እና ከጌታችን እየሱስ ክርስቶስ የመጣውን መንፈስ ቅዱስ ተቀበል . . ." ከዚህ ቀን በኋላ ተቀባዩ በእግዚአብሔር ቤት እንግዳ አይሆንም። ከቅዱሳን ጋር ሙሉ ዜግነት ተሰጥቶታል ይባላል። ከዚህ በኋላ ቁርባን መውሰድ ይጀምራል።

ቅዱስ ቁርባን

ቅዱስ ቁርባን የሚከናወነው ሳይቦካ በተጋገረ ህብስት ላይ ሶስት ጠብታ ወይን ተደርጎበት በካህን ተባርኮ ለተቀባዩ ሲሰጥ ነው። "ስጋዬን ያልበላ ደሜን ያልጠጣ ሕይወት የለውም" በተባለው መሠረት አማኞች በየሳምንቱ ቅዱስ ቁርባን መውሰድ ይጠበቅባቸዋል። ይህም በቅዳሴ ሥርዓት ውስጥ ይከናወናል።

የቅዳሴ ሥርዓት

የአዲስ ሐዋሪያት ቤተ ክርስቲያን የቅዳሴ ሥርዓት ዘወትር እሁድ የሚከናወን ሲሆን ዝርዝሩም እንደሚከተለው ነው።

1- መዝሙር በመዘመር (በጋራ) ይጀመራል።

2- ቄሱ ጸሎት ያደርሳሉ።

3- ትምህርት ይሰጣል (ርዕሱ ዋናው ሐዋሪያ ባስተላለፉት መመሪያ መሰረት መሆን ይገባዋል)

4- አንድ ወንድም እንዲያስተምር ይጋበዝና መዘምራን ከዘመሩ በኋላ ትምህርቱ ይሰጣል።

5- አቡነ ዘበሰማያት (አባታችን ሆይ) ይጸለያል።

6- የሃጢያት ስርየት ይታወጃል (ሃጢያታችሁ ይቅር ተብሏል እንደ ማለት)

7- ሕብስቱና ወይኑ ተባርኮ ቅዱስ ቁርባኑ ይሰጣል። (ጥምቀትና ጎትመት አሚልተው ለተቀበሉ ብቻ)

8- ስብሃት (የምስጋና ጸሎት) ይጸለያል።

9- አሜን ይባላል (በዜማ መልክ ሆኖ ሶስት ጊዜ በመደጋገም)

10- መሪውና ዲያቆናቱ ቀድመው ምዕመናንን በማስከተል ይወጣሉ።

"ሰላም" ተባብለውም ወደ የቤታቸው ይለያያሉ።

የእምነቱ ፍሬ ሃሳቦች

እምነቱ በአጠቃላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ሆኖ አንዳንድ ትኩረት የሚሰጥባቸው ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።

እግዚአብሔር በልጁ በእየሱስ ክርስቶስ ስጋ ለብሶ መገለጹን የእግዚአብሔርን ቃል የሚያሰራጩና ጸጋውንም የሚያድሉ መንፈስ ቅዱስ የሚያቀብሉ (በቅዱስ ጎትመት) ሐዋሪያት ናቸው። የሐዋሪያት አገልግሎት የቀድሞዎቹ እንዳለፉ ተቋርጦ የነበረ ቢሆንም አሁን እንደገና ከ19ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ ቀጥሏል። ቤተ ክርስቲያንን የሚመሠርቱትና የሚመሩት ሐዋሪያት መሆን ይገባዋል። በትንሣኤ ጊዜ እየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ ሲመጣ 144000 ከሆኑ ጻድቃን ጋር (የአሁኖቹን ሐዋሪያት ጨምሮ) አንድ ሺ ዓመታት ይገዛል። በዚህን ጊዜ ሌሎች በቀድሞው ዘመናት የክርስትያን እምነት ለማወቅ ዕድል ያልነበራቸው ሁሉ አሁን እኩል ዕድል ይሰጣቸዋል። ሰይጣን በዚህን ጊዜ ታስሮ ስለሚቆይ ዘመኑ ፍጹም የሰላም ዘመን ይሆናል። "ተኩላ ከበግ ጋር ይቀመጣል። ነብርም ከፍየል ጋር። አንበሳም እንደበሬ ገለባ ይበላል፤ ከላሞች ጋርም አብሮ ይወጣል"። የተባለው ትንቢት ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል ይባላል። በዘመኑ

መጨረሻ ሰይጣን ተፈቶ ይለቀቃል። ሕዝቦችንም ለማሳሳት ይሞክራል። ከዚያ በኋላ የመጨረሻ ፍርድ ይሰጣል። እርግጥ በአሁኑ ዘመን ገሐነመ እሣት የሚባል ነገር አለ ተብሎ አይታመንም። መኮነን ማለት ከጌታ እየሱስ ክርስቶስ ርቆ መገኘትና ብቸኛ በመሆን ዘለዓለም ሲጸጸቱ መሆር ነው ተብሎ ይታሰባል። የዳኑትም ከእግዚአብሔር ጋር በሀብረት የዘለዓለም ደስታን ይካፈላሉ። ይህም ጌታ አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርን በሚፈጥርበት ይሆናል።

የእስልምና ሃይማኖት

መግቢያ

የእስልምና ሃይማኖት በሰባተኛው ምዕተ ዓመት ተጀምሮ በአጭር ጊዜ ውስጥ በመስፋፋት በዓለም ዙሪያ ሊዳረስ የቻለ ነው። ዛሬ ወደ ቢሊዮን የሚጠጉ ተከታዮች አሉት።

ሃይማኖቱ የተጀመረው በሳኡዲት አረቢያ በሜካ ከተማ ነው። ነቢዩ መሐመድ እንዳስረዳው አላህ (እግዚአብሔር) የገለጸለትን ዕውቀት ወይም እውነታ ለሕዝብ አስተማረ። እነኝህም ትምህርቶችና ትዕዛዛት በኋላ ተሰብስበው በአንድ ጥራዝ ተዘጋጁ። ይህ መጽሀፍ ዛሬ በሰፊው የሚታወቀው ቅዱስ ቁርአን ነው። የሃይማኖቱ ዋና መሠረትም ይህ ቅዱስ መጽሀፍ ነው። በሙስሊሞች እንደሚታመነው በዚህ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ቃላት በቀጥታ በመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለመሐመድ የተነገሩት ናቸው። የመጽሀፉም ኦርጂናል ኮፒ በመንግስተ ሰማያት በአላህ ዙፋን አጠገብ ተቀምጠ ይኖል።

እርግጥ የመጽሀፉ አቀራረብ ቅደም ተከተል ለነቢዩ መሐመድ እንደተነገረው ላይሆን ይችላል። ይህ በ114 ሱራዎች (ምዕራፎች) የተከፈለ መጽሀፍ የምዕራፎቹ አቀራረብ በአጭር ጸሎት በመጀመር ከዚያም ከትልቁ ምዕራፍ ወደ ትንሿ ምዕራፍ በቅደም ተከተል የተቀመጠ ይመስላል። በሜካ ከተማ የተገለጸለትና በሜዲና ከተማ የተገለጸለት ሁሉ በአንድ ላይሆነው ቀርበዋል።

ሌላው የሃይማኖት መጽሀፍ ሱና የተባለው ነው። ይህ ስለ ነቢዩ መሐመድ የሕይወት ታሪክ ስለ አስተምሮቱ እና ስለተአምራቱ የሚገልጽ በፀኛው ምዕተ ዓመት የተቀነባበረ መጽሀፍ ነው። እርግጥ ይህንን መጽሀፍ ሁሉም የእስልምና ተከታዮች ይቀበሉታል ለማለት ሳይሆን የሳኡዲት አረቢያ እና የሌሎች በርካታ አገሮች ዜጎች የሚቀበሉት ዋነኛ ሰነድ ነው። አማኞቹም ሱናይት ሙስሊሞች በመባል ተለይተው ይታወቃሉ።

የእስልምና ሃይማኖት ይዘት

የእስልምና ሃይማኖትን ዓለም አቀፍ ደረጃ ሊያደርሰው የቻለው መሰረታዊ ምክንያት ሃይማኖቱ ቀላል እና በሰፊው ሕዝብ ዘንድ ግንዛቤ ሊያሣድርና ሊታመንበት በመቻሉ ነው። እምነቱ በአንድ እግዚአብሔር

አላህ ነው። መሐመድ ነቢዩ ነው። አላህ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ። አዳምና ሄዋን (የመጀመሪያዎቹ ሰዎች) በሃጢያታቸው የተነሣ ከገነት ወጡ። ከዚያም በኋላ የአላህን ቃል ለማስተማር ብዙ ነቢያት ተልከዋል። ለምሣሌ የኖህ የአብርሃም፣የሙሴ ስራዎች ይታመንባቸዋል። ይስሀቅ ያዕቆብ ዮናስ፣ኢዮብ ሰለሞን፣ዳዊት እንዲሁም እስማኤል የእግዚአብሔር መልዕክተኞች መሆናቸው ይታመናል። እየሱስ ክርስቶስም በአላህ እንደተላከ ነቢይ ይወሰዳል። ትምህርቱም ተቀባይነት አለው። የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑና በአይሁዳውያን ተሰቅሎ ሞቶ በሶስተኛው ቀን ማረጉ ግን አይታመንበትም። ስለሆነም ስላሴዎች አይታመንባቸውም። እየሱስ ግን በመጨረሻው በአላህ ፈቃድ ወደ ሰማይ መወሰዱ ይታመንበታል።

ቅዱስ ቁርዐን ስለ ድንግል ማርያም አንድ ሱራ (ምዕራፍ) አለው። 19ኛው ሱራ ርዕሱ ሱራማርያም ሲሆን እሷን በሚመለከት በሰፊው የተጻፈበት ነው። የእየሱስ ስም በቁርዓን ውስጥ 25 ጊዜ ተጠቅሷል ይባላል። ማርያም እየሱስን በድንግልናዋ መውለዷን ለዚህም በቅድሚያ የተመረጠች የዓለም ሴቶች ሁሉ በላይ መሆኗንና ይህንንም መልአኩ ገብርኤል እንደነገራት ሁሉ ተቀባይነት አለው። ግን በመንፈስ ቅዱስ ጣልቃ ገብነት ሳይሆን እግዚአብሔር ይሁን ባለ ብቻ የተጸነሰ ነው። እየሱስም የተለያዩ ተአምራት መስራቱን (ለምሣሌ አልአዛርን ከሙታን ማስነሣቱን) ሙስሊሞች ይቀበላሉ። ነገር ግን እየሱስ ክርስቶስ ነቢይ እንጂ አምላክ አይደለም በማለት ክርክር አላቸው። ከመከራከሪያ ነጥቦች አንዳንዱን ለማስታወስ ያህል፡- ራሱ ለእግዚአብሔር ይጸልይ እንደነበረ እንዲሁም በራሱ አንደበት ራሱን እንደአምላክ አለመግለጹ እና የሰው ልጅ ማለቱን ያሰምሩበታል። "እኔና አባቴ አንድ ነን" (ዮሐ 10÷30) ያለው በሥልጣን ሳይሆን በተግባር ማለቱና እንዲሁም "መጀመሪያ ቃል ነበረ . . . ቃልም እግዚአብሔር ነበረ . . . (ዮሐ 1÷1) ተብሎ የተጻፈው የትርጉምና የአቀራረብ ጉዳይ መሆኑን ያምናሉ። የዓለም መጨረሻ ሲመጣ ሙታን እንደሚነሱ የታመነ ነው። ለፍርድም ይቀርባሉ። እንደየስራቸው ጻድቃን ወደመንግሥተ ሰማያት ሲገቡ ሃጥአን ደግሞ ወደገሃነም ይወርዳሉ።

በተረፈ ግን አላህ ከላካቸው ነቢያት ታላቁና የመጨረሻው መሐመድ ነው። ቅዱስ ቁርዓንንም ያመጣልን እሱ ነው። በአይሁዳውያን መጻህፍት የተተነበየው ታላቅ መሪ እሱ ነው። እግዚአብሔር እየተባለ የተጻፈለትም አላህ ነው። ግን አይሁዶች እና ክርስቲያኖች ይህንን ስላልተቀበሉ ተሳስተዋል። (ሱራ 4÷136) የሙስሊሞች አምስቱ ዋና ተግባሮች የሚከተሉት ናቸው። ሀ) እምነትን መግለጽ፣ ለ) መስገድ፣ ሐ) መጸም፣ መ) መመጽወትና ሠ) ከተቻለ የሐጂ ጉዞ (ወደ ሜካ ከተማ) ማድረግ። (ስለዝርዝሩ ገጽ 123 ይመልከቱ)። ነገር ግን አንድ ሙስሊም ከነዚህ ትዕዛዛት አንዱን በወቅቱ ለመፈጸም የሚያዳግተው ሁኔታ ሲፈጠርበት ሊያስተላልፈው ወይም ሊያሻሽለው ይችላል። ለምሣሌ በህመም ምክንያት ጸም መጸም የከበደው ሰው ጾሙን አስተላልፎ በሌላ ቀን ሊያካክሰው

ይችላል። የሙስሊሞች ጾም ማለት ከንጋት እሰከ ምሽት ምንም ዓይነት ምግብና መጠጥ አለመቅመስ ማለት ሲሆን ሌሊቱን ግን እንደተፈለገ ለመመገብ ይቻላል።

በሌሎች ሃይማኖቶች አማኞች ዘንድ ቅሬታንና ተቃውሞን የሚያስከትለው አንዱ የሙስሊሞች እምነት መንፈሳዊ ጦርነት (ጂሃድ) ነው። በዚህ አስተምሮት መሰረት በጣኦታትና በአማልክት የሚያምኑ ወገኖችን መዋጋትና ከተቻለ ማሳመን ነው። ካልተቻለ ደግሞ ማጥፋትና ንብረታቸውንም መውረስና መካፈል ነው ቁርዓን 8÷39 እና 41)። በዚህ መሠረት ጦርነቶች ተካሂደዋል። ስለሆነም ለሃይማኖቱ በስፋት መስፋፋት ረድቷል። መላው የሰሜን አፍሪካ አገሮች የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች እንዲሁም መካከለኛውና ደቡብ ምሥራቅ የእስያ አህጉር ክፍሎች በአንጻራዊ መንገድ በአጭር ጊዜ ውስጥ የእስልምናን ሃይማኖት ተቀብለዋል።

በምሥራቅ አፍሪካ ቀንድ ክርስቲያን ሆና የቀረችው ኢትዮጵያ ብቻ ነበረች። ይህም የሆነው ነቢዩ መሐመድ "ኢትዮጵያን አትንኩ" ባለው መሰረት ነው ይባላል። ነቢዩ ወደ ሜዲና በሸሸበት ጊዜ ወገኖቹ በከፊል ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በደህና ተስተናግደው ኖረው ስለነበር ኢትዮጵያ በነቢዩ ዓይን ልዩ ከበሬታ ስላተረፈች ሳይሆን አይቀርም። ዛሬ የጂሃድ መንፈሱ ምን ለማለት እና ለምን ዓላማ እንደሆነ እየተጠና እና ውጫዊ ጦርነትን ሳይሆን ውስጣዊ የእምነት ጥንካሬን ለማጉልበት እየተሞከረ ነው።

በተረፈ ሃይማኖቱ ለምዕመናኑ የወሰነው ስነ ምግባር ቀላል እና ተግባራዊ ሊደረግ የሚችል ነው። ለምሣሌ "ደግ ለስራልህ ደግ መልስለት፣በክፉ የመጣብህን በዚያው መልክ መልሰው፤ ቸር እና ደግሁን፣ ድሆችን ዕርዳ" በዚህ አንጻር "ጠላቶችህን አፍቅራቸው" የሚለውን ዓይነት የክርስቲያን ሃይማኖት ትዕዛዝ ተግባራዊ ለማድረግ ከባድ መሆኑ ይመለከታል።

ማህበራዊ ኑሮንም በተመለከተ ህጉ ቀላል ነው። ደሃ እና ሃብታም መኖራቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። የግል ሐብት በህግ ተከብሮ ይኖራል። በንግድ ላይ ማትረፍ ህጋዊ እና ተገቢ ነው። በሃራጣ ማበደር ግን ሃጢያት ነው።

እንግዲህ እነዚህ እምነቶች እና ትዕዛዛት ማንም ሰው ሊፈጽማቸው የሚችሉና ለግንዛቤም የማያስቸግሩ ስለሆኑ ተቀባይነት ሊያገኙ ይችላሉ።

ምናልባት በነዚህ ምክንያቶች ሞሮኮ ሊሆን ይችላል ክርስቲያኖች ወደ ሙስሊምነት ሲቀየሩ እንጂ ሙስሊሞች ወደ ክርስቲያንነት ሲቀየሩ በብዛት የማናየው።

ነቢዩ መሐመድ

መሐመድ በ570 ዓ.ም ገደማ በሳዑዲት አረቢያ በሜካ ከተማ ተወለደ። አባቱ አብደላህ ሲሆን እናቱ አሚናት ትባላለች። መሐመድ አባቱ የሞተበት ሳይወለድ ሲሆን እናቱ ደግሞ የስድስት ዓመት ልጅ ሲሆን ነው። ስለዚህ አስተዳደጉ መጀመሪያ በአያቱ በአቶ አብዱል ሙጠሊብ ቤት ሲሆን እሱም ከ2 ዓመት በኋላ ሲሞት ከአጎቱ ከአቶ አቡጣሊብ ቤት በእረኝነት አደገ። በአደገ ጊዜም በግመል ንግድ ከተሰማሩ ነጋዴዎች ጋር በመገናኘት ግመል እየነዳላቸው ወደ አቢሲኒያ ወደ ግብጽ እና መካከለኛው ምስራቅ ይጓዝ እንደነበር ተጽፏል። መሐመድ በስራው ጠባይ የተነሣና በሜካ አካባቢ በነበረውም ሁኔታ የተነሣ ከብዙ ሰዎች ጋር በመገናኘት ሰፊ አመለካከት አዳብሮ ነበረ።

በዚያን ጊዜ ሜካ የንግድ ማዕከል ነበረች። ኢትዮጵያ እና ሌሎች የአካባቢ አገሮች ከእስያ አገሮች (ለምሣሌ ሶሪያ፣ፍልስጤም) ጋር የሚገናኙት በሜካ መስመር ነበረ። ስለሆነም የተለያዩ ዜጎች በሜካ ይገናኙና ይኖሩ ነበረ።* በተጨማሪም የሮማው መንግስት እስራኤልን በወረረ ጊዜ አይሁዳውያን ከአገር ስለተሰደዱ ከፊሎቹ ወደ ሳዑዲት አረቢያ አቅንተው በሜካ አካባቢ ሰፈሩ። ከዚያም ወዲህ ክርስቲያኖች በሚሲዮን ስራ ገብተው የወንጌልን ቃል ለማዳረስ ሲሉ በብዛት ወደዚሁ ከተማ መጥተው ይኖሩ ነበረ።

ነገር ግን ከሁሉም በላይ ጎልቶ የሚታይ የነበረው የነዋሪዎቹ ባህል በጣአታት ማምለክ ነበረ። እጅግ ብዙ ዓይነት ጣአታት ነበሩ። መሐመድ በዚህ ሁኔታ ያዝን ነበረ።

መሐመድ ሃያ አምስት ዓመት ዕድሜ ሲሆነው ወ/ሮ ከዲጃ ከምትባል ቆንጆ እና ሃብታም ነጋዴ ጋር ተፋቅረው ተጋቡ። እርሷ የሶስት ልጆች እናትና የአርባ ዓመት ዕድሜ የሆናት በከተማው ታዋቂ እመቤት ብትሆንም የመሐመድ ግርማ ሞገስ እንዲሁም የስነምግባሩ ጠንካራነት መስጧት ስለነበር በጋራ ፍላጎት ተጋቡ። አስራ አምስት ዓመታት አብረው በመኖር ሶስት ሴቶች ልጆች አፍርተዋል።

መሐመድ አርባ ዓመት ዕድሜ ሲሞላው ራዕይ ማየት ጀመረ። በ"ሒራ" ተራራ ላይ በዋሻ ውስጥ ሲጸልይ ቆይቶ በኋላም መልአኩ ጅብሪል ተገልጾለት መሐመድ የአላህ ነቢይ እንዲሆን የተመረጠ መሆኑንና ሕዝቡ በአንድ በአላህ ብቻ እንዲያምኑ እንዲያስተምር መታዘዙን አስታወቀው። መሐመድም በዚያው ትምህርቱን መስጠት ቀጠለ። በየቦታው እየዞረ

---

*መሐመድ በተወለደበት ዘመን የመን የኢትዮጵያ ግዛት ነበረችና አገረ ገዢው አብርሃ ክርስትናን ለማዳረስ ወደ ሜካ ዘመተ። ሰራዊቱን የሚቋቋም ሃይል ስላልነበራቸው ነዋሪዎቹ ሸሹ። ግን ተአምር ተሰራ፣የወፎች መንጋ በሰራዊቱ ላይ የድንጋይ ናዳ አዘነበባቸው እና መለሳቸው። (ሱራ 105)።

ጣአታትን በሚያመልኩ ሰዎች መሃል በመኖኖት "ሌላ አምላክ ከአላህ በስተቀር የለም፣ መሐመድም ነቢዩ ነው" እያለ ያስተምር ጀመረ። ነገር ግን በጣአታትና አማልክት ያምኑ የነበሩ ሕዝቦች በቀጥታ ሊቀበሉት አልቻሉም። መሐመድም ሲያስተምር አብርሃም አባታቸው ጣአታትን እንዴት እንዳጠፉ አስተማረ። በቅዱስ ቁርአን መሰረት እንዲሁም በመጽሀፍ ቅዱስ መሰረት አብርሃም ሁለት ሴቶች ነበሩት። ከአንዷ (ሳራ ከምትባል ሚስቱ) ይስሐቅን ሲወልድ አስቀድሞ ግን ከሌላዋ (አጋር ከምትባለው) እስማኤልን ወልዶ ነበር። የይስሐቅ ልጅ ያዕቆብ ዘሮቹ እስራኤላውያን ሲሆኑ የእስማኤል ዘሮች ደግሞ አረቦች ናቸው። ስለዚህ አብርሃም በእግዚአብሔር የተባረከ የሁሉም አባት ነው።

ነገር ግን በጣአታት ማምለክ ቢቀር በዚህ የተነሣ ገቢያቸው የሚቀርባቸው በርካታ ሰዎች ነበሩ። እነሱም ሜካ የብዙ ሃይ ማኖቶች መናኸሪያ እና የተለያዩ ዜጎች መኖሪያ መሆኗ ቀርቶ በአንድ ሃይማኖት ጥላ ስር ትወድቃለች የሚል ስጋት በማን ጸባረቅ ትምህርቱን ተቃወሙ። ስለሆነም በጎሳው መካከል መከፋፈል መጣ። መሐመድ በአስር ዓመታት ውስጥ አቡበከር እና ኡማር የመሳሰሉትን ታዋቂ ደቀ መዛሙርት ቢያተርፍ እና በርካታ ተከታዮችን ቢያፈራም ሌሎች ደግሞ በርካታ ተቃዋሚዎች ስለተነሱበት ከተማውን ትቶ መሄድ ተገደደ፤ ወደሜዲና ከተማ ተሰደደ። ይህ ስደት (ሄጂራ) በ622 ዓ.ም ሲሆን ይህ ዘመን የሙስሊሞች ዘመን አቆጣጠር የጀመረበት ነው።

መሐመድ የሜዲናን ነዋሪዎች አስተምሮ አሳምኖ ሃይሉን በማሰባሰብና ወታደራዊ ጦር በማደራጀት በ630 ዓ.ም ወደ ሜካ ሊመለስ ቻለ። በዚያም ጠላቶቹን አሸንፎ ከተማዋን አስገብሮ የጣአታትን እምነት ከስር መሰረቱ ነቃቅሎ አጠፋ። ከዚያ በኋላ የቁማር ጨዋታንና የመጠጥ ስካርንም አስወገደ። በዚህ ሁኔታ የእስልምና ሃይማኖትም እየተስፋፋ ሄደ። ወደ ሌሎች አካባቢዎችም መሰራጨት ጀመረ።

መሐመድ በ632 ዓ.ም ሲሞት አስከሬኑ በሜዲና ከተማ ራሱ አሰርቶት በነበረው መስጊድ አጠገብ በሚገኘው በባለቤቱ በወ/ሮ አይሻ መኖሪያ ቤት ውስጥ በክብር አረፈ።

<u>የእስልምና መሰረታዊ ተግባሮች</u>

የእስልምና ተግባሮች በአምስት የእምነት ምስሶዎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። እነሱም፣

1- <u>እምነትን መግለጽ</u> (ሻሃዳ)

እስልምናን ለመቀበል የመጀመሪያው ማረጋገጫ የሚከተለውን መመስከር ነው። "ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ መሆኑን እና ነቢዩ መሐመድ የእርሱ መልዕክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ" ይህ ምስክርነት በአንድ ጊዜ የአማልክትንና የጣአታትን አምልኮት ያስክዳል። ነቢዩ መሐመድንም በተመለከተ ከሌሎች ቀደምት ነቢያት ሁሉ ታላቁና የመጨረሻው መሆኑን ያስ ምርበታል። ይህ ምስክርነት በየጸሎቱ የሚደጋገም ነው።

2- በቀን አምስት ጊዜ ሶላት መስገድ

ስግደት የሚከናወነው በየቀኑ አምስት ጊዜ በተወሰኑ ሰዓታት ነው። ይኸውም ኟት ሁለት ጊዜ ቀትር ላይ አራት ጊዜ በአስር ሰዓት ግዳማ አራት ጊዜ፣ ጀምበር ከጠለቀች በኋላ ሶስት ጊዜ፣ በምሽት ላይ አራት ጊዜ ይሰገዳል። የስግደቶቹም መለያ ስም እንደ ቅደም ተከተላቸው ሱብሂ ወይም ፈጂር፣ ዙሁር፣ ዐሱር፣ መግሪብ፣ እና ዒሻአ ይባላሉ።

ሁል ጊዜ ስግደት ከመደረጉ ቀደም ብሎ ይፋ ጥሪ ይደረጋል። ይህም የሙስሊም ህብረተሰብ አንድ ላይ ሆኖ ሊሰግድ እንዲችል ጊዜውን ለሁሉም ለማስታወቅ የሚደረግ ጥሪ ነው። ጊዜውና አቅሙ የፈቀደላቸው መስጊድ ይሰበሰባሉ። የቀሩት በየቤታቸው ሆነው ይፈጽማሉ።

የጥሪው መልዕክት የተወሰነ ነው። ጠሪው ሰው ሙዐዚዝን ወይም አዛን አድራጊ ይባላል። ሙዐዚዝኑ ከመስጊድ ከፍታ ላይ በመሆን ፊቱን ወደ ሜካ አዙሮ ጆሮዎቹን በሁለት ጣቶቹ ደፍኖ ይዞ የሚከተለውን ጥሪ በታላቅ ድምጽ ያስተላልፋል። ይህ ጥሪ በየቀኑ የሚሰማ ስለሆነ ለመከታተል እንዲያስችለን ቃል በቃል አቀርበዋለሁ።*

"አሏሁ አክበር (አራት ጊዜ)
አሸሀዱ አንላኢላህ አልለሏህ (ሁለት ጊዜ)
አሸሀዱ አንነ ሙሐመዲን ረሡሉሏህ (ሁለት ጊዜ)
ሐይያ ዐለልሰላህ (ሁለት ጊዜ) ፊቱን ወደቀኝ አዙሮ
ሐይያ ዐለልፈላህ (ሁለት ጊዜ) ፊቱን ወደ ግራ አዞሮ
አሏህ አክበር (ሁለት ጊዜ)
ላኢላህ ኢልለ-ሏህ (አንድ ጊዜ)
ትርጉሙም እንደሚከተለው ነው።
አላህ ከሁሉም በላይ ትልቅ ነው።
ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩን እመሰክራለሁ።
መሐመድ የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ።*
ወደ ሶላት ኑ።
ፍላጎታችሁን ወደምታገኙበት ኑ።
አላህ ከሁሉም በላይ ትልቅ ነው።
ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም።
በኟት ጥሪ ላይ (ለፈጅር ሶላት) ከአምስተኛው መስመር ቀጥሎ፡-

---

* ይህንን ጥሪ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሜዲና ያስተላለፈው ሙአዝዚን ድምጻዊው ኢትዮጵያዊ ቢላል እንደነበረ ተዘግቧል።

"አስ ሶላተ ኸይሩን ሚነን-ነውም" ይባላል። (ሁለት ጊዜ) ትርጉሙም፡

"ሶላት ከእንቅልፍ ይበልጣል" ማለት ነው።

ሙአዝዚኑ ሁለተኛ ጥሪ ሲደግም ሶላት ሊጀመር ነው ተዘጋጁ የሚል ሐረግ (ቀድ ቃመቲስ ሶላት) ጨምሮ ሁለት ጊዜ ይደጋግመዋል። ከዚያም "አሏህ አክበር" በሚለው ቀጥሎ ያጠናቅቃል።

ምዕመናን ጸሎት ቤት ከመግባታቸው በፊት መጽዳት (ውዱእ) ያስፈልጋቸዋል። ስለሆነም ለምሣሌ በየመስጊድ መግቢያ ላይ በሚገኝ ውሀ አማካኝነት እጅ፣ አፍ፣ አፍንጫ፣ ሙሉ ፊት፣ ክንድ ራስ፣(በማበስ ብቻ) ጆሮ እና እግር በጥንቃቄ ይታጠባሉ ከዚያም ስግደቱ ይቀጥላል።**

ሰጋጁ ፊቱን ወደ ሜካ አቅጣጫ አዙሮ በመቆም "አሏህ አክበር" በማለት ይጀምራል። እጆቹንም ወደ ጆሮ ግንዱ ከፍ አድርጎ መዳፉን በማሳየት መልሶ ከደረቱ በታች ያሳርፋል። እንዲሁ እንደቆመም አጭር የመግቢያ ጸሎት ያደርግና የቁርዓንን መክፈቻ ምዕራፍ ይደግማል። ከዚያም ሌላ ተጨማሪ የቁርዓን ምዕራፍ ወይም አንቀጽ መርጠ ይደግማል። ይህን ሲጨርስ እጆቹን አንስቶ አሏህ አክበር ካለ በኋላ ከወገቡ ጎንበስ ብሎ በእጆቹ ጉልበቱን ይደገፍና ጀርባውን አግድም ቀጥ አድርጎ "ክብሩ ይስፋ) የሚል ዓይነት የምስጋና ጸሎት ያቀርባል። ከዚያም ቀጥ ብሎ እየቆመ ሳለ እጆቹን እንደቀድሞው ወደ ጆሮ ግንዱ በማንሳት "አላህ የሚያመሰግነውን ሰው ይቀበለዋል። ጌታ ሆይ ምስጋና ላንተ ይግባህ ይላል።

ቀጥሎም "አሏሁ አክበር" እያለ በግንባሩ መሬት ይነካል። በዚህ ሁኔታ ሲሆን የተወሰኑ የሰውነቱ ክፍሎች የግድ መሬት መንካት አለባቸው። እነሱም ግንባር፣ የአፍንጫ ጫፍ፣ሁለቱም የእጆች መዳፎች፣ሁለቱም ጉልበቶችና የሁለቱም እግር ጣቶች ውስጣዊ ክፍል ናቸው። በዚህን ጊዜም "ምስጋና ይድረስህ ጌታዬ የሁሉ በላይ" እንደማለት ይላል (ሶስት ጊዜ)። ሌላ ጸሎትም ያክልበታል። ለምሣሌ "ጌታዬ ይቅርበለኝ ምህረትህ አይለየኝ ድረሻ ፈንታዬን ስጠኝ፣ አንተ መንገዱን ምራኝ" ይላል።

በመጨረሻም "አሏሁ አክበር" በማለት ቀና ብሎ ይቀመጣል። አቀማመጡም በግራ እግሩ ላይ ሆኖ ቀኝ እግሩ ግን እንደቀድሞው እንደ ተንበረከከ ይቀራል። እጆቹንም ጭኖቹ ላይ በማሳረፍ አጭር ጸሎት ያደርሳል። ለምሣሌ "አላህ ሆይ ይቅር በለኝ ምህረትም አድርግልኝ ቀጥተኛውንም መንገድ ምራኝ፣ጤንነትም ስጠኝ፣ሀላል የሆነ (የተፈቀደ) ችሮታ አድርግልኝ፣በደረጃም ከፍ አድርገኝ" ሊል ይችላል። ከዚህ በኋላ እንደገና በግንባሩ መሬት በመንካት (እንደፊተኛው) ጸሎቱን እንደዚያው ይደግማል። በዚህም የመጀመሪያው ዙር ስግደት ይፈጸማል። ይህ እንግዲህ ሷት ሷት ሁለት ጊዜ ሲደገም ቀንና ማታም በሀጉ መሰረት ተደጋግሞ ይጸለያል።

** የሚያረክሱ ሁኔታዎች ካልተከሰቱ ሷት የሚደረገው ውዱእ ለዚያ ቀን ሙሉ ሊያገለግል ይችላል።

በመጨረሻው ዙር እግሩ ላይ ቁጭ ብሎ እና በሁለት እጁ ጉልበቱን ተደግፎ ምስክርነቱን ይገልጻል። ነቢዩ መሐመድንና ቤተሰቡን ይመርቃል። ከዚያም ፊቱን ወደ ቀኝና ወደግራ በማዞር በየተራ የአላህ ሰላም በእናንተ ላይ ይሁን በማለት ስግደቱን ያጠናቅቃል። ካስፈለገው ግን ከዚያም በመቀጠል ጣቶቹን ወደ ላይ በማመልከት የራሱን የግል ጸሎት ሊያክልበት ይችላል።

ዕለተ ዓርብ ሲሆን የቻለ ሙስሊም ሁሉ ቀትር ላይ በአቅራቢያው ባለ መስጊድ ይሰበሰባል። ይህ አብሮ የመስገድ ስርዓት ደማቅ የሆነ ማህበራዊ ስርዓት ነው።

ከዚህ የበለጡ ግዙፍ ስብሰባዎች የሚደረጉት ለምሳሌ በኢድ አልፈጥር (ረመዳን) እና በኢድአልአድሀ (አረፋ) ጊዜ ሲሆን ዓለም አቀፋዊው የምዕመናን ስብሰባ ደግሞ በየዓመቱ ካዕባን ለመጎብኘት ሜካ ከተማ የሚገናኙበት ነው።

ማስታወሻ፡-

ሶላትን መስገድ (በቀን አምስት ጊዜ) ግዴታ ነው። ሶላትን ሳይሰግድ በሰንካላ ምክንያት የተወ ሰው በስንፍናው ስለሆነ አማጺ (ፉሲቅ) ነው፣ጭራሽ ከተወ ግን ከሐዲ (ከፊር) ነው። ለማንኛውም አማጺ ከሆነ ለመቀጣጫነት ሲባል ይገደላል። ከሐዲ ከሆነም ደግሞ በከሐዲነቱ ይገደላል ሲሉ አንዳንድ የመዝሃብ መሪዎችና ኢማሞች አቋም ወስደዋል።* ግን ያም ባይሆን ሙስሊሞች ሶላትን መተው ማለት በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ይሆናል።

3- ግዴታ ምጽዋት መስጠት (ዘካ መክፈል)

ምጽዋት መስጠት በቅዱስ ቁርዓን የታዘዘ ነው። ማንም ሰው ክግቢው ጥቂት እየቀነሰ መስጠት አለበት። ይህም ከእህል ምርቱ፣ ከፍራፍሬ ምርቱ፣ ከከብቱ ወይም ከወርቁ . . . ወዘተ . . . እያንዣ በየጊዜው የተወሰነ ድርሻ ለሌለው ወገኑ ማካፈል አለበት ማለት ነው (2.5% ያህል)።

በተለምዶ ዘካ የሚሰጠው ብዙውን ጊዜ በረመዳን ወቀት ነው። አንዳንድ ቦታ የሃይማኖት መሪዎች ወይም ድርጅቶች ተወክለው ምጽዋቱን በማሰባሰብ እንደዕርዳታ ማስተባበሪያ ይሰራሉ። ሆኖም ስጠታ ሁሉ በፈቃደኝነት እንጂ አስገዳጅ ባህርይ የለውም። ይህ ሰፊውን ድሃ ወገን ለመርዳት በጣም ጠቃሚ ተግባር ነው።

4- መጸም

ሙስሊሞች እንዲጸሙ ከታዘዙት አንዱ ከዓመቱ በዘጠነኛው ወር (ረመዳን በተባለው) የሚጸመው ነው። ሌሎችም በህግ ሳይሆን በፈቃደኝነት የሚጸሙ አሉ። ሙስሊሞች በሚጸሙበት ጊዜ ከንጋት እስከ ምሽት

*የሶላት መማሪያ ነጃሺ አሳታሚ (1988)። ገጽ 13-14

(ጀምበር ከመውጣቷ እስከ መጥለቋ) ከምግብና መጠጥ ይታቀባሉ። ሌሊት ግን የቻሉትን የፈለጉትን በደንቡ መሰረት ሊመገቡ ይችላሉ። ቀን ለመጾም የማይገደዱት ታማሚዎች፣ መንገደኞች እና በየምክንያቱ ያልቻሉ ናቸው። እነዚህ ግን በሚቀጥለው ወር ማካካስ ይኖርባቸዋል። አንድ ጿሚ ጾሙን አፈረሰ የሚያሰኘው ምግብ መጠጥ ሲጎራ፣ ሲወሰድ ወይም አውቆ ሲያስታውክ ወይም ግብረ ስጋ ግንኙነት ሲፈጽም ነው። ይህ እንግዲህ መካካስ ይኖርበታል። በጾም ጊዜ ምንም ዓይነት የሰውን ስሜት የሚጎዳ የሚያናድድ ወይም ፍትወት የሚቀሰቅስ ወሬ፣ ትችት፣ አሉባልታ ወይም ብልግና መነገር የለበትም። እያወቁ ምራቅ መዋጥም ክልክል ነው።

5- <u>ሐጂ ማድረግ</u> (ካዕባን መጎብኘት)

ሙስሊሞች የሆኑ ሁሉ ቢያንስ አንድ ጊዜ ሜካ ወደሚገኘው ታላቁ መስጊድ ጉዞ ማድረግ አለባቸው (አቅሙና ጤንነቱ ያላቸው)። ይህም ከዓመቱ በ12ኛው ወር (ዙል-ሂጃ በተባለው) ነው። የጉዞው ስርዓት የተለያዩ ክንውኖችን ያካትታል።

1ኛ- ሃራም (የሜካ ቅዱስ ክልል) ከመግባታቸው በፊት ምዕመናን ራሳቸውን ያጸዳሉ።

ይህም መጀመሪያ በመታጠብና 2 ጊዜ በመስገድ ነው። ከዚያም ልብሣቸውን ቀይረው ነጭ ቀሚስ ይለብሳሉ።

2ኛ- ሜካ እንደገቡ ታላቁን መስጊድ ይሳለማሉ ከዚያም የካዕባን ድንጋይ ሰባት ጊዜ ያዞራሉ። (ታዎፍ) ሁለት ጊዜ ሰግደውም ከዘምዘም ጉድጓድ ጠበል ይጠጣሉ።

የጉዞው ስርዓት የሚጀመረው በዙል-ሂጃ ወር በ7ኛው ቀን ነው። በመስጊዱ ስግደት ይደረጋል። ከቁርዓንም ትምህርት ይሰጣል። (ኩትባ)። ስለ ሃጂ ገለጻ ይደረጋል። ዙል ሂጂ 8 ቀን ወደ ሚና ከተማ (8 ኪሎ ሜትር ርቀት) ይኬድና ይታደራል። በማግስቱ ስግደት ይደረግና ወደ አራፋት (8 ኪሎ ሜትር) ይኬዳል። እዚያም እኩለ ቀን አለፍ ሲል ሁሉም ተሰብስቦ በሚገኝበት ስግደት ይከናወናል። ከዚያም ዋንኛው ስርዓት (ውቁፍ) ይጀመራል። ሁሉም ይቆሙና ነቢዩ መሐመድ በዚህ ቦታ ለመጨረሻ ጊዜ የሰጠውን የመሰናበቻ ትምህርት በማስታወስ በኢማም ትምህርት ይሰጣል።

ጀምበር እንደጠለቀች የመድፍ ተኩስ የስነ ስርዓቱን መጠናቀቅ ያበስራል። ያን ጊዜ በፍጥነት አራፋትን ጥለው በመውጣት ወደ ሜካ ይጓዛሉ። ሙዝዳሊፋ (7 ኪሎ ሜትር) ሲደርሱ ስግደት አድርሰው ሊያድሩ ይችላሉ። በማግስቱ ጀምበር ስትወጣ ስግደት ተደርጎ ጉዞ ይጀመራል። ሚና መንደር ሲደርሱ በሰይጣን በተመሰሉት ሶስት የድንጋይ ምስሎች በእያንዳንዳቸው ላይ ሰባት ድንጋይ ይወረውሩባቸዋል። ይህም ሰይጣንን ለማውገዝና ፈተናውን ለመቋቋም ሲሆን ሰይጣን አብርሃምን የተፈታተነውን በማስታወስ ነው። ከዚያም አብርሃም ልጁን እስማዔልን ለመስዋዕት ሲያቀርብ የበግ ሙክት የቀረበለትን በማስታወስ በግ ፍየል ወይም ግመል

በማረድ ታላቅ መስዋዕት ያቀርባሉ። ይበላሉ። ይህ የአረፋ በዓል ነው። ከዚያም ጸጉራቸውን ተላጭተው (ሴቶች ከሆኑ ለምልክት ተቆርጠው ልብሳቸውን ይቀይራሉ በተቻለም አዲስ ልብስ ይለብሳሉ። ከዚያም ወደ ሜካ ተጉዘው የካዕባን ድንጋይ ሰባት ጊዜ ይዞራሉ። በመጨረሻም ከአልሳፋ ወደ አልማርዋ (385 ሜትር ርቀት) በተቻለ ፍጥነት ይሮጣሉ። እዚያም ጸሎት አድርሰው ይመለሳሉ። ይህ ሰባት ጊዜ ይደጋገማል።

<u>ማስታወሻ፡-</u>

ዛሬ ረዥም የእግር ጉዞ በዘመናዊ አውቶቡስና መኪና ሊከናወን ስለሚችልና በየመንገዱም ማረፊያ ድንኳን ስለሚኖር የሃጂ ጉዞ ከባድ አይሆንም።


ሌሎች ተግባራት

ከአምስቱ መሰረታዊ ተግባራት በተጨማሪ ሌሎች መከበር ያለባቸው ተግባሮች አሉ። ለምሣሌ የግል ተግባርን በተመለከተ ሙስሊም የአሳማ ስጋ አይበላም፣ ቁማር አይጫወትም በአራጣ አያበድርም፣ ወይንጠጅ (አልኮል) አይጠጣም። ተባርኮ ያልታረደ ስጋ አይበላም።

ቅዱስ ቁርዓን የምዕመናኑን የግል ኑሮ ብቻ ሳይሆን ማህበራዊ ኑሮአቸውንም በተመለከተ መመሪያ ይሰጣል። ለምሣሌ ጋብቻ የሚከለከል በት የዝምድና ዓይነት፣የሚች ውርስ ለቀሪ ዘመዶች የሚከፋፈልበት ደንብ፣ የፍቺ (የባልና ሚስት) ስርዓት ወዘተ በዚህ ውስጥ ይካተታሉ። ስለሆነም ሃይማኖታዊ ፍርድ ቤት (ሸሪዓ) ከዚህ ይመነጫል። እንግዲህ አንድ ሙስሊም ህግጋትን ሊያከብርና ሊተገብር የሚችለው ከሌሎች የማህበረሰቡ አባላት ጋር በመተባበር ነው። ስለሆነም የራሱንም መብት ለመጠበቅ፣ ሃላፊነቱንም ሊወጣ እንዲበቃ ከሌሎች ምዕመናን ጋር መተባበርና መረዳዳት ግዴታው ይሆናል። የሁሉም የነቃ ተሳትፎ እና ጥረት አስፈላጊ ነው።

በሌላ አነጋገር በእስልምና ሃይማኖት መሰረት ሃይማኖትም እንደ አገር የጋራ ይሆናል። ማህበራዊ ሃላፊነትም ይኖረዋል። ዛሬ የሻሪያ ህግ ብሔራዊ ህግ የሆነባቸው አገሮሽ ጥቂት አይደሉም። ለምሣሌ ሱዳን፣ ሊቢያ፣ ኢራንና ሳኡዲት አረቢያ ይህንን ህግ ተግባራዊ ካደረጉት አገሮች መካከል ናቸው። ስለሆነም ሌባ ሰርቆ ተይዞ ከተፈረደበት ቀኝ እጁን ይቆረጣል። እንዲሁም ለምሣሌ ሚስት ስታመነዝር ከተገኘች እና የሞት ፍርድ ከተፈረደባት አንገቷን በሰይፍ ትቆረጣለች ወዘተ. . .።

በተጨማሪ ሴቶችን በተመለከተ ቀብር ቦታ መገኘት እንደማይገባቸው ባሎቻቸው ሶስት ጊዜ ደጋግመው “ፈትቼሻለሁ” ካሏቸው ሚስትነታቸው ወዲያው እንደሚቀር፣ ሐብት ንብረት መውረስን በተመለከተ ደግሞ ሴት ከሶስት አንድ እጅ የበለጠ ለማግኘት አለመቻሏ እና ከወንድ ጋር የምትካፈል ከሆነም ሴቷ የወንዱን ግማሽ ያህል ብቻ እንድታገኝ መደረጉ የእነዚህ አገሮች የብሔራዊ ህግ አካሎች ናቸው። (ስለ ውርስ ህግ በቁራን ሱራ ፬፣11-12 በዝርዝር ተሰጥቷል።)



ካዕባ - የሙስሊሞች ዋና ቅዱስ ቦታ እና የቂብላ (ስግደት) አቅጣጫ

የሃይማኖቱ መከፋፈል

ለእስልምና ሃይማኖት መከፋፈል ምክንያት ሆኖ የሚቀርበው ብዙውን ጊዜ የስልጣን ውርስ ነው። ነቢዩ መሐመድ ወንድ ልጅ አልነበረውም። ስለሆነም እሱ ሲሞት ስልጣኑንና ሃላፊነቱን የመውረስ ጉዳይ ጥያቄ አስነሣ እርግጥ በሃይማኖት መጽሀፍት አተረጓጎም ልዩነቶች ይኖራሉ። በተለይ ሃይማኖቱ ተስፋፍቶ ከምዕራብ አፍሪካ እስከ መካከለኛው ምስራቅ እና እስከሩቅ ምስራቅ ሲደርስ የሰዎች አመለካከት ለየት ማለቱ አይቀርም።

ነቢዩ መሐመድ ሲሞት በእርሱ እግር የተተኩት ካሊፍ መጀመሪያ አቡበክር ከዚያ በኋላ ደግሞ ኡመር (አማር) እና አስማን ነበሩ። እነዚህ ካሊፎች የመሐመድ የዘር ሃረግ የላቸውም። ሆኖም በችሎታቸው እና በእምነት ጥንካሬያቸው ታምኖባቸው በሕዝብ የተመረጡ ነበሩ። ነገር ግን እየቆየ ሲሄድ ይህ ሙሉ ተቀባይነት አጣ። ስለሆነም ልዩነት ተፈጠረ።

የሺያት እስልምና ተከታዮች

በፋርስ (ኢራን) የተጀመረ አንድ ንቅናቄ ወይም ፓርቲ አሊ የተባለን ሰው በመሪነት ይዞ ተነሳ። አሊ ከነቢዩ መሐመድ ጋር በአያት ይገናኛሉ። በዚያም ላይ አሊ ፋጢማን (የመሐመድን ሴት ልጅ) በማግባቱ አማች ነው። ስለሆነም የመሪነት ሥልጣን ለእርሱ ዘር እንደሚገባ አስታውቆ ተነሳ። መንፈሳዊ የአመራር ስልጣን ለነቢዩ መሐመድ የተሰጠው በዚሁ በእርሱ የዘር ግንድ እንዲቀጥል ነው እንጂ ማንም ተራ ሰው ባለመብት ሊሆን አይገባውም። በዚህ መነሻነት አሊ ጦርነት ቢገጥምም በፍልሚያው ተሸነፈ እሱም ተገደለ። ሆኖም ቀሪዎቹ ተከታዮች በኢራን ተሰባሰበው እንደገና ተጠናከሩ። እነሱ ዛሬ ሺያት (ወይም የአሊ "ፓርቲ") በመባል ከሌሎች ሙስሊሞች ተለይተው ይኖሩ። ትክክለኛው የስልጣን ተዋረድና ህጋዊ አሰራር የእነሱ መሆኑን ያምናሉ። እምነትንም በተመለከተ ሱና የተባለውን ስለነቢዩ መሐመድ የሕይወት ታሪክ የሚገልጸውን መንፈሳዊ መጽሀፍ አይቀበሉም። (በነአቡበከር እና አስማን አመራር የተዘጋጀ በመሆኑ)። ይህ ሃይማኖት እየተስፋፋ ሄዶ በ1500 ዓ.ም የፋርስ (ኢራን) ብሔራዊ ሃይማኖት ሊሆን በቅቷል።

ከዚህ ቀደም ባሉት ዘመናት እንደገና ተመሣሣይ የውርስ ጥያቄ ተነስቶ ሌላ መከፋፈል ተፈጥሮ ነበረ። ይህም በ878 ዓ.ም ነበረ።

የአሊ ዝርያ የሆነው 12ኛው ካሊፍ፡- መሐመድ አል-ሙንጣዘር ተሰወረ! ስለዚህ መንበረ ስልጣኑ ክፍት ሆነ። ነገር ግን በአማኞች ዘንድ ይህ ሰው መሲህ ሆኖ አንድ ቀን ተመልሶ እንደሚመጣ ያምናሉ። ይህ (አል) መሃዲ (መሲህ) ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ አንድ የሃይማኖት ሊቃውንት ቡድን (አያቶላ) ተመርጦ በተጠባባቂነት የአስተዳዳሪነቱን ሃላፊነት ተረክቦ ይመራል።

አል (መሃዲ) በዓለም መጨረሻ ተመልሶ ስለሚመጣ ይጠ በቃል።* ዛሬ ሺያቶች የራሣቸው ልዩ ስርዓት፤ ህግ እና የቁራን አተረጓጎም አላቸው።

እንደገና ደግሞ ከሺያት ፓርቲ ተገንጥሎ የወጣ ሃይማኖት ይኸ ል። የዚህ አዲሱ ሃይማኖት ተከታዮች እስማኤላውያን ይባላሉ። በእነሱ እምነት የሺያት ኢማም የዘር ሐረግ በትክክል አልወረደም። ስድስተኛው ኢማም በሞተበት ወቅት ሰባተኛው እና ህጋዊ ወራሹ ሙሳ አልካሲም መሆን አልነበረበትም። የእርሱ ታላቅ ወንድም (እስማኤል) ህጋዊ ወራሽ መሆን ነበረበት። እርግጥ ይህ ሕጋዊ ወራሽ በሕጻንነቱ ስለሞተ ወራሽ አላተረፈም። ቢሆንም ግን በህጋዊ አሰራር ከሆነ የመጨረሻው ኢማም እሱ መሆኑ ነው። እስማኤላውያን የራሣቸው ልዩ አሰራር ያላቸውና ጠንካራ የሚሲዮን ተግባር ያከናወኑ ናቸው።

እንደገና ከነዚህ (እስማኤላውያን) የሚገነጠሉ ድሩዝ ሙስሊሞች የሚባሉ አሉ። አልሃኪም የተባለው የድሩዝ አማኞች መንፈሳዊ መሪ በ1020 ዓ.ም ሞተ ቢባልም በትክክል ግን ወደ ሰማይ የአረገ ስለሆነ ዳግም ተመልሶ እንደሚመጣ ይታመናል። ድሩዝ ሙስሊሞች የስግደት ቀናቸው ሐሙስ እንጂ ዐርብ አይደለም ይባላል። ጋብቻቸውም አንድ ለአንድ ብቻ ነው።

ከሻይት እስልምና ተለይቶ የወጣው ሌላው ሃይማኖት በሃይ ሲሆን ይህ አድማሱን በማስፋትና ሌሎቹንም ሃይማኖቶች በማቀፍ ዓለም አቀፍ ዕውቅናን አትርፏል። (ገጽ 138 ይመልከቱ)።

የሱና እስልምና ተከታዮች

ዛሬ በዓለም ዙሪያ የሚኖሩ አብዛኞቹ ሙስሊሞች (በሳኡዲት አረቢያ የሚኖሩት ዋናዎቹ መሪዎች ጭምር) የሱና እምነት ተከታዮች ናቸው። (የሺያት ፓርቲ ተገንጥሎ የወጣው ከዚህ ሃይማኖት ነበረ) እነዚህ የሱና ዕምነት ተከታዮች "ሱና" በተባለው መንፈሳዊ መጽሀፍ ጭምር የሚያምኑ ናቸው። ይህ የመሐመድን ሕይወት ታሪክና ተአምራቱን የሚያወሳ መጽሀፍ ነው። ቅዱስ ቁርአን የእግዚአብሔር ቃል መሆኑ የነዚህም መሰረታዊ እምነት ነው። እርግጥ በጊዜ ሂደት አንዳንድ እምነቶችና ልምዶች ላላ ወደ ማለት አዘንብለው ነበረ። ነገር ግን በ18ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ አካባቢ አንድ ወሳኝ ምዕራፍ ተከፈተ። መሐመድ አብደልዋሃብ (በ1792 የሞተ) እስልምና ወደ ጥንቱና ንጹሁ እምነት መመለስ አለበት በማለት ተነሳ። እስልምና ከምዕራባውያን የባህል ብክለት መንጻት አለበት ሲልም አስተማረ። የእርሱ ተከታዮች ዋሃቢስ ይባላሉ። ዋሃቢስ ከመካከለኛው ሳውዲት አረቢያ አካባቢ ተነስተው እየተጠናከሩ

* ከ1881-1898 በግብጽ በኩል ወደ ሱዳን ከዚያም ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ዘልቆ የመጣው የማህዲ ንቅናቄ በጦር መሪው መሐመድ አህመድ የተመራ ሲሆን ይህ የጦር መሪ ራሱን "ማህዲ" ብሎ አሳታወቀ። የመጀመሪያው ተልዕኮዉ የአፍሪካን ሙሲሊሞች ከአውሮፓ ቅኝ ግዛት ነጻ ማውጣት ነው በማለት አስታወቆ ሲነሣ ከአጼ ዮሐንስ ጋርም ጦርነት ገጥሞ አንገታቸውን መቁረጡ ይታወቃል።

መጡ። በመካከሉም ከሱድ (Suud) ቤተሰብ ትኩረትን አገኙ። የሱድ ቤተሰብ በዋና ከተማው በሪያድ የነበረ የጣዢ መደብ ነው። የዋሃቢስ ድርጅት ከሱድ ቤተሰብ ጋር በመተባበር በ1806 ዓ.ም ሜካ ከተማን ያዙ። በዚያ ይገኝ የነበረውንም መጤ-ባህል እና አስተሳሰብ አስወገዱ። ከዚያም እየተስፋፉ ወደ ሌሎች ክልሎችና አገሮች መዝመት ጀመሩ። ነገር ግን ግብጽ ላይ ሲደርሱ በ1818 ዓ.ም ከግብጽ መሪ መሐመድ አሊ ጋር ጦርነት ገጥመው ተሸነፉ። ሂደታቸውም በዚያው ተገታ። ሆኖም የሱድ ቤተሰብ ሥልጣን በአረቢያ መስፋፋት ቀጥሎ በ1932 ዓ.ም በቤተሰባቸው ስም የሳዑዲት አረቢያን ንጉሣዊ መንግስት መሰረቱ። ከዚያ ወዲህ የዋሃቢ እምነት ብሔራዊ ሃይማኖት ሆኖ ዛሬም ሜካ በማዕከልነት ለዓለም ሙስሊሞች ሁሉ ታገለግላለች።

መስጊድ

መስጊድ በጣም ጉልህ ሕንጻ ስለሆነ በሩቅ ይታያል። ረጅም ፎቅ ይኖረዋል። ለጸሎት ጥሪ የሚተላለፈው ከዚያ ከፍታ ላይ ነው። "አሏሁ አክበር" እየተባለ በየቀኑ አምስት ጊዜ ጥሪ ይተላለፍበታል። ከዚህ ፎቅ ጎን ትልቅ ክብ (ግማሽ ሉል) ጣሪያ ያለው እና የእስልምና መለያ የሆነው ግማሽ ጨረቃ ምልክት ቅርጽ ከበላዩ የሚታይበት ሕንጻ ይኖራል። ይህ መስጊድ ነው።

በመስጊዱ ውስጥ ሰፊ አዳራሽ አለ። ከውጭ ሲገቡ አዳራሹ መጨረሻ ላይ ትንሽ በር መሣይ ብትኖር ይህች ሜካ ከተማ የሚገኝባትን አቅጣጫ (ቂብላ) የምታመለክት ትሆናለች። ስግደት ሁልጊዜ የሚደረገው ወደዚያ አቅጣጫ ነው። ከፊት በጎን በኩል ሰብከት መስጫ መድረክ (በደረጃ የሚወጣበት)ይኖራል።

ከአዳራሹ መግቢያ ላይ ሴቶች ወደ ሚቀመጡበት ሰገነት (ፎቅ) የሚያስወጣ ደረጃ ይኖራል። ፎቅ ከሌለ ምድር ቤት ከታች ይኖራል። አለበለዚያ ከጎን በኩል ሌላ ክፍል ወይም አዳራሽ ይኖርና ይህ ለሴቶች ያገለግላል። ሰነ ስርዓቱን ከወንዶች ጋር በአንድ ላይ ለማከናወን እንዲቻል የጸሎት መሪው ድምጽ በድምጽ ማጉያ ሊተላለፍላቸው ይችላል።

ከአዳራሹ ውጭ በር አጠገብ ውሃ ይኖራል። ይህ ምዕመናን ሁሉ ለጸሎት ከመግባታቸው በፊት የሚጸዳዱበት ነው።

ዓርብ ቀትር ላይ ሁልጊዜም ስግደት ስለሚኖር ሰብሰባው ትልቅ ነው። ሰነ ስርዓቱን ለማካሄድ የሚኖሩት መንፈሳዊ መሪዎች 1/ ኢማም የጸሎት መሪ 2/ ሰባኪ፡- (የዕለቱን ስብከት የሚያቀርበው እና 3/ ሙአዘዚን (ጥሪውን ለምዕመናን የሚስተላልፈው) ናቸው። እንደ መስጊዱ ትልቅነት ወይም አነስተኛነት ብዙ ኢማሞችና ሙአዘዚኖች ሊኖሩ ሲችሉ አንድ ወይም ሁለት ሆነውም ሰነ ስርዓቱን ሊያካሂዱ ይችላሉ።

በመስጊዱ ውስጥም ሆነ በአካባቢው ምንም ዓይነት ስዕል ወይም ቅርጻ ቅርጽ አይታይም። ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም። አላህም በስዕል አይገለጽም "አላህ ፍጡርን አይመስልም፣ፍጡራንም እሱን አይመስሉም (112፣4)

በዓላት

በሙስሊም እምነት ተከታዮች ዘንድ ከሚከበሩት በዓላት ውስጥ አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው።

	የወር ቀናት	የበዓሉ ምክንያት
1- ሙሃራም	1 ቀን	የአዲስ ዓመት መጀመሪያ ቀን።
2- ራቢ	1 ቀን*	መውሊድ፣የነቢዩ መሐመድ ልደት።
3- ረጀብ	27 ቀን	ነቢዩመሐመድ ወደ መንግስተ ሰማያት ደርሶ የተመለሰበት (በእየሩሳሌም በኩል)
4- ረመዳን	1 ቀን	የጾም መግቢያ።
5- ረመዳን	27 ቀን	ቅዱስ ቁርዓን ለነቢዩ መሐመድ ከሰማይ የወረደለት ቀን
6- ሸዋል	1 ቀን*	ኢድ አልፈጥር (ጾም የሚፈታበት ቀን)።
7- ዙልሂጃ	8-13 ቀን	የሜካ ጉዞ በዓል።
8- ዙልሂጃ	10 ቀን*	አረፋ፣መስዋዕት የመስጫ ታላቅ በዓል።

ዓርብ ቀን ሁል ጊዜ የስግደት ቀን ነው። (በተወሰነ ስዓት)።

በእስልምና ዘመን አቆጣጠር የዓመቱ ወሮች 12 ናቸው። ነገር ግን ወሩ የጨረቃ ወር ነው። ስለዚህ እያንዳንዱ የበዓል ቀን በየዓመቱ ዞሮ ሲመጣ በእኛ አቆጣጠር በተለያዩ ወራትና ቀናት ላይ ሊውል ይችላል። ለምሳሌ መውሊድ በአንድ ዓመት ውስጥ ሁለት ጊዜ ሊደርስ ይችላል። ለዚህ ምክንያቱን ለመረዳት ስለጨረቃ ወር ጠለቅ ብለን እንመልከት።

የጨረቃ ወር

እንደሚታወቀው ጨረቃ ትወለዳለች፣ ታድጋለች። ሙሉ ጨረቃ ከሆነች በኋላ ደግሞ እንደገና እየቀነሰች በመሄድ ትጠፋና እንደገና ትወለዳለች።

የጨረቃ ወር የሚባለው ጨረቃ ከተወለደችበት (እንደቀሟን ደጋን ከታየችበት) ዕለት ጀምሮ አንድ ዙር እስኪሞላ ነው።

*እነዚህ ቀናት በኢትዮጵያ ብሔራዊ በዓላት ሆነው ይውላሉ።

በዚህ ዓይነት 12 ወር ሲቆጠርና ሲሞላ አንድ ዓመት ይባላል። (ይህ የጨረቃ ዓመት መሆኑ ነው)።

ይህ አቆጣጠር ከመደበኛው የዓመት አቆጣጠር የሚለይበት መንገድ አለው። ጨረቃ ዙሯን ለማሟላት የሚፈጅባት ጊዜ 29½ ቀን ነው። ይህ ማለት አንድ ወር (30 ቀን) ለመሙላት ግማሽ ቀን ይቀራታል ማለት ነው። በዚህ ዓይነት በመደበኛው 12 ወር ውስጥ የስድስት ቀናት ልዩነት ይታያል። ጳጉሜን ጨምሮ ደግሞ በአንድ ዓመት ውስጥ የ11 ቀን ልዩነት ይከሰታል ማለት ነው።

የሙስሊሞች እና የአይሁዳውያን የዘመን አቆጣጠር በዚህ በጨረቃ ወር ላይ የተመሰረተ ነው። አይሁዳውያን ዓመታቸውን ከመደበኛው አሰራር (ማለትም ከዓለም አቀፉ አሰራር) ጋር ለማስተካከል ሲሉ አንዳንዶቹን ወሮቻቸውን አራዝመዋቸዋል።

በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ግን ህጉ እንደተጠበቀ ይገኛል። ስለዚህም በዓላት በየዓመቱ በአስራ አንድ ቀናት እየቀደሙ ይደርሳሉ።

ሱፍ ኢዝም

የዚህ ዕምነት ተከታዮች ምናልባት ባለ በርኖሶች ሊባሉ ይችሉ ይሆናል። ቃሉ የመጣው ሱፍ ወይም ከበግ ጸጉር የሚፈተል ልብስ ከሚለው ነው። ምዕመናኑ ይህን ዓይነት አለባበስ ስለሚ ያዘወትሩ ይኸው ቃል መለያቸው ሆነ። ምዕመናኑ በምናኔ የሚኖሩ ናቸው። የዚህን የምድራዊውን ዓለም በመናቅ እና ስጋዊ ፍላጎትን በማሸነፍ የአላህን መንገድ በጥሞና በመከተል ጸጋውን ለመቀበል የሚያስችላቸውን ኑሮ ለመኖር ወደ ገዳም የገቡ ናቸው።

አንዳንድ ቦታ መንግስታትም ቦታ ስለለገሷቸው በየገዳማቱ አካባቢ በቂ መተዳደሪያ ተመቻችላቸው። ሕዝቡም እንደ አስተማሪ እና መንፈሳዊ መሪ ስለሚወስዳቸው ድጋፉን ሰጣቸው። ስለሆነም ትምህርታቸው ተቀባይነት አገኘ። በመከራ ጊዜም አጽናኝ እና አበረታች አንዳንዴም የባሰ ሁኔታ ሲያጋጥም መሸሻ ከለላ ሆኑ።

ከጊዜ በኋላ ግን ጽድቅን ለማግኘት የሚያስፈልጉት ሁኔታዎች ጠበቅ እንዲሉ ተደረጉ። ምድራዊውን ዓለም ለመኖርና በኋላም ለመጽደቅ ሁለቱንም ለማሟላት አስቸጋሪ እየሆነ መጣ። ለምሳሌ አንድ ሰው ፍጹም ሆኖ ከአላህ ጋር እስከመሆን ደረጃ ለመድረስ የተለያዩ ደረጃዎችን ማለፍ ይኖርበታል። ይህም 1/ ንስሃ ገብቶ ከክፉ ነገር ሁሉ መራቅ

2/ ሃብትና ንብረትን ንቆ እና ትቶ ደሃ መሆን፣

3/ በእምነት ተጠናክሮ እና ጸንቶ በትዕግስት መቀመጥ፣

4/ የመጨረሻው ደረጃ እውነትን፣ መጨበጥ መቻል እና ዕርካታ ማግኘት።

የመጨረሻው ደረጃ ቅዱስ ወደ መሆን አደረሰ ማለት ነው፡ይህም ተአምር ለመሥራት ያበቃል።

ሌሎች ሙስሊሞች ይህንን ለመቀበል አልፈለጉም። ይህ አስተምሮት በጣም ከባድ ስለሆነ ለመፈጸም አስቸጋሪ ሆነ። በዚሁ የተነሣ ልዩነት እየተፈጠረ መጣ። በ922 ዓ.ም ማንሱር ሃል አላጅ (Hal allaj) የመጨረሻው ደረጃ በመድረሱ "መብቃቱን" አስታወቀ። ሌሎቹ ይህንን ባለመቀበል ገደሉት። ተከታዮቹ ደግሞ ወደ መልአክ ደረጃ ከፍ ስላደረጉት ዛሬ ለኢራን ሱፊዎች በመልአክነቱ ይታወቃል።

ነገር ግን ይህንን በተራ ሙስሊሞችና ሱፊዎች መካከል ያለውን ልዩነት መፍታት አስፈላጊ በመሆኑ በታላቁ መንፈሳዊ መሪ በአልጋዛሊ (Al-Ghazali) (በ1111 የሞተ) ብርቱ ጥረት ስምምነት ተደረሰ። አልጋዛሊ እንዳስተማረው በጣም መንፈሳዊ መሆን ሕልመኛ ያደርጋል። በጣም ምድራዊ (ዓለማዊ) መሆንም ከአላህ ያርቃል። ስለዚህ ሁለቱም ዳርቻዎች መልካም ስላይደሉ መካከለኛውን መንገድ እንዲይዙ ሁሉንም ወገኖች አስተማረ።

ከዚህን ጊዜ ጀምሮ ሱፊዎች ሌላ ዕቅድ ዘረጉ። ይህም በድህነት ተቆራምዶ ሕይወትን ከመግፋት ይልቅ ሃይማኖቱን በሰፊው ለማስፋፋት የበኩላቸውን ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው ወሰኑ። ስለሆነም በሰራዊት መልክ እየተደራጁና የጦር መሪዎ ቻቸውን እየመረጡ ዙረው መዋጋት ጀመሩ። ስማቸውም ደርቡሾች በመባል ይታወቃል። ደርቡሾች በምሥራቅ አፍሪካ በኩል ወደ ሐረር በመግባት ግራኝመሐመድን ይዘው ብዙ ጦርነት አካሂደዋል። ሃይማኖቱን አስፋፍተዋል። ትምህርት ቤቶችን ከፍተዋል። የአማኞችንም ቁጥር በእጅጉ ሊያበራክቱ ችለዋል።

ዛሬ የሁሉም ወካይ ሃይማኖት የሱኒ እስልምና ነው። በአጠቃላይ ግን የእስልምና ሃይማኖት ሐቀኛ ዜጎችን በማፍራት፣ ሌብነትን፣ ጉቦኝነትንና ስካርን ከነዚህ ጋር የተያያዙ ወንጀሎ ችንም ስለሚቀንስ በታዳጊ አገሮች መንግሥታት ዘንድ ትኩረትን እየሳበ ነው፤እየተስፋፋም ነው።

እስልምና በኢትዮጵያ

የእስልምና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በነቢዩ መሐመድ ዘመን ነው። ምናልባት ከሳኡዲት አረቢያ ውጭ ወደ ሌላ አገር ሲደርስ ኢትዮጵያ ከመጀመሪያዎቹ ቀዳሚ አገሮች አንዲ ልትሆን ትችላለች።

ነቢዩ መሐመድ ሃይማኖቱን ማስተማር ሲጀምር የሜካ ከተማ ገዢዎችና ሃብታሞች በጣአታት መወገድ ምክንያት ጥቅማጥቅ ማቸው እንደሚቀርባቸው በመስጋት የመሐመድን ትምህርት ተቃወሙ። በእርሱና በተከታዮቹ ላይም ተነሱባቸው። ስለዚህ ነቢዩ መሐመድ እና ከፊል ተከታዮቹ ወደ ሜዲና ከተማ ሲሸሹ ሌሎቹ ወደ ኢትዮጵያ (እንግዳ ተቀባይና ቸር ህዝብ ወደሚኖርባት የሐበሻ ምድር) እንዲሻገሩ መከራቸው።

ስለሆነም መጀመሪያ አስራ ስድስት ሰዎች (11 ወንዶችና 5 ሴቶች) በአዱሊስ ወደብ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ደረሱ። እንደገናም ሌሎች 101 ሰዎች (83 ወንዶችና 18 ሴቶች) ተጨመሩ። ከእነዚህ ስደተኞች መካከል ሳውዳ (ነቢዩ ከከዲጃ ሞት በኋላ ያገባት) እንዲሁም የነብዩ ሴት ልጅ ሩቅያ ይገኙበታል። በኋላ የሩቅያ ባል ኡስማን ነበረ። ኡስማን ከነቢዩ መሐመድ በኋላ 3ኛ ኢማም ሆኖ የተሾመ (644-665) ሲሆን ቅዱስ ቁርዓን የተጠናቀረው በእርሱ አመራር ዘመን እንደሆነ ይታመናል።*

ሩቅያና ወገኖቿ አስራ አምስት አመታት ያህል በኢትዮጵያ እንደኖሩ ተዘግቧል። ንጉሥ አርማህም መልካም አቀባበል አድርገውላቸው እንደነበረና በመጨረሻም ነቢዩ መሐመድ በድል አድራጊነት ወደ ሜካ ሲመለስ ኢትዮጵያ የነበሩትም ወደ አገራቸው መመለሳቸው ተዘግቧል። በዚህ አጋጣሚ ነቢዩ መሐመድ ለንጉሡ በላከው ደብዳቤ ለዜጎቹ ስለተደረገላቸው መልካም አቀባበል ምሥጋናውን ገልጾ በዚያውም ስለሃይማኖቱ ይዘት ገለጻ አክሎበታል።

በዚህም መሠረት ለምሣሌ ሙሴ እና አብርሃም ነቢያት መሆናቸው፣ ለሙሴ ከሰማይ የወረዱለት ትዕዛዛትና ህግጋት የሚታመንባቸው መሆናቸው፣ ኢሳ (እየሱስ) በመንፈስ ቅዱስ ሃይል ከድንግል ማርያም የተወለደ መሆኑ እና እሱ የሰጣቸው ትምህርቶችና የሰራቸው ተአምራትም ሁሉ የሚታመንባቸው መሆኑ ተብራርቷል።

እርግጥ በኋላ የበለጠ ግልጽ እየሆነ ሲሄድ እየሱስ የሚወሰደው በአምላክነቱ ሳይሆን በነቢይነቱ ነው። ሌሎች የእስልምና ሃይማኖት ዝርዝር ይዘቶችም እያደር ግልጽ እየሆኑ መጡ በአፍሪካ አህጉርም በሰፊው ተስፋፉ ከመሐመድም ሞት በኋላ ስልጣኑን የወረሱት ኢማም አቡበክር፣ ኢማም ኡመር ቀጥሎም በይበልጥ አስተዋጽኦ ያደረጉት ኢማም ኡስማን ሃይማኖቱን ለማስፋፋት ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል። የኢትዮጵያ ምሥራቃዊ አካባቢ ነዋሪዎች የሃይማኖቱ ተከታዮች የሆኑት ከዚያን ዘመን ጀምሮ ነው።

ሂደቱ ቀስ በቀስ ሲቀጥል ቆይቶ በኋላ በግራኝ መሐመድ ዘመን ፈጣን እርምጃ አሳየ። ግራኝ መሐመድ (አህመድ ኢብራሂም) ከታላቁ የኦቶማን መንግሥት የጦር መሣሪያ ዕርዳታ ለማግኘት በመቻሉ እና ከኢራን፣ ከቱርክ፣ ከሳኡዲት አረቢያ እና ከፓኪስታን የተውጣጡ ተዋጊዎች (ደርቡሾች) ተሳታፊ ስለሆኑ በኦርቶዶክሱ ንጉሥ አጼ ልብነ ድንግል ሰራዊት ላይ ጦርነት አውጆ በ1529 ዓ.ም አሸነፈ። ይህ ትልቅ እርምጃ ነበረ። ግራኝ መሐመድ ለሚቀጥሉት አስራ አምስት ዓመታት ሲገዛ የሃይማኖት ትምህርትን በማስተማር የቁርዓን ትምህርት ቤቶችን በመክፈትና

---

* የነቢዩን አስተምሮት የሚያስታውሱት እያለቁ ሲሄዱ ጉዳዩ ስላሳሰበው ኡስማን 20 አስታዋሾችን ሰብስቦ ተራ በተራ እያስታወሱ እንዲናገሩ አደረገ። ሊቃውንትም በማስታወሻ እየያዙ አመሳክረው መዘገቡ። ይህ ንባብ ቅዱስ ቁርዓን ሆነ። ይዘቱም ትክክለኛ የነቢዩ ገለጻና የአላህ ቃል እንደሆነ የታመነ ነው።

መጻህፍትን በሰፊው በማዳረስ ሃይማኖቱን አስፋፋ። ወሎ፣ ራያ፣ አዘቦ፣ የጁ፣ጉራጌ፣ሊሙ፣ጅማ፣አርሲ፣ባሌ፣እና ሐረር የመሳሰሉት በዘመኑ ታዋቂ የነበሩ ክልሎች ትምህርት ቤት ተከፍቶላቸው ሃይማኖቱን ሊማሩ ችለዋል።

እርግጥ ግራኝ መሐመድ በፖርቹጋል ሰራዊትና መሣሪያ ረዳትነት በአጼ ልብነ ድንግል ልጅ በንጉሥ አጼ ገላውዴዎስ ተሸንፏል። ሆኖም ሃይማኖቱ በሕዝቡ ዘንድ ይኖራል።

የማህዲ ንቅናቄ በሰሜን በኩል ከግብጽ ተነስቶ በሱዳንና በቀይ ባህር በኩል ወደ ኢትዮጵያ የደረሰው በ1881-1898 ዓ.ም መካከል ነው። ሰራዊቱ ከአሉላ አባ ነጋ ጋር በተለያዩ የጦር ሜዳዎች (ዶግአሊ፣ጉራ) ፍልሚያ አድርገዋል። በመጨረሻም አጼ ዮሐንስን መተማ ላይ ገጥመው በ1889 ዓ.ም አሸንፈው የንጉሡን ራስ ቆርጠው ወሰደዋል። የእንግሊዝና የፈረንሳይ ጦር እሰከደረሰ ድረስም ሃይማኖቱን አስተምረዋል። አስፋፍተዋል።

አሁን በ20ኛው ምዕተ ዓመት የእስልምናን ሃይማኖት በኢት ዮጵያ ለማስፋፋት በርካታ አጋጣሚዎች ተከስተዋል። በ1913 ዓ.ም የነገሡት ልጅ ኢያሱ እስልምናን መርጠው ተቀብለዋል። በአላቸው ሥልጣን መሰረትም ሀይማኖቱን በመላ አገሪቱ ለማስ ፋፋትና ብሔራዊ ሃይማኖት ለማድረግም ይችሉ ነበረ። ነገር ግን አስተዳደራቸው የዘለቀው ለሶስት ዓመት ብቻ ሆነ። በዚያን ጊዜ ውስጥ ሃይማኖቱ በምስራቅና በሰሜን ኢትዮጵያ ተጠናክሯል። ሆኖም የማዕከላዊ መንግሥቱ ባለሥልጣናት ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ስለነበሩ አድመውባቸው ከሥልጣን አወረዱዋቸው። የኢያሱ አባትም ራስ ሚካኤል (የቀድሞ ስማቸው ራስ ዓሊ) ልጃቸውን መልሰው ለማንገስ ጦርነት ቢገጥሙም በሰገሌ ጦርነት ተሸንፈዋል።[24] በ1916 ዓ.ም ጀምሮ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴነት ከ1930-1974 ዓ.ም በንጉሥነት ሲያስተዳድሩ የኖሩት አጼ ሃይለ ስላሴ ኦርቶዶክስ ከመሆናቸውም በላይ የሃይማ ኖታቸው ጽኑ ደጋፊ ነበሩ።

ሆኖም የእስልምና ሃይማኖት በየክልሉ መስፋፋቱን አላቋረ ጠም። በ1974 ዓ.ም የኦርቶዶክስ እምነት ብሔራዊ ሃይማኖት መሆኑ ሲቀር እንዲሁም ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ የእምነት ነጻነት በበለጠ ሲረጋገጥና ሲደገፍ በተጨማሪም የቁርዓን ትምህርት ቤቶች መስጊዶች መምህራንን መጻህፍት እንዲሁም የውጭ ዕርዳታ መጠን እየተበራከተ ሲመጣ ዛሬ ዕድገቱ በአስተማማኝ ሁኔታ እየቀጠለ መጥቷል።

የበሃይ ሃይማኖት

መግቢያ፡-

የባሃይ ሃይማኖት የተጀመረው ወይም የተገለጸው በኢራን አገር በሺራዝ ከተማ ግንቦት 22 ቀን 1844 ዓ.ም ነው። የመጀመሪያው ንቅናቄ መሪ መሐመድ አሊ የተባለ ነጋዴ ነበረ። በክልሉ በነበረው የሺያት እስልምና ሃይማኖት ተከታዮች መካከል መከፋፈል በተከሰተበት ወቅት መሐመድ አሊ በአንደኛው ክፍል በመሆን ተነስቶ ራሱን አሳወቀ።

እርግጥ መሐመድ አሊ ገና ሲነሳ ጀምሮ ራሱን እንደ መሲህ አላቀረበም። "ከእኔ በኋላ ታላቅ መሲህ ይመጣል እኔም መንገዱን ላመቻች በቅድሚያ የተላኩ ነኝ" በማለት ጀመረ። ነገር ግን ያራሱን ያሳወቀበት ቀን የሃይማኖቱ ዘመን አቆጣጠር የመጀመሪያ ቀን ሆነ። ለዓለም ታሪክም አዲስ ምዕራፍ የተከፈተበት ዘመን እንደሆነ ተወሰደ። መሐመድ አሊም "ባብ" የሚል ስም ተሰጠው። ይህም "በር" ማለት ሲሆን በዓለም ሕዝብ እና በእግዚአብሔር መካከል የተገኘ አስታራቂ እና የገነት በር ከፋች እንደማለት ነው።

ከባብ በኋላ የመጣው ታላቁ ነቢይና ሃይማኖቱን በዝርዝር ያስቀመጠው ሁሴን አሊ ኑር ነው። ይህም ዛሬ ባሃኡላ በሚል የተከበረ ስም ይለያል። ከበሃኡላ በኋላ የመሪነቱን ስፍራ የተረከበው ልጁ አብዱል ባሃ ነው። በመጨረሻም የአብዱልባሃ የልጅ ልጅ ከዩኒቨርስቲ ተጠርቶ የመሪነቱን ሃላፊነት እንዲወርስ ተደረገ። ይህም ሾጊ ኢፈንዲ ነው።

እንግዲህ ሃይማኖቱ የተመሰረተው በ19ኛው ምዕተ ዓመት በመሆኑ እና የአራት ተከታዮች መሪዎች አመራር በማግኘቱ የመሻሻል የማደግ እና የመስተካከል ዕድልና ጊዜ አግኝቷል። የሳይንሳዊ አመለካከት ባህልም ሰርጾበታል። የምዕራባውያን የፖለቲካ አመራርና የሰራተኛ ማህበር መብት የመሳሰሉ ዘመናዊ አደረጃጀቶችም ተንጸባርቀውበታል። ስለሆነም የዘመኑ ሃይማኖት ተብሎ ቢወሰድ ያስኬዳል። መሠረተ ሃሳቡ ግን በእስልምና ሃይማኖት ላይ የተገነባ ነው።

የሃይማኖቱ ይዘት

የበሃይ ሃይማኖት ሁሉን አቀፍ በመሆኑ ለአገላለጽ እንዲያመች በየዘርፉ ማየት ይሻላል።

ሀ- ሃይማኖቶችን በተመለከተ

የበሃይ ሃይማኖት ራሱን ከሌሎች ሃይማኖቶች አግልሎ አያስቀምጥም። ሁሉንም ያቅፋል። ያጠቃልላል። ሃይማኖቶች ዛሬ የተለያዩ መስለው የሚታዩት በሕዝቦች የተለያየ የዕድገት ደረጃ የተነሣ ነው። የሁሉም

አመለካከት እየዳበረና እየረቀቀ ሲመጣ እምነቶችም ወደ አንድ አቅጣጫ ያመራሉ። በኋላም አንድ ሃይማኖት ብቻ ይሆናሉ።

ባለፉት ዘመናት የተላኩት ነቢያት ለሕዝቡ ደረጃ እንዲመጥኑ ነው። እግዚአብሔር በየወቅቱ ነቢያትና መልእክተኞችን ይልካል። በነሱም አማካኝነት ሃሳቡን ፈቃዱን ይገልጻል። ስለዚህ የሁሉም ሃይማኖቶች ነቢያትና መልእክተኞች መከበር አለባቸው፤ በእኩል ደረጃም መታየት አለባቸው። ኖህ አብርሃም ሙሴ ቡድሃ እየሱስ፣መሀመድ ባብ እና ባሃኡላህ በቅደም ተከተል የተላኩልን መልእክተኞች ናቸው። በተላኩበት ዘመን ወቅቱ የፈቀደውን ያህል ትምህርት ሰጥተዋል። ስለሆነም ዛሬ አንዱን ከሌላው ማበላለጥ ስህተት ነው። ሃያማኖቶች ሁሉ በየፊናቸው መከበር አለባቸው። በእኩልነትም መታየት አለባቸው። ስለዚህም ዛሬ በበሃይ ሃይማኖት ስርዓት ጋብቻ ሲከናወን ጥቅሶች የሚነበቡት ከመጽሀፍ ቅዱስና ከቁርዓን ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ቅዱስ መጽሀፍትም ጭምር ሊሆን ይችላል። እርግጥ በሃይም የራሱ የሆነ በባሃኡላህ የተጻፈ አጠቃላይ ስርዓት አለው። ወደፊት ግን ሃይማኖቶች ሁሉ አንድ እንዲሆኑ ማድረግ እና በአንድ የእምነት ጥላ ስር መሰባሰብ አስፈላጊ ነው። ስለሆነም የበሃይ ሃይማኖት ተከታዮች ይህንን እውን ለማድረግ ጥረት እንዲያደርጉ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ቃል ኪዳን ነው።

ለ- <u>ፖለቲካዊ አደረጃጀት</u>

የዓለም ፖለቲካን በተመለከተ አንድ የዓለም ፓርላማ መቋቋም አለበት። አገሮች ሁሉ በእኩልነት ይወከላሉ። ይህ አንድ የዓለም አስተዳደር ይሆናል። አስተዳደሩ በውስጡ ሶስት አካላት ይኖሩታል። እነዚህም ህግ አውጪ ህግ አስፈጻሚ እና የፍትህ አካላት ይሆናሉ።

የሁሉም የበላይ ባለሥልጣን የሚሆነው በአማኞች የተመረጡ እና በየደረጃው እየተዋቀሩ የሚወጡ አባላት ናቸው። የመጨረሻው ባለሥልጣን ዓለም አቀፍ ቤተ-ፍትህ (Universal House of Justice) የሚባለው ነው።

የዚህ አካል አመራረጥ በዲሞክራሲያዊ አሰራር በአማኞች ምርጫ ስርዓት ቢሆንም ስልጣኑ ግን ከሕዝብ በተገኘ ብቻ አይደለም። በዓለም ዲሞክራሲዎች መካከል ያለው ጦርነትና የእርስ በርስ እልቂት መሰረቱ የሕዝቦች አለመስማማት ነው። በድምጽ ብልጫ መርህ መስራት ምንግዜም ተዋህዶን አያረጋግጥም። የዓለም አቀፍ ቤተ ፍትህ አባላት መመሪያ የሚቀበሉት ከእግዚአብሔር ነው። ስለዚህ "ስልጣኑ የሰፊው ሕዝብ ነው" የሚለው አመለካከት በጥንቃቄ መታየት ያለበት ነው።

አንድ የዓለም አስተዳደር መኖር የሕዝቦችን መግባባት ስለሚጠይቅ ጭምር አንድ የዓለም ቋንቋ መኖር ወይም መፈጠር አለበት ከብሔራዊ ቋንቋ በተጓዳኝ የሚሰራበት እና ሁሉም ሊግባባ የሚችልበት ቋንቋ ተመርጦ እና ተጠንቶ በስራ ላይ መዋል አለበት።

የዩኒቨርሳል ቤተ ፍትህን ውሣኔ የሚቃረን ሁሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚቃረን በመሆኑ ተገቢው ቅጣት ወይም የእርምት እርምጃ ይወሰድበታል። ይህ ቤተ ፍትህ ባይቋቋምም እንኳ ለፍትህዊ መንግሥት ሁሉ ፍጹም ታዛዥ እና ተገዢ መሆን ግዴታ ነው። ለውጥ የሚመጣው በእግዚአብሔር ዕርዳታ ነው። እግዚአብሔር ፈቃዱ ሲሆን ለውጥ ያመጣል። ተገቢ ወቅቱም ሲደርስ ነቢያት ይልካል። እነሱም ትክክለኛውን ትምህርት ይሰጣሉ። እስከዚያው ግን ልዩነት በመፍጠር የተቃውሞ ሰልፍ ማካሄድ መንግሥትን በትግልና በጦርነት መገልበጥ አይፈቀድም። ማንኛውም የባሃይ እምነት ተከታይ በዚህ ዓይነት ትግል ውስጥ ተሳታፊ አይሆንም። የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሲሆን ለውጡ ራሱ ይመጣልና።

ሐ. <u>የኤኮኖሚ ስርዓት</u>

በዓለም ላይ አንድ መንግሥት ሲመሰረት ኤኮኖሚው ለሁሉም እንዲያገለግል ሆኖ ይደራጃል። በዚህን ጊዜ ትግል ፉክክር፣እርስ በርስ ትንቅንቅ ሁሉ ይቀራሉ። እነዚህ ለሰው ሰብዓዊ ክብር ተጻራሪ የሆኑ ናቸውና እነሱ ተወግደው መከባበር መተሳሰብና መረዳዳት ቦታቸውን ይወስዳሉ።

ሃብት የሕይወት ማኖሪያ ነው እንጂ በራሱ የሕይወት ግብ አይደለም። ስለዚህ ሌሎች እየደኸዩ ጥቂቶቹ በጣም መክበር አይገባቸውም። እርግጥ ሰው ሁሉ እኩል አይደለም፤ ሊሆንም አይችልም። ደሃ እና ሐብታም ይኖራሉ። ባለሐብት ደግሞ መከበር አለበት። ልዩ ተሰጥኦም እንዲሁ ይከበራል። ሁሉም የሚሆነው በእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና።

ነገር ግን ሃብት ለሁሉም እንዲደርስ አመቺ ሁኔታ መፈጠር አለበት። ሃብታም ገደብ እንዲኖረውና ደሃም እንዳይሰቃይ ፍትሐዊ የገቢ ማዳረስ ህግ መውጣት አለበት። ለምሣሌ ተቀጣሪ ሰራተኛ ከደመወዙ በተጨማሪ የፋብሪካው ትርፍ ተካፋይ መሆን አለበት። እርግጥ ይህ በስምምነት መሆን አለበት ከስምምነቱ ውጭ የሆነ ወይም ተጻራሪ ድርጊት የፈጸመ ሰራተኛ በመንግሥት መቀጣት አለበት። ስርዓቱን ማፍረስ ሃጢያት ነውና።

ውርስ ለሁሉም ተወላጅ በእኩል መደላደል አለበት። ግን ተወላጅ ብቻ ሳይሆን የሚች መንፈሳዊ አስተማሪም የውርሱ ድርሻ ይኖረዋል።

እርሻ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው ነው። ስራ ሁሉ ክቡር ነው። ስለዚህ ሁሉም ሰው እንደተሰጥኦው ለራሱና ለህብረተሰቡ በሚጠቅም መንገድ መሰማራት አለበት።

ከሁሉም ይልቅ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ የሚሆነው ሰው መስራት ሲችል ግን ቁጭ ብሎ በልመና የሚኖር ነው።

መ. ማህበራዊ ኑሮ

የባሃይ ሃይማኖት ትምህርት ቀደም ሲል የነበሩትን ሃይማኖቶች በሚከተለው ዓይነት ይመለከታቸዋል። ያለፉት አብዛኞቹ ሃይማኖቶች

የግለሰቦችን ሁኔታ የሚመለከቱ ነበሩ። ለምሣሌ ክርስትና ሃይማኖት በፍቅር በመኖር የተሟላ ሕይወት ስለመኖር ያስተምራል። የቡድሃ ሃይማኖትም በራስ ጥረት እንዴት ፍጽምና ለማግኘት እንደሚቻል ይገልጻል። ነገር ግን ሕይወት በግለሰብ ደረጃ ብቻ የሚወሰን አይደለም። በዚህ የተነሣ የተሟላ ትምህርት አይሰጥም ነበረ። እርግጥ ይህ ትምህርት በዚያ ወቅት ለዚያ ደረጃ ህብረተሰብ በቂ ነበረ።

እየሱስ ክርስቶስም ስለ ግለሰቦች ነፍስ ማዳን ያስተማረው ትክክል ነበረ። በዚያን ጊዜ ጎሳ፣ ብሔር፣ ነገድ ነበሩ። ያን ጊዜ ሁሉም አህጉራት እንኳ መኖራቸው አይታወቅም ነበረ። ስለዚህ በዚያን ጊዜ ስለ ዓለም ኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ሕይወት መናገር ጊዜውም አይፈቅድም ነበረ። ዛሬ ግን ዓለም ትንሽ ሆናለች። ስለዚህ ሁሉም ካልተባበረ ጥረቱ ውጤት አይኖረውም። በዚህ የተነሳ ማህበራዊ ህግ መደንገግ አለበት። መንግሥት በሃይማኖት ረገድ ሚና መጫወት አለበት። ነቢዩ መሐመድ ይህንን ስራ ጀምሮት ነበረ። ነገር ግን ዛሬም ቢሆን ከሃይማኖታዊ መንግሥታት ይልቅ ምድራዊ መንግስታት ነግሰውና ጎልተው ይታያሉ።

የእግዚአብሔር ፈቃድ ግን የሰው ልጅ በአንድ ሆኖ በሰላም በአንድነትና በወንድማማችነት እንዲኖርና እንዲያድግ ነው። የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመቀበልና ፈቃዱንም ለመፈጸም ዝግጁ የሚሆነው በአንድ የእምነት ጥላ ስር በወንድማማችነት ሲኖር ነው። ስለዚህ እምነትና ተግባር ተዋህደው በአንድ ዓይነት መመራት አለባቸው።

ሰዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅና ህጉንም ለመፈጸም የሚችሉት ግን በቅድሚያ የእግዚአብሔርን ነቢይ ሲቀበሉ ነው። ነቢይ ማለት ደግሞ ከእግዚአብሔር የተላከ ነው። ስለዚህ ትምህርቱን መቀበል አለባቸው። በአጠቃላይ የሃይማኖት ትምህርት በየአገሩ በየትምህርት ቤቱ መሰጠት አለበት። የእግዚአብሔርን ህግ ለመረዳት የሚቻለው በጸም በጸሎት በውይይትና በትምህርት ነው። ትምህርት ደግሞ መጨረሻ የለውም። ለአሁኑ ወቅት የባሃኡላን ትምህርት መከታተል የሁሉም ግዴታ ነው። ባለሥልጣኖች በዚህ አስፈላጊነት ይመኑ።

የበሃይ ሃይማኖት የማህበራዊ ሕይወትን የሚገዛ መሆኑን ያሰመረበት ባሃኡላህ ራሱ ነው። "የእምነት አንድነትን ለማስከበር ሲባል የአንድነት ቃል ኪዳናችንን ከማያከብሩ ወይም ከማይሰማሙ አባላት ጋር ምንም አይነት ማህበራዊ ግንኙነት እንዳያደርግ የበሃይ አማኝ ሁሉ ታዟል ሲል ነቢዩ ደንግጓል።

የነቢያቱ አስተምሮት

ሀ- ባብ (1819 -1850)

ባብ (ሰይድ አሊ መሐመድ) በ1844 ዓ.ም ተነስቶ ራሱን ሲያሳውቅ የታላቁ መሲህ መምጫ ስለደረሰ ለእርሱ መንገዱን ለማዘጋጀት ቀድሜ

የተላክሁ ነኝ በማለት ነበረ። በሺያት እስልምና መሰረት በሥልጣን ላይ እያለ ተሰውሮ የነበረው 12ኛው (ማህዲ) ኢማም (ገጽ 130 ይመልከቱ) የሰውን ልጅ ወደ ወርቃማው ዘመን ሊያሸጋግረው ተመልሶ ይመጣል። እስከዚያው የሃላፊነቱ ቦታ በባለአደራዎቹ ተይዞ የመሲሁን ዳግመኛ ምጽአት በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ።

ይህ በዓለም ፍጻሜ እንደሚሆን የታመነበት ነው። አሁን በሕዝቡ እምነት መሰረት ባብ የተላከው ይህንኑ ለማብሰርና ህዝቡን ለማስተማር ነው።

ባብ ራሱ ስለ 12ኛው ኢማም መናገሩ ግልጽ የሆነ የለም። ግን የዓለም መጨረሻ በ1844 ዓ.ም እንደሚሆን ሕዝቡ ይተነብይ ነበረ። ያጊዜ መጥቶ አለፈ። ሙስሊሞች ነቢዩ መሐመድ የመጨረሻው ነቢይ መሆኑን በጽኑ ያምኑ ስለነበር ይህንን ሃሰተኛ ነቢይ ብለው አሳሰሩት። ይህ የሆነው በ1847 ነበረ። ከዚያ በኋላ መከፋፈል በመፈጠሩ ጦርነት ተነስቶ እሰከ 20,000 ምዕመናን አለቁ ይባላል። ባብ ራሱ በዚህ መካከል በእስር ቤት እንዳለ ተፈርዶበት ሐምሌ 9 ቀን 1850 ዓ.ም በጥይት ተገደለ። ያ ቀን ዛሬም የመስዋዕት ቀን ተደርጎ በዓለም በሃይ ተከታዮች ዘንድ ይከበራል።

ባብ በሕይወት ዘመኑ ብዙ አስተምሯል። ብዙም ጽፏል። አስተምሮቱ ስለ እኩልነት እና ስለወንድማማችነት ነበረ። እርግጥ ይህ እኩልነት እምነቱን ለተቀበሉ ሙስሊሞች ብቻ ነበረ። ከዚህ እምነት ውጪ የነበሩትን ሰዎች በግዴታም ቢሆን ለማሳመን ሲባል የሚወሰደውን እርምጃ አልተቃወመም። አልከለከለምም።

በበሃይ አስተምሮት መሠረት የነቢዩ መምጣት በቅድሚያ በቅዱሳት መጻሕፍት ተተንብዮ ነበረ። ስለሆነም የመጀመሪያው ደቀመዝሙሩ ከሩቅ አካባቢ እየተመራ የደረሰው ከወር በላይ ብቻውን ሆኖ ሲጸልይ ቆይቶ በኋላም በቅዱስ መጻህፍት የተጻፉትን ምልክቶች እና ቀናት በማጥናት ጊዜው ሲደርስ ጉዞውን በመጀመር ነው። ይህ የደከመ መንገደኛ ሺራዝ ከተማ (ኢራን) ደርሶ ወደ ነቢዩ ቤት ሲያመራ ነቢዩ ራሱ አውቆ ይጠብቀው ነበርና ወጥቶ ተገናኘው። በዚህ ዓይነት ሌሎችም ደቀመዛሙርት በራሳቸው መጥተው ጠቅላላ ቁጥራቸው 18 ሲሞላ ባብ ማስተማር ጀመረ ይባላል።

ባብ በሚያስተምርበት ጊዜ የሚያጋጥመው ጥያቄ መሐመድ የመጨረሻው ነቢይ ሆኖ ሣለ እርሱ ከየት ሊመጣ እንደቻለ ነበረ። እሱም እንደሚከተለው አስረድቷል። እርግጥ ነቢዩ መሐመድ የመጨረሻው ነቢይ ነበረ። በቅዱስ ቁርዓን የተገለጸው ትክክል ነው። ሆኖም ያ የትንቢት ዘመን ነበረ። ያም ለ6000 ዓመታት ዘለቀ። አሁን ግን የትንቢት ዘመኑ ተፈጸመ። እነሆ አዲስ ዘመን ተጀመረ። በአዳም የተጀመረው ዘመን በኖህ በአብርሃም በእየሱስ እና በመሐመድ ቀጥሎ አሁን አለቀ። ከእንግዲህ ትንቢትን እውን የማድረጊያው ዘመን ግንቦት 22 ቀን 1844 ዓ.ም የተጀመረው ሲሆን

ይህም ለሚቀጥለው 500.000 ዓመታት ይዘልቃል። ይህ ትንቢት እና ዝርዝር ሁኔታዎች በበለጠ የተብራሩት በሚቀጥሉት ዘመናት ነው።

ባብ ግን ስድስት ዓመት ሲያስተምር ኖሮ በሰላሣ ዓመቱ በአደባባይ ተሰዋ።

ባሃኡላህ (1817-1892)

ባሃኡላህ የሚኒስትር ልጅ ነበረ። ገና በህጻንነቱ ጀምሮ ብሩህ የነበረና ሳይማር በማወቁ በቀሳውስት ዘንድ የተደነቀ የተከበረ ነበረ። መንግሥት የአባቱን ማዕረግ ሊሰጠው ዝግጁ ቢሆንም ልጁ ስልጣኑን አልፈለገም። እንዲያውም በምድራዊ ሃብት ባለማመን ንብረቱን ጎንጻ ይሰጥ ነበረ። ተፈጥሮን በእጅጉ ይወዳል፣ ሰዎችና ህጻናትም ይወዱት ነበረ። በየሄደበትም ቦታ እየተከተሉ ይከቡት ነበረ። ይህ ልጅ (ስሙ ሁሴን አሊ ነበረ) በቴህራን ዋና ከተማ (ኢራን) ሲኖር የባብ አስተምሮት ደረሰው። ያን ጊዜ የ27 ዓመት ወጣት የነበረው ሁሴን በባብ ተልዕኮ አምኖበት እሱም ወዲያው ሊያስተምር ተነሳ። ግን ሐብቱ ተወርሶ እሱም ለ4 ወር እስር ቤት ገባ። በእስር ቤት እንዳለ ነበረ ራዕይ የተገለጸለት። ወዲያውም ባብ ሞተ።

ሁሴንም በወቅቱ በጣም ስለታመመ ተፈታ እና ቤተሰቡን (ሚስቱንና ልጆቹን) ይዞ ወደ ባግዳድ ዋና ከተማ (ኢራቅ) ተሰደደ። ከእስር ዓመት የስደት ኑሮ በኋላ ወደ ቱርክ ለመጓዝ ተነሳ። በዚህን ጊዜ ነበረ ከባግዳድ ወጣ ብሎ በአቅራቢያው ለ12 ቀናት ቆይታ ሲያደርግ "ታላቁ አስተማሪ" እና በቅዱሳት መጽሀፍት የተነገረው ማህዲ እሱ መሆኑን ለዓለም ያስታወቀው። ይህ ጊዜ (ሚያዝያ 21 - ግንቦት 2) ዛሬም በአማኞች ዘንድ ያታሰባል። ሁሴን በቱርክ አምስት ዓመት ከ4 ወር ቆይቶ በኋላም ወደ ፍልስጥኤም እስር ቤት ተጋዘ። ለዘጠኝ ዓመታት ከታሰረ በኋላ ወደ ቁም እስር ተቀይሮለት ግንቦት 29 ቀን በ1892 አረፈ። ታላቁ ነቢይ ሀጉን አስተምሮ እውነቱን ገልጾ በዚህ ቀን አረገ ይባላል።

በሃኡላህ በምድር ላይ ቆይታው ዘመን ብዙ ጽፏል። እስከዛሬም ያልተተረጎሙ በርካታ ሰነዶች ይገኛሉ።

የአስተምሮቱ መሠረት ግን ፍቅርና ሰላም ነው። ቀደም ሲል ሃይማኖቱን በውዴታም በግዴታም ማስፋፋት በተግባር ይውል ነበረ። በሃኡላህ ግን ይህንን ፍጹም ቀየረው። እምነት በሃይል መጫን የለበትም እንዲያውም በሥልጣን ላይ ላለው መንግሥት ተገዢ መሆን ይገባል። እግዚአብሔር ፈቃዱ እስኪፈጸም ድረስም በትዕግስት መጠበቅ ያስፈልጋል አለ። ይህ ከወቅቱ የእስልምና አስተምሮት በጣም የተለየ ሆነ የባሃይን ሃይማኖት ከእስልምና ለይቶ ያስቀመጠው ይኸው ነው። ከሃዲዎችና ሌሎች አማኞችም ሃይማኖቱን ለመቀበል የቀለላቸው ለዚህ ጭምር ነው ይባላል።

ስለዚህ ይህንን በዝርዝር ማየት ያስፈልጋል። እንደሚታወቀው ነቢዩ መሐመድ እስልምናን ሲመሰርት በሰላም መንገድ አልተቀበሉትም።

ስለሆነም ከሜካ ከተማ ተባሮ ወደ ሜዲና ሄደ። ከዚያ በኋላ ጦር ሰራዊት መገንባት ነበረበት። ጣኦታትንና አማልክትን ለማጥፋት ሌላ አማራጭ አልነበረውምና። ግን ጦር ሰራዊቱን ሲገነባ ቀለብ አስፈላጊ ነበረና ለዚህም ወደ ሶሪያ እና አካባቢው ከሚመላለሱት የግመል ንግድ ሸቀጦች መካፈል ነበረበት።** በዚህ ዓይነት ከ8 ዓመት በኋላ ሜካ ከተማን አሸንፎ ገብቶ ስልጣኑን በመረከብ ጣኦታትን በሙሉ አስወገደ። በዚህ ሂደት የነቢዩ አስተምሮት ከሃዲዎችን መዋጋት የአላህ ትዕዛዝ መሆኑን የሚገልጽ ነበረ። ሃይማኖትም በሙሉ እስልምና እስኪሆን መጋደል የሙስሊሞች ግዴታ እንደሆነ አስገነዘበ። ሰዎች በጣኦታትና በአማልክት በማመን የአላህን ክብር እንዲቀንሱ አይፈቀድላቸውም። ስለዚህ "በአላህ ሃይማኖት ተጋደሉ" (2፣244)* "ሃይማኖት ሁሉ ለአላህ ብቻ እስከሚሆን ድረስ ተጋደሉዋቸው" (8፣39) በማለት አስተማረ።

እርግጥ የመጽሀፍ ቅዱስ ሰዎች (አይሁዶችና ክርስቲያኖች) ለሞት አይዳረጉም ነበረ። እነርሱ ራሣቸውን አስገዝተው ከተቀመጡ ቀረጥ እየከፈሉ ይኑሩ። ከዚያ ውጭ ግን በአላህና በመጨረሻው ቀን የማያምኑትን አላህና መልዕክተኛው እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትን ተዋጉዋቸው። (9፣29)። እነዚያንም የካዱትን ባገኛችሁ ጊዜ አንገታቸውን በሏቸው። በጦርነቱ መጨረሻም እጃቸውን የሰጡትን ማሰሪያውን አጥብቁ። . . . አላህ ቢሻ ከነሱ (ያለጦር) በተበቀለ ነበረ። ግን ከፊላችሁን በከፊሉ ሊሞክር (በዚህ አዘዛችሁ) . . . (47፣4) ስለዚህ "ባገኛችኋቸውም ስፍራ ሁሉ ግደሉዋቸው። ከአወጧችሁም ስፍራ አውጧቸው። መከራም ከመግደል ይልቅ የበረታች ናት" (2፣91)።

በዚህ አጋጣሚ አይሁዶችም እግዚአብሔር በሙሴ አማካኝነት ከግብጽ ካወጣቸው በኋላም በኢያሱ የጦር መሪነት ሲዋጉ ራሱ ከጎናቸው እንደነበርና እንዲያሸንፉ ፈቃዱ እንደሆነ በመጽሀፈ ኢያሱ የተቀመጠው ትዝ ይለናል። (ገጽ 34-35 ይመልከቱ)።

በሃኡላህ ግን ይህንን ሁሉ ቀየረው ታላቅነቱ የታወቀው በዚህ ጭምር ነው። ባሃኡላህ ለሃይማኖት ሲባል መዋጋት ተገቢ አለመሆኑንና እግዚአብሔር ወደፊት ፈቃዱ በሆነ ጊዜ ሁሉ ሌሎች ነቢያትን በመላክ ፈቃዱ እንዲፈጸም እንደሚያደርግ አስተማረ። ስለዚህ የሰው ልጅ ሃላፊነት ሃይማኖቶችን ወይም ነቢያትን አንዱን ከሌላው ማበላለጥ ሳይሆን ሁሉንም ባሉበት አቅፎ መቀበል ነው። ሁላቸውም ቢሆኑ በጊዜያቸውና በቦታቸው ትክክል ነበሩና። ሌላው ቀርቶ መንግሥታትን እንኳ በጦር ሃይል ወይም በትግል መቃወም አስፈላጊ አይደለም። በትዕግስት መጠበቅ እና መግባባትንና መተባበርን ማራመድ ይገባል እንጂ። ይህ የባሃኡላህ ሃይማኖት ከዘመኑ አስተሳሰብ ከመጽሀፍ ቅዱስና ከወቅቱ ሳይንስ ጋርም ሊራመድ ቻለ።

** ዘኒው ኢንሳይክሎፔዲያ ብሪታኒካ ቅጽ 22፣ገጽ 3

* እነዚህ ጥቅሶች ከቅዱስ ቁርዓን (ከእንግሊዝኛው) ናቸው።

እንዲሁም በባሃኡላህ አስተምሮት መሰረት ሃይማኖቱን በጭፍን መቀበል ተገቢ አይደለም። አጥንቶ እና ተመራምሮ በነጻነት ስሜት መደረግ ያለበት ነው። ቄስ እና ባህታዊ አያስፈልጉም። አስተማሪም ሆነ ነፍስ አባት ተፈላጊ አይደሉም። ማንም ሰው ማንበብ እስከቻለ ድረስ አንብቦ ሊረዳ ይችላል። ስለሆነም አንድ ሰው የራሱን ሃይማኖት ትቶ ሳይሆን እንደ ያዘ ወደዚህኛው ሊሸጋገር ይችላል። በሌላ አነጋገር ሰው በሃይማኖት ልዩነት የተነሣ ቅራኔ ውስጥ አይገባም። ይህ ትልቅ መርህ ነው። ለሃይማኖቱ ሰፊ ተቀባይነት ማግኘትም በርከፋች ነው።

የባሃይ እምነት መሰረት የተጣለው እና ለዓለም አቀፍ ታዋቂነት የበቃው በዚህ እና ቀደም ሲል በተቀመጠው የሃይማኖት ይዘት (ገጽ 138) መሰረት ነው። የበሃይ ሃይማኖት ስሙን ያገኘው ከዚሁ ከመስራቹ ከባሃኡላህ ነው። ባሃኡላህ መጨረሻ በሰጠው ኑዛዜ ልጁ (አብዱልባሃ) ስልጣኑንና ሃላፊነቱን እንዲወርስ አዟል።

አብዱልባሃ (1844-1921)

አብዱልባሃ ከልጅነቱ ጀምሮ ከአባቱ ጋር ሲሰደድ የኖረ ነው። በሰምንት ዓመቱ ከአገሩ ወጥቶ ባግዳድ ሄደ። በኋላም በአባቱ እግር ተተክቶ ሲያስተምር እንዲታሰር ተፈረደበት። አብዱልባሃ ለአርባ ዓመታት እንደታሰረ ይነገራል። ሆኖም ማስተማሩንና መጻፍን አላቋረጠም። የአብዱልባሃ ተልዕኮ 1ኛ/ የእምነቱ ተርጓሚ እንዲሆን ሲሆን 2ኛ/ የቃል ኪዳን ተቀባይ ነው። ባሃኡላህ የተናገረውንና ያስተማረውን ተርጎሞ እና አብራርቶ ማስፋፋት ድርሻው ነው። ይህ ካልሆነ በሰዎች መካከል የተለያየ አመለካከት እንደሚከሰትና የሃይማኖት መከፋፈል ሊመጣ እንደሚችል በሃኡላህ በማወቁ አንድ ተርጓሚ ብቻ እንዲኖረው የደነገገው ስለዚህ ነው። አብዱልባሃ ወደ ምዕራብ አውሮፓ እና ወደ አሜሪካ በመጓዝ ሃይማኖቱን ያስተዋወቀ እና በርካታ ተከታዮችን ሊያፈራ የቻለ ታላቅ ሐዋሪያዊ ስራ የሰራ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን በሰው ልጆች ስም የተረከበ ነው። በመሰረቱ ባሃኡላህ የተላከው የሰውን ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር ለማገናኘት ነበረ። ግን የሰው ልጅ በግለሰብ አመለካከት ደረጃ እንጂ ማህበራዊ አመለካከቱ የዳበረ ስላልነበረ ወቅቱ አመቺ አልነበረም። ስለሆነም እግዚአብሔር አብዱልባሃን ሰጠን።

አብዱል ባሃ ቃል ኪዳኑን ተቀበለ። ይህም የሰው ልጅ አንድ ሆኖ በአንድ ሰርዓት ስር በአንድእምነት ሆኖ የእግዚአብሔርን ጸጋ እንዲቀበል እና ህጉንም እንዲፈጽም ዝግጁ ለማድረግ ነው። እንደሚታወሰው አዲሱ ዘመን ግንቦት 22 ቀን 1844 ተጀምሯል። ይህ ለ500.000 ዓመታት ይዘልቅና ከዚያ በኋላ አዲስ ዙር እንደገና ይጀመራል። በነኝህ ዓመታት ውስጥ በየጊዜው ነቢያት እየተላኩ መጥተው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይገልጻሉ፣ ያስረዳሉ። ይህም በግምት በየአንድ ሺ ዓመታት ነው።

አሁን የባሃይ ተልዕኮ ተግባራዊ እንዲሆን አንድ ሺ ዓመት ይፈጃል። በዚህ ጊዜ ውስጥ መንግሥታት ይዋሃዳሉ፣ እምነት አንድ ይሆናል። ፍትህ ይነግሣል። የጾታ እና የዘር እኩልነት ይረጋገጣል። በአንድ ቋንቋ መነጋገር ደረጃ ይደረሳል። በአንድ ዓይነት ሚዛን መስራት ይቻላል። በአጠቃላይ የኤኮኖሚ ቀውስ ይወገዳል። ወርቃማው ዘመን ይሰፍናል። ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነ የሰው ልጆች በዚህ መንገድ ፈቃዱን ለመፈጸም ጥረት እንዲያደርጉ አብዱልባሃ በሰው ልጆች ስምቃል ኪዳን ተቀበለ።

አብዱል ባሃ በ1921 ዓ.ም ሲሞት ይህንን ቃል ኪዳኑን ለባሃይ አማኞች አስተላለፈ። ስለዚህ በቃልኪዳኑ መሠረት የባሃይ እምነት ተከታዮች ሁሉ ትምህርቱን ማሰራጨት አለባቸው። ለዚህም የእግዚአብሔር እርዳታ አይለያቸውም።

ሾጊ ኢፌንዲ (1897-1957)

ሾጊ ኤፌንዲ የአብዱልባሃ የልጅ ልጅ ነው። ይህም የመንፈሳዊ መሪ ሥልጣን በኑዛዜ የተላለፈለት ገና በ24 ዓመት ዕድሜው በእንግሊዝ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ በነበረበት ወቅት ነው። ሃላፊነቱም በባለአደራ ጠባቂነት (ጋርዲያን) ሲሆን ኢፌንዲ በነበረው የትምህርት ደረጃ በምዕራባውያን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ይዘት ግንዛቤ በመታገዝ ቀደም ሲል የተጻፉትን መንፈሳዊ መጻህፍት እየመረጠ ከፐርሺያ ቋንቋ ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሟል። አስተምሯል፣አስፋፍቷል።

ሾጊ ከሰራቸው ስራዎች ዋንኛው የአስተዳደሩን መዋቅር ሊዘረጋ መቻሉ ነው። አማኞችን በማሰባሰብ በተለያዩ ቀበሌዎች ኮሚቴዎችን አዋቀረ። ከዚህም በመነሣት በየደረጃው እያስመረጠ ብሔራዊ ኮሜቴዎችን አደራጀ። ለመጀመሪያ ጊዜ በ1963 ዓ.ም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተዋቅሮ በስራ ላይ ሊውል የቻለው ዓለም አቀፍ ቤተ-ፍትህ የዚህ ውጤት ነው። የአስተዳደር ሀሳቸን በመቅረጽና በስራ ላይበማዋል እንዲሁም ህትመቶችን በማዘጋጀትና በማሰራጨት ሃይማኖቱን ለዓለም አቀፍ ከበሬታ ያበቃው እሱ ነው።

ሾጊ ኢፌንዲ ለ36 ዓመታት ድርጅቱን በሙሉ ሥልጣንና ኃላፊነት ከመራ በኋላ በሞተበት ጊዜ ወራሽ ስላልመደበና ህጋዊ ወራሾቹንም ስላወገዘ ዛሬ ሃይማኖቱ የዘር ግንድ የሆነ ወራሽ ባለሥልጣን የለውም። ሆኖም ዋናው ማዕከል ሃይፋ ከተማ (እስራኤል) የሚገኘው እና በየአምስት ዓመቱ በዲሞክራሲያዊ አሰራር እየተመረጠ ሃላፊነቱን የሚረከበው ዓለም አቀፍ ቤተ-ፍትህ ተግባሩን ያከናውናል።

የባሃይ ተግባራት

ባሃዮች መጸምና መጸለይ ይጠበቅባቸዋል። ከእግዚአብሔር የሚያገናኘው አካልን በጸም አድክሞ መንፈስን አበርትቶ በጸሎት መቅረብ ነው። ጸሎት በየቀኑ ይከናወናል። ይህም በስግደት መልክ ነው። ጸሎት በቀን

ሶስት ጊዜ ሊሆን ይችላል። አለበለዚያ በአንድ ሊያበቃ ይችላል። መቅረት ግን አይችልም። ከስግደት በፊትም በአካል ንጹህ ሆኖ መገኘት ይገባል። ስለሆነም በውሃ መጽዳት (መታጠብ) ነው።

የጸሎት (ስግደት) አቅጣጫው ወደ ባሃኡላህ መቃብር ሲሆን ይህም የፍልስጤም አቅጣጫ መሆኑ ነው። ባሃዮች በየቀኑ ስብሰባ ያደርጋሉ። ከጸሎት፣ ጥናት፣ እና ውይይት በኋላ ቡራኬ ተቋርሰው ስነ ስርዓቱ ይፈጸማል።

ጾም ማለት ከእህል ውኃ መታቀብ ነው። ይህም ከንጋት እሰከ ምሽት ነው። ጾም የሚጾመው በባሃይ ዘመን አቆጣጠር በመጨረሻው ወር ነው። ይህም ለ19 ቀናት (መጋቢት 1-20 ቀን) ነው። የጾም መፍቻ ቀን በአዲሱ ዓመት መጀመሪያ ላይ ስለሚውል ፋሲካና አዲሱ ዓመት አንድ ቀን ይደርሳሉ ይከበራሉ። በጾም ወራት የታመሙ ሰዎችና ነፍሰጡሮች እንዲሁም መንገደኞችና ሕጻናት እንዲጾሙ አይገደዱም።

የሃጂ ጉዞ ከተቻለ ይደረጋል። በቀድሞው ዘመን ሃጂ ጉዞው የሚደረገው ወደ ባብ የትውልድ ስፍራ (ሺራዝ ከተማ) እንዲሁም ወደ ባሃኡላህ ትውልድ ቦታ (ባግዳድ) ነበረ። ነገር ግን በቅርቡ በ1979 ዓ.ም የባብ ቤት በኢራን አብዮት ወቅት ስለፈረሰ ጉዞው ወደ መቃብር ቦታዎች ሆኗል። የባብ መቃብር ቦታ ሃይፋ እስራኤል ሲሆን የባሃኡላህ ደግሞ በፍልስጤም አገር በከርሜል ተራራ ግርጌ በአካ ነው።

የሾጊ ኢፌንዲ መቃብር ቦታም (በለንደን የሚገኝ) የሃጂ ስፍራ መሆን ጀምሯል።

ቤተ ጸሎት

የበሃይ ቤተ መቅደስ ሁሉ ዘጠኝ መግቢያ በሮች እንዲኖሩት ሆኖ የተሰራ ነው። ደጆቹም መግቢያ መንገዶቹም ዘጠኝ ናቸው። ጣሪያው ግን አንድ ወጥ ሆኖ በክብ ቅርጽ ዓይነት ይሰራል። የዚህም ትርጉም ሲተነተን የሰው ልጅ ዘር አንድ ብቻ ነው። ሃይማኖቱም አንድ ሁሉን አቀፍ ነው። ስለዚህ ከማንኛውም ዘጠኝ የምድር አቅጣጫዎች የሚመጣ ሁሉ በቀጥታ ሊገባ የሚችልበት መግቢያ በር አለው ማለት ነው። ቤተ ጸሎቱ ውስጥ ያሉት ዋና ዋና ቋሚ ምሶሶዎችም ዘጠኝ ይሆናሉ። በነዚህ ላይ የተለያዩ ሃይማኖቶችን የሚወክሉ አርማዎች ሊሰቀሉ ይችላሉ። ለምሳሌ የክርስቲያን መስቀል የእስልምና ግማሽ ጨረቃና ኮከብ የአይሁዶች ባለ ስድስት ጫፍ ኮከብ እና የባሃይ ባለ ዘጠኝ ጫፍ ኮከብ . . . ወዘተ።

በዚህ ዓይነት ሃይማኖቱ ሁሉንም ሊያቅፍ ይሞክራል። ሌላው ቀርቶ በአንዳንድ ሃይማኖቶች ያሉ ትንቢቶች እንኳ በበሃይ መምጣት እንደተፈጸመ ይነገራል። ለምሳሌ በቡድሂዝም ያለው የሰላምና የፍቅር ቡድሃ መምጣት፣በሂንዱይዝም ያለው የታላቁ ክሪሽና በ10ኛው አቫታር መልክ ደግሞ መምጣት በባሃኡላህ መምጣት ተፈጽመዋል። የክርስቶስ ዳግመኛ

መምጣት (የዓለም ፍጻሜ) በ1844 ዓ.ም እንደተከናወነ ነው፣ዛሬ ያለው አዲስ ዓለም ነውና!

በዓላት

የበሃይ በዓላት የሚከተሉት ናቸው።

በዓላት	ቀናት	የበዓሉ መከበሪያ ሰዓት
አዲስ ዓመት እና ፋሲካ	መጋቢት 21	
ባብ ተልዕኮውን የገለጸበት	ግንቦት 23/1844	ግንቦት 22 ቀን ማታ 2 ሰዓት
ባሃኡላህ ልደት	ሀዳር 12/1817	
ባብ ልደት	ጥቅምት 20/1819	
አብዱልባሃ ልደት	ግንቦት 23/1844	
ባሃኡላህ ዕርገት	ግንቦት 29/1892	ግንቦት 28 ሌሊት ዘጠኝ ሰዓት (ታስቦ የሚውል)
አብዱልባሃ ቃልኪዳን የተቀበለበት	ሀዳር 26/1921	
አብዱልባሃ ዕርገት	ሀዳር 28/1921	(ታስቦ የሚውል)
ባብ የተሰዋበት	ሐምሌ 9/1850	እኩለ ቀን (ቀትር)
ባሃኡላህ ነቢይነቱን የገለጸበት (በባግዳድ አጠገብ የ12 ቀናት ቆይታ ወቅት)	ሚያዝያ 21፣29፣ እና ግንቦት 2 ቀን	በዘጠኝ ሰዓት

የዘመን አቆጣጠር

ባብ ለሰው ልጅ አዲስ ዘመን ከፈተ። አይሁዶች ክርስቲ ያኖችና ሙስሊሞች የነበራቸው ካላንደር (የዘመን አቆጣጠር) ተዘጋ። ባብ እና ባሃኡላህ ትንቢት መጽሀፍን ዘጉ። ያለፈው ዕዳ፣ ጥላቻ፣ የዘር ልዩነት በደል አለፈ። አዲስ ዘመን ተበሰረ። ስለሆነም አዲስ ካላንደር አስፈለገ።

ባብ በወሰነው መሠረት አንድ ዓመት 19 ወራት ይኖሩታል። አንድ ወር ደግሞ 19 ቀናት ይኖሩታል ስለሆነም አስራ ዘጠኝ ወራት 19x19=361 ቀናት ይኖሯቸዋል። አራት ቀናትም በጳጉሜ መልክ በ18ኛውና በ19ኛው ወራት መካከል ይጨመራሉ። በየአራት ዓመትም አንድ ጊዜ አምስት ቀናት እንዲሆኑ ይደረጋል።

ቀናት የሚቆጠሩት ከምሽት በመጀመር ነው። ለምሳሌ መጋቢት 21 ቀን የሚገባው መጋቢት 20 ቀን ማታ በ12 ሰዓት ሆኖ የሚያልቀውም መጋቢት 21 ቀን ማታ በ12 ሰዓት ነው።

እንግዲህ ዘመን አቆጣጠርን በተመለከተ እ.አ.አ. 2000 ዓ.ም የሚሆነው በባሃይ ዘመን አቆጣጠር 156 ይሆናል።

ማጠቃለያ

የባሃይ ሃይማኖት በ19ኛው ምዕተ ዓመት የተጀመረና በአራት መንፈሳዊ ባለሥልጣናት ተከታታይ አስተምሮት ከመቶ ዓመት በላይ ድጋፍ ያገኘ፣ከክርስትና እና ከእስልምና ሃይማኖቶች መሰረት የተነሣ የምዕራቡን ዓለም ፍልስፍናም ያጣቀስ በመሆኑ ሰፊ አመለካከት አለው።

የባሃይን መንፈሳዊ መጻሀፍት በምንመለከትበት ጊዜ "ከራሱ ይልቅ ወንድሙን የሚያስቀድም የተባረከ ነው። ራስህ ሃጢያተኛ ሆነህ እያለ የሌሎችን ሃጢያት ለማመልከት ብትሞ ክር በነፍስህ ይፈረድብሃል" የመሳሰሉት ጥቅሶች ሲነበቡ የመጽሀፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ያስታውሱናል። ሃይማኖቱ የግል ጉዳይን ብቻ ሳይወስን ማህበራዊ ኑሮንም እንደሚገዛ ሲታይ እንዲሁም የጸም የጸሎት ስርዓትን ስንመለከትም ከእስልምና ሃይማኖት ጋር ያለው ተመሣሣይነት ግልጽ ይሆናል።

አልኮል እና ሱስ የሚያስይዙ ነገሮችን መጠጣት ክልክል መሆኑና ለጋብቻ መፈጸም የተጋቢዎቹ አራቱም (ወይም በሕይወት ያሉት) ወላጆች መፍቀድ እንደሚያስፈልግ ሲታይ እንዲሁም ለመንግሥት ታዛዥ መሆንና የመሳሰሉት ትዕዛዛት ከሞላ ጎደል የሁሉም ሃይማኖቶች የጋራ ባህርይ ናቸው።

የሃይማኖት መሰራችን ትዕዛዝ የመቀበል እና ቃሉን የማሰራጨት ግዴታም የሚጠበቅ ነው። ግን የመጨረሻው መሲህ ወይም መሃዲ ማን ነው? የሚለው ልዩነት መፍጠሩ ግዴታ ነው። ባብ እንዲገደል ምክንያት ከሆኑት አንዱ ነቢዩ መሐመድ የመጨረሻው ነቢይ ነው የሚለውን የእስልምና ሃይማኖት ቀኖና መቃረኑ ነው። ግን በባሃይ እምነት መሰረት በሃኡላህ እና አብዱልባሃ ስጋ የለበሱ ቢሆኑም በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ የተወለዱ ናቸው። በመጨረሻም አርገዋል። የበሃይን ሃይማኖት ዘመናዊ ከሚያደርጉት አንዱ የአዝጋሚ ለውጥን ሂደትም በእምነትነቱ እንጻር ሊቀበል መቻሉ ነው። ሰው በዚህ ዓለም ላይ የሚጫወተው የራሱ ሚና አለው።

ስልጣኔን ማሳደግ አለበት። ከኋላ ቀርነት ተላቆ ወደ ላቀ የዕድገት ደረጃ መድረስ ራሱ ግብ ነው። በዚሁ አንጻር ወደ እግዚአብሔር በጎ ፈቃድና ጸጋ የሚያቀርብ ነው። ስለዚህ በስልጣኔ ጎዳና መግፋት ራሱ ምድራዊ ብቻ ሳይሆን ሰማያዊ ግዴታ ነው።

የባሃይ ሃይማኖት ከሞት በኋላ የሚከተለውን ዓለም በግነት እና በገሃነም ዓይን አይመለከተውም ከፋትና ደግነት ያላቸው ልዩነት ለእግዚአብሔር ጸጋ የመቅረብና ያለመቅረብ ጉዳይ ብቻ ነው። ስቃይና መከራ ሳይሆን የማዘንና የመጸጸት አስተሳሰብ ነው። እስከዚያው ድረስ ግን ዓለማችን ብዙ ዘመናት እንደምትኖር የበሃይ ሃይማኖት አስቱምሮት ነው።

መደምደሚያ

አንድ አባባል አለ፡- "ሃይማኖትና የአልኮል መጠጥ የሌለው ህብረተሰብበ ከቶ የለም" ሃይማኖት ማለት በእሣት በወንዝ ወይም በጸሐይ ከማምለክ ጀምሮ በአንድ አምላክ እሰከ ማምለክ የሚደርስ ነው። ሰዎች ደካሞች ነን። ከአቅማችን በላይ የሆነ ፈተና ሲመጣብን የሚቃጣን ሰሜት ወደ በላይ አካል መሄድ ነው። ታላቅ ወንድም፣ አባት፣ ዘመድ፣ ወገን፣ ህግ እንዲደርስልን እንጥራለን። ካልሆነም ወደ ጸሎት፣ እርግማን፣ ሰለት፣ እንሄዳለን።

ከጥንትም ጀምሮ ስጠታ ወይም እጅ መንሻ መስጠት የተለመደ ነው። ለበላይ አካል መታያ ይዞ መቅረብ የተዘጉ በሮችን እንኳ ያስከፍታል። ከመስሪያ ቤት ባለሥልጣን (ወይም ዘበኛ) ጀምሮ እሰከ መንግሥት መሪ ድረስ በዚህ (በጉቦ ቅሌት) የተያዙና በሕዝብ መገናኛ ዘዴ የተጋለጡ እንኳ እጅግ በርካታ ናቸው። በእጅ መንሻ ችግሮቻቸውን ያቃለሉ ግን ያልታወቀባቸው ስንት አሉ?

ታድያ የጥንት ሰዎች ከባዱን የኑሮ ፈተናቸውን ለመወጣት ሲሉ አንዳንድ የእጅ መንሻ ሙከራዎች ቢያደርጉ ምን ያስደንቃል? ለምሣሌ በመግቢያችን ምዕራፍ የጠቀስነው የኢንካ ጎሣዎች የተራራው እሳተ ገሞራ እየፈነዳ የቀለጠ ድንጋይ ቁልቁል በማጉረፍ ሰብል ሲያጠፋባቸው አየር ሲመርዝባቸው መብረቅ ሲጥልባቸው የተራራውን አምላክ መማጸንና ማስታገስ እንዴት መሞከር አይገባቸውም? ለሰሩት ሃጢያት ዋጋው ደም ነውና መስዋዕት መስጠት ይጠበቅባቸዋል ማለት ነው። እርግጥ ተሰዊው እንዳይሰቃይ በቅድሚያ በአልኮል ማስከር አንድ ሰብዓዊ መንገድ ነው። ዛሬም ቢሆን የኮኬይን ንግድን እግዚአብሔር እንዲጠብቅ የሰው መስዋዕት መሰጠቱ ተደርሶበታል። (በ1988 ዓ.ም አንድ የኮሌጅ ተማሪ ለምርምር ብሎ ፔሩ አገር ቢሄድ እንዲሁ ጥቅም ላይ አውለውታል)።

ዛሬ ግን ረሃብ፣ መብረቅ፣ ተስቦ፣ በሽታ ነቀርሳ፣ ወዘተ ... የእግዚአብሔር ቁጣ አይደሉም። እግዚአብሔር የተማሩትን የሰለጠኑትን ሕዝቦች ትቶ የኋላ ቀር ህብረተሰብን ብቻ ለመጉዳት ሲል በእነሱ ላይ የሚያመጣው ቅጣት አይደለም። ዕውቀቱ ገንዘቡ ካለ እነዚህ በቁጥጥር ስር ሊውሉ የሚችሉ ናቸው። የተፈጥሮ ህግጋትን በማጥናት ሳይንስ ከነዚህ መከራዎች አድኖናል። ለዚህ እግዚአብሔርን ማስቸገር ወይም ማማረር ተገቢ አልሆነም።

ይህ የዕድገት ሂደት በዚህ ዓይነት ይቀጥላል። ሌሎች ችግሮችንም ያቃልላል።

ነገር ግን የተፈጥሮ ምስጢር በቀላሉ ግልጽ የሚሆን አይደለም። የሰነከዋክብት ሳይንስ የደረሰበትን ግንዛቤ ወረድ ብለን የምንመለከተው ሲሆን እዚያም ባንደርስ ከወዲሁ ውስጠ ባህርያችንን ብንመረምር ተፈጥሮ ጥልቅ መሆኗ ግልጽ ይሆንልናል። በአጭሩ የአንጎላችን አሰራር እንኳ ገና

በሚገባ አይታወቅም። ህልም እንኳ እንዴት እንደምናይ አይታወቅም። በነቃን ጊዜ እንኳ የማናስበውን ያላየነውንና ያልወጠነውን ነገር በህልማችን ስናቀነባብረዉና ስንፈታው ራሣችን በራሳችን እንደነቃለን። ተሌፓቲ፣ ሂፕኖሲስ፣ ራዕይ፣ የመሳሰሉት የማይገለጹ ክስተቶች አሉ። በዚህ ሁኔታ ሃይማኖት ብርታትን የሚሰጥ መንፈስን የሚያረጋጋ፣ ብሎም ሞትን የመሰለ አስፈሪ ነገር እንኳ ቀላል የሚያደርግ ነው።

በምድራዊው ሕይወትም ቢሆን ሃይማኖት ሰላምን አስፍኖ የኖረ ነው። የፖሊስ ሃይል በማይደርስበት በሰፊው የገጠር አገር ጎበዙንና ደካማውን ትልቁንና ትንሹን አስማምቶ የሚያኖረው እግዚአብሔርን መፍራት ብቻ ነው። እርግጥ የእግዜአብሔር ባሕርይ እና ትርጓሜው እንደሕብረተሰቡ ይለያያል። ለምሳሌ የቡዲሂዝም አመለካከትና የክርስቲያን አመለካከት የተለያዩ ናቸው። ግን አንዱ ከሌላው ይበልጣል አንልም። እኔ የኔን ዕምነት የያዝኩት ይበልጡን በአጋጣሚ እንጂ በምርጫ አለመሆኑ መታሰብ አለበት። ለምሳሌ በሜካ ከተማ ተወልዶ ያደገ ልጅ የቡድሃን ሃይማኖት ለማወቅ እና ለመምረጥ ያለው ዕድል ጥቂት ነው። በኮሚኒስት ቻይና የኖረ ሰው የካቶሊክ ሃይማኖትን ለመማርና ለመምረጥ የነበረው ዕድል ትንሽ ነበር። ዛሬም የአይሁድን ሃይማኖት የሚያስተምሩባቸው ክልሎች ጥቂት ናቸው።...ወዘተ አብዛኛው ሕዝብ የያዘው ሃይማኖት በአካባቢው ስለነበረ የተማረው ሆኖ እንጂ ከብዙ ሃይማኖቶች መርጠ የወሰደው አይደለም። ስለሆነም የራሱን አብልጠ የሌሎቹን አሳንሶ ማየት ቅር ሊያሰኝ ይችላል።

ሰው ለሃይማኖቱ ቀናተኛ ነው። ሃይማኖት ከሌለ ኑሮ ትርጉም ሊያጣ ይችላል። መከራን ለመቻል ችግርን ለመቋቋም ወይም ለመታገል ብሎም ሞትን ለመዳፈር ብርታቱን የሚሰጠን ሃይማኖት ነው። ይህ ከወደቀ ከፈረሰ ጉልበታችን እንደ ተብረከረከና ተስፋችን እንደጨለመ ይቆጠራልና ይህ እንዲሆን አንፈቅድም። ስለዚህም ሃይማኖታችን ሲሰደብ ሲጥላላ ቆመን ለማየት አንሻም። እርግጥ አጥባቂነት ደረጃ ይኖረዋል። ስለዚህም ነው ሳልማንሩሽዲ የተባለ እንግሊዛዊ ደራሲ የእስልምናን ሃይማኖት ሰድቧልና እሱን ለገደለ ሰው ሁለት ሚሊዮን ዶላር ለመሸለም የኢራን መንግስት ያስታወቀው። ሰይጣናዊ ግጥሞች (ሳታኒክ ቨርሰስ) የተባለውን ይህን መጽሐፉን የተረጎሙትና ያሳተሙት ጣሊያናዊው እና ጃፓናዊ ግለሰቦችም ከሞት አላመለጡም። የባንግላዴሽ ወጣት ደራሲ ታስሊማ ናስሪን ግን ቅዱስ ቁራን ተሻሽሎ መጻፍ አለበት ስላለች በ5000 ዶላር ክፍያ እንድትገደል ታዞ የነበረ ሲሆን በዘመድ ብርታት ወደ ስዊድን አገር ልታመልጥ የቻለች መሆንዋ ይታወሰናል። አጥፍቶሀ ጥፋ በሚል መርህ በእስራኤል ፣ በህንድ፣ በስሪላንካእና በሌሎች አገሮች የተፈጸሙ የሀይወት ማጥፋት ክስተቶች እንዲሁ የዕምነቱ ጠንካራነት ወይም (አክራሪነት) ውጤት ናቸው።

ከዚያ በመለስ ግን በሰላማዊ መንገድ ብዙ ሐዋርያዊ ሥራዎች ይካሄዳሉ። ይህም ሃይማኖቱን ለማስፋፋትና ተከታዮቹን ለማብዛት

የእግዚአብሔርን ቃል ላልሰሙትም ቃሉን ለማድረስ ነው። የዓለም መጨረሻ የሚመጣው ወንጌል በዓለም ዙሪያ ከተሰበከ በኋላ ነው። (ማቲ24፣14) ስለዚህ ጥርጊያ መንገዱን ማዘጋጀት ይገባል። (ማቴ 3:3)። የሮማው ጳጳስ (ዮሐንስ ጳውሎስ 2ኛ) ለዚህ ሐዋሪያዊ ተልዕኮው ሲል ወደ ሰባ አገሮችን እየዞረ ቃሉን አድርሷል። የወንጌልን ቃል ለማዳረስ ጀርመናዊው ቦንኬ ኢትዮጵያ ድረስ መጥቶ ብዙ ፈውሷል ብዙ ውዝግብም ተፈጥሯል። የጄሆቫ ምስክሮች የያህዌን (የእግዚአብሔርን) ቃል ለማሰማት ሰዎች እንዲመጡላቸው ሳይጠብቁ በየቤቱ እየዞሩ ያስተምራሉ። ሌሎች ደግሞ በማህበር ተደራጅተው መጽሐፍ ቅዱስን በሚሊዮን ቁጥር በማሳተም እየዞሩ በነጻ ያድላሉ። የእስልምና ሃይማኖትና ሌሎችም እንደየደንባቸውና ህጋቸው ሐዋሪያዊ ተልዕኮ ያከናውናሉ። ይህ በአብዛኛው በምዕመናን ላይ የተጣለ ግዴታ ሆኖም ይታያል። ለምሣሌ በቅዱስ ቁርዓን "ውከትም እስከማትገኝ፣ ሃይማኖትም ሁሉ ለአላህ ብቻ እስከሚሆን ድረስ (ከሃዲዎችን) ተጋደሉዋቸው" (ሱራ 8፣39 ይላል። በመጽሀፍ ቅዱስም "ሂዱና አህዛብን ሁሉ . . . እያጠመቃችሁ ያዘዝኳችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀመዛሙርቴ አድርጓቸው (ማቴ 28፣19-30) ይላል።

አንድ የቡድሂዝም መጽሀፍም እንደሚያስቀምጠው ቡድሃ ዕለተ ሞቱ በተቃረበ ጊዜ "እኔ የሰጠኋችሁና ያስተማርኳችሁ ሁሉ ከሞትኩ በኋላ መመሪያችሁ እንዲሆን" በማለት ተከታዮቹን አዟል። በተጨማሪ ግን መጽሀፍት ከሚሉት በስተቀር መጨመር ወይንም መቀነስ ፍጹም ፍጹም የተከለከለ ነው። ቅዱስ ቁርዓን ከሰማይ የወረደ ስለሆነ መጨመርም ሆነ መቀነስ የማይታሰብ ነው። መጽሀፍ ቅዱስም እንደሚያስቀምጠው "ማንም በዚህ ላይ አንዳች ቢጨምር እግዚአብሔር በዚህ መጽሀፍ የተጻፉትን መቅሰፍቶች ይጨምርበታል። ማንም . . . አንዳች ቢያጎድል . . . እግዚአብሔር ዕድሉን ያጎድልበታል። (ራዕ 22፣18-19)። ሌሎችም ሃይማኖቶች የየራሳቸውን የተሟላ እውነታ አድርገው ይገልጻሉ። ስለዚህ ይህ ሁኔታዎችን ጥብቅ ያደርጋቸዋል።

በሌላ በኩል ግን ከተለመደው ሃይማኖታዊ አስተምሮት እያፈነገጡ ታሪክ የሚፈጥሩም ጥቂት አይደሉም። ማርቲን ሉተር የፕሮቴስታንት ሃይማኖትን የመሰረተው ከካቶሊክ ምንኩስና ኑሮው አፈንግጦ በመውጣት ነው። እርግጥ ይህ የሆነው ሃይማኖቱን በሙሉ በመካድ ሳይሆን አተረጓጎሙንና የትኩረት አቅጣጫውን ለየት ባለ መንገድ በመውሰድ ነው። ዛሬ በዓለም ላይ ያሉት ከ260 በላይ የክርስትና እምነት ዓይነቶች የተቋቋሙት በተመሳሳይ መንገድ ነው ግን ጭራሽ ከመንገድ የወጡም ሰዎች ጥቂት አይደሉም። የወላጆቻቸውን ሃይማኖት ትተው ሌላ የያዙ በርካታ ናቸው። የራሳቸውንም እምነት በየመንገዱ የቀየሩ ብዙሃን ናቸው። ይህ መሆን የለበትም ለማለት አይደለም። የሃይማኖት ነጻነት መኖር ያለበት ነውና። ግን በነጻነት ስም ፍጹም ተስፈንጣሪ የሆኑ አመለካከቶች ሲከሰቱ የሃይማኖትን ነጻነት በማጎናጸፍ ዝናቸው የታወቁ ሕብረተሰቦች

እንኳን የማይቀበሉት ሁኔታ ያጋጥማቸዋል። ለምሣሌ አንቶኒ ፍሪማን የተባለ የአንግሊካን (የእንግሊዝ) ቄስ ነበረ። መደበኛ ሰባኪ በመሆኑ በየሳምንቱ መጽሀፍ ቅዱስን በማስተማሩ በርካታ ምዕመናን ተከታዮች ነበሩት። ሆኖም በ1994 ዓ.ም ይህ ቄስ ከመደበኛ ስራው ተባረረ። ምክንያቱም አንድ እሱ የደረሰው መጽሐፍ (እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ በሚል ርዕስ የተጻፈ) ምዕመናንን አስኮረፈ። እንደ ፍሪማን አዲስ ግንዛቤ እግዚአብሔር የሚባል ለብቻው የተቀመጠ ነገር የለም። ይህ የእኛ የሰዎች ፈጠራ ነው። በእኛ ሰብዓዊ ስሜት፣ የእኛን በጎ አመለካከት ሀልውና ሰጥተነው ውበት ጨምረንበት ያስቀመጥነው የፈጠራ ውጤት ነው።*

ይህወደ ቡድሂዝም ሃይማኖት የሚያመራ መሆኑ ነው። እንደምናስታውሰው በቡድሃ አስተምሮት መሰረት የሃጢያት መሰረቱ ክፋ ምኞት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ ምኞት ራሱ ነው። ሰው ምኞቱን መቆጣጠርና ብሎም ማስወገድ ከቻለ ፈተና ውስጥ አይገባም። ከሃጢያት ቀለበትም ሊወጣ ይችላል። ስለሆነም የሁለንተናዊ በጎ መንፈስ (ኒርቫና) አካል ይሆናል። እግዚአብሔር ማለትም ይህ ሁለንተናዊ መንፈስ እንጂ ለብቻው ያለ አይደለም። ስለሆነም ሰዎች የራሳችንን ኑሮ ለማስተካከል በምናደርገው ጥረት የኒርቫና ሚና ካለበት በጣም ትንሽ ነው።

ዛሬ ሳይንሳዊ አመለካከትም ከሞላ ጎደል ወደዚሁ ጣልቃ አለመግባት አቅጣጫ እያመራ ይመስላል። ዓለማችን የተፈጥሮ ሁሉ ማዕከል ሆና መታሰቧ (ጸሐይና ከዋክብት ሁሉ በእርሷ ዙሪያ እንዲሆኑ የተፈጠሩ መሆኑ) ከቀረ ውሎ አድሯል። ፍጥረት ሰፊ ሀዋ መሆኑ እና መሬታችንም በግዙፍ ፍጥረቶች መካከል እንደ ቅንጣት መቆጠሯ አልቀረም።

ከዋክብት በሰማይ የተዘረጉት እሷን ለማድመቅ ሳይሆን እነሱም እንደ ጸሐይ የራሳቸውን ዑደት የሚያከናውኑ አካላት ናቸው። በራሳቸው የተፈጥሮ ህግ መሰረትም የሚወለዱ የሚያድጉና የሚያረጁ ናቸው። ይህ ዓይነት የከዋክብት ጥናት (ሥነ-ፈለግ) የሰውን አስተሳሰብ በእጅጉ የቀየረው ሲሆን ጥናቱም የተመሰረተው ከየከዋክብቱ በሚደርሰን ብርሃን (ጨረር) ጥናት ነው።

እንደሚታወቀው የብርሃን (ጨረር) የጉዞ ፍጥነት 300,000 ኪሎ ሜትር በሴኮንድ ነው። በዚህ ፍጥነቱ ምድርን ሲዞር በአንዲት ሴኮንድ ሰባት ጊዜ ይዞራታል። በደቂቃ ውስጥ ከ400 ጊዜ በላይ ይዞራታል። ይህ ርቀት ቢዘረጋ ረጅም ነው። ይህ እንግዲህ የአንዲት ደቂቃ ጉዞ ነው። ብርሃን በዚህ ፍጥነቱ ለስምንት ደቂቃዎች ቢጓዝ ጸሐይ ጋር ይደርሳል። ለአንድ ሰዓት ቢጓዝ ጸሐይን አልፎ ስድስት እጥፍ ይርቃል። አንድ ሙሉ ቀን ቢጓዝስ? አንድ ሳምንት ቢጓዝስ? በዚህ ዓይነት አራት ዓመት ከሶስት ወር ቢጓዝ ቅርባችን ወደ ሆነችው ከከብ (አልፋ ሴንታውሪ የተባለች) ጋር

* ኒውስ ዊክ ነሐሴ 15 ቀን 1994 ዓ.ም

ይደርሳል። ቤት ኤልጉዝ የተባለች ኮከብ ጋር ለመድረስ 296 ዓመታት ይፈጃል። (ይህ ግዙፍ ኮከብ ከመሬት እስከ ጸሐይ ያለውን ርቀት እጥፍ በውስጡ ያካትታል።) ሩቅ ወደሆነች አንድ ኳዛር ለመድረስ እሰከ ቢሊዮን ዓመታት ይፈጃል።

ዩናይትድ ስቴትስ ኸብል በተባለው የጠፈር መንኮራኩር ቴሌስኮፕ አማካኝነት አስር ቢሊዮን ገደማ ዓመታት ተጉዞ ወደ ምድራችን የደረሰ ብርሃን ሰብስበዋል። በዚያ ርቀት የሚገኙ ለተራ ዓይናችን የማይታዩን በርካታ ጋላክሲዎች አሉ። ዛሬ እንደሚገመተው በሀዋ ውስጥ እሰከ 50 ቢሊዮን ጋላክሲዎች አሉ። በእያንዳንዱ ጋላክሲ ውስጥ የሚገኙት ከዋክብት በሚሊዮን ሳይሆን በቢሊዮን የሚቆጠሩ ናቸው። እነዚህ ሁሉ በእቶን ይንቀለቀላሉ ይበራሉ ይንቦገቦጋሉ። በባዶ ሀዋ ዝም ብለው ያጨራሉ። ለምን? ማን ያያቸዋል? ለማንስ ይጠቅማሉ? በነሱ ዙሪያ ሀያዋን ይኖሩ ይሆን? እሰከ ዛሬ ከግምት በስተቀር የሚያውቅ የለም። ግን በቅርቡ በ35 የብርሀን ዓመት ርቀት ላይ ሁለት መሬት መሰል ፕላኔቶች በሌሎች ከዋክብት ዙሪያ ተገኝተዋል ይባላል። እንግዲህ ራቅ ካልን ሌሎች በሺ የሚቆጠሩ ይኖራሉ። ግን በእኛ ዙሪያ እንኳ ስምንት መሬት መሰል ፕላኔቶች አሉ። እንደኛይቱ መሬት እነሱም በጸሐይ ዙሪያ ያዞራሉ። የራሣቸውም ቀንና ሌሊት አላቸው። ስለሆነም ይነጋል፣ይመሻል ብርድና ቁር ሙቀትና ሐሩር ይፈራረቅባቸዋል። ድንጋይ ይግላል። ይቀዘቅዛል። አውሎ ነፋስ ይነፍሳል። ያተረማምሣል። እሳተገሞራ ይፈነዳል። አካባቢውን ያደባልቃል። ሕይወት ግን የለም። የተፈጥሮን ተአምር የሚገነዘብ እና የሚያደንቅ ሕያው የለም። ይህ ታድያ "የመኖራቸው ትርጉሙ ዓላማው ምንድ ነው?" የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል። እርግጥ ከእይታችን ውጭ የሆኑ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ከዋክብት ተፈጥረዋል። ፕላኔቶችም ሌሎችም አብረው ተፈጥረዋል። ሁሉም ይኖራሉ። ዕድሜያቸውንም ሲጨርሱ ይከስማሉ። ግን ታድያ ለምን ተፈጠሩ? ግዑዝ ነገር አስቦ የሚሰራው ነገር ሳይኖረው በተፈጥሮ ህግ ብቻ የሚንቀሳቀስ የሚዞር ያሚሽከረከር የሚግል የሚቀዘቅዝ የሚፈነዳ የሚርመሰመስ፣ ቀንና ሌሊት የሚፈራረቅበት ዘመናት በከንቱ የሚቆጠሩበት በመጨረሻም የሚከስምበት ነው። ይህ ሁሉ ክስተት ተልዕኮው ምን ቢሆን ነው? አገልግሎቱስ ምኑ ላይ ነው?

ለእኛ በምድር ላይ ለምንኖረው ሰዎች ደግነት ትርጉም አለው። ኑሮአችንን ለመኖርና ለማመቻቸት ተገቢው ማህበራዊ ግንኙነት ስለሚያስፈልግ ሊሆን ይችላል። የሃይማኖት ህግም በመሆኑም ሊሆን ይችላል።

ግን ሕያዋን በሌሉበትና ግዑዛን በተፈጥሮ ህግጋት መሰረት ብቻ በሚንቀሳቀሱበት ዓለም ደግነትና ክፋት ምን ትርጉም ይኖረዋል? መኖርና

አለመኖርስ ምን ጉዳት ያስከትላል? ማንስ ይሰማል? ማንስ ይገነዘባል? ቢሆንስ ምን ለውጥ ያመጣል? በአጭሩ የዚህ ሁሉ ምስጢሩ ምን ይሆን?

በአንድ ነገር ሁሉም ይስማማል፡- ከዚህ ተፈጥሮ ሁሉ በስተጀርባ አንድ ሃይል አለ። ከዋክብት ራሳቸውን አይፈጥሩም። ሌላው ቢቀር የሁሉም መሰረታዊ ቁስ የሆነው ሃይድሮጅን ራሱን አይፈጥርም። ስለዚህ ፈጣሪ ይኖረዋል። ግን ፈጣሪው ያንን ካደረገ በኋላ በነዚህ ግዑዝ ነገሮች እንቅስቃሴ ውስጥ ጣልቃ አይገባም። መ ለባትም አያስፈልግም። በተሰ ጣቸው ህግ መሰረት ይሳሳባሉ ይዞራሉ ይንቀሳቀሳሉ፣ ያበራሉ፣ በኋላም ይከስማሉ።

ይህ ግንዛቤ የሰው ልጅ ስነፈለክን አጥንቶ የደረሰበት ነው። ግን ታላቁ የተፈጥሮ ሚስጥር በአንድ የዕውቀት ዘርፍ ብቻ የሚደረስበት አይመስለኝም። ሌሎች ዘርፎችንም ማጥናትና ማገናዘብ ይገባናል።

ሥነ-ሕይወት በዚህ ረገድ ምን ይላል? ይህ ሕይወት ስላላቸው ነገሮች የሚያጠና ነው። በዓለማችን ውስጥ ከሚሊዮን የሚበልጡ የፍጥረት ዓይነቶች አሉ። ሰው፣ ዝንጀሮ፣ አሜባ፣ አይጥ . . . ወዘተ። ሁሉም ሕያው ናቸው። ግን ሁሉም በእኩል ደረጃ ላይ ያሉ አይደሉም። በሳይንሱ መሰረት ሕይወት የተጀመረው በአንድ ሕዋስ ነው። ቀስ በቀስ እየተራቀቀና እየተደራጀ በሚሊዮን ዓመታት አዝጋሚ ለውጥ ሉሲ (ድንቅነሽ) ያለችበት ደረጃ ተደረሰ በሚቀጥሉት 2½ ሚሊዮን ዓመታት ደግሞ እዚህ ደረጃ ተደርሷል። ይህ ለውጥ ይቀጥላል። ዕድገቱም ይቀጥላል። ግን ዕድገቱ በየት አቅጣጫ ነው? መንገድ ሁሉ መጨረሻ የሌለው አይደለም። ተሂዶ ተሂዶ የሚቆምበት ደረጃ ይደረሳል። ጭልፊት መጨረሻ ደረጃ ደርሳ ሊሆን ይችላል። በሰማይ እየተንሳፈፈች እሰከበረረች እና በዚሁ አኗኗር እሰከቀጠለች ድረስ ክብደቷን ያለገደብ ልትጨምር አትችልም። ፍጥነቷም ከክብደቷ ጋር የተያያዘ ስለሆነ ክብደቷ የአደን ችሎታዋን ውሱን ያደርገዋል። ስለዚህ አካሏን ቀይራ ወጥመድ ወይም መሰፈንጠሪያ ሰርታ አይጥ ታድንበታለች ተብሎ አይጠበቅም። ሌሎች ብዙዎች እንስሳትም እንዲሁ መጨረሻቸው የደረሱ ይመስላሉ። አንበሳም በሁለት እግሩ ቆሞ ግብርና ይማራል ተብሎ አይገመትም። ከዚህ መካከል ትልቅ የዕድገት ዕድል ያለው አሁንም ሰው ነው። ይህም በአንጎሉ ረገድ ነው። ዛሬ በዕድገት መሰላል ላይ ከፍተኛውን ቦታ ይዞ የሚገኘው ፍጡር ሰው ነው። ሰው ደግሞ እዚህ ደረጃ የደረሰው በጉልበቱ ብርታት ከአንበሳ በልጦ ሳይሆን ወይም በሩጫ ከጥንቸል ፈጥኖ ሳይሆን (. . . ወዘተ) በአንጎሉ ከሁሉም ልቆ ነው። ስለዚህም ነው። ስለተፈጥሮ ረቂቅነት በበለጠ ሊገነዘብ የበቃው። ይህ የዕድገቱ ጉዞ ወደፊትም ሊቀጥል እንደሚችል ተስፋ ይደረጋል። እርግጥ ዕድገቱ ወይም ለውጡ በየት አቅጣጫ እንደሚሆን በቅድሚያ ለማወቅ ያስቸግራል። የአካባቢው ለውጥ አንዳንድ ባህሪያትን የሚያጎለብት ሌሎችን አልአስፈላጊ የሚያደርጋቸው ሊሆን ይችላል። (ሲያደርግም ኖሯል) ግን ሰፊ ዕድል ያለው በአንጎል ዕድገት

መንገድ ሳይሆን አይቀርም። ከሌሎች ፍጡራን የምንለየው በአንጎላችን በመሆኑ የዕድገት ሂደቱ የሚያዋጣን በዚሁ መንገድ ብንቀጥል ነው። የእግዚአብሔርን ስራ ልናደንቅ የቻልነውም በዚሁ በተቀዳጀነው ተሰጥኦ ነው። ስለዚህ የወደፊት ዕድገታችንም በዚሁ አቅጣጫ እንዲሆን የታቀደ ይመስላል።

እንግዲህ በሳይንስ አመለካከትም ብንሄድ "የመኖር ትርጉም ምንድነው?" የሚለው ዋነኛ ጥያቄ እዚህ ላይ መልስ ያገኛል። የተፈጥሮ ሀግ ዕድገትን ያመለክታል። ህዋ ተፈጠረ ጸሐይና መሬት ተገኙ። መሬት ስትቀዘቅዝና ውሃ ሲገኝ ከጊዜ በኋላ ሕይወት ተፈጠረ። ይህ እያደገ በዓይነትም እየበዛ ሄደ። መጨረሻ ላይ ሰው ተገኘ። ይህ የዕድገት ሂደት ከቀጠለ ለዚህ ዋናው መሣሪያ የሚሆነው የሰው ልጅ ነው። ስለዚህ ይህ ዕድገት እንዲቀጥል የሰው ልጅ ሚናውን ተገንዝቦ ሂደቱን መርዳት ማፍጠን አለበት። የሰው ሃላፊነቱ እዚህ ላይ ነው። የዕድገቱ ሂደት ወደየት እንደሚያደርሰው አሁን ሊያውቅ አይችልም። እነ ድንቅነሽ ዘራቸው ወደፊት ህዋን እንደሚዳስስ መቸ ገመቱና! ዕድገቱ የተፈጥሮን ትርጉም በበለጠ ለመረዳት የባለቤቱን (ፈጣሪውን) ተአምር ስራ በበለጠ ለማድነቅ ከሰው ልጅ የሚፈለገውንም ሁሉ ለመፈጸም የሚያስችል ሊሆን ይችላል።

ለማንኛውም ዕድገቱ መቀጠል እንዳለበት የሳይንስ ምኞት ነው። ይህ ደግሞ የሚሆነው በሁለት መንገድ ነው።

1- ሰው የራሱን ችሎታና ተሰጥኦ ማዳበር አለበት። የአዝጋሚ ለውጥ ዕድገት በየትኛው አቅጣጫ እንደሚዘልቅ ማንም በቅድሚያ አያውቅምና ይህ በአካልም በአእምሮም ሊሆን ይችላል። የአካባቢው ለውጥ አንዳንድ ባህሪያትን ከሌሎች በማስበለጥ ሊመርጥ ስለሚችል ችሎታን ማዳበር ጠቃሚ ነው። ለምሣሌ አንድ ሰው የረዥም ሩጫ ተሰጥኦ ሊኖረው ይችላል። ሌላው ቼስ መጫወት ሌላው ሙዚቃ መጫወት እንዲሁም ሌላው የሂሳብ ተሰጥኦ ይኖረዋል። . . . ወዘተ። ሁሉም ሰው ልዩ ተሰጥኦውን ፈልጎ ማግኘትና ብሎም ማዳበር አለበት። በዚህም መጠቀም መብቱ ነው።

2ኛ- ሰው የሚኖርበትን ህብረተሰብ ደህንነት መጠበቅና ማጎልበት አለበት። ሰው ብቻውን ሊኖር አይችልም። የአዝጋሚ ለውጥ ዕድገትም የሚከናወነው በተከታታይ ትውልዶች የተከማቸ መሻሻል ነው። ስለዚህ የሕብረተሰቡ ሕያውነት ወሳኝ ነው። ዝቅተኛ ነፍሳት እንኳ ለማህበራዊ ሕልውና ሲሉ ሕይወታቸውን እስከማጣት የሚዋጉ አሉ። ሰው ደግሞ ከዚህ በተጨማሪ ምግቡን ለማግኘት ልብሱን ለመስራት፡ጤንነቱን በህክምና ለመጠበቅ . . . ወዘተ የሕብረተሰቡን ትብብር ይፈልጋል። እራሱ እንደ ተማረ ሁሉ የወደፊቱንም ትውልድ አስተምሮ ማለፍ አለበት። ባህሉን አዳብሮ ማውረስ ማስተላለፍ አለበት። ስለዚህ ከሌሎች የማህበረሰቡ አባላት ጋር መተጋገዝ፣ መግባባት፣ መተሳሰብና መረዳዳት የተፈጥሮ ህግና ማህበራዊ ግዴታው ይሆናል። ሃይማኖትም ቢሆን የሚያራምደው ይህንኑ የፍቅር የሰላምና የመረዳዳት መንፈስ ነው።

ሌሎች የዕውቀት ዘርፎችም በየፊናቸው የሚሉት አላቸው። በዚህም የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ወይም የሚያስጨብጡት እውነታ ይኖራል። ዋናው ፍሬ ነገር ግን ሁላችንም በየግላችንም ሆነ በጋራ ሆነን ቀጣይ እድገት እንድናስገኝ መተባበር፣ መረዳዳት፣ መማማርና በርትተን መስራት አለብን። ይህ እንግዲህ ራሱ አንድ ፍልስፍና ወይም አንድ ሃይማኖት ነው፤ የሳይንስ ሃይማኖት!! እርግጥ የሕይወት ጉዞ እንዲቀጥል መንገዱም እንዳይሰለች ለማድረግ በደስታ መጓዝ ይመረጣል። ረሹም የአውቶቡስ ጉዞ እንኳ በሙዚቃ ይታጀባል። መቀመጫውም እንዲደላ ሙከራ ይደረጋል። ግን አውቶቡሱ ሁሉ እኩል አይደለም። በሕይወት ጉዞም ላይ ሁሉም እኩል ላይደላው ይችላል። በችሎታው ለመጠቀምም ዕድል ላያገኝ ይችላል።

ይህ ከአገር ወደ አገር ይለያያል፣ ከመንግሥት ወደ መንግሥት ይለያያል። ይህ ምክንያት ይኖረዋል። የተፈጥሮ ሐብት ዕድልም ይወስነዋል። ዋናው ነገር ግን ጉዞው ቢደላው ባይደላም መጓዙ ላይ ነው። ጉዞው ዕድገት ነው። ዕድገትም የተፈጥሮ ህግ ነው። ይህንን ለማሳከት መረዳዳትና መተሳሰብ መተጋገዝ ወሳኝ ነው።

ይህ ግን አዲስ ነገር አይደለም። ሃይማኖቶች ሁሉ ሲያስተምሩ የኖሩት ነው። የተቸገሩትን መርዳት፣ ባልንጀራን ማፍቀር፣ ሰውን አለመጉዳት፣ ክፉ አለመሥራት የሚሉት ሁሉ ቅዱሳት መጽሀፍት የሚያስተምሯቸው ናቸው።

ይህ እንግዲህ ወደ እምነት ውህደት የሚያመራ መሆኑ ነው። ግን ይህ መሆን ያለበት ነው። ምክንያቱም እውነታ አንድ ነች። ዓለማችንም አንድ ነች። ስለዚህ ፈጣሪዋም አንድ ነው። ባህርዩና ትዕዛዛቱም ለተለያየ ህብረተሰብ የተለየ ሊሆን አይችልም።

ሳይንስን ማጥናት ያስገኘልን ሌላው ነገር ለእግዚአብሔር የምናቀርበው ጥያቄ በዓይነቱ እየቀነሰ መምጣቱ ነው። ኋላቀር ህብረተሰብ ለችግሩ መፍትሔ ለማግኘት የሚቀናው ጸሎት ነው። ሌላ አማራጭ የለውምና። ግን ሳይንስ እያደገ ሲሄድ ለአንዳንድ ችግሮች መፍትሔ ይሰጣል። የተማረ ሰው አጥንቱ ቢሰበር ወይም ሳንባ ነቀርሳ ቢይዘው ወይም የጥርስ ሕመም ቢያሰቃየው አቤቱታውን ወደ እግዚአብሔር ለማድረስ ሱባኤ አይገባም። ተነስቶ ወደ ሐኪም ቤት በመሄድ በመድሃኒት ይገላገላል፣ ሳይንስ የጀርሞችን ምስጢር አሳውቆናል። እግዚአብሔር አእምሮን የሰጠን ይህንን ነገር እንድንደርስበትና ራሳችንን እንድንረዳ ፈቃዱ ቢሆን ነውና!!

ሳይንስ እስከ ዛሬም ብዙ አገልግሎት እንደሰጠን ልብ እንላለን። የውሃ ፏፏቴ ለዘመናት በከንቱ ሲፈስ እንደኖረ ይታወቃል። ያንን ገድበንና ከትረን ኮረንቲ ለማመንጨት በቅተናል። በመሆኑም ለከተሞቻችን ብርሃንን ለፋብሪካዎቻችን አንቀሳቃሽ ሃይልን ማግኘታችንን የሚያወግዝ ማን አለ? በቤንዚን ተጠቅመን ተሽከርካሪዎችን በማስኬድ ያቃለልነውን የትራንስፖርት ችግር የሚቃወም ማን አለ? መድሃኒት በማግኘትስ

የስንታችንን ሰቃይና መከራ ልናስታግስ ችለናል? ይህ ሁሉ የሳይንስ ድል ነው። በአጭሩ የሰውን ልጅ ከኋላቀርነት አላቆ ለስልጣኔ ያበቀው ይበልጡን ሳይንስ ነው። ይህ እንግዲህ እግዚአብሔር የሚወደው እንጂ የሚጠላው አይሆንም። እንዲያውም ፈቃዱና ዕቅዱ ነው ብዬ አምናለሁ።

ስለዚህ አትመራመሩ የሚሉትን አትቀበሏቸው። እነሱ ስላላወቁት ብቻ እግዚአብሔር እንደከለከለ አድርገው የሚቆጡትን አትመኗቸው። የኋላ ኋላ እውነት ተደብቃ ላትቀር መሬት ክብ ናት በማለቱ በቁሙ እንዲቃጠል የተፈረደበት ሳይንቲስቱ ብሩኖ በእውነት ግፍ ተሰርቶበታል።

ወደፊትም ቢሆን ሳይንስ ዕድገቱን አያቋርጥም። በበለጠ እንድናውቅ እና ራሳችንን እንድንረዳ መንገዱ ይኸው ነው። እርግጥ የሰውን ባህርይ ስንመለከት ሳይንስ አንድ "ድክመት" አለው። እንደሚታወቀው የሰው ልጅ ደካማ ነው። ድጋፍ ያስፈልገዋል። ሲታመም፣ ሲቸገር፣ ሲጨነቅ፣ "አለሁልህ" የሚለው ይፈልጋል። ብሶቱን የሚረዳለት ውስጣዊ ስሜቱን የሚገነዘብለት "አለኝታ" እንዲኖረው ይወዳል። ሳይንስ ይህን አያሟላም። ሳይንስ በድን ነው። በሃይማኖት መንገድ የሚሄድ ሰው ግን የመንፈስ ሰላም አለው። ችግሮችንም በልበ ሙሉነት የመቅርብ ችሎታ ይኖረዋል።

በዓለማችን ላይ የመንፈስ ሰላም የጠፋው ሰዎች ባለመስማማታቸውና ብሎም ፍጅት በመኖሩ ነው። ለዚህም አንዱ ዋና ምክንያት ሀብታም እና ድሃ መኖሩ ነው። ሁሉም እኩል ራቁቱን ተወልዶ እያለ አንዱ ሲሰቃይ ሌላው በድሎት ሲንደላቀቅ ሁኔታውን መቀበሉ ለሀሊናም ይከብዳል። ባለፉት ዘመናት የተለያዩ የፖለቲካ ስርዓቶች ይህንን ችግር ለማቃለል ሙከራ አድርገዋል። ለምሣሌ የኮሚኒስት ስርዓት ሁሉም ተካፍሎ እንዲኖር ለማድረግ ሞክሮ ነበረ። ነገር ግን ይህ ደግሞ ለአጠቃላይ ኢኮኖሚ ዕድገት መሰናክል መሆኑ ይገለጻል። ዕድገት የሚገኘው በውድድር ዓለም ነው ተብሏል። ይህም አንዱ የሰው ልጅ ባህርይ ከሆነ መቀበል ነው። እንግዲህ ከዚህ በመነሣት ምን ማድረግ አለብን? ስንል ያሉን አማራጮች በየደረጃው ይለያያሉ።

የቡድሂዝም አስተምሮት ጥንቱን እንዳስቀመጠው እጅግም ሃብታም፣ እጅግም ደሃ መሆን አግባብ አይደለም። በተንደላቀቀ ኑሮ መዋኘትም ሆነ በስቃይና በመከራ ራስን መበደል ሁለቱም አይበጁም ወርቃማው መንገድ ሆኖ የሚወሰደው መካከለኛው አኗኗር ነው።

ይህ የቡድሃ አስተምሮት ለዓለም ሕዝቦች ሁሉ ሥራ ላይ ሊውል ቢችል ምንኛ መልካም ነበር? ይህ ተካፍሎ ተረዳድቶና አብሮ ሰርቶ መኖርን ያስችላል። ይህ የጋርዮሽ ስርዓትን መልሶ ለማስፈን ነው የሚል ተቃውሞ ይገጥመው ከሆነ ደግሞ ሌላ አማራጭ መፈለግ ነው። ለተቸገሩ መርዳትና ማካፈል በአብዛኛው ሃይማኖት ያለ ህግ ነውና ሁሉም እንደየገቢው ወይም እንደየትርፉ በፐርሰንት እያሰላ መርዳት ቢችል ይህም ሌላው ጥሩ መንገድ ነው። ግን ለዚህም ባንበቃ እና ራስ ወዳድ ሆነን ብንገኝ የጥንታዊው የአይሁድነት ሃይማኖት ፈላስፋና አስተማሪ የረቢ

ሂሌል አስተምሮት የመጨረሻ ገደብ ነው። እየሱስም በምድር ሳለ ያደነቀለት ነው። የቄሳሩ ወታደር ወደ ረቢ ሂሌል ቀርቦ "በአንድ እግሬ እንደቆምኩ ቅዱስ የሆነውን ህግ ሁሉ ልታስተምረኝ ትችላለህን? ብሎ ቢጠይቀው የሰጠው መልስ እንደሚከተለው ሰሞር ነበር። "በአንተ ላይ ቢደረግብህ የማትወደውን በሌላው ላይ አታድርግ"። ይህንን የማይቀበል ሰውም ሆነ ሃይማኖት ሁሉ ችግር አለበት፣ ችግርም ያስከትላል።

አባሪ

የኢትዮጵያ ምዕመናን ቁጥር በሃይማኖት ሲከፋፈል።*

(የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ መ/ቤት በ1994 ዓ.ም ባደረገው ቆጠራ መሰረት)

ክልል	ኦርቶዶክስ	ካቶሊክ	ፕሮቴስትንት	ሙስሊም	ባህላዊ	ሌሎች	ያልታወቀ
ትግራይ	2,992,305	12,489	1,136	127,657	53	251	2,376
አማራ	11,264,421	937	11,392	2,541,836	2,734	6897	6080
ኦሮሚያ	7,621,727	107,310	1,588,310	8,178,085	778,359	180,235	19794
ደቡብ ሕዝቦች	2,862,734	307604	3,611,583	1,735,214	1,594,374	249,892	90791
ድሬደዋ	86,777	1,818	3,668	158,871	13	349	368
ሐረሪ	49,954	603	1,231	78,952	34	123	242
ጋምቤላ	39,187	5,205	71,478	8362	16,699	20,653	813
ቤኒሻንጉል ጉምዝ	135,727	2451	24,774	193,730	60346	6836	568
አዲስ አበባ	1,732,374	16,488	81,759	267,693	385	12,384	1654

* የአፋርና የሱማሌ ክልሎች አሃዝ ባይደርሰኝም አብዛኞቹ ሙስሊሞች መሆናቸው የታወቀ ነው።

ዋቢ መጻህፍት

1. Andersen K.T	A Brief History of Mekaneyesus Church; Danish Evangelical Mission 1979; Denmark.
2. Aren, Gustar	Evangelical Pioneers of Ethiopia; EFS Folaget 1978; Stockholm
3. Aymro Wondimagegnehu &Motovu J. (editors)	The Ethiopian Orthodox Church; The Ethiopian Orthodox Mission 1970; Addis Ababa
4. Fitch F.M	One God-the way we worship him Lothrop & Shepard Co. 1944 U.S.A
5. Hinnels J.R(ed)	A handbook of living religions; Penguin Books ltd. 1984 Middlesex, England
6. Tokarevs	History of Religion; Progress Publishers 1989 Moscow
7. Zachner R.C (ed)	The Hutchinson Encyclopedia of living Faiths; Helicon Publishing Ltd. (4th ed) 1988 Oxford, England



“ሩጫዬን ጨርሻለሁ፤ ሃይማኖቴንም ጠብቄያለሁ” የሚለው የመቃብር ሃውልት ጽሁፍ ከፍተኛ የሃይማኖት ጽናትን ይገልጻል። ለዚህ ጽናት ብዙ መስዋዕት ተከፍሏል። በታሪክ እንደተመዘገበው ባለፉት ዘመናት ሰዎች ለሃይማኖታቸው ሲሉ በመኪና ተዳምጠዋል፤ በእሳት ውስጥ ተቃጥለዋል፤ በጥይት ተደብድበዋል፤ በመጥረቢያም ተቆራርጠዋል። በዚህ ዓይነት ህይወታቸውን ሰጥተዋል።

በሌላ በኩል “አትግደል” የሚለውን የሃይማኖት ህግ በእጅጉ በማክበር የሕይወት ዘመናቸውን በልመና እና በችግር የሚገፉ አሉ። ይህም መሬት በሚታረስበት ጊዜ በአፈር ውስጥ የሚኖሩት ጥቃቅን ነፍሳት ይገደላሉ በሚል ስጋት አርሶ መብላት ተከል ክለው ነው።

ሌሎች ደግሞ ፈንጂ ታጥቀውና ለብሰው የፖለቲካ ተቃዋሚ ዎች ወገኖች መካከል ገብተው ፈንጂውን በማቀጣጠል ራሳቸው ተበታትነውና ሌሎችንም በታትነው የሚያልፉ አሉ። እነዚህም እንደ እምነታቸው መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ ነው።

ግን እውን ሁሉም የሃይማኖት መስራቾች እስከዚህ በዝርዝር ደንግገው ኖሯል? ለመሆኑ የሃይማኖት አነሣስ እንዴት ነበረ? በዘመናችን ያስከተለውስ “መሻሻል” ምን መልክ ያዘ? ይህን በተ መለከተ ሁላችንም ሃይማኖታችንን በበለጠ አውቀን እንድናጠናክር እንዲሁም ወገኖቻችን ለራሳቸው አቅፈው የያዙትን እምነታቸውን እንድንረዳላቸው ዛሬ ለማህበራዊ ኑሮአችን አስፈላጊ ሆኗል። ስለሆነም ለቀላል ግንዛቤ እንዲረዳ የሃይማኖቶቹ መሰረተሃሳብና ይዘታቸው በአጭር በአጭሩ ቀርቧል።